# ABS

## @Amharicbookstore

ABS የተመረጡ የአማርኛ መፅሀፍት
የሚቀርብበት የቴሌግራም ቻናል።

# የሀብት መንገድ

# Rich Dad Poor Dad

ሀብታሞች ለልጆቻቸው ስለገንዘብ የሚያስተምሯቸው ድሆችና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ግን የማያውቁት ምስጢር!

በሮበርት ኪዮሳኪ

ከሻሮን ሌችተር ጋር በመተባበር

ትርጉም፦ ብርሃኑ በላቸው

# የሀብት መንገድ

# Rich Dad Poor Dad

ሮበርት ኪዮሳኪ

ከሻሮን ሌችተር ጋር በመተባበር

ትርጉም፡ ብርሃኑ በላቸው

© የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው::

የመጀመሪያ ዕትም ፡- ሐምሌ 2004 ዓ.ም.

ሁለተኛ ዕትም፡- ሰኔ 2007 ዓ.ም.

ሦስተኛ ዕትም፡- ሐምሌ 2008 ዓ.ም.

# ማውጫ


| አርዕስት | ገጽ |
| --- | --- |
| መግቢያ | 5 |
| ምዕራፍ አንድ | |
| ሀብታም አባት፤ደሃ አባት | 18 |
| ምዕራፍ ሁለት | |
| አንደኛው ትምህርት | |
| ሀብታሞች ለገንዘብ ብለው አይሰሩም | 25 |
| ምዕራፍ ሶስት | |
| ሁለተኛው ትምህርት | |
| ገንዘብ ነክ ዕውቀት ለምን ያስፈልጋል? | 59 |
| ምዕራፍ አራት | |
| ሦስተኛው ትምህርት | |
| ያለህበትን ቢዝነስ እወቅ | 79 |
| ምዕራፍ አምስት | |
| አራተኛው ትምህርት | |
| የግብር ታሪክ እና የኮርፖሬሽኖች ሚና | 89 |
| ምዕራፍ ስድስት | |
| አምስተኛው ትምህርት | |
| ገንዘብን የፈጠሩት ሀብታሞች ናቸው | 102 |
| ምዕራፍ ሰባት | |
| ስድስተኛው ትምህርት | |
| ለመማር እንጂ ለገንዘብ አትስራ | 122 |
| ምዕራፍ ስምንት | |
| ፈተናዎችን ማለፍ | 135 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ | |
| መጀመር | 148 |
| ምዕራፍ አስር | |
| ተጨማሪ ትፈልጋለህ? | 166 |

# መግቢያ

## ፍላጎት አለ

ትምህርት ቤት ልጆችን ለእውነተኛው ዓለም ዝግጁ ያደርጋቸዋል? ‹ጠንክረህ በማጥናት ጥሩ ውጤት ካስመዘገብክ በርካታ ጥቅማ ጥቅሞች ያሉት ባለወፍራም ደመወዝ ሥራ ታገኛለህ፡፡› ቤተሰቦቼ የሚሉኝ ይህንኑ ነበር፡፡ የሕይወታቸው ትልቁ ዓላማ እኔና ታላቅ እህቴ በህይወታችን ትልቁን ስኬት እንድንጎናፀፍ የሚያበቃንን የኮሌጅ ትምህርት እንድናገኝ ማድረግ ነበር፡፡ በመጨረሻ በ1976 ከፍሎሪዳ ስቴት ዩኒቨርስቲ በአካውንቲንግ ስመረቅ የወላጆቼ ሕልም እውን ሆነ፡፡ በሕይወታቸው ታላቁ ስኬት ነበር፡፡ መጀመሪያ በታቀደው መሰረት በ‹ቢግ-8› የአካውንቲንግ ተቋም ውስጥ ተቀጠርኩ፡፡

ባለቤቴ ማይክልም የተከተለው ተመሳሳይ መንገድ ነው፡፡ ሁለታችንም ጠንክረው ከሚሰሩና ለሥራቸው ልዩ ሥነ ምግባር ካላቸው ቤተሰቦች ነው የተገኘነው፡፡ ማይክልም በዲግሪ ተመርቋል፡፡ መጀመሪያ በምህንድስና በኋላ ላይ ደግሞ በሕግ፡፡ እንደተመረቀም ዋሽንግተን ውስጥ የፈጠራ መብት ላይ የሚሰራ የተከበረ የሕግ ተቋም ስለቀጠረው የወደፊት ሕይወቱ የተቃና መሰለ፡፡ ዕድሜው ሳይገፋ ጡረታ መውጣት እንደሚችል አሰበ፡፡

በሥራዎቻችን ውጤታማ ብንኾንም ነገሮች እንደጠበቅናቸው አልሆኑም፡፡ ሁለታችንም አሳማኝ በሆኑ ምክንያቶች ሥራ ብንቀያይርም የተትረፈረፈ የጡረታ ገንዘብ በስማችን ለማስመዝገብ አልቻልንም፡፡ የጡረታ ቁጠባችን የሚያድገው በግላችን በምናስቀምጠው ገንዘብ ብቻ ሆነ፡፡

ማይክልና እኔ የተሳካ ትዳርና ሶስት ልጆች አሉን፡፡ ይህንን በምፅፍበት ጊዜ ሁለቱ ኮሌጅ ውስጥ ሲሆኑ አንደኛው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እየጀመረ ነው፡፡ ልጆቻችን የተሻለ ትምህርት እንዲያገኙ ከፍ ያለ ገንዘብ አውጥተናል፡፡

በ1996 አንድ ቀን አንደኛው ልጄ ከትምህርት ቤት ግራ ተጋብቶ ተመለሰ። ተሰላችቶና ማጥናትም አስጠልቶት ነበር። በእውነተኛው ዓለም ላይ ተግባራዊ የማላደርገውን ዕውቀት በማጥናት ጊዜዬን የማጠፋበት ምክንያት ምንድነው? ሲል ሞገተኝ።

ማሰብ ሳያስፈልገኝ ‹‹ምክንያቱም ጥሩ ውጤት ካላመጣህ ወደኮሌጅ መግባት አትችልም›› አልኩት።

‹‹ኮሌጅ ብገባም ባልገባም ሀብታም መሆኔ አይቀርም›› ሲል መለሰልኝ።

‹‹ከኮሌጅ ካልተመረቅህ ጥሩ ሥራ አታገኝማ!›› አልኩት በእናት ጭንቀት። ‹‹ታዲያ ጥሩ ሥራ ካላገኘህ ሀብታም ለመሆን የምታስበው እንዴት ነው?››

ልጄ ባለመርካት ስሜት ጭንቅላቱን ነቀነቀ። እንዲህ ዐይነቱን ምልልስ ከዚህ በፊትም ደጋግመን ፈፅመነዋል። አንገቱን ደፋቶ ዐይኖቹን አቁለጨለጨ። የእናትነት ምክሬ ዛሬም እንደሁልጊዜውም ሰሚ አላገኘም ማለት ነው።

‹‹እማ›› ሲል ጀመረ። አሁን ማዳመጥ የእኔ ተራ ሆነ‹‹ ከጊዜው ጋር እንራመድ እንጂ! እስኪ ዞር ዞር ብለሽ ተመልከቺ። ሀብታሞቹ ሀብታም የኾኑት በትምህርታቸው የተነሳ አይደለም። ማይክል ጆርዳንና ማዶናን ተመልከቺ ቢልጌት የሃርቫርድ ትምህርቱን አቋርጦ ነው ማይክሮሶፍትን መስርቶ ገና በሰላሳዎቹ ዕድሜው የአሜሪካ ሀብታም ሰው ለመሆን የቻለው። በትምህርቱ ሰነፍ የተባለ ነገር ግን በዓመት ከ4 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ የሚያገኝ የቤዝ ቦል ተጫዋች አውቃለሁ።››

በመካከላችን ረዥም ዝምታ ሰፈነ። ለልጄ የምሰጠው ምክር ወላጆቼ ለእኔ ይሰጡኝ ከነበረው ጋር አንድ ዓይነት መሆኑ እየተገለጠልኝ ነበር። በዙሪያችን ያለው ዓለም ተቀይሯል፤ ምክሩ ግን አልተቀየረም።

ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ ለስኬታማነት ማረጋገጫ መኾኑ አክትሟል። ይህንኑ ሀቅም ከልጆቻችን በስተቀር ማንም ያስተዋለው አይመስልም።

‹‹እማ›› ቀጠለ ‹‹እንዳንቺና እንደ አባቴ ላቤን አንጠፍጥፌ መሥራት አልፈልግም። ብዙ ገንዘብ ታገኛላችሁ የምንኖረውም በአሻንጉሊቶች በተሞላ ትልቅ

ቤት ውስጥ ነው። ምክርሽን የምቀበል ከኾነ መጨረሻዬ እናንተን መምሰል ይኾናል፡ ብዙ አሰራለሁ፣ የምከፍለው ታክስና ዕዳዬም ይጨምራል። ቋሚ ሥራ የሚባል ነገር ቀርቷል። ምክንያቱም ስራተኛ ቅነሳና ድርጅትን ማመጣጠን የሚባሉ ነገሮች መጥተዋል። አሁን አሁን ከኮሌጅ የሚመረቁ ተቀጣሪዎች እናንተ ከተቀጠራችሁበት የገንዘብ ዋጋ ባነሰ እንደሚቀጠሩም አውቃለሁ። ሐኪሞችን ተመልከቻቸው። በፊት ያገኙ የነበረውን ያህል ገንዘብ አሁን አያገኙም። በማህበራዊ ዋስትና ወይም በድርጅት ጡረታ ላይ መተማመን እንደማይቻል አውቃለሁ። አዲስ መልስ እፈልጋለሁ።››

ትክክል ነበር። አዲስ መልስ ፈልጓል፤ እኔም። የወላጆቼ ምክር ምናልባት ከ1945 በፊት ለተወለዱ ሰዎች ሰርቶ ይኾናል። በየዕለቱ በሚቀያየረው ዓለም ውስጥ ለተወለድን ለእኛ ግን አደገኛ ነው። ከእንግዲህ ለልጆቼ ‹‹ትምህርት ቤት ሂዱ፣ በርትታችሁ አጥኑና ጥሩ ውጤት አስመዝግባችሁ ጥሩሥራ ፈልጉ›› ልላቸው አልችልም።

የልጆቼን ትምህርት ለመምራት አዲስ መንገድ መቀየስ እንዳለብኝ ተገንዝቤያለሁ፡ እንደእናትም እንደ አካውንታንትም ልጆቻችን በትምህርት ቤት በቂ የገንዘብ ዕውቀት ሲያገኙ አለመቻላቸው ያስጨንቀኛል። ብዙዎች የአሁን ዘመን ታዳጊዎች ገና ሁለተኛ ደረጃን ሳይለቁ ክሬዲት ካርድ ይኖራቸዋል። ነገር ግን በገንዘብ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸውም ኾነ በክሬዲት ካርዶች ላይ ድርብርብ ወለድ እንዴት እንደሚሰራ የሚያውቁት ነገር የለም። በአጭሩ ስናስቀምጠው ስለገንዘብ በቂ ዕውቀት ሳይኖራቸው ከቁጠባ ይልቅ ወጪዎች ልዩ ትኩረት ከሚሰጥበት ዓለም ጋር ለመቀላቀል ዝግጁ አይደሉም።

የመጀመሪያ ልጀ በመጀመሪያ ዓመት የኮሌጅ ቆይታው በክሬዲት ካርድ ዕዳ ተዘፍቆ ሲመጣ ክሬዲት ካርዶቹን እንዲያጠፋቸው ከማድረግም በዘለለ ልጆቼን በገንዘብ ጉዳይ እንዴት ላሰለጥናቸው እንደሚገባ የሚያስተምረኝን ፕሮግራም ፍለጋ ጀመርኩ።

ባለፈው ዓመት አንድ ቀን ባለቤቴ ከቢሮው ደወለልኝ። ‹‹ልታገኚው የሚገባ አንድ ሰው አለ›› አለኝ። ‹‹ሮበርት ኪዮሳኪ ይባላል። ነጋዴና ኢንቨስተር ሲኾን

ለአንድ ትምህርታዊ ፕሮግራም የፈጠራ ባለቤት መብት ለማግኘት እያመለከተ ነው። ስትፈልጊ የነበረው ነገር ይህንን ይመስለኛል።››

**በትክክል ስፈልገው የነበረውን**

ባለቤቴ ማይክ ሮበርት ኪዮሳኪ በማዘጋጀት ላይ የሚገኘው ‹‹CASH FLOW›› የተሰኘ ጨዋታ በጣም ስለመሰጠው ሁለታችንም በጨዋታው የሙከራ ሂደት ተሳታፊ እንድንሆን ነገሮችን አመቻቸ። ትምህርታዊ ጨዋታ በመሆኑ በኮሌጅ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ የነበረችው ልጄ ተሳታፊ እንድትሆን ስጠይቃት ፈቃደኛ ሆነች።

15 ያህል ሰዎች በሶስት ምድብ ተከፍለን በሙከራው ላይ ተሳተፍን። ማይክ ትክክል ነበር። ስፈልግ የኖርኩት ትምህርታዊ ፕሮግራም ይኸው ነው። የሚመስለው ባለቀለም የሞኖፖሊ ቦርድ ሆኖ መሃሉ ላይ ጥሩ የለበሰ አይጥ አለ። ይሁንና ከሞኖፖሊ በተለየ መልኩ ሁለት ልብ መስመሮች አሉ። አንድ ከውስጥ አንድ ከውጪ። የጨዋታው ዓላማ ከውስጣዊ መስመር መውጣትና (ሮበርት ራት ሬስ ብሎ ከሚጠራው) ሮበርት ‹‹ፈጣኑ መስመር›› ብሎ ወደሚጠራው ውጫዊ መስመር መድረስ ነው። ‹‹ፈጣኑ መስመር›› ሀብታሞች በእውነተኛው ዓለም የሚጫወቱትን ጨዋታ የሚያሳይ ነው።

ሮበርት ስለ ‹‹ራት ሬስ›› አብራራልን።

‹‹የአብዛኛውን የተማረና ጠንክሮ የሚሰራ ሰው ሕይወት ብትመለከቱት ተመሳሳይ ጎዳና ነው ያለው። ልጁ ተወልዶ ወደትምህርት ቤት ያመራል። ልጁ ጥሩ ውጤት አግኝቶ ኮሌጅ መግባት ሲችል ወላጆቹ ይኮሩበታል፤ ይደሰታሉ። ከዚያም ልጁ ይመረቅና ምናልባትም ሁለተኛ ዲግሪውን ይሰራና አስቀድሞ እንደታቀደው ያደርጋል። ጥሩና የተረጋጋ ሥራ ፍለጋ። ልጁ የሚፈልገውን ሥራ ያገኘውና ሐኪም፣ ጠበቃ ይሆናል፣ ወይም መንግስትን ያገለግላል። በአጠቃላይ ልጁ ገንዘብ መሥራት፤ ክሬዲት ካርዶችም በብዛት ጥቅም ላይ መዋል ይጀምራሉ።

‹‹የሚያጠፋው ገንዘብ ስላለው ልጁ ሌሎች እሱን መሰል ወጣቶች ወደሚዝናኑባቸው ቦታዎች ይሄዳል፤ ይዝናናል፤ የፍቅር ጓደኝነት ይመሰርታል፤

ምናልባትም ያገባል። አሁን ሕይወት ድንቅ ትሆናለች። ምክንያቱም ወንዱም ሴቷም ይሰራሉ። ሁለት ገቢዎች ማግኘት መታደል ነው። ስኬታማነት ይሰማቸዋል። ቤትና መኪና ለመግዛት ልጆቻቸውን ይዘው ሽርሽር ለመሄድ ይወስናሉ። የሚያስፈልጋቸው ገንዘብ እጅግ ከፍ ይላል። ደስተኞቹ ጥንዶች ሥራቸው አስፈላጊ ነገር መሆኑን ያምኑበትና ጠንክረው መሥራት ይጀምራሉ፤ እድገት ለማግኘትም ይጥራሉ። ጠንካራ ሰራተኞች ይሆናሉ። የተሻለ ገንዘብ ማግኘት እንዲችሉም ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርታቸውን ያሻሽላሉ። ምናልባትም ሁለተኛ ሥራ ይጀምራሉ። ገቢያቸው ከፍ ይላል። በዚያው ልክ ግን የሚከፍሉት የገቢ ታክስ፣ የአዲሱ ቤታቸው ወጪ እንዲሁም ማህበራዊ ዋስትና ክፍያቸው ያድጋል። ወርሃዊ ደመወዛቸው ከፍተኛ ሆኖ ሳለ የት እንደሚገባ ግን ግራ ይገባቸዋል። የተወሰኑ አክሲዮኖችን ይገዛሉ። የልጆቻቸው እድሜ አምስት ወይም ስድስት ሲደርስ ለትምህርት ቤት የሚሆን ገንዘብ ማስቀመጥ የሚያስፈልግበት ጊዜ ይመጣል፣ ጎን ለጎንም ለጡረታቸው የሚሆን ቁጠባም እንዲሁ።

‹‹እነዚያ ከ35 ዓመታት በፊት የተወለዱት ደስተኛ ጥንዶች አሁን ቀሪዎቹን የሥራ ዘመናት ወጥመድ ውስጥ ገብተው ያሳልፏቸዋል። የሚሰሩት ለድርጅቱ ባለቤት፣ ለመንግስት ግብር እንዲሁም ለባንኮች የብድርና የክሬዲት ካርድ ዕዳን ለመክፈል ይሆናል።

‹‹ከዚያም ልጆቻቸውን ጠንክራችሁ አጥኑ፣ ጥሩ ውጤት አምጡና ጥሩና አስተማማኝ ሥራ አግኙ›› ብለው ይመክራሉ። ስለገንዘብ ምንም የተማሩት ነገር የለም። አዙሪቱ በቀጣዩ ትውልድ ዘንድም ይቀጥላል። ራት ሬስ ይህ ነው።

ከራት ሬስ ለማምለጥ ብቸኛው መንገድ ምናልባትም ከምንም በላይ የሚከብዱት ሁለት ዘርፎች (አካውንቲንግና ኢንቨስቲንግ) መረዳት ነው። በአንድ ወቅት በታላቅ የአካውንቲንግ ተቋም ውስጥ እንደሰራ ሰርቲፋይድ ፕሮፌሽናል አካውንታት ሮበርት እነዚህን ሁለት ዘርፎች አስደሳችና አጓጊ የጨዋታ አካላት ያደረገበት መንገድ አስደነቀኝ። ጨዋታው አጓጊና አስደሳች በመሆኑ ከራት ሬስ ለመውጣት በርትተን ስንሰራ እየተማርን መሆኑን ረስተነው ነበር፡

ከሙከራው በኋላ ከልጁ ጋር ከሰዓት በኋላውን ከዚህ ቀደም ተወያይተንባቸው የማናውቃቸውን ሀሳቦች በማንሸራሸር በአስደሳች ሁኔታ አሳለፍነው። እንደአካውንታንት ኢንካም ስቴትመንትና ባላንስ ሺትን በሚያሳትት ጨዋታ ሰይ መሳተፍ አስደሳች ነበር። እናም ልጁን ጨምሮ በዙሪያዬ የነበሩትን ሰዎች ያልገቧቸውን ነገሮች በማብራራት አግዛቸው ነበር።

እኔ ጨዋታውን በ5 ደቂቃ ውስጥ ሳጠናቅቅ ጨዋታው ግን ለሶስት ሰዓታት ቀጥሎ ተካሄደ።

በኔ ጠረጴዛ ዙሪያ አንድ የባንክ ሰራተኛ፣አንድ ነጋዴና አንድ የኮምፒዩተር ፕሮግራመር ነበሩ።በጣም ያስደነገጠኝ ነገር እነዚህ ሰዎች በሕይወታቸው በጣም አስፈላጊ ስለኾነው የሂሳብ አያያዝም ሆነ ኢንቨስትመንት ምንም ዓይነት እውቀት የሌላቸው መኾኑ ነበር።በሕይወታቸው ውስጥ የገንዘብ ፍሰታቸውን እንዴት ይቆጣጠሩታል ስልም ተገረምኩ።የ19 ዓመቷ ልጄ ነገሩን ባትረዳው ይገባኛል፤እነዚህ የበሰሉና ከእሷ እጥፍ በሚኾን ዕድሜ ላይ የሚገኙት ግን አለመረዳታቸው ያስደንቃል።

ከጨዋታው ከወጣሁ በኋላ ለሁለት ሰዓታት ልጄና ሌሎች ሰዎች ጨዋታውን እንዴት እንደሚያካሂዱት እየተከታተልኩ ነበር። ምንም እንኳን ሰዎቹ እየተማሩ በመኾናቸው ደስተኛ ብሆንም ስለገንዘብ ያላቸው ግንዛቤ እጅግ ዝቅ ያለ መኾኑ ግን አስደንግጦኛል።በገቢያቸውና በባላንስ ሺታቸው መካከል ያለውን ግንኙነት አይረዱትም።ንብረት ሲገዙና ሲሸጡ እያንዳንዱ የንግድ ሂደት ወርሃዊ የገንዘብ ፍሰታቸው ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ይረሱታል።በእውነተኛው ዓለምም በርካታ ሚሊየን ሰዎች እነዚህን ትምህርቶች ባለማግኘታቸው በገንዘብ ችግር ውስጥ እንደሚዳክሩ አሰብኩ።

ደስ የሚለው ነገር ጨዋታውን ለማሸነፍ ያላቸው ፍላጎት እውነታውን በመሸፈኑ ዕድለኛ ናቸው ስል ለራሴ አሰብኩ። ሮበርት ጨዋታው እንዲያበቃ ካደረገ በኋላ ለ15 ደቂቃ ያህል ስለ "ካሽፍሎው" ጨዋታ እንድንነጋገር አደረገን።

በኔ ጠረጴዛ ዙሪያ ከነበሩት መካከል ነጋዴው ደስተኛ አልነበረም:: ጨዋታውን አልወደደውም::‹‹ይህንን ማወቅ አያስፈልገኝም::›› አለ ጮክ ብሎ:: ‹‹ስለዚህ ጉዳይ የሂሳብ ባለሙያዎችን፣የባንክ ሰራተኞችንና ጠበቆችን እቀጥራለሁ››::

የሮበርት ምላሽ ‹‹ሀብታም ያልሆኑ በርካታ የሂሳብ ባለሙያዎች መኖራቸውን አስተውለሃል? የባንክ ሰራተኞች፣ጠበቆች፣የስቶክ ደላሎችና የሪል ስቴት ደላሎችም እንዲሁ::ብዙ ያውቃሉ፤ጎበዝ ናቸው፤ነገር ግን አብዛኞቹ ሀብታም አይደሉም::ትምህርት ቤቶች ሀብታሞች የሚያውቁትን ስለማያስተምሩ ምክር የምንጠይቀው ከነዚህ ሰዎች ነው:: ነገር ግን አንድ ቀን በጠዋት ወደስራ ለመግባት እየተጣደፍክ የትራፊክ መብራት ላይ ቆመህ ወደ ግራ ስትመለከት የሂሳብ ባለሙያህም እንዳንተው በመብራት ተይዞ ታየዋለህ:: ወደ ቀኝ ስትዞር ደግሞ የባንክ ባለሙያህን ታየዋለህ::ያ አንዳች ነገር ሊነግርህ ይገባል::››

የኮምፒዩተር ፕሮግራመሩም ደስተኛ አልነበረም:: ‹‹ይህንን የሚያስተምረኝ ሶፍትዌር መግዛት እችል ነበር›› አለ::

በአንፃሩ የባንክ ባለሙያው ተነሳስቶ ነበር::‹‹ የሂሳቡን ክፍል ትምህርት ቤት ውስጥ ተምሬው ነበር::ነገር ግን በእውነተኛው ዓለም እንዴት እንደምጠቀምበት አላውቅም ነበር:: አሁን አውቄያለሁ:: ከአዙሪቱ ራሴን ማውጣት አለብኝ›› አለ::

ከሁሉም በላይ ልቤን የነካኝ ግን የልጇ አስተያየት ነበር::

‹‹የሚያዝናና ትምህርት ነበር:: ገንዘብ እንዴት እንደሚሰራና እንዴት መነገድ እንደሚገባ ተምሬያለሁ››አለች::

አክላም ‹‹አሁን ሙያዬን የምመርጠው የሚከፈለኝን መጠን አስቤ ወይም የቅጥር ደህንነት ለማግኘት ሳይሆን ለምፈልገው ዓይነት ስራ መሆን እንደሚገባው አውቄያለሁ:: ይህ ጨዋታ የሚያስተምረውን ካወቅሁ የምፈልገውን መስራትም ሆነ ልቤ የፈቀደውን ማጥናት እችላለሁ:: ይህንን ከተማርኩ እንደአብዛኞቹ የክፍል ጓደኞቼ ስለ ቅጥርና ማህበራዊ ዋስትና አልጨነቅም::››

ከጨዋታው በኋላ ከሮበርት ጋር ለመወያየት ባልችልም ሌላ ጊዜ ተገናኝተን ከጨዋታው በኋላ ከሮበርት ጋር ለመወያየት ባልችልም ሌላ ጊዜ ተገናኝተን ስለፕሮጀክቱ ለማውራት ቀጠሮ ያዝን::በጨዋታው አማካኝነት በርካቶች ሀብታም

እንዲሆኑ እንደሚፈልግ ስላወቅሁ ስለ ዕቅዶቹ ተጨማሪ ነገሮችን ለመስማት ጓጉቼ ነበር፡፡

በቀጣዩ ሳምንት ባለቤቴና እኔ ሮበርትና ባለቤቱን ለእራት ጋበዝናቸው፡፡ በዚህ መልኩ ስንገናኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ቢሆንም ለዓመታት የምንተዋወቅ ያህል ነበር የተግባባነው፡፡ በርካታ የጋራ ነገሮች እንዳሉን አስተዋልን፡፡ ከስፖርት እስከ ምግብ ምርጫዎቻችን ብሎም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን አንስተን ተነጋገርን፡፡ አብዛኞቹ አሜሪካውያን በጡረታቸው ዘመን ስለምን ገንዘብ እንደማይኖራቸው፣ስለ ማህበራዊ ዋስትናና የሕክምና ዋስትና ረዥም ጊዜ ወስደን አወራን፡፡ ልጄ የ75 ሚሊየን ወላዶችን ጡረታ ወጪ ለመሸፈን ትገደዳለች? በጡረታ ቁጠባ ላይ መተማመን ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ተግባባን፡፡

የሮበርት ቀዳሚ ስጋት በአሜሪካም ሆነ በመላው ዓለም ባላቸውና በሌላቸው መካከል ያለው ክፍተት እያደገ መምጣቱ ነው፡፡ ሮበርት ሥራ በመፍጠርና በንግድ ዓለም ሲዞር ከቆየ በኋላ በ47 ዓመቱ ጡረታ ለመውጣት ችሎ ነበር፡፡ ወደሥራ የተመለሰው እኔ ለልጆቼ ያለኝን ዓይነት ስጋት እሱም ጋ ስላለ ነው፡፡ ዓለም እየተቀየረች ትምህርት ግን ባለበት እየሄደ እንደሆነ አውቋል፡፡ እንደሮበርት እምነት ህጻናት ጊዜያቸውን በትምህርት ቤት የሚያሳልፉት ለሕይወታቸው የማይጠቅሟቸውን በርካታ ነገሮች ሲማሩ ነው፡፡

‹‹ዛሬ ለአንድ ልጅ ሊመከር የሚችለው አደገኛው ምክር‹ ተምረህ ጥሩ ውጤት አምጣና አስተማማኝ ሥራ አግኝ› የሚለው ነው›› ይላል ደጋግሞ፡፡ ‹‹ ይሀ ያለፈበትና መጥፎ ምክር ነው፡፡ በአውሮፓ፣እስያና ደቡብ አሜሪካ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ብታዩ ኖሮ እናንተም የእኔን ስጋት ትጋሩ ነበር›› ይላል፡፡

ሮበርት የልጆቻችሁ የወደፊት ሕይወት አስተማማኝ የገንዘብ መሰረት ላይ እንዲገነባ የምትፈልጉ ከሆነ በአሮጌው ደንብ ልትመሩ አትችሉም ብሎ ያስባል፡፡

‹‹አሮጌ ደንብ ስትል ምን ማለትህ ነው›› የሚል ጥያቄ አቀረብኩለት፡፡

‹‹ አንድ ኩባንያ አቅሙን ሊያሳንስ ሲያቅድ ምን ይፈጠራል?›› አለኝ፡፡

‹‹ሰዎች ከሥራ ይቀነሳሉ፡፡ ቤተሰቦች ይጎዳሉ፡፡ የሥራ አጦች ቁጥር ከፍ ይላል››

‹‹አዎ። ግን አክስዮን ሽያጭ ዝርዝር ውስጥ ያለ ኩባንያ በእንደዚህ ዓይነቱ ጊዜ ምን ያጋጥመዋል?››

‹‹ የአክስዮኖቹ ዋጋ ከፍ ይላል።የሰራተኛ ወጪ ሲቀነስ ገበያው ይደራል።››

‹‹ልክ ነው። እናም የአክስዮኑ ዋጋ ከፍ ሲል እንደኔ ዓይነቶቹ የአክስዮን ባለድርሻዎች ሀብታችን ያድጋል። ለዚህ ነው በተለየ ደንብ መጫወት ማለቴ። ተቀጣሪዎች ሲሸነፉ ነጋዴዎች ያሸንፋሉ።››

ሮበርት ማብራራት የፈለገው በተቀጣሪና በቀጣሪ መካከል ስላለው ልዩነት ብቻ ሳይሆን የራስን ዕድል በራስ ስለመወሰንና የመወሰን ስልጣኑን ለሌላ አሳልፎ በመስጠት መካከል ስላለው ልዩነትም ነው።

‹‹ለአብዛኞቹ ግን ያ ነገር ለምን እንደሚከሰት አይገባቸውም። ፍትሃዊ እንዳልሆነ ብቻ ነው የሚያስቡት።››

‹‹ለዚህ ነው ልጅን ጥሩ ትምህርት አግኝ ብሎ መምከር ብቻውን ሞኝነት የሚኾነው›› አለ። ‹‹ከትምህርት ቤት የሚገኘው ትምህርት ልጆችን ለእውነተኛው ዓለም ያዘጋጃል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። እያንዳንዱ ልጅ ተጨማሪ ትምህርት ያስፈልገዋል። የተለየ ትምህርት። እናም ደንቡን መረዳት አለባቸው። የተለዩትን ደንቦች።››

‹‹ሀብታሞች የሚመሩባቸው ደንቦች አሉ፤ቀሪዎቹ 95 ከመቶ ሰዎች የሚመሩባቸው ደንቦችም እንዲሁ። 95 ከመቶዎቹ እነዚያን ደንቦች የሚማሩቸው ከትምህርት ቤትና ከቤት ነው። በዚህ የተነሳ ነው ልጅን ጠንክረህ አጥናና ጥሩ ውጤት አስመዝግብ አስተማማኝ ሥራም ፈልግ ብሎ መምከር አዋጪ ያልሆነው።የዚህ ዘመን ልጆች ደረጃው ከፍ ያለ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል፤አሁን ያለው የትምህርት ስርዓት ግን ይህንን ማድረግ አይችልም። ያላቸው የኮምፒዩተር ብዛት ወይም ትምህርት ቤቶቹ የሚያወጡት ወጪ አያስጨንቀኝም። አንድ የትምህርት ሥርዐት የማያውቀውን ነገር እንዴት ሊያስተምር ይችላል?››

ታዲያ ወላጆች ትምህርት ቤት የማያስተምራቸውን ለልጆቻቸው የሚያስተምሩት እንዴት ነው? ሂሳብ አያያዝን ለልጆች ማስተማር እንዲሰለቹ አያደርጋቸውም?ለራሴ

ንግድ ውስጥ ለመግባት ስጋት እያለብኝ ለልጆቼ ማስተማር የምችለው እንዴት ነው?ልጆቼን ከስጋት ነጻ በሆነው መንገድ እንዲንቀሳቀሱ ከመምከር ይልቅ ጨዋታውን በብልጠት እንዲወጡት ማስተማርን መረጥኩ።

‹‹ታዲያ ልጆችን እስካሁን የተነጋገርንባቸውን ነገሮች የምታስተምራቸው እንዴት ነው? ወላጆችስ ለራሳቸው የማይረዱትን ነገር ቀለል አድርገው እንዲያቀርቡት የምናደርገው በምን መንገድ ነው?›› ስል ጠየቅሁት።

‹‹በዘርፉ ላይ መጽሐፍ ጽፌያለሁ›› አለ።

‹‹የት አለ?››

‹‹ኮምፒዩተሬ ውስጥ። ለዓመታት በተበታተነ ሁኔታ እዚያ ውስጥ ተቀምጦ ቆይቷል።በየጊዜው እጨምርበታለሁ፤ ነገር ግን አሰባስቤ ለማደራጀት አልቻልኩም። የመጀመሪያው መጽሐፌ ከፍተኛ ሽያጭ ካስመዘገበ በኋላ ነው ይኸኛውን መጻፍ የጀመርኩት።ነገር ግን በተበጣጠሰ ሁኔታ ነው ያለው።››

በእርግጥም በተበታተነ ሁኔታ ነበር ያለው። የተበታተነውን ካነበብኩ በኋላ በውስጡ ጠቃሚ ነገር እንዳለና ሌሎችም ሊያውቁት የሚገባ መኾኑን ስላመንኩበት መጽሐፉን ከሮበርት ጋር በጋራ ለማዘጋጀት ወሰንኩ።

አንድ ታዳጊ ምን ያህል የገንዘብ ዕውቀት እንደሚያስፈልገው ሮበርትን ጠየቅኩት። እንደልጁ ኹኔታ ይወሰናል አለኝ።በልጅነት ዘመኑ ሀብታም መኾን ይፈልግ እንደነበርና የሚያስተምረው ሀብታም አባት በማግኘቱ ዕድለኛ እንደነበረ ያውቃል። የስኬት ብቸኛው መሰረት ትምህርት እንደኾነ ያምናል ሮበርት። ሙያዊ ክህሎቶች በጣም አስፈላጊ እንደኾኑት ሁሉ የገንዘብና የተግባቦት ክህሎቶችም እጅግ አስፈላጊ ናቸው።

ቀጥሎ የሚመጣው ሮበርት ከደሀውና ከሀብታም አባቱ ጋር ባሳለፋቸው ጊዜያት በሕይወት ዘመኑ ያዳበራቸው ክህሎቶች ታሪክ ነው። የሁለቱ አባቶቹ ንጽጽር ጠቃሚ አቋም እንዲያዳብር አስችሎታል። የመጽሐፉን አርትኦት የሠራሁትና ያቀናጀሁት እኔ ነኝ። ይህንን መጽሐፍ የምታነቡ የሂሳብ ባለሙያዎች ብትኖሩ የሂሳብ ዕውቀታችሁን ወደጎን አድርጋችሁ ከሮበርት ዕይታ ተቋደሱ። ምንም እንኳን አብዛኞቹ ዕይታዎቹ

በርካታ የአካውንቲንግ ደንቦችን የሚቃረኑ ቢሆኑም ስኬታማ ነጋዴዎች ውሳኔዎቻቸውን የሚቃኙባቸውን መንገዶች የሚያሳዩ ናቸው።

እንደወላጅ ልጆቻችንን ትምህርት ቤት ገብታችሁ ጥሩ ውጤት አምጡ ብለን ስንመክራቸው ያንን የምናደርገው ከልማድ በመነሳት ነው። ሁሌም ትክክለኛው መንገድ እሱ ነበር። ሮበርትን መጀመሪያ ሳገኘው ዕሳቤው አግራሞትን ፈጥሮብኝ ነበር። ሁለት አባቶች እንደነበረው ሰው ሮበርት ለሁለት ግቦች እንዲሰራ ተምሯል። የተማረው አባቱ ለኮርፖሬሽን እንዲሰራ ሀብታሙ አባቱ ደግሞ የኮርፖሬሽን ባለቤት እንዲሆን ይመክሩት ነበር። ሁለቱም መንገዶች ትምህርት ቢያስፈልጋቸውም የጥናት ዘርፉ ግን የተለያየ ነው። የተማረው አባቱ ሮበርት ጎበዝ እንዲሆን ይፈልጋል። ሀብታሙ አባቱ ደግሞ ጎበዝ ሰዎችን እንዴት መቅጠር እንደሚቻል እንዲማር ይፈልጋል።

ባለሁለት አባት መሆን በርካታ ችግሮችን ፈጥሯል። የሮበርት ወላጅ አባት የሃዋይ ግዛት የትምህርት ተቆጣጣሪ ነበር። ሮበርት 16 ዓመት ሲሞላው «በትምህርትህ ጥሩ ውጤት ካላመጣህ ጥሩ ሥራ አታገኝም» የሚለው ምክር የሚያሳድርበት ተፅዕኖ እናሳ ኾነ። የሕይወት መስመሩ ለኮርፖሬሽን መስራት ሳይሆን የኮርፖሬሽን ባለቤት መኾን እንደኾነ አስቀድሞ ወስኗል። እንዲያውም በጣም ጎበዝ የትምህርት ቤት አማካሪ ባያጋጥመው ኖሮ ኮሌጅ መግባቱ ራሱ አጠራጣሪ ነበር። ይህንን እሱም ያምናል። የራሱን ንብረት ለማፍራት ጓጉቶ የነበረ ቢሆንም መጨረሻ ላይ የኮሌጅ ትምህርቱ ጠቃሚ ስንቅ እንደሚኾነው ተስማማ።

እውነቱን ለመናገር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ሀሳቦች ለብዙዎቹ ወላጆች የሕልም ያህል የኾኑና ልማድን የሚያናጉ ናቸው። የተወሰኑ ወላጆች ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲቆዩ ለማድረግ በመባከን ላይ ናቸው።ነገር ግን ጊዜው እየተለዋወጠ ከመኾኑ አንጻር እንደወላጅ ለአዳዲስ ሀሳቦች ራሳችንን መክፈት ይኖርብናል።ልጆችን ተቀጣሪ እንዲኾኑ መምከር ከሚያገኙት ገቢ ውስጥ በርካታውን ለታክስና ለማህበራዊ ዋስትና እንዲያባክኑ ማድረግ ነው። ግብር የሰዎች ትልቁ ወጪ መኾኑም እውነት ነው። አዳዲስ ዕሳቤዎች ያስፈልጋሉ፤ይህ መጽሐፍም የያዘው እነሱን ነው።

ሮበርት ኪዮሳኪ

## የሀብት መንገድ

ሮበርት እንደሚለው ሀብታሞች ልጆቻቸውን የሚያስተምሩት በተለየ መንገድ ነው። ሮበርት እንደሚለው ሀብታሞች ልጆቻቸውን በቤት ውስጥ በራት ጠረጴዛ ዙሪያ ነው የሚያስተምሩት። እነዚህ ሀሳቦች ልጆቻችሁ ጋር ልትወያዩባቸው የምትፈልጓቸው ላይሆኑ ይችላሉ። ቢሆንም ምናልባትም ልጆቻችሁ ጋር ልትወያዩባቸው የምትፈልጓቸው ላይሆኑ ይችላሉ። ቢሆንም ስለተመለከታችኋቸው አመሰግናለሁ። ፍለጋችሁን እንድትገፉበትም እመክራለሁ። እንደ እናትና እንደ ተቀጣሪ ጥሩ ውጤት የማስመዝገብና ስራ የመፈለግ ፅንሰ ሀሳብ ያለፈበት አስተሳሰብ ነው። ልጆቻችን ከዚህ የተሻለ ምክር ያስፈልጋቸዋል። አዳዲስ ሀሳቦችና የተለየ ትምህርት ያስፈልገናል።ምናልባትም ልጆቻችን ጥሩ ተቀጣሪ እንዲሆኑ ከመንገር ጎን ለጎን የራሳቸውን ኮርፖሬሽን ለማቋቋም እንዲጥሩ ማበረታታት መጥፎ ሀሳብ አይደለም። እንደ እናት ይህ መጽሐፍ ሌሎችን ወላጆችም እንደሚያግዛቸው ተስፋዬ ነው።ማንም ሰው ምርጫው ከሆነ ባለፀጋ መሆን እንደሚችል የሮበርት መልዕክት ነው። ዛሬ የጽዳት ሰራተኛ፣አትክልተኛ ወይም ሥራ አጥ ብትሆን እንኳን ራስህንና የምትወዳቸውን የተሻለ ገንዘብ ነክ ዕውቀት እንዲኖራችሁ ለማድረግ ትችላለህ። ገንዘብ ነክ ዕውቀት የገንዘብ ችግራችንን በአእምሯችን አማካኝነት የምንፈታበት መላ መሆኑን ልብ በል።

ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በተለቀና በፈጠነ ሁኔታ በዓለም ዘንድ ለውጦች እየተካሄዱ ነው። ማንም እርግጡን ሊያውቅ አይችልም፣ነገር ግን ወደፊት አሁን ከምናውቀው እውነታ የተለዩ ለውጦች እንደሚመጡ እርግጥ ነው።የወደፊቱን ማን ያውቃል? ያም ሆነ ይህ ያሉን አማራጮች ሁለት ናቸው። በጥንቃቄ መጫወት እና በብልጠት ለመጫወት ተምሮና ተዘጋጅቶ ብሉም የእናንተንና የልጆቻችሁን ገንዘብ ነክ ዕውቀት አዳብሮ መጠበቅ።

ሻሮን ሌችተር

# ሀብታም አባት፤ደሃ አባት

# ምዕራፍ አንድ

# ሀብታም አባት፤ደሃ አባት

**በሮበርት ኪዮሳኪ**

ሁለት አባቶች ነበሩኝ፤ሀብታምና ደሃ። አንደኛው በጣም የተማረና ባለዶክትሬት ዲግሪ የአራት ዓመቱን የኮሌጅ ትምህርት ከሁለት ዓመት ባነሰ ጊዜ ለማጠናቀቅ የቻለ ጎበዝ ነው። ከዚያም ወደ ስታንፎርድ ዩኒቨርሲቲ አምርቶ ተጨማሪ ጥናቱን በሙሉ ስኮላርሺፕ አካሂዷል። ሌላኛው አባቴ ደግሞ ከስምንተኛ ክፍል አላለፈም።

ሁለቱም አባቶቼ ሕይወታቸውን ጠንክረው በመሥራት ያሳለፉ ስኬታማ ሰዎች ናቸው። ሁለቱም በቂ ገቢ ያገኙ ነበር። እንዲያም ሆኖ አንደኛው ሕይወቱን የገፋው በገንዘብ ችግር ሲዳክር ነው። ሌላኛው ግን ከሃዋይ ባለጸጋ ሰዎች መካከል አንዱ ለመሆን ችሏል።አንደኛው ለቤተሰቡ፣ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ለቤተክርስቲያን በርካታ ሚሊዮን ዶላሮች ትቶ ሲያልፍ ሌላኛው ደግሞ የሚከፈሉ ዕዳዎች ትቶ ነው የሞተው።

ሁለቱም ጠንካራ፣ባለግርማ ሞገስና ተፅዕኖ ፈጣሪ ነበሩ። ሁለቱም ምክር ይለግሱኝ ነበር፤ምክራቸው ግን አንድ ዓይነት አልነበረም። ሁለቱም በትምህርት አጥብቀው ያምናሉ፤ምን ዓይነት ትምህርት በሚለው ግን ይለያያሉ።

አንድ አባት ብቻ ቢኖረኝ ኖሮ ምክሩን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ምርጫው ቀላል በሆነ ነበር። ከሁለት አባቶች ምክር ማግኘት ግን የሁለት ሰዎችን አመለካከት የማነጻጸር ዕድል ሰጠኝ፤የደሃና የሀብታም።

ችግሩ በወቅቱ ሀብታሙ ሀብታም ደሃውም ደሃ አልሆኑም ነበር። ሁለቱም ሥራቸውን በማካሄድ ላይ ሲሆኑ ሁለቱም የገንዘብ ውጣ ውረድ ላይ ነበሩ። ልዩነታቸው በገንዘብ ላይ ባላቸው አመለካከት ነበር።

ለምሳሌ አንደኛው አባቴ «የገንዘብ ፍቅር የመጥፎ ነገሮች ሁሉ ምንጭ ነው።» ሲል ሌላኛው ደግሞ «የገንዘብ እጦት የመጥፎ ነገሮች ሁሉ ምንጭ ነው» ይላል።

እንደ ታዳጊ በሁለት ጠንካራ አባቶች ተጽዕኖ ስር መውደቅ አስቸጋሪ ነበር። ጥሩ ልጅ መሆንና ሁለቱንም ማዳመጥ እፈልጋለሁ። ግን ሁለቱም የሚሉት አንድ ዓይነት አልነበረም።በተለይ በገንዘብ በኩል ያላቸው አመለካከት በሁለት ጥግ የሚገኝ ስለነበር ያደግሁት በመገረምና በጉጉት ነበር። ሁለቱም የሚሉትን ደጋግሜ በማሰብ ረዥም ጊዜ አሳልፍ ነበር።





ብቻዬን የምሆንባቸውን ጊዜያት ያሳለፍኳቸው «ምን ማለቱ ነው?» የሚለውን ጥያቄ ለራሴ በማቅረብ የሁለቱንም አባቶች ንግግር ስመረምር ነው። «አዎ ልክ ነው። በሀሳቡ እስማማለሁ» ማለት ወይም « ሽማግሌው የሚለውን አያውቅም» ብሎ በሀሳቡ አለመስማማት ቀላል ነበር። በምትኩ ሁለት የምወዳቸው አባቶቼ ልጅ መሆኔ በብርቱ አስቤ የራሴን ምርጫ እንዳካሂድ አስገደደኝ።

ሀብታሞች የበለጠ ሀብታም፣ድሆች የበለጠ ደሃ የሚሆኑበት መካከለኛ ገቢ ያላቸው ደግሞ የማያቋርጥ ትግል ውስጥ የሚገቡበት ምክንያት የገንዘብ ትምህርት የሚሰጠው በትምህርት ቤት ሳይሆን በቤት ውስጥ በመሆኑ ነው። አብዛኞቻችን ስለገንዘብ የምንማረው ከወላጆቻችን ነው። እናም ደሃ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚነግሩት «በትምህርትህ ጥሩ ውጤት አስመዝግብ» የሚለውን ነው። ልጁ ግን በጥሩ ውጤት ግን ደግሞ በደሃ ሰው የአእምሮ ይዞታ ከትምህርት ቤት ይመረቃል። ልጁ ገና ታዳጊ እያለ የተማረው ነው።

ስለገንዘብ በትምህርት ቤት ውስጥ ትምህርት አይሰጥም። የትምህርት ቤቶች ትኩረት በሙያዊ ዕውቀቶች ላይ እንጂ በገንዘብ ዕውቀት ላይ አይደለም። ይህ ሀቅ ሀኪሞች፣አካውንታንቶችና የባንክ ባለሙያዎች በጣም ጎበዝ ሆነው ለምን በገንዘብ ችግር ውስጥ እንደሚዳክሩ ይገልጻል። ሀገራዊ ዕዳችንና የገንዘብ ቀውስ ስለገንዘብ ምንም ዕውቀትም ሆነ ስልጠና የሌላቸው ፖለቲከኞችና ኃላፊዎች በሚወስዷቸው ውሳኔዎች የተነሳ የሚከሰት ነው።

ሁለት ተጽዕኖ ፈጣሪ አባቶች ስለነበሩኝ ከሁለቱም ትምህርት ቀስሜያለሁ። ስለሁለቱም አባቶቼ ምክሮች ማብሰልሰልና የእያንዳንዳቸውን ሕይወት መመርመር በጣም ጠቅሞኛል። ለምሳሌ አንደኛው አባቴ «ላደርገው አልችልም» የሚል ልምድ ሲኖርበት ሌላኛው አባቴ ደግሞ እነዚያን ቃላት አይወዳቸውም። በምትኩ «እንዴት ላደርገው እችላለሁ?» የሚለውን ጥያቄ ማቅረብ ይወዳል። አንደኛው ከወጥመዱ ሲያወጣህ ሌላኛው ግን እንድታስብ ያደርግሃል። ሀብታሙ አባቴ ይህንን ሲያብራራው «ላደርገው አልችልም ማለት አእምሮህ ስራ እንዲያቆም ያደርገዋል። እንዴት ላደርገው እችላለሁ ብለህ ስትጠይቅ ግን አእምሮህ ስራ ይጀምራል» ይላል። የተመኘኸውን ነገር ሁሉ ግዛ ማለቱ አይደለም። አእምሮን ዘወትር ስራ በማሰራት ግን ያምናል። « አእምሮዬን በየቀኑ ባሰራሁት ቁጥር እየሰፋና እየተሰለጠ ይሄዳል ። አእምሮዬ ሲሰፋ ደግሞ የማገኘው ገንዘብም ይሰፋል።» ይላል። ላደርገው አልችልም ማለት የስንፍና መገለጫ መሆኑንም ይናገራል።

ሁለቱም አባቶቼ ጠንካራ ሰራተኞች ቢሆኑም ገንዘብን በተመለከተ አንደኛው ጭንቅላቱን እንደሚያስተኛው ሌላኛው ደግሞ ጭንቅላቱን ማሰራት ልማዱ እንዳደረገው ተረዳሁ።

በሂደትም አንደኛው ጠንካራ የገንዘብ መሰረት ሲያዳብር ሌላኛው ደግሞ ደካማ የገንዘብ ይዞታ ውስጥ ገባ፡፡ ልክ በየቀኑ ወደስፖርት ቤት እምርቶ በሚለማመደውና ቤቱ ቁጭ ብሉ ቴሌቪዥን በሚመለከተው መካከል የሚኖረውን ዓይነት ልዩነት ነው፡፡ መደበኛ ስፖርት ጤናማነትን እንደሚያሳድግ ሁሉ አእምሮን ማሰራትም የሀብትን መንገድ ያሰፋል፡፡ ስንፍና ሀብትንም ጤናንም ይቀንሳል፡፡

ሁለቱ አባቶቼ ተቃራኒ አመለካከቶች ነበሯቸው፡፡ አንደኛው ድሆችን ለመንከባከብ ሀብታሞች ከፍ ያለ ግብር መክፈል አለባቸው ብሎ ሲያምን ሌላኛው ግን ግብር የሚሰሩትን እየቀጣ የማይሰሩትን የሚያበረታታ ሂደት ነው ይለዋል፡፡

አንደኛው አባት‹‹ጠንክረህ አጥናና የምትሰራበት ኩባንያ ፈልግ›› ብሎ ሲመክር ሌላኛው ግን ‹‹ ጠንክረህ አጥናና የምትገዛው ጥሩ ኩባንያ ፈልግ›› ይላል፡፡

አንደኛው ‹‹ ሀብታም ያልሆንኩት እናንተ ልጆቼ ስላላችሁ ነው›› ሲል ሌላኛው ‹‹ሀብታም መሆን ያለብኝ እናንተ ልጆቼ ስላላችሁ ነው›› ይላል፡፡

አንደኛው በምንሰባሰብበት ወቅት ስለገንዘብ እንዲወራ ሲያበረታታ ሌላኛው ግን የገንዘብ ወሬ በምንም ዓይነት መልኩ እንዳይነሳ ይከለክላል፡፡

አንደኛው ‹‹ ገንዘብን በተመለከተ ተጠንቀቁ፤አስጊ ንግድ ውስጥ እንዳትገቡ›› ሲል ሌላኛው ‹‹ ስጋቱን ማስወገዱን ተማሩ›› ይላል፡፡

አንደኛው ‹‹ ቤታችን ትልቁና አስተማማኙ ንብረታችን ነው›› ብሎ ሲያምን ሌላኛው ‹‹ቤቱ ዕዳ ነው፡፡ ቤትህን እንደታላቅ ንብረት የምትቆጥር ከሆነ አደጋ ውስጥ ነህ›› ብሎ ያምናል፡፡

ሁለቱም አባቶቼ ዕዳቸውን በጊዜው ይከፍላሉ፡፡ ይሁንና አንደኛው መጀመሪያ ላይ ሲከፍል ሌላኛው መጨረሻ ላይ ይከፍላል፡፡

አንደኛው ፍላጎቱን አንድ ኩባንያ ወይም መንግስት ሊያሟላለት እንደሚገባ ያምናል፡፡ ዘወትር ስለ ደመወዝ ጭማሪ ፤ስለ ጡረታ አበል፤ የህክምና ጥቅማጥቅሞች፤አረፍትና የመሳሰሉት ይጨነቃል፡፡ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው ሥራ ከምንም በላይ አስፈላጊ እንደሆነ ያምናል፡፡ ‹‹ለመንግስት በርትቼ በማገልገሌ ነው እነዚህን ጥቅሞች የማገኘው›› ማለትን ያዘወትራል፡፡

ሌላኛው በገንዘብ ራስን በመቻል ነው የሚያምነው፡፡ የተቀጣሪነት ስነልቦና በርካቶችን ደሃ አድርጎ ያስቀረ ነው በሚል አይወደውም፡፡

አንደኛው ጥቂት ዶላሮችን ለመቆጠብ ይጣጣራል፤ሌላኛው አትራፊ ንግዶችን በቀላሉ ይፈጥራል፡፡



አንደኛው አባቴ ጥሩ ሥራ እንዳገኝ ጥሩ የማንነት መግለጫ እንዴት እ
ሲያስተምረኝ ሌላኛው ግን ጠንካራና ውጤታማ የንግድ ዕቅዶችን የማዘጋጅበትን ነሁ፡፡
የምፈጥርበትን መንገድ ያስተምረኝ

ባለሁለት አባት መሆኔ ሀሳቦች በሰዎች ሕይወት ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ እንድረዳ አስችሎኛል፡፡ ሰዎች ሕይወታቸውን የሚፈጥሩት በሀሳቦቻቸው መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡

ለምሳሌ ደሀው አባቴ ሁሌም‹‹መቼም ሀብታም አልሆንም›› ይል ነበር፡፡ እናም ያ ምኞቱ ዕውን ኾነ፡፡ በአንጻሩ ሀብታሙ አባቴ ዘወትር ለራሱ የሚያረጋግጠው ሀብታምነቱን ነበር፡፡ ‹‹ እኔ ሀብታም ነኝ፤ሀብታሞች ደግሞ ይህንን አያደርጉም፡፡›› የመሳሰሉ ነገሮችን ያዘወትራል፡፡ ከኪሳራ በኋላ የገንዘብ ችግር ውስጥ ኾና እንኳን ራሱን ሀብታም እንደሆነ አድርጎ መውሰድ ይቀናዋል፡፡ ‹‹በድህነትና በቺስታነት መካከል ልዩነት አለ፡፡ቺስታነት ጊዜያዊ ፤ድህነት ግን ዘለዐለማዊ ነው፡፡›› ይላል፡፡

ደሀው አባቴ ‹‹ለገንዘብ ፍላጎት የለኝም›› ወይም‹‹ገንዘብ ለውጥ አያመጣም›› ማለትን ሲያበዛ ሀብታሙ አባቴ ግን ‹‹ገንዘብ ኃይል ነው›› ይላል፡፡

የሀሳቦቻችንን ኃይል ምናልባትም አላወቅነውም ይሆናል፡፡እኔ ግን ለሀሳቦቼ ልዩ ትኩረት መስጠት እንዳለብኝ የተገነዘብኩት ገና በልጅነቴ ነበር፡፡ ደሀው አባቴ ደሀ የኾነው በሚያገኘው ገቢ ምክንያት ሳይሆን በሀሳቦቹና በተግባሮቹ የተነሳ መሆኑን አስተውያለሁ፡፡ በልጅነቴ ባለሁለት አባት በመሆኔ የትኞቹን ሀሳቦች መምረጥ እንዳለብኝ በሚገባ ተምሬያለሁ፡፡ ማንን ነው ላዳምጠው የሚገባኝ፤ሀብታሙን ወይስ ደሀውን አባቴን?

ሁለቱም ትምህርት እጅግ ወሳኝ ነገር በመሆኑ ላይ አንድ ዓይነት አቋም ቢኖራቸውም በአስፈላጊው የትምህርት አይነት ላይ ግን የሀሳብ ልዩነት ነበራቸው፡፡ አንደኛው ጠንክሬ አጥንቼ ጥሩ ዉጤት በማምጣት ጥሩ ክፍያ የሚያስገኝልኝን ሥራ እንድፈልግ ሲመክረኝ ሌላኛው ደግሞ ሀብታም መሆን የምችልበትን መንገድ እንዳጠና፣ገንዘብ የሚሰራበትን መንገድ እንድገነዘብና ገንዘብን የማሰራበትን መንገድ እንዳውቅ ይጎተጉተኛል፡፡ ደጋግሞ የሚለኝ ‹‹ለገንዘብ አልሰራም፤ገንዘብ ለእኔ ይሰራልኛል›› የሚለውን አባባል ነበር፡፡

በዘጠኝ አመቴ ገንዘብን በተመለከተ ከሀብታሙ አባቴ ትምህርት መቅሰምን መረጥኩ፡፡ በዚህም ውሳኔዬ ምክንያት ምንም እንኳን የኮሌጅ ዲግሪዎችን የሰበሰበው ደሀው አባቴ ቢሆንም እሱን ላለማዳመጥ ወሰንኩ፡፡

## ትምህርት ከሮበርት ፍሮስት

ሮበርት ፍሮስት የማደንቀው ባለቅኔ ነው፡፡በርካታ የምወዳቸው ግጥሞች ቢኖሩትም በጣም የምመርጠው ‹‹ያልተኬደበት መንገድ›› የተሰኘውን ነው፡፡ ምክሩን በየቀኑ በተግባር አውለዋለሁ፡፡

## ያልተኬደበት መንገድ

ከፊቴ ያለው ጎዳና ለሁለት የተከፈለ፣

በሁለቱም መንገድ የመሄድ አማራጭ ስለሌለ፣

በአንደኛው መሄድ መምረጥ ግዴታዩ በመኾኑ፣

አንዱን ከሩቅ ሳጤነው የተሞላ ነው በደደኑ፣

ምንጠራ የሚያስፈልገው ዳዋ የዋጠው ነው ደኑ፡፡

ሌላኛው ግን ሰዎች አዘውትረው የረገጡት፣

እጅግ የተለመደው መኾኑን አስተዋልኩት፣

መንገድ ወደመንገድ እንደሚያደርስ ሲያውቀው ልቤ፣

ሳልመለስ እንደምችል እየጠረጠረ ቀልቤ፣

ብዙም ያልተኬደበትን መንገድ በድፍረት ነበር የመረጥኩት፣

ለውጥ የፈጠረልኝም እሱን ኾኖ ነው ያገኘሁት፡፡

*ሮበርት ፍሮስት(1916)*





ለውጡንም የፈጠረው ይኸው ነበር፡፡

ለዓመታት የሮበርት ፍሮስትን ግጥም እየመላለስኩ አሰላስየዋለሁ፡፡ የተማረውን አባቴን ምክር ላለመቀበል መወሰን የሚያሳምም ውሳኔ ነበር፤ ቀጣዩን ሕይወቴን መስመር ያስያዘልኝ ውሳኔ ግን እሱ ነው፡፡

አእምሮየየ አንዴ ከወሰነ በኋላ ስለገንዘብ መማሬን ጀመርኩ፡፡ሀብታሙ አባቴ ለ30 ዓመታት ዕድሜዩ 39 እስከሚሞላ ድረስ አስተምሮኛል፡፡ የሚገባኝን ያህል ማወቄን ሲረዳ ነው ማስተማሩን ያቆመው፡፡

ገንዘብ ከኃይል ምንጮች አንደኛው ነው፡፡ ገንዘብ ይመጣል ይሄዳል፤ከሁሉም የሚበልጠው ግን ስለገንዘብ የሚኖረን ግንዛቤ ነው፡፡

ስለገንዘብ መማር የጀመርኩት ከ9 ዓመቴ ጀምሮ በመሆኑ ሀብታሙ አባቴ የሚነግረኝ ነገሮች ቀላል ነበሩ፡፡ ለሰላሳ ዓመታትም ይደጋገሙ የነበሩት ስድስት ትምህርቶች ነበሩ፡፡ ይህ መጽሐፍ ሀብታሙ አባቴ ያስተማረኝን ስድስቱን ትምህርቶች ቀለል ባለ መልኩ ለማቅረብ የሞከርኩበት ነው፡፡ ትምህርቶቹ መልስ እንዲሆኑ ሳይሆን መንገድ ጠራጊ እንዲሆኑ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በዓለም ላይ የሚፈጠሩ ነገሮች ምንም ቢሆኑ እናንተና ልጆቻችሁ ሀብታሞች መሆን እንድትችሉ ለማስቻል መንገድ የሚጠርጉ ወሳኝ ቁልፎች ናቸው፡፡

## ትምህርት አንድ፡፡

# ሀብታሞች ለገንዘብ ብለው አይሰሩም





## ምዕራፍ ሁለት

## አንደኛው ትምህርት

# ሀብታሞች ለገንዘብ ብለው አይሰሩም

‹‹አባዬ ሀብታም መሆን እንዴት እንደምችል ልትነግረኝ ትችላለህ?››

አባቴ የሚያነበውን ጋዜጣ አስቀመጠና ‹‹ሀብታም መሆን የፈለግከው ለምንድነው?›› አለኝ፡፡

‹‹ምክንያቱም ዛሬ የጂሚ እናት ልጇንና ሌሎች ሶስት ጓደኞቹንበአዲሱ ካዲላካቸው አሳፍራ ለሽርሽር ወደ ባህር ዳርቻ ወሰደቻቸው፡፡ እኔና ማይክ ግን አልተጋበዝንም፡፡ ያልጋበዙን ድሀ ልጆች በመሆናችን እንደሆነ ነገሩን፡፡››

‹‹እንደዚያ አሏችሁ?››

‹‹አዎን›› ስል መለስኩ በሚቴ ተጎድቶ፡፡

አባቴ ጭንቅላቱን በመገረም ነቅንቆ መነጽሩን አስተካክሎ ጋዜጣውን ወደመ፣ንበቡ ተመለሰ፡፡ እኔ ግን ምላሹን ጥበቃ ቆሜ ቆየሁ፡፡

ዓመቱ 1956 ሲሆን ዕድሜዬ ዘጠኝ ነበር፡፡ እንዲጋጣሚ ሆኖ የምንማረው ሀብታሞች ልጆቻቸውን በሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ነበር የምማረው፡፡ እስከ ስድተኛ ክፍል ነጋዴዎችና የስኳር ፋብሪካው ሥራ አስኪያጆች ልጆቻቸውን አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ያስተምራሉ፡፡ ከስድስተኛ ክፍል በኋላ ግን የሀብታሞቹ ልጆች ወደግል ትምህርት ቤት ያመራሉ፡፡ እኛ የምንኖረው የግል ትምህርት ቤቱ በሚገኝበት አቅጣጫ ስለነበር እኔም እዚያ እማራለሁ፡፡ መኖሪያችን ከመንገዱ ወዲያ ማዶ ቢሆን ኖሮ ግን ከእንደኔ ወላጆቹ ዓይነት ከተወለዱ ልጆች ጋር ለመማር እገደድ ነበር፡፡

በመጨረሻ አባቴ ጋዜጣውን አስቀመጠ፡፡ እያሰበ እንደቆየ ገብቶኛል፡፡

‹‹መልካም ልጄ›› ቀስ ብሎ ጀመረ፡፡‹‹ ሀብታም መሆን ከፈለግህ ገንዘብ መስራት እንዴት እንደምትችል መማር አለብህ›› አለኝ፡፡

‹‹ገንዘብ የምሰራው እንዴት ነው?››

‹‹ጭንቅላትህን ተጠቀምበት›› አለኝ ፈገግ እያለ፡፡

ጥምረት ተፈጠረ

በቀጣዩ ጠዋት ለማይክ አባቴ የነገረኝን ነገርኩት:: እስከማውቀው ድረስ ትምህርተ ቤታችን ውስጥ ብቸኛዎቹ የደሃ ልጆች ማይክና እኔ ነበርን:: በርግጥ እኛ ያን ያህል የደሃ ልጆች አልነበርንም፤ነገር ግን ያ ስሜት የሚያድርብን ሌሎቹ አዲስ የቅርጫት ኳስ ጓንት፣አዲስ ብስክሌት፣ሌሎችም በርካታ አዳዲስ ነገሮች ስላሏቸው ነው::

እናትና አባቶቻችን ምግብ፣መጠለያና ልብሶች ያቀርቡልናል:: አባቴ‹‹ ሌላ ነገር የምትፈልግ ከሆነ ሰርተህ አግኘው›› ማለትን ያዘወትር ነበር:: የምንፈልጋቸው ነገሮች ቢኖሩም የ9 ዐመት ልጆች ሆነን ልንሰራ የምንችላቸው ስራዎች ግን አልነበሩም::

‹‹ታዲያ ገንዘብ የምንሰራው እንዴት ነው?›› ሲል ጠየቀኝ ማይክ::

‹‹እኔ እንጃ›› አልኩና ‹‹ ግን አጋሬ መሆን ትፈልጋለህ?›› አልኩት::

ተስማማ::እናም በዚያው ሳምንት ቅዳሜ ማይክ የመጀመሪያው የቢዝነስ አጋሬ ሆነ:: ጠዋቱን በሙሉ አዳዲስ ሀሳቦችን ስናወጣ ስናወርድ አሳለፍነው:: በመጨረሻ ማይክ ከሳይንስ መጽሀፍ ያነበበውን አንድ የቢዝነስ ሀሳብ ለመሞከር ወሰንን::

ለበርካታ ቀጣይ ሳምንታትም እኔና ማይክ ጎረቤቶቻችን ቤት እያንኳኳን የተጠቀሙባቸውን የጥርስ ሳሙና ማስቀመጫዎች እንዲሰጡን እየጠየቅን ሰበሰብን:: በመጨረሻ በቂ የሰበሰብን ሲመስለን ሲዱን በማቅለጥ ሳንቲሞች ለመስራት በበርሜል እሳት አያይዘን ጀመርን::

ይህንን በምንሰራበት ወቅት ድንገት የደረሰብን አባቴ ‹‹ልጆች ምን እየሰራችሁ ነው?›› ሲል ጠየቀን::

‹‹እንድናደርግ የነነገርከንን እየሰራን ነው:: በቅርቡ ሀብታም እንሆናለን›› አልኩት::

አባዬ በሥራችን ከጓደኛው ጋር ተሳሳቀብንና ገንዘብ መስራት የባንኮችና የመንግስት መብት ብቻ መሆኑን ነገረን::

ሕልማችን ጨለማ ዋጠው::

‹‹ሕገ ወጥ ነው እያልከን ነው?›› ማይክ ነበር ጠያቂው::

‹‹አዎ ሕገ ወጥ ነው::›› አለ አባዬ::‹‹ ነገር ግን ንጹህ የፈጠራ ክህሎት ነው ሳያችሁት::እናም በሃሳቦቻችሁ ቀጥሉባቸው::ኮርቼባችኋለሁ›› አለን::



‹‹ልጆች ደሃ የምትሆኑት ተስፋ ከቆረጣችሁ ብቻ ነው:: ሀብታም መሆን የምጥፈልጉ ከሆነ እኔን ምክር አትጠይቁኝ፤የማይክን አባት አማክሩት::››

‹‹የእኔን አባትን? አባቴ ገንዘብ መስራት ላይ ጎበዝ ከሆነ አሪፍ መኪና የሌለን ለምንድነው?›› ሲል ጠየቀ ማይክ::

‹‹አሪፍ መኪናና ጥሩ ቤት አለህ ማለት ሀብታም ነህ ማለት ላይሆን ይችላል:: አባትህ ከእኔ ይለያል ማይክ:: አባትህ የኸነ ዓይነት የንግድ ግዛት እየገነባ ነው፤ እንደምጠረጥረው ከሆነም በቅርብ ጊዜ ውስጥ በጣም ሀብታም ይሆናል::››

ማይክና እኔ ከአባቴ ምክር በኋላ ሊድ በማቅለጥ ያ[illegible]ማለቅነውን ቦታ አጸዳድንና ማይክ ወደቤቱ ሄደ:: አባቱን በተቻለ ፍጥነት አናግሮት እንደሚደውልልኝም ቃል ገብቶ ነበር::

ማታ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ማይክ ደወለ::

‹‹እሺ|በቀጠዩ ቅዳሜ›› አልኩትና ስልኩን ዘጋሁት:: የማይክ አባት አግኝቶ ሊያናግረን ፈቃደኛ ሆኗል::

ቅዳሜ በማለዳ ከጠዋቱ 1 ሰዓት ተኩል ሲሆን፣ ከመኖሪያ ቤቴ በመውጣት ድሆች በብዛት ወደሚኖሩበት የከተማው ክፍል የሚያደርሰኝን የከተማ አውቶቡስ ያዝኩኝ::

ትምህርቶቹ ተጀመሩ

‹‹በሰዓት 10 ሳንቲም እከፍላችኋለሁ!››

ይህ ክፍያ እኤአ በ1956 ዓ.ም እንኳን ባለው የገንዘብ አቅም ዝቅተኛ የሚባል ነበር::

በዕለቱ እኔና ማይክል ከጠዋቱ በ2 ሰዓት ከአባቱ ጋር ተገናኘን:: የማይክ አባት በወቅቱ ፋታ የማይሰጥ ስራ ይዞ ነበር:: እኔ የማይክ አባት ወደሚገኝበት ትንሽዬ ንፁህና ቀለል ወደምትለው ቢሮ ስደርስ ማይክም በሩ ላይ አገኘኝ::

‹‹አባዬ ስልክ እያነጋገረ ነው፤ እስኪጨርስ ድረስ፣ አረፍ ብለህ ጠብቀው›› በማለት በሩን ከፈተልኝ::

ሌሎችም ወረፋ ጠባቂዎች ሲኖሩ አንደኛው ከአጠገቤ የቆመው የመጋዘን ኃላፊው ሊሆን ሌቶቹ ደግሞ ምግብ ቤቱን ያስተዳድራሉ። መጀመሪያ ያየችው የግንባታ ተቆጣጣሪ ከዚህ ከምንገኝበት 50 ማይልስ ርቀት ላይ የሚገኘው የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ዋና ኃላፊ ነው።

‹‹ስራው ሁሉ በተቃና ሁኔታ እየተካሄደ ነው?›› ስል ጠየቅኩት

‹‹ሁሉም ባይሆንም በአብዛኛው ግን በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል›› ብሎኝ ከአጠገቤ በመቀመጥ ወንበሩን ሳበው።

ማይክ በመቀጠልም ‹‹አባቴን ገንዘብ እንዴት ልናፈራ እንደምንችል ጠይቄው ነበር›› አለኝ።

‹‹እና ምን አለህ?›› በጉጉት ጠየቅኩት

‹‹ፈገግ ብሎ! ስጦታ እንደሚሰጠን ነግሮኛል›› አለ ማይክ።

‹‹እ...መልካም ነዋ›› አልኩት።

የተቀምጥኩበት ወንበር ላይ ተደላድዬ በመቀመጥ ስንቀሳቀስ! የወንበሩ እግሮች እንከን እንዳለባቸው ተገነዘብኩ።

‹‹ስጦታው ምን እንደሆን ታውቃለህ?››

‹‹በእርግጥ አላውቅም! በሂደት ማወቃችን ግን አይቀርም›› ብሎ ማይክ መለሰልኝ።

በድንገት የማይክን አባት ድምፅ ሰማን! እኛ ወዳለንበት እየቀረበ ነበር። እኔና ማይክም ከተቀመጥንበት ተነስተን ቆም ብለን ጠበቅነው።

‹‹ልጆች ተዘጋጅታችኋል?›› በማለት ከጎናችን ተቀመጠ።

ሁለታችንም በመስማማት ጭንቅላታችንን በመነቅነቅ ዝግጁነታችንን አረጋግጠንና ከፊት ለፊቱ ተቀመጥን።

የአባትየው ተክለ ሰውነት ግዙፍ ሲሆን፣ ቁመቱም ረጅም የሚባል አይነት ነው። ከአባቱ ጋር የሚቀራረብ ተክለ ሰውነት ነው ያለው። በማንነት ደረጃ ግን ሲመዘኑ የሚለያዩ ይሁን እንጂ! ሁለቱም ያላቸው ብርታት ሳይመሳሰል አይቀርም።

‹‹ሰሞኑን ማይክ ገንዘብን እንዴት ማፍራት እንደሚቻል ማወቅ እንደምትፈልግ ነግሮኛ ነበር። ሮበርት ትክክል ነኝ?›› በማለት አባትየው ጠየቀኝ።





በመስማማት ጭንቅላቴን ነቀነቅኩኝ፤በንግግሩና በፈገግታው ውስጥ የሆነ ኃያል ነገር እንዳለው መረዳት ይቻላል።

‹‹መልካም። ስጦታዬ ይህ ነው፤ በሚገባ አስተምራችዋለሁ። ይሁን እንጂ ትምህርቱ ልክ እንደ መደበኛው ት/ቤት አይደለም። ከእናንተ የሚጠበቀው ለእኔ ማገልገል ብቻ ነው። ከዚያ ውጪ የማትሰሩልኝ ከሆነ አላስተምራችሁም። በሥራ ፈጣን ከሆናችሁ፣ በፈጣን ሁኔታ አስተምራችኋለሁ። እናንተ በክፍል ውስጥ ተቀምጣችሁ መማር የምትፈልጉ ሊሆን ይችላል። ግን ሰዓቴን ትጨርሳላችሁ። ይህ ነው እንግዲህ የእኔ ስጦታ! መቀበል ወይም መተው ትችላላችሁ›› ብሎ ንግግሩን ጨረሰ።

‹‹መጠየቅ እችላለሁ?›› አልኩኝ።

‹‹አይሆንም ምርጫው የእናንተ ነው። መቀበል ወይም መተው ብቻ ነው። ብዙ ሥራ ስላለብኝ ሰዓቴን አታጥፉ። ሀሳቤን ካልተቀበላችሁ! የተመኛችሁትን ገንዘብና ሀብት ማፍራት አትችሉም። ዕድል ይመጣል ይሄዳል። በውሳኔ መቁረጥ ትልቅ ብቃት ነው። ዕድል መጥቶላችኋል! ለጠየቃችሁትም አማራጭ አላችሁ!›› ብሎ ፈገግ አለ።

‹‹ተስማምቻለሁ›› አልኩኝ። ማይክም በመስማማት ቃሉን ደገመው።

‹‹መልካም›› አለ የማይክ አባት። ቀጠለናም

‹‹ወ/ሮ ማርቲን በአስር ደቂቃዎች ውስጥ ትመጣለች። ለስዝርዝሩ ከተነጋገርን በኋላ ወደ ሱፐር ማርኬት በመሄድ ሥራ መጀመር ትችላላችሁ። በሰዓት አስር ሳንቲም እከፍላችኋለሁ! የምትሰሩት ዘወትር ቅዳሜ ለሦስት ሰዓት ብቻ ይሆናል።››

‹‹እኔ ግን የእግር ኳስ ጨዋታ አለብኝ›› በማለት ተናገርኩኝ።

የማይክ አባት ድምፁን ለስለስ አድርጎ ‹‹ተቀበሉት ወይም ተውት›› አለ።

‹‹ተቀብያለሁ›› ስል መለስኩ! ከእግር ኳስ ጨዋታ ይልቅ ሥራና ትምህርትን ቅዳሜ ለማድረግ በመወሰን።

ከ30 ማንቲም በኋላ

እኔና ጓደኛዬ ማይክ ቅዳሜ ከጠዋቱ 3 ሰዓት ሲሆን እንደተለመደው ከወ/ሮ ማርቲን ጋር በሥራ ላይ እንገኛለን።

ወ/ሮ ማርቲን ሩህሩህና ታጋሽ ሴት ነበረች። ዘወትር እኔና ማይክን ስታየን፣ ሁለት ወንድ ልጆችዋን እንደምታስታውሳቸው ትነግረናለች። በአሁኑ ወቅት ልጆቿ ትላልቅ ሆነው፣ የራሳቸውን ህይወት እየኖሩ ይገኛሉ።

ወ/ሮ ማርቲን ከርህራሄዋ ጎን ስርዓት የምታስር አይነት ሴት ነበረች። የሥራ ድርሻዋም በሱፐር ማርኬት ውስጥ ያሉ ዕቃዎችን መቆጣጠር ሲሆን፣ የእኛ ደግሞ ዕቃዎቹን ማፅዳት እና አቧራ ያለባቸውን ማራገፍ ነበር። ይሁን እንጂ ሥራው አሰልቺ ነበር።

‹ሀብታሙ አባቴ› በማለት የምጠራው የማይክ አባት ከሌሎች ቢዝነሶች ሌላ፣ ዘጠኝ አነስ አነስ ያሉ ሱፐር ማርኬቶች ያሉት ሲሆን፣ በሀንፃዎቹ ሥርም ሰፋፊ የመኪና ማቆሚያዎቹን ያካትታል። ከሱፐር ማርኬቱ አገጠብ አነስተኛ ግሮሰሪ ሲኖረው ወተት፣ ዳቦና ሲጋራ የመሳሰሉ ሸቀጦችን ይሸጣል። አካባቢው ሞቃታማ በመሆኑ፣ ሁሌም ቢሆን የሱፐር ማርኬቱ በሮች ክፍት ነው የሚደረጉት፤ በዚህም የተነሳ በንፋስም ይሁን በመኪና ለሚነሳው አቧራ የተጋለጠ በመሆኑ፣ ዘወትር ማፅዳትን ይጠይቃል።

እኔና ማይክ ሥራችንን ከጀመርን ሦስት ሳምንት አለፈን። ሁሌም የሦስት ሰዓት ሥራችንን በተመለከተ ለወ/ሮ ማርቲን ሪፖርት ማድረግ ያስፈልገን ነበር። ቀትር ላይ ሥራው ሲጠናቀቅ በሁለታችን እጆች ላይ ሰላሳ ሰላሳ ሣንቲሞችን ታስቀምጥልናለች። በወቅቱ በዘጠኝ ዓመት ዕድሜዬ (በ1950ዎች አጋማሽ) የ30 ሣንቲም ክፍያ የሚያስደስት አልነበረም። በወቅቱ የቀልድ መፅሀፎች የሚሸጡት በ10 ሳንቲም ስለነበረ እኔም ወደ ቤቴ የምገባው እነኚህኑ መፅሀፍት ገዝቼ ነበር።

በአራተኛው ሳምንታችን በዕለተ ረቡዕ ሥራውን ለማቆም ወሰንኩኝ። በመጀመሪያ ከማይክ አባት ጋር የተስማማሁት፣ እንዴት ገንዘብ ማፍራት እንደምችል ለመማር ብዬ እንጂ ሌላ አልነበረም። ሆኖም ከመማር ይልቅ እነሆ ባሪያ ሆኛለሁ። የአስር ሳንቲም ተገዢ። የማይክንም አባት ከዚያ ጊዜ ወዲህ አግኝቸው አላውቅም።

. ‹‹ሥራውን ላቆም ነው›› በምሳ ሰዓት ለማይክ ነገርኩት። የት/ቤት ምሳ የሚገርም አይነት ነው - በዚህም ት/ቤቱ ሰልችቶኛል። በየሳምንቱ ቅዳሜ ቅዳሜ እየሰራሁ የማገኛት 30 ሳንቲምም በህይወቴ ምንም አይነት ለውጥ የምታመጣ አይደለችም።





ማይክ ይህንን ስነግረው ፈገግ አለ።

‹‹ምን የሚያስቅ ነገር አለ?›› በቁጣ ተናገርኩ።

‹‹አይ፣ ይህ እንደሚያጋጥም አባቴ ነግሮኝ ነበር ያ ትዝ ብሎኝ ነው የሳቅኩት። ስራውን ለማቆም ዝግጁ ስትሆን፣ አንተን ማግኘት እንደሚፈልግ ነግሮኛል›› አለ።

‹‹ምን? እስኪሰለቸኝ ድረስ ነበር የሚጠብቀው?››

‹‹ማለት ይቻላል!›› ማይክ መለሰና ቀጠለና ‹‹አባዬ በባህሪው ከአንተ አባት ይለያል። ሌሎች እናትና አባት ማስተማርና መንገር ይወዳሉ። አባዬ ግን እንደዚህ አይደለም። ብዙም አያወራም፣ ቃላቶቹም ቁጥብ ናቸው። እስከ መጪው ቅዳሜ ድረስ ጠብቀው ሥራውን ለመተው እንደተዘጋጀህ እነግረዋለሁ።››

‹‹ከሥራ ተሰናብቻለሁ ማለትህ ነው?››

‹‹በእርግጥ ላይሆን ይችላል ! ግን አባዬ ሁሉንም ነገር ያስረዳሃል›› አለኝ።

**በቅዳሜ ተራ ጥበቃ**

ጓደኛዬ እንዳለው አባቱን በአካል አግኝቼ የማነጋግርበት ቀን ደረሰ። ወላጅ አባቴም ቢሆን በዕለቱ በጣም ተናዶ ነበር። ‹‹ይህ ሰው የህይወትህን መብት በመጋፋት ላይ ስለሆነ ሊመረምር ይገባል›› ሲል ተናገረ።

የተማረው ደሃው አባቴ፣ ማግኘት የሚገባኝን ማግኘት እንደሚኖርብኝ ይነግረኝ ነበር። ቢያንስ ቢያንስ በሰዓት 25 ሳንቲም ሊሆን ይገባል ይላል።

‹‹ያን የማይረባ ሥራ መተው አለብህ›› ይለኝ ነበር በጓደኛዬ አባት አንጀቱ እያረረ። ቅዳሜ፣ ከጠዋቱ 2 ሰዓት ሲሆን ወደነማይክ ቤት አመራሁ።

‹‹አረፍ ብለህ ተራህን ጠብቅ›› ብሎኝ የማይክ አባት፣ ከመኝታ ቤቱ ጎን ወዳለችው ቢሮው በመግባት ከዕይታዬ ተሰወረ።

ጓደኛዬን ለማግኘት ቤቱን ሁሉ ብቃኝም ማይክን አጣሁት። በውስጤ መረጋጋት ባይኖርም ከአራት ሳምንት በፊት እዚሁ ቤት ውስጥ ያየኋቸው እነዚያ ሴቶች አሁንም አሉ። ብቸኝነት እንዳይሰማኝ በማሰብ ፈገግ እያሉ ይመለከቱኛል።

አርባ አምስት ደቂቃ ነጎደ፣ ለራሴ መነጫነጭ ጀመርኩ። የማይክ አባት ከሁለት ሴቶች ጋር ሲነጋገርም 35 ደቂቃዎች ሲያጠፉ፣ ከዚያም ከአንድ ትልቅ አዛውንት ጋር ደግሞ ለ20 ደቂቃዎች ተነጋገሯል።

ቤቱ ወና ቢሆንም፣ እኔም የማይክ አባት እስኪጠራኝ መጠበቄን ቀጠልኩ:: ቢሮ ውስጥ ሆኖ ስልክ ሲያነጋግር ድምፁን እሰማዋለሁ:: እኔን በመናቅ ይሁን እንጃ ሲያነጋግረኝ ግን ፍቃደኛ አልሆነም:: ለመሄድ ወሰንኩና የማላውቀው ምክንያት ትንሽ እንድታገስ አደረገኝ::

በስተመጨረሻ ከ15 ደቂቃዎች በኋላ፣ ልክ ሦስት ሰዓት ሲሆን፣ «ሀብታሙ አባቴ» ከቢሮው በመውጣት ድምፁ ሳያሰማ በምልክት ወደ ቢሮው እንድገባ ጠራኝ::

«እንደሚገባኝ ደሞዝ ጭማሪ ካላገኘሁ ስራ የማቆም እርምጃዎች ለመውሰድ ተዘጋጅተሃል» በማለት ወደ መቀመጫው አመራ::

«ቃልህን አልጠበቅክም» አልኩትና መቀጠል አልቻልኩም እንባዬ ቀደመኝ፣ በእርግጥ የዘጠኝ ዓመት ልጅ ያን ያን የመሰለ ግዙፍ ሰው ማነጋገር ይከብደዋል::

«ለሰራሁልህ እንደምታስተምረኝ ቃል ገብተሃል፣ እኔም በምችለው አቅሜ የቤዝ ቦል ጨዋታዬን በመተው ስሰራ ነበር:: አንተ ግን ቃልህን አልጠበቅክም ምንም ያደረግክልኝ ነገር የለም:: ራስ ወዳድና ለሰራተኞችህ የምታስብ አይደለህም:: እንድጠብቅህ አደረግከኝ እንጂ፣ ምንም ያገኘሁት ነገር የለም:: እኔ ልጅ ነኝ:: እንክብካቤ ያሻኝ ነበር ግን ምንም ያገኘሁት ነገር የለም::»

ሀብታሙ አባቴ ከወንበሩ ብድግ ብሎ እየጠናኝ ትኩር ብሎ አየኝ::

«መልካም ከአንድ ወር ባለ ጊዜ ውስጥ እንደ ብዙዎቹ ተቀጣሪዎች እንደምትሆን አልተጠራጠርኩም ነበር» አለኝ

«ምን?» ስል ጠየቅኩት የተናገረው እንዳልገባኝ ለማሳወቅ ፈልጌ::

«ይገባሃል ብዬ አስብ ነበር:: አንተ ግን እየነገርከኝ ነው ያለው ብለህ አስበሃል:: እንግዲህ መጥፎው ጎን ይ ነው:: ...እኔ ግን እያስተማርኩህ ነበር» ብሎ መለሰልኝ::

«ምን አስተማርከኝ - ምንም» በቁጣ ተናገርኩት:: «ለመስራት ተስማምቼ በሰራሁበት ወቅት እንኳን ምንም ያዋራኸኝ የለም:: ለመንግስት ማሳወቅ አለብኝ:: የህፃናት መብትን የሚያከብር ህግ እንዳለ ታውቃለህ:: አባቴ ደግሞ የሚሰራው እዚያ ነው::»

«ይገርማል» አለ በለበጣ፣ «አንዳንድ እኔ ጋ የሚሰሩ ሰዎችን መሰልከኝ:: እነሱ ወይ ራሳቸው ሥራውን ይተዋሉ ወይም አባርራቸዋለሁ» አለ::





«ከእንግዲህ ምን ያሻሃል፣ ቃልህን አጠፍክብኝ፣ ስርቼልህ ምንም ያስተማርከኝ ነገር የለም» መለስኩለት::

«እንዳላስተማርኩህ በምን አወቅክ?» ብሎ ጠየቀኝ::

«መልካም ሥራ ሰርቼያለሁ አንተ ግን አላነጋገርከኝም:: አላስተማርከኝም» ስል መለስኩ::

«ማስተማር ማለት ማውራት ነው እንዴ?» ጠየቀኝ::

«አዎ» አልኩት

«ያ ትምህርት ቤት ብቻ ነው ያለው» ፈገግ ብሎ መለሰ::

«እዚያ ደግሞ ስለህይወት የምትማርበት አይደለም:: ህይወት በራሱ ትልቁ ት/ቤት ነው:: ህይወት ስታስተምርህ ውይይት ወይም ንግግር የላትም:: እንድትማር ግን ህይወት ሁኔታዎችን በማሳየት ትገፋፋሀለች:: በቃ፣ እንተን ማስተማር የምፈልገው ነገር እሱ»

«ይህ ሰው ምንድን ነው የሚለው?፣ በማለት ራሴን ጠየቅኩት:: ህይወት ራስዋ በሁኔታዎች በመገፋፋት ታስተምርሃለች? ማለት ነው:: ዝም ብሎ ለማሳመን በሚል የገለፀልኝ ስለመሰለኝ ስራውን ለማቋረጥ ወሰንኩ::

«ህይወት ራስዋ ት/ቤት ናት:: ከቻልክ መልካም ውጤት ታገኛለህ:: ካልሆነ ደግሞ አትማርባትም:: በተቃኒው በራስህ ላይ ትፈርድብሃለች:: ሰዎች ሁለት ነገሮችን ያደርጋሉ:: አንዳንዶች ከህይወታቸው በመማር ቀጣይ ህይወታቸውን ያሳምራሉ፣ ሌሎች ደግሞ በተቃራኒው በህይወታቸው እየተማረሩ የራሳቸውን አቅጣጫ ይስታሉ - ከዚያም በአለቃቸው ላይ ወይም በሥራቸው ላይ ይፈርዳሉ - በሚስታቸው ወይም በባላቸው ያሳብባሉ:: እነዚህ ሰዎች ያልገባቸው ነገር ህይወት ወደአንድ ሁኔታ እንደምትገፋቸው ነው» ሲል ዘርዝሮ ተናገረ::

ይሁን እንጂ ከተናገረው ነገር የገባኝ አንድም የለም::

«ሕይወት ሁሉንም ወደዚህ ዑደት ትገፋለች:: አንዳንዶች ተሸንፈው እጅ ሲሰጡ፣ ሌሎች ይፋለምዋታል:: በውጤቱም ይማሩበታል:: መገፋታቸው ትምህርት እንደሆነ በማመን ትልቅ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ:: ፍልሚያውን ያሸነፉ ድልን ሲቀዳጁ፣

የተሸነፉ ደግሞ ድልና ስኬትን ከራሳቸው ያሸሻሉ:: አንተም ተጋፍጠህ ህይወትን ማሸነፍ አለብህ›› አለኝ::

ከመቀመጫው ተነስቶ አሮጌውን የእንጨት መስኮት ዘጋው::

ከመቀመጫው ተነስቶ... ‹‹ከተማርክ ብልህ ትሆናለህ - ሀብትና ደስታ ያንተ ይሆናሉ›› ይህ ካልሆነ ግን

ማማረር ብቻ ህይወትህን ይሞላዋል:: በሚከፈልህም አትረካም - ዘወትር ከአለቃህ ጋር መጋጨትን ታዘወትራለህ:: ያንን ማድረግህ ችግርህን የሚፈታና ሀብትን የሚሰጥህ ይመስልሃል::››

ሀብታሙ አባቴ በእንክሮ እንደማዳምጠው ለማወቅ ተመለከተኝ:: አይን ለአይን ተገጣጠምን:: በሀሳብ ተግባባን:: በስተመጨረሻ መልዕክቱን ተቀበልኩ:: ይሁን እንጂ አሁንም እሱን መውቀስ አላቆምኩም:: ለማወቅ መጠየቅ አለብኝ - ህይወትን ለመፋለም::

ቀጠለና ‹‹ሆሞተ ኮስታራና መማር የማትፈልግ ከሆነ ህይወትህ በከንቱ ያልቃል:: ጠንካራ ሰራተኛ ከሆንክ መስሎችህን ማግኘትህ አይቀርም:: ሆኖም ዕውነታው እጅ እንድትሰጥ ያደርግሃል:: አሸነፍኩ ማለት ስትጀምር ድል ይሸሽሃል:: አንተና አንተ ብቻ ይህን የህይወት ትግል ትጋፈጣላችሁ::››

ከማይክ ጋር አይን ለአይን ተገጣጠምን:: መልዕክቱ እስኪገባን ድረስ ለአስር ሰኮንድ ያህል መተያየቱ ቀጠለ::

‹‹እያስገደድከኝ ነው እይደል›› ስል ጠየቅኩት::

‹‹አንዳንዶች ሊሉ ይችላሉ›› ብሎ ፈገግ አለ::

ሀብታሙ አባቴ ቀጠለና ‹‹ጣፋጭ ህይወትን ሰጥቼህ ነበር:: ››

‹‹የምን ጣፋጭ ህይወት?›› ቁጣ የተቀላቀለበት ቢሆንም ለማማርና ለማወቅ ጉጉት ያልተለየው ምላሽ ሰጠሁት::

‹‹እናንተ ሁለት ልጆች ብቻ ናችሁ ከዚሁ ሁሉ 150 ሰራተኞቼ መካከል ስለሀብት ማፍራት ለማወቅ የጠየቃችሁኝ:: ሌሎቹ ግን ሥራ ይፈልጋሉ በምላሹ ክፍያ ይጠብቃሉ:: ሀብት ማፍራትን በተመለከተ ጠይቀውኝ አያውቁም›› አለ::

ሳዳምጠው ቆየሁ:: ‹‹ሀብት ማፍራት እንደምትፈልጉ ማይክ ሲነግረኝ፣ በህይወታችሁ ሙሉ ዕለት በዕለት የምትለማመዱት እንደሆነ አሰብኩኝ:: እንደበቴ





እስኪደክመው ልነግራችሁ እችል ነበር:: ሆኖም ለውጥ አያመጣም:: ስለዚህ በተግባር እንድትረዱት 10 ሳንቲም በሰዓት ለእንዳንዳችሁ በመክፈል እንድትሰሩ አደረግኩ›› አለ::

‹‹ስለዚህ ምን ተማርኩኝ? 10 ሳንቲም በሰዓት ማግኘቴ ብርቅ ነው?›› ብዬ ጠየቅኩት ቀጠልኩናም

‹‹ከመማር ይልቅ ልክ እንደሌሎች ሰራተኞችህ ተበዘበዝኩ›› አልኩት:: ሀብታሙ አባቴ ትከሻውን ወደ ኋላ በመለጠጥ ከት ብሎ ሳቀ::

ከዚያም ‹‹ሀሳብህን ብትቀይር ይሻልሃል:: እኔን መወንጀል አቁም እኔ ችግር ፈጣሪ እንደሆንኩ ካመንክ ሌሎች ጋ መስራት ትችላለህ:: አንተ ጋ ችግር እንዳለ ተረዳና ራስህን ለውጥ:: በማስተዋል የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ጣር:: ብዙ ሰዎች ሌሎች ሲቀየሩ ማየት ይመርጣሉ:: ግን ራሳቸውን ዞር ብለው አያዩም:: ቀለል ባለ ቋንቋ ስነግርህ የሌሎችን ለውጥ ከማየትና ሌሎችን ከመለወጥ ራስን መለወጥ ይቀላል›› ብሎ መለሰልኝ::

‹‹አልገባኝም›› አልኩት::

‹‹በራስህ ችግር እኔን አትውቀስ››

ሀብታሙ አባቴ ትዕግስቱ እንዳለቀ ከንግግሩ ያስታውቃል:: እኔም መለስኩና ‹‹የምትከፍለኝ ግን 10 ሳንቲም ብቻ ነው›› አልኩት

‹‹እና ምን ተማርክ?›› ሳቅ እያለ ጠየቀኝ

‹‹ጉልበቴን ትበዘብዛለህ›› ብዬ መለስኩለት::

‹‹ተመልከት አሁንም እኔን ችግር ፈጣሪ እያደረግክ ነው›› አለኝ::

‹‹እናስ አይደለህም?››

‹‹ደህና::ይህን አመለካከት ያዝ፤ በውጤቱም ምንም አትማርም ቀጥልበት፣ ችግር ፈጣሪ እንደሆንክ ትቀጥላለህ፡ ሌላ ምን ምርጫ አለህ?›› አለኝ::

እኔም ‹‹የተሻለ ክፍያና ክብር ካላገኘሁ ሀብት ማፍራት እንደምችል ካላስተማርከኝ አልሰራም›› አልኩት፡

‹‹መልካም ይህንን ነው ብዙ ሰዎች የሚያደርጉት:: ሥራ ያቆማሉ! በምትኩም ሌላ ሥራ ይፈልጋሉ! የተሻለን ክፍያ በመመኘትና ችግራቸውን ለመቅረፍ:: ነገር ግን የሚገርመው በብዛት አይሳካላቸውም::›› አለና ንግግሩን ገታ::

«እና ምንድነው ችግሬን የሚፈታው?» ስል ጠየቅኩት፡፡ ቀጠልኩናም

«የምትከፍለኝን 10 ሳንቲም በፀጋ ተቀብሎ መኖር?» አልኩት፡፡

«የምትከፍለኝን 10 ሳንቲም በፀጋ ተቀብሎ መኖር?» አልኩት፡፡ እነርሱና ቤተሰቦቻቸው

ሳቅ አለና «ያንን ነው ሌሎች የሚያደርጉት፡፡ እነርሱና ቤተሰቦቻቸው ሳይጠይቁ በተስፋ

እንደሚቸገሩ እያወቁ በፀጋ ይቀበሉታል፡፡ ሆኖም ጭማሪን ሳይጠይቁ በተስፋ

ይጠባበቃሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ የትርፍ ሰዓት ሥራን ይሰራሉ፡፡»

በእንክሮ ለማዳመጥ ራሴን ይበልጥ አተጋሁ፡፡ የህይወት ተሞክሮው እንደሆነ

አሰብኩና «ችግሬን ምን ይፈታዋል?» በድጋሚ ጠየቅኩት፡፡

ይኼኔ እናቴን ነካ አደረገኝና «በቀጣይ ትረዳዋለህ» አለ፡፡

በዚያን ጊዜ ነበር የራሱን እና የተቀጣሪዎቹን እንዲሁም ደሃና የተማረውን

የወላጅ አባቴን ተሞክሮ በንፅፅር እያሳየኝ ሊያስረዳኝ የሞከረው፡፡

ይህ ነው እንግዲህ እርሱን በጣም ሃብታም ያደረገው፤ በሃዋይ ግዛት

የተማረውን ወላጅ አባቴን ደግሞ ያደኸየው፡፡ ጥቂት ነገር ልዩነት ፈጠረ፡፡

ሀብታሙ አባቴ መልሶ መላልሶ የሚነግረኝ ይህንኑ ነበር፤

*ትምህርት አንድ፡-*

«ድሆችና መካከለኛ ገቢ ያላቸው የሚሰሩት ለዕለት ጉርስ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት ሲሆን ሀብታሞች ግን ሀብትን ለማዳበር ወይም ለማብዛት ነው፡፡»

በዚያን ውብ ቅዳሜ ጠዋት ደሃው ወላጅ አባቴ ካስተማረኝ የተለየ ነገር ነው የተማርኩት፡፡ የሚገርመው የዘጠኝ ዓመት ልጅ ብሆንም፣ ሁለቱም አባቶቼ እንድማር ነበር ፍላጎታቸው፡፡ ሆኖም በተለያየ መልኩ ወላጅ አባቴ በትምህርት እንድበረታና ጥሩ ክፍያን እንዳገኝ ሲሆን፤ ሃብታሙ አባቴ ግን ሀብትን እንድፈጥር ነበር፡፡ ወላጅ አባቴ ዘወትር «ልጄ እንድታጠናና የተሻለ ውጤትን በማስመዝገብ፣ ጥሩ ሥራ እንድትይዝልኝ እፈልጋለሁ» ይለኛል፡፡ በተቃራኒው ሀብታሙ አባቴ ግን፣ ሀብት እንዴት እንደሚፈራና ለውጥ እንደሚመጣ ይነግረኝ ነበር፡፡ ይህን ደግሞ ከት/ቤት ሳይሆን በተግባር እንደምማረው ያሳስበኝ ጀመረ፡፡ ቀጠል አደረገና «በ10 ሳንቲም ክፍያ በመስራትህ ስለተናደድክ ደስ ብሎኛል፡፡ ባትናደድና በ10 ሳንቲሙ ደስተኛ ብትሆን ኖሮ ምናልባት ማስተማሬን አቆም ነበር፡፡





«እየሀ ትክክለኛ ትምህርት ቁርጠኝነት እና ጉጉትን ይፈልጋል፡፡ ጉጉት ደግሞ ከፍተኛ ድርሻን ይይዛል፡፡ በውስጡም ውጥረት አለው፡፡ ወደ ገንዘብ ስንመጣ ብዙ ሰዎች በአግባቡ የማይጠቀሙበት ከፍርሃት ጋር ስለሚያንቀሳቅሱ ነው፡፡ ለማደግና ለመሻሻል ደግሞ ጉጉትን ከጥረት ጋር ደምረው አይዙትም፡፡

«ለዚያ ነው ታዲያ ትንሽ ስራን በትንሽ ሳንቲም የሚሰሩት?» ስል ጠየቅኩት፡፡

«አዎ» ብሎ መለሰልኝ፡፡ ቀጠል አደረገና፡-

«ጥቂቶች ልክ እንደመንግስትና የስኳር ማምረቻ ድርጅት ስለማልከፍል ‹የሰውን ጉልበት ይበዘብዛል› ይላሉ፡፡ እኔ ግን የራሳቸውን ጉልበት ራሳቸው በዘበዙት ነው የምለው፡፡ ፍርሃታቸው ነው ለዕድገታቸው ማነቆ የሆነባቸው» ሲል ገለፀልኝ፡፡

«በደንብ መክፈል እንደሚገባህ አትገንዘብም?» በማለት ጠየቅሁ፡፡

«ፈፅሞ፡፡ ምክንያቱም ደሞዝ ማብዛት ችግራቸውን አይፈታም፡፡ እስኪ ወላጅ አባትህን ተመልከት፣ ስለተማረ ክፍያው ጥሩ ነው ግን ከብድር ሊወጣ አልቻለም፡፡

«ለዚያም ነው 10 ሳንቲም በሰዓት ... » ፈገግ አለና «የትምህርት አካል የሆነው፡፡» ብሎ ተናገረ፡፡

«አስተውል አባትህ ጥሩ ውጤት አስመዝግቦ ተማረ፤ በጥሩ ክፍያም እየሰራ ነው፡፡ ሲማር ግን ገንዘብን እንዴት እንደሚያበለፅግ የቀሰመው ዕውቀት የለም፡፡ ስራ ላይም የገንዘብ እጥረት እንዴት እንደሚቀረፍ አልተማረም፡፡ ችግሩ ደግሞ ገንዘብን በሥራ ማግኘት የዕለት ችግሩ መፍቻ ብቻ እንደሆነ ማሰቡ ላይ ነው» አለ፡፡

«አንተ እንደዚያ አይደለህም?» ብዬ ጠየቁት

«አይደለሁም» አለ

«የዕለት ጉርስ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት ከሆነ ምኞትህ በት/ቤት ልትማረው ትችላለህ፡፡ ሀብትን ለማሳደግ ከተመኘህ ደግሞ በተግባር እኔ አስተምርሃለሁ» አለኝ

« ሌሎችስ ይሄን አይፈልጉም?» ስል ጠየቅኩት፡፡

«አዎ» አለኝ፡፡ ቀጠለና «ምክንያቱ ደግሞ ስለገንዘብ ያላቸው አመለካከት ከፍተኛ ክፍተት ስላለበት ብቻ ነው፡፡ ክፍተቱ ደግሞ ፍርሃትን ይወልዳል» ሲል መለሰልኝ»

«አልገባኝም» አልኩት፡፡

‹‹ስለዚህ አትጨነቅ፣ ፍርሃት ብቻ እንደዚህ እንደማያደርጋቸው ተረዳ። የቤት ኪራይ መክፈል፣ ገንዘብን በፈለጉት ጊዜ እንደሚያገኙ ማመን፣ ስራን ለቆ ሌላ ስራ የመፈለግ ስጋት ወዘተ ስላለባቸው ብዙዎች ተቀጣሪ በመሆን ወጥመድ ውስጥ ይገባሉ።

‹‹ሀብት የሚበፅግበትና ገንዘብም የሚሰራበት አካሄድ ሙሉ በሙሉ ልዩ ነው ማለትህ ነው?›› ስል ጠየቅኩት።

‹‹በእርግጥ አዎ›› ሀብታሙ አባቴ መለሰ። በዚያ ውብ ብርሃናማ ቅዳሜ ጠዋት ለደቂቀዎች ፀጥ አልን። ይኸኔ ጓደኞቼ ቤዝ ቦል እየተጫወቱ እንደሆነ ትዝ አለኝ፤እኔ ግን በ10 ሳንቲም ክፍያ ሥራዬን ለመቀጠል ወሰንኩ። ጓደኞቼም በት/ቤት ያላገኙትን ስለሀብት ዕውቀት ገበየሁ።

‹‹አሁን ለመጀመር ተዘጋጅተሃል?›› ሲል ጠየቀኝ።

‹‹በእርግጥ አዎ›› ስል መለስኩ።

‹‹ቃሌን አከብራለሁ!፣ ከመሰረቱ ሳስተምርህም ቃል እገባልሃለሁ። በዚህ ዕድሜህ ስለሀብት ማፍራት ለማወቅ መጣርህ መልካም ነው። ይህን ጊዜ በ5 ዓመት ስታባዛው ደግሞ ሀብታም እንደምትሆን ይሰማኛል›› አለ።

‹‹ማለት?›› ጠየቅኩት

‹‹ለማለት የፈለግኩት ለገንዘብ ከሰራህ የዕለት ጉርስህን እሰብክ ማለት ሲሆን፣ ገንዘብን ለማዳበር ከሰራህ ደግሞ ሀብትን ለመፍጠር እየጣርክ ነው ማለት ነው›› አለኝ። ከዚያም ‹‹ወ/ሮ ማርቲን ሶስት 10 ሳንቲሞች ስትሰጥህ ምን ተሰማህ? ›› ብሎ ጠየቀኝ።

‹‹ብቂ እንዳልሆነ እና ምንም ልሰራበት እንደማልችል ሲሰማኝ ተናደድኩኝ›› አልኩት።

እርሱም ‹‹ይህ እንግዲህ ብዙዎች የሚሰማቸው ነው። በተለይ ደሞዝ ሲያገኙ፣ ግብር ሲቆረጥባቸው። አንተ ግን ቢያንስ ቢያንስ ምንም የተቆረጠ ነገር የለብህም››

‹‹ደመወዛቸው ሙሉው አይከፈላቸውም ማለት ነው?›› ብዬ በመገረም ጠየቅኩት።

‹‹አዎ ሙሉውን አያገኙም፣ መንግስትም የድርሻውን ይወስዳል››

‹‹ይህ እንዴት ነው የሚሆነው?›› ጠየቅኩት





‹‹ግብር›› አለኝ። ቀጠል አደረገና፣ ‹‹ለሰራኸው ሥራ ሲከፈልህ ግብር ይቆረጥብሃል፤ ስትገዛም እንደዚሁ። በባንክም ገንዘብህን ስታስቀምጥ ግብር ትከፍላለህ፤ ስትሞትም ለመቃብርህ ግብር ይከፈላል።››

‹‹መንግስት ይህን እንዲፈፅም ህዝቡ ለምን ይፈቅዳል?›› ብዬ ስጠይቀው፣ ሀብታሙ አባቴ ፈገግ አለና ‹‹ኃብታሞች እንኳ ጉዳያቸው አይደለም። ደሃዎችና መካከለኛ ገቢ ያላቸው እንጂ›› ብሎ ከመለሰልኝ በኋላ ‹‹እኔ የማገኘው ገቢ ከወላጅ አባትህ ገቢ ቢበልጥም፣ የበለጠ ግብር የሚከፍለው ግን እርሱ ነው›› ብሎ ሊያስረዳኝ ሞከረ። ‹‹ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?›› ጠየቅኩት። ለዘጠኝ አመት ልጅ እንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ሳይገባው ይችላል። አሁንም ደግሜ፣ ‹‹ መንግስት ይህን ሲያደርግ ህዝቡ እንዴት ፍቃደኛ ሆነ?›› ብዬ ጠየቅኩ።

ሀብታሙ አባቴ ለደቂቃዎች ፀጥ ብሎ ተቀመጠ። ሁኔታውን ስገምተው ዝም ብዬ ከምናገር እርሱን እንድሰማ ሳይፈልግ የቀረ አልመሰለኝም።

በመጨረሻም ፀጥ ብዬ መስማቴን የመረጥኩ ቢሆንም፣ የምሰማቸው ነገሮችን አልወደድኳቸውም። ወላጅ አባቴ ዘወትር ግብር መክፈልን በተመለከተ ሲያማርር ብቻ ነው የምሰማው። ግን በማማረሩ የለወጠው ነገር የለም - ህይወት በራስዋ ወዳጅ አባቴን እንዲህ እንዲሆን እየገፋፋችው ይሆን?

ሀብታሙ አባቴ በመቀመጫው ላይ ተሰጥጦ ተቀመጠና በአንክሮ ተመለከተኝ።

‹‹ለመማር ተዘጋጀህ?›› ብሎ ጠየቀኝ።

ጭንቅላቴን በመወዝወዝ መስማማቴን ገለፅኩ።

‹‹እንዳልኩህ ገንዘብን ማሰራትና ሀብትን ማዳበር በዘወትር ህይወታችን ውስጥ እንደ ትምህርት ቤት የምንማረው ትምህርት ነው። በተጨማሪም በየዕለቱ የምትለማመደው ጭምር ማለቴ ነው።

‹‹ተማሪዎች ከኮሌጅ ተመርቀው ለመውጣት 4 ዓመት ይፈጅባቸዋል። የእኔ ትምህርት ግን የህይወት ተሞክሮ ስለሆነ በህይወት እስካለሁ ድረስ የምትማረው ነው። እያልቅም። ብዙ ሰዎች የትምህርት አንዱን ተምረህ ስትጨርስ ወደ ሌላው ትቀጥላለህ፤ ዓይነቱን በሚገባ አያጠኑም። ከዚያም ወደ ሥራው አለም ይገባሉ - ክፍያ ማግኘት ይጀምራሉ - የዕለት ጉርስና መሠረታዊ ነገሮች ያሟሉባቸዋል። በቃ በዚህ አዙሪት ውስጥ

ሆነው ኑሮን ይገፋሉ:: የሚገርምህ ነገር ዘወትር ስለገንዘብ ችግር ሲያወሩ ትሰማለህ:: ከችግራቸው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመለናበት ብዙ ገንዘብን ለማግኘት ይመኛሉ:: ከነዚህ ውስጥ ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው ስለ ገንዘብ አጠቃቀም ምንም እውቀት እንደሌላቸውና የችግሩ ምንጭ ራሳቸው እንደሆኑ ሲያወሩ የምትሰማው::

‹‹ስለዚህ ወላጅ አባቴ የግብር ክፍያ ችግር ስላለበት ነው ገንዘቡን በአግባቡ መጠቀም ያልቻለው?›› ግራ ተጋብቼ ጠየቅኩት::

‹‹ተመልከት›› አለ ሀብታሙ አባቴ ‹‹ግብር ማለት ገንዘብን እንዴት ማሰራት እንደምትችል ማስተማሪያ መንገድ ነው:: ዛሬ ገንዘብን ለሥራ ለመጠቀም ያለህ ሞራል የሚፈትሽበት ጊዜ ነው:: ብዙዎች ይህን አያደርጉም:: ትምህርት ይማራሉ:: ይመረቃሉ በሙያቸው እየሰሩ ገንዘብ መቀበል ብቻ ነው:: በዚህ ሂደት ግን እነዚህ ሰዎች አንድ ቀን በከባድ የገንዘብ እጥረት ውስጥ ይዘፈቃሉ:: ሆኖም ያቺኑ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ሥራቸውን አያቆሙም:: እኔ ይህንን ድርጊት ነው ለገንዘብ ብቻ መስራት እያልኩ የምገልፀው:: እንደ እኔ እምነት ግን ገንዘቡ ለአንተ መስራት አለበት እንጂ አንተ ለገንዘብ ብቻ ብለህ መሥራት የለብህም የምለው:: ይህንን በአጠቃላይ ጨርሶ ለመማር ወኔው አለህ?››

ጭንቅላቴን ወዘወዝ አድርጌ ‹‹አዎ›› አልኩት:: ‹‹መልካም አሁን ወደ ስራህ ተመለስ! እኔም ምንም አልከፍልህም›› አለኝ::

‹‹ምን?›› በመገረም ጠየቅኩት::

‹‹ሰምተኸኛል! ምንም አልከፍልህም›› ልክ እንደ በፊቱ ለተመሳሳይ ሰዓት ትሰራለህ ግን እንደበፊቱ በሰዓት 10 ሳንቲም ክፍያ የለህም:: አንተው ራስህ ገንዘብ ለአንተ እንዲሰራ መማር እፈልጋለሁ በማለትህ ምንም ክፍያ ሊኖርህ አይችልም››

ያለውን ማመን አቃተኝ::

‹‹ከማይክ ጋር ተነጋግረን ነበርኮ:: በአሁኑ ጊዜ የሚሰራው ያለክፍያ መኾኑን አጫውቶኛል:: አይከፈለኝም ብሎ ሰዓት እንኳ አያባክንም - ጥድፊያው በሙሉ ወደ ሥራው ነው›› አለኝ

‹‹ያ ተገቢ አይደለም›› ስል ጮኽኩ:: ‹‹ልትከፍለኝ ይገባል!››



‹‹ለመማር እፈልጋለሁ ብለሃል:: ይህን ካልተማርክ ልክ እንዳየሃቸው ሁለት ሴቶችና አንድ ጎልማሳ ወንድ እንደምትሆን አትጠራጠር›› አለኝ::

‹‹እነዚህ ሠራተኞቼ ገንዘብ ለማግኘት ብቻ የሚሰሩና መቼም ከስራ እንደማናባርራቸው ተስፋ አድርገው የሚኖሩ ናቸው:: ወይም እንደ ወላጅ አባትህ ለከፍተት መሙያ በሚል በሚሰራው ሥራ ብዙ ብር የሚያገኝ ቢሆንም፣ አሁንም ቢሆን ተጨማሪ ብር አግኝቶ ችግሮቹ እንደሚፈቱለት ያምናል:: አንተም ይህን የምትፈልግ ከሆነ፣ 10 ሳንቲም እየሰጠሁ አሰራሃለሁ:: ሌላው አማራጭ ደግሞ አንዳንዶች እንደሚያደርጉት ስራህን ትተህ ሌላ ስራ ፈልግ::›› አለኝ ምርጫውን በእኔ በመተው::

‹‹ምን ላድርግ?›› ስለ ጠየቅኩት::

እናቴን በጣቶቹ ነካ ነካ እያደረገ ‹‹ተጠቀምበት›› አለኝ:: ቀጠለና ‹‹ይህን ከተጠቀምክ ዘወትር ታመሰግነኛለህ! ሀብታምም ትሆናለህ›› ብሎ አደፋፈረኝ::

ግራ በመጋባት ፈዝዤ ለደቂቃዎች እዚያው ቆምኩኝ:: የመጣሁት ለደሞዝ ጭማሪ ነበር እርሱ ግን የባሰውኑ ምንም እንደማይከፍለኝ ነገረኝ::

በድጋሚ እናቴን በጣቶቹ ነካካና ‹‹ዕድሉን ተጠቀም፣ ወደ ሥራህም ተመለስ! ክፍያ ግን አትጠብቅ›› አለኝ፡

*ትምህርት 1፦ ሀብታሞች የሚሰሩት ለገንዘብ አይደለም*

ለደሃው አባቴ ክፍያ እንደማላገኝ አልተናገርኩም:: ሊረዳኝ ስለማይችል መንገሩ አስፈላጊ እንዳልሆነ ተረድቻለሁ:: እኔም ነገሩ ገና አልገባኝም::

ለሦስት ሳምንት ዘወትር ቅዳሜ ከማይክ ጋር ሆኜ ያለክፍያ መስራታችንን ቀጠልን:: ስራውን እየተለማመድኩት ስለመጣሁ የመሰልቸት ባህሪ ሊሰማኝ አልቻለም:: አሁን ያጣሁት ሁለት ነገሮችን ብቻ ነው፤ የቤዝ ቦል ጨዋታና የኮሚክ መፅሃፍቶች መግዣ ሳንቲም::

በሦስተኛው ሳምንት ሀብታሙ አባቴ መኪናውን በመኪና ማቆሚያ ቦታ ሲያቆም የሞተሩን ድምፅ ሰማን:: ከዚያም እሱ ወደ ግምጃ ቤቱ ዘለቀና ወ/ሮ ማርቲንን ከጨበጣት በኋላ ስለ ሥራ እየጠየቃት ወደ አይስክሬሙ መደርደሪያ አመራ:: ሁለት አይስክሬሞቹን እንስቶ አንዱን ለእኔ፣ ሌለውን ደግሞ ለማይክ በሚመስል መልኩ ይዞ እየት አደረገን::

‹‹ት ልጆች ትንሽ ጉፋስ እንቀበል›› አለን። አውራ ጎዳናውን ካቋረጥን በኋላ የመኪና ማቆሚያውን ሥፍራ አለፍ እንዳልን ወደ ትልቁ የስፖርት መስክ አምርተን በትልቁ የአግዳሚ ወንበር ላይ አረፍ አልን። አይስክሬሞቹን ሰጠን። በሜዳው ላይ ኳስ የሚጫወቱ ልጆችም ነበሩ።

‹‹ሥራ እንዴት ነው ልጆች?›› ሲል ጠየቀን።

‹‹ጥሩ ነው›› ማይክ መለሰ።

እኔም በመስማማት መለስኩ።

‹‹ትምህርት አገኛችሁ ከሥራው?›› ጠየቀን

የተመካከረን ይመስል ሁለታችንም እኩል ጭንቅላታችንን በመነቅነቅ ስምምነታችንን ገለፅን።

### ከሕይወት ታላላቅ ማነቆዎች አንዱን ማስወገድ

‹‹ደህና። አሁን እየተረዳችሁኝ እንደሆነ ይሰማኛል። ዋናውንና በህይወታችሁ ትልቁ ትምህርት ላይ ትኩረት አድርጋችኋል። በዚህም ከተማራችሁበት ደስታ፣ነፃነትና ደህንነትን ትቀዳጃላችሁ። ካልሆነ ደግሞ ልክ እንደነዚህ ኳስ እንደሚጫወቱ ልጆች ወይ እንደ ወ/ሮ ማርቲን ትሆናላችሁ። እነዚህ ሰዎች በጥቂት ክፍያም ቢሆን ጠንክረው ይሰራሉ። ለስራቸው ደህንነት ያስባሉ። በአመት ለሦስት ሳምንት ሽርሽር ይወጣሉ። ከዚያም ከ45 ዓመት የሥራ አገልግሎት ዘመን በኋላ ጡረታ ይወጣሉ። ይህ ሂደት የሚያስደስታችሁ ከሆነ በሰዓት 25 ሳንቲም ልከፍላችሁ እችላለሁ›› አለና ንግግሩን ገታ አደረገ።

‹‹እነዚህ ጠንካራ ሰዎች ኾነው ሳለ አንተ ግን እያሾፍክባቸው ነው ›› አልኩት።

ፈገግ አለ ሀብታሙ አባቴ።

‹‹ወ/ሮ ማርቲን ለእኔ እንደ እናት ናት። በእርሷ ላይ የሚጨክን አንጀት የለኝም። ይህን እንደምሳሌ ያነሳሁት እናንተን ማስተማር ስላለብኝ ነው። ትምህርቱን ሰፋና ገላጭ አድርጌ ላሳያችሁ፤ ግንዛቤያችሁም ይሰፋል ብዬ አምናለሁ። ብዙዎች የሚገነዘቡትም ይህንን ነው። ራዕያቸው ጠባብ በመሆኑ የተከበቡትን ወጥመድ አይረዱትም፤ አያዩትም።





እኔና ማይክ ስናዳምጥ ቆየን። ንግግሩን በሚገባ የተረዳነው ባይሆንም በንግግሩ ውስጥ ጭካኔዎች ያሉ ይመስላል። ይሁን እንጂ ሊያስተምረን እና ሊያሳውቀን የፈለገው ነገር እንዳለ መረዳት ችለናል።

ፈገግ አለና ‹‹25 ሳንቲም በሰዓት ጥሩ ነው? ልባችሁንስ ደስ አያሰኝም?›› ሲል ጠየቀን። በመቃወም ጭንቅላቴን ወዘወዝኩና ‹‹አይ›› አልኩት በውስጤ የሚሰማኝ ነገር እንዳይታወቅብኝ እየጣርኩ። አዎ! 25 ሳንቲም ለእኔ የተሻለ ክፍያ ነው።

‹‹እሺ በሰዓት አንድ ዶላር ልክፈላችሁ?›› በማለት ቀጥሎ ተናገረ።

የልቤ ምት ጨመረ። በሚከፈለኝ ዶላር ምን እንደሚያደርግበት ከወዲሁ ማሰብ ጀመርኩኝ።

የሰማሁትን ለማመን ቢከብደኝም ምንም መተንፈስ አልፈለግኩም።

‹‹እሺ! በሰዓት ሁለት ዶላር ላድርግላችሁ›› ሲለን ትንሽዋ ጭንቅላቴ ለመፈንዳት ተቃረበች። በወቅቱ ማለት በ1956 ዓ.ም በሰዓት ሁለት ዶላር ሊከፈለኝ ከቻለ ሀብታሙ ሕፃን እንደምሆን ጥርጥር የለውም። ይህን ያህልም ይከፈለኛል ብዬ አላስብም። ‹እሺ› ብዬ ለመስማማትም ፈለግኩ። ብስክሌተኛና ቤዝ ቦል ተጫዋች ጓደኞቼን በመጋበዝ ተወዳጅነትን ማግኘት ፈለግኩ። ከሁሉም በላይ ጂሚና ሌሎች ሀብታም ጓደኞቼ ‹ደሃ› ብለው መጥራታቸውን ሲያቆሙ ነው። ሆኖም አሁንም ዝምታን ነው የመረጥኩት።

እርግጥ ነው ሁለት ዶላር ክፍያ የምፈልገው አይነት ነው፤ ግን መናገርን አልመረጥኩም - አዕምሮዬም ተጨናንቋል።

አይስሬሙ ቀልጦ ወደ ጣቶቼ ሲደርስ ተሰማኝ።

ሀብታሙ አባቴ ሁለታችንንም በትኩረት እየተመለከተን ነው። ዐይኖቹን ከፊቶ እየገመገመን እና ስሜታችንን እያጠና እንደሆነ ተረድተናል።

ከሁሉም በላይ በውስጣችን የተደረገልንን ጭማሪ የመቀበል ክፊል ዝንባሌ እንዳለው ተረድቷል። በሌላ በኩል በሁሉም የሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ደካማ ጎን እንዳለውና ለክፊል የፍላጎት መገለጫ ነፍሱ ራሱን የማያስገዛ መሆኑን ከእኛ ውስጥ እንዳለ አውቆታል። እዚህ ጋር ዋናው መመለስ ያለበት ጥያቄ ግን የትኛው ጎን ነው እንደጥንካሬ ሊወሰድ የሚገባው የሚለው ነው። በሕይወቱ ውስጥ የበርካታ ሰዎችን ነፍላዊ ዝንባሌዎችን ሲፈትሽ እንደቆየ እሙን ነው። በተለይ የሰዎችን ውስጣዊ ዝንባሌ

ሲያደርግላቸው ነፍሳቸውን በመቅጠር ቃለ መጠይቅ ሲያደርግላቸው ነፍሳቸውን
ለመረዳት ሲል፣ ሰራተኞችን በመቅጠር ቃለ መጠይቅ
ፍርፍርፕ አድርጎ ሲፈትሽ ቆይቷል።

ፍርጥርጥ አድርጎ ሲፈትሽ ቆይቷል።
ፍርጥርጥ አድርጎ ሲፈትሽ ቆይቷል። ‹‹እሺ በሰዓት አምስት ዶላር ይሁንላችሁ›› ሲል ጠየቀን።

ቀጠል አደረገና ‹‹እሺ በሰዓት አምስት ዶላር ይሁንላችሁ›› ሲል ጠየቀን።

ቀጠል አደረገና ‹‹እሺ በሰዓት አምስት ዶላር ይሁንላችሁ›› ሲል ተሰማኝ። አንድ ነገር መልኩን እየቀየረ
ወዲያው ውስጤ ፀጥ ረጭ ሲል ተሰማኝ። አንድ ነገር መልኩን እየቀየረ
መጥቷል። የአሁኑ የክፍያ ጥያቄ መጠን በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ጉዳዩ የይስሙላ
አይነት የሚመስል ነው። በዚያ ዘመን እንኳን እኛ፣ ትልልቆቹም ይህንን ያህል ክፍያ
አያገኙም ነበር። ከዚያም ፈተናው ሲጠናቀቅ፣ በመሃከላችን ፀጥታ ነገሰ። በቀስታ ወደ
ማይክ እያየሁ ነበር። ከዚያም ፈተናው ሲጠናቀቅ፣ በመሃከላችን ፀጥታ ነገሰ።
ግራዬ ገልመጥ ብዬ ማይክን አየት አደረግኩት።

ግራዬ ገልመጥ ብዬ ማይክን አየት አደረግኩት።
ግራዬ ገልመጥ ብዬ ማይክን አየት አደረግኩት። በፍላጎት የተሞላው የነፍሴ ክፍል ፀጥ አለ።

እሱም እያየኝ ነበር።ደካማውና በፍላጎት የተሞላው የነፍሴ ክፍል ፀጥ አለ።
በተቃራኒው ሌኛውና ክፍያን የሚያስቀድመው ነፍሴ በአዲስ መልክ ሲነቃቃ ተሰማኝ።
ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ፀጥታና እርግጠኝነት የተመላበት መንፈስ ወደ አዕምሮዬና ነፍሴ
ውስጥ መግባቱን ተረዳሁ። እርግጠኛ ነኝ ማይክም ውስጥ ተመሳሳይ ሁኔታ ነው
የተፈፀመው።

‹‹መልካም›› አለ ሀብታሙ አባቴ ‹‹ብዙ ሰዎች ዋጋ ይፈልጋሉ። ምክንያቱም
ስሜታቸው በፍርሃትና በስግብግብነት የተሞላ ስለሆነ ነው። ልብ በሉ በመጀመሪያ
ስሜታቸው በፍርሃት የሚሞላው ያለ ገንዘብ መኖር ስለማይችሉ ነው። በርትተው
ይሰራሉ፤ ክፍያንም ሲያገኙ ስግብግብነት ስለሚከተል የሚፈልጉትን ሁሉ በገንዘብ
ይገዛሉ። ይህ ነው እንግዲህ አካሄዱ›› ሲል ተናገረ።

‹‹የምን አካሄድ?›› ስል ጠየቅኩ።

‹‹ከእንቅልፍ መንቃት፣ ልብስን ለብሶ፣ ቁርስ በልቶ ወደ ስራ መሄድ ከዚያም
ቤት ኪራይ እና የዕለት ተዕለት ወጪን በወርሃዊ ወይም በሳምንታዊ ደሞዝ እየሸፈኑ
መሄድ ... ይቀጥላል። በዚያው መጠን መላ ህይወታቸውም ከዚህ አዙሪት ውስጥ ሆኖ
በሚቀጥል የፍርሃት እና ራስ ወዳድነት ስሜት በውስጣቸው እየነገሰ ይመጣል። የተሻለ
ገንዘብም ሲያገኙ ሂደቱም መቀጠሉ አይቀርም። ወጪያቸውም በዚያው ልክ
ይጨምራል።

‹‹ሌላ አማራጭ አለ?›› ማይክ ጠየቀው።





‹‹አለ›› ረጋ ብሎ መለሰ። ‹‹ነገር ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው ይህንን የሚረዱት››
ሲልም ቀለል አድርጎ ተናገረ።

‹‹እና ምንድነው የኛው አማራጭ?›› ማይክ በድጋሚ ጠየቀው።

‹‹ይህንንማ እናንተው ራሳችሁ በሥራ ሂደት ውስጥ እንድትደርሱበት ነው
የምፈልገው። ለዚያም ነው የአንድ ሰዓት የሥራ ክፍያን ከ10 ሳንቲም እስከ አምስት
ዶላር አማራጭ አድርጌ ያስቀመጥኩላችሁ።››

‹‹ፍንጭ የለም?በስራው በጣም ስለተዳከምን እና ያለስራ ክፍያ እየሰራን ስለሆነ፣
ብርታት ይሆነን ዘንድ ጠቆም ብታደርገን› ብሎ ማይክ ተስማመጠ።

‹‹ደህና፣ የመጀመሪያው እርምጃ እውነትን መናገሩ ላይ ነው›› ሀብታሙ አባቴ
ተናገረ።

‹‹‹እየዋሸንህ አይደለም›› በማለት ለማስረዳት ሞከርኩ።

‹‹እየዋሻችሁኝ ነው እያልኩ አይደለሁም፤ እኔ የምለው እውነቱን ልንገራችሁ
ነው›› አለን።

‹‹ምንን በተመለከተ ነው ስለ እውነት ልትነግረን የፈለግከው?››

‹‹አንተ እያልክ ያለኸው፣ በዚህ ፓርክ ውስጥ ስለሚገኙትና ከአንተ ጋር
አብረውህ ስለሚሰሩት ነው። ለምሳሌ ወ/ሮ ማርቲን ... እነርሱ እንደዚያ ማድረግ
አልቻሉም?›› እኔ ነበርኩ የጠየቅኩት።

‹‹አይመስለኝም። ምክንያቱም ያላቸውን ገንዘብ ከማሰራትና ሀብትን ከማዳበር
ይልቅ ገንዘቡ ክፍተትን እንዲሞላ ብቻ ነው የሚጠቀሙበት። አዕምሮአቸውን ከመጠቀም
ይልቅ በስሜት ይመራሉ።›› በማለት ተናገረ።

ቀጥሎም ‹‹ጥቂት ደሞዝ ያገኛሉ፤ ያቺንም ፍርሃትና ስግብግብነት በተሞላበት
ሁኔታ ለዕለት ጉርስና ለዕለት ወጪ ማዋሉን ይቀጥላሉ። አስተውሉ፣ ደሞዝ
ቢጨምርላቸው እንኳ ፍላጎታቸው ስለሚጨምር ገንዘቡን ማውጣታቸው አይቀርም።
ገንዘቡ እንዲሰራና ሌላ ተጨማሪ ገንዘብን እንዲያመጣ አያደርጉትም›› በማለት ንግግሩን
ገታ አደረገ።

‹‹ስለዚህ ስሜታቸው አመለካከታቸውን ያሸንፈዋል?›› አለ ማይክ።

‹‹አዎ… ልክ ነህ … እውነቱ ምን እንደሆነ ከማሰላሰል ይልቅ ለስሜታቸው ይገዛሉ:: ፍርሃትን በመሸሸና ካለባቸው ችግር ለመራቅ ሲሉ ሥራ ይሰራሉ:: በምላሹም የሚያገኙትን ገንዘብ ለዕለት ወጪያቸው ያውሉታል›› ፍርሃት በራሱ ወጥመድ በመሆኑ ብዙዎችም ከዚህ ህይወታቸው የዕለት የተዕለት ህይወታቸው በዚህ ዐይነት ይቀጥላል:: ብዙዎችም ከዚህ ህይወታቸው የተነሳ የሚፈጥርባቸው ጭንቀት ከቀን እልፎ በሌሊትም እንቅልፍ ይነሳቸዋል:: አሁንም በአዕምሮአቸው የሚሰሩት ይህንን ፍርሃትን ለማሸነፍና ከፍርሃትም ለማምለጥ ይሆናል:: በአዕምሮአቸው ከማሰብ ይልቅ በገንዘባቸው ማሰብ ስለሚጀምሩ ህይወታቸው ከፍርሃት መላቀቅ አይችልም::››

እኔና ማይክ በንግግሩ ብንስማማም ሙሉ በሙሉ ግን ተረድተነዋል ወይም ገብቶናል ለማለት ግን አይቻልም:: ልክ እንደ ሀብታሙ አባቱ ያሉ ትልልቅ ሰዎች ከተናገሩ በኋላ ፊታቸው ላይ ምንም ዐይነት ስሜት እንደማይታይባቸውና እንደማይገረሙ ሳስተዉል ደነቀኝ::

ሀብታሙ አባቱ ቀጠለና ‹‹እናንተ ልጆች ከፍርሃት ወጥመድ ራሳችሁን አውጡ! ይህንንም ከእኔ መማር አለባችሁ:: ሀብታም መሆን ብቻ ከዚህ አያወጣም:: ነፃ የሚያወጣው ከፍርሃት ወጥመድ ራስን ማላቀቅ ብቻ ነው›› ብሎ ንግግሩን ጨረሰ::

በመደነቅ ‹‹ሃብታም መሆን በራሱ ከፍርሃት ነፃ አያወጣም እንዴ?›› በማለት ጠየቅኩት::

‹‹አዎ አያወጣም›› አለና ‹‹ሌላው ችግር ስግብግብነት ነው:: አንዳንዶቹ መቋመጥ ይሉታል:: እኔ በግሌ የተሻለ ነገርን ለመስራትና ለማግኘት መቋመጥ መልካም ነው እላለሁ:: ሰዎችም የሚሰሩት ይህንን ለማምጣት ነው:: የተሻለ ሀሴትን ለማግኘት - ሆኖም የሚገርመው በገንዘብ የሚገኝ ደስታ እድሜው አጭር ሲሆን፣ የገንዘቡ እቅም በዋዣቀ ቁጥር ፍርሃትን እና ስግብግብነትን መፍጠሩ አይቀርም:: ስለሆነም ገንዘብ ሰዎችን ከፍርሃትና ከስግብግበነት የሚያወጣ ኃይል አይደለም›› ሲል መለሰልኝ::

‹‹ይህ ሀብታሞችን ያካትታል?›› ማይክ ነበር ጠያቂው::

‹‹አዎ›› አለ ሀብታሙ አባቱ:: ‹‹በርግጥም የአንዳንድ ሀብታሞች የሀብት ሚስጥር ከፍርሃትና መቋመጥ ጋር ሲያያዝ፣ የገንዘብ መኖር ፍርሃትን ያስወግዳል ብለው ያምናሉ::››





‹‹በዚህም መንገድ ድህነትን ጨርሶ እንደመንቃቂያ ዘዴ አድርገው ያስቡታል:: በመሆኑም ሀብት መሰብሰብን ይቀጥላሉ:: አንዳንድ ወዳጆቼ ሀብት ቢኖራቸውም ከመጠን በላይ ሲሰሩ ይታያሉ:: ሀብታቸውን እንዳያጡ ስለሚፈሩ፣ በሚሊዮን የሚቆጠር ሀብት እንኳ ቢኖራቸው ደሃ በነበሩ ጊዜ ከተሰማቸው ፍርሃት በባሰ መልኩ ስለሚፈጠርባቸው ያለ ዕፍረት ሌት ተቀን መሥራትን የሙጢኝ ይላሉ:: ከፍርሃት ለመላቀቅ ያካበቱት ሀብትም መላ አይዘይድላቸውም - ይባስ በሎ የመንፈስ እረፍት ይነሳቸዋል:: ደካማውና ለሀብት የሚንሰፈሰፈው የማንነታቸው ክፍልም መልሶ ራሳቸውን ሲያስጨንቃቸው ይታየል::

የሚያምር ቪላ ቤታቸው፣ ውድ መኪኖቻቸውና የተንደላቀቀ አኗኗራቸውን ማጣትን ሲያስቡት ያስጨንቃቸዋል:: በመጨረሻም ሀብታቸውን ማጣት ሲጀምሩ፣ ጓደኛ፣ ወዳጅ፣ እንዲሁም ጠላታቸው ሳይቀር ‹ምን አለ? ምን አሉ?› እያሉ መጨነቅ ይጀምራሉ:: ስለሆነም ብዙዎች በመንፈስ ጭንቀት የተነሳ አዕምሮአቸው የተወጠረና ተስፋ የቆረጡ ይሆናሉ››::

‹‹ታዲያ ድሆች የተሻለ ደስታ አላቸው ማለት ነው?›› ብዬ ጠየቅኩት::

‹‹አይመስለኝም! በገንዘብ አለመኖር ልክ ገንዘቡ እያላቸው ደስታን በገንዘብ የገዙ የመሰላቸው ጥገኞች ይፈጠራሉ፤ በአንፃሩ ገንዘብም ባይኖራቸው ወደፊት ደስታን በገንዘብ እንገዛለን ብለው በሚያስቡ መካከል ልዩነት የለውም!››

ይህን እየተነጋገርን ባለንበት ወቅት አንድ አዛውንት የጎዳና ተዳዳሪ ባጠገባችን አለፉና በአካባባው የሚገኙትን የቆሻሻ መጣያ ሳጥኖች መልከት መልከት ማድረግ ጀመሩ::

ሀብታሙ አባቴ፣ ከቦርሳው ውስጥ ዶላር አውጥቶ ለሽማግሌው ሲሰጣቸው አዛውንቱ ዕድላቸውን እያመሰገኑ ከቦታው ወዲያውኑ ተሰወሩ::

‹‹የእኔ ሰራተኞች በቀን 8 ሰዓት ለገንዘብ ሲሉ እየሰሩ፣ ‹እኔ ለገንዘቡ ግድ የለኝም› ይላሉ:: ይህ እንግዲህ ልብ በሉ እውነትን እንደ መካድ የሚቆጠር ነው:: ለገንዘብ ግድ ከሌላቸው ያን ያህል ሰዓት በቀን ውስጥ መልፋት ለምን አስፈለጋቸው? እንደዚህ ዐይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች ከአዕምሮ ህመምተኛ በምንም አይለዩም ቢባል ሀሰት ወይም የተጋነነ ነው ሊባል ይችል ይሆን?›› አለ::

ሀብታሙ አባቴን ሳደምጠው፣ በአዕምሮዬ ድንገት ወላጅ አባቴ መጣብኝ። አዎ
ወላጅ አባቴ ሁሌም ለገንዘብ ግድ የለኝም የምሰራውም ሥራዬን ስለምወደው ነው ይላል።
‹‹ስለዚህ ምን ማድረግ አለብን? መፍትሄ የሚሆነው ስግብግብነትና ፍርሃት
እስኪወገዱ ድረስ መስራት ነው?›› በማለት ጠየቅኩት።

‹‹አይደለም። ይህም ቢሆን ጊዜን ማባከን ነው፤ ስሜት የሰውነታችሁ አንዱ መገለጫ ነው፤ ቃሉም ኃይል ከሚለው ጋር ጥብቅ ትስስር አለው።ስሜትህ ዕውነት ላይ የተመሰረተ ይሁን፤ አዕምሮን መጠቀም ደግሞ ስሜታዊነትን ለማረቅ ይረዳል።››

‹‹ምንድን ነው?›› በማለት ማይክ ጉዳዩ እንዳልገባው በሚጠቁም መልኩ ጥያቄውን አቀረበ።

‹‹አሁን ስላልኩት ነገር ባይገባችሁም ብዙም አትጨነቁ። አንድ ቀን አንድ በአንድ ሊታወሳችሁ ይገባል። በስሜት ውስጥ ሆናችሁ ለመወሰን አትጣደፉ፣ ተመልካችነትን ምረጡ። ብዙዎች ስሜታቸው እንደሚያሳስታቸው አይረዱም። ለዚያም ነው ስህተት ውስጥ የሚገቡት። እናንተ ግን በስሜት ማሰብን ፈጽሞ አታስቡት። ስሜት ሌላ ... ሃሳብ ሌላ።››

‹‹እስኪ ምሳሌ ብትሰጠን ትችላለህ? ጠየቅኩት።

‹‹መልካም፣ ለምሳሌ አንድ ሰው ሥራ እፈልጋለሁ ሲል በአብዛኛው በስሜቱ ተመርቶ ነው፡ ያለገንዘብ የመኖር ፍርሃት ደግሞ እንደዚያ እንዲል ያደርገዋል።››

‹‹ሆኖም ሰዎች የቤት ኪራይ ካለባቸው የግድ ገንዘብ ይፈልጋሉ›› አልኩት።

‹‹ልክ ነው እኔ የምለው እንደዚያ እንዲያስቡ የሚያደርጋቸው ፍርሃት ነው ነው።››

‹‹አልገባኝም›› ማይክ ጠየቀ።

‹‹ለምሳሌ ገንዘብ የማጣት ስሜት እያደር ከጨመረና ስራን አግኝቶ ፍርሃትን መዋጋት በምትኩ የማኖር ከሆነ፣ እራሳቸውን እንደዚህ ሊሉ ይጠይቃሉ።›› ስራው ይህን ችግር በዘላቂነት በመፍታት መፍትሄ ይሆናልን?› በእኔ አመለካከት አይሆንም ነው የምለው። በተለይ የሰውን ዕድሜ ዘመን ስናይ ይህ ሊሆን አይችልም። ለረጅም ዘመን ችግር የአጭር ዘመን መፍትሄ አያዛልቅም ነው እያልኩ ያለሁት። ስራን በመስራት



የዕለት ችግርን ለመውጣት ግን የገንዘብ አጠቃቀምን በሚገባ ማወቁ ትልቁን ሚና ይጫወታል›› አለን

‹‹አባዬ ግን አጥና፣ጥሩ ውጤት በትምህርት አስመዝግብ ከዚያ የተሻለ ሥራን ታገኛለህ ይለኛል›› በማለት በመጨናነቅ ስሜት ተናገርኩኝ።

‹‹አዎ ያለው ይገባኛል። ብዙዎች ምክራቸው ይኸው ነው። አብዛኞዎች አማራጭ የሌለው መልካም የህይወት መንገድ እንደሆነ ያምናሉ። ይሁን እንጂ የሚገርመው ነገር፣ እንዲህ የሚሉት በውስጣቸው ፍርሃትን ስለሚይዙ ነው። ፍርሃቱም እንደዚያ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል።››

‹‹አባቴ ያንን ያለኝ ስለሚፈራ ነው?››

‹‹አዎ ገንዘብ ባለማግኘትህ ምክንያት ከማህበረሰቡ እንዳትገለልበት በመፍራት ነው። አደራ ተረዳኝ፣ አባትህ ይወድሃል፣ የተሻለ ነገር እንዲገጥምህ ይመኛል። ፍርሃቱንም ለማሸነፍ ትምህርትና ስራ ወደር የሌላቸው መፍትሄዎች እንደሆኑ ያምናል። ግን ልብ በል አባትህ ተማር፤ ተመረቀ። ከዚያም ጥሩ ሥራን በመያዝ ጥሩ ገቢ እያገኘ ነው። ፍርሃቱ ግን የለም? በጠዋት ወደ ሥራው የሚጣደፈው ገንዘብ እንዳላጣ የሚለው ስጋት አይደለም? አንተንስ ትምህርት ቤት ሂድ የሚልህ ከዚያ የመነጨ አይደለም?››

‹‹ስለዚህ አንተ ምን ትመክረኛለህ?›› ጠየቅኩት።

‹‹በበኩሌ ላስተምራችሁ የምፈልገው፣ የገንዘብን ሃይል እንድትረዱ ነው። የገንዘብ እንድትፈሩት ሳይሆን እንድትማሩበት ለማድረግ ሲሆን፣ ይህን ማድረግ ብቻ ባሪያ ከመሆን ትድናላችሁ። ይህንን እንግዲህ በትምህርት ቤት ውስጥ አትማሩትም›› በማለት ንግግሩን ገታ።

በስተመጨረሻ ነበር፣ ስለ ገንዘብ ያለንን አስተሳሰብ በአዕምሮአችን ውስጥ እንዲሰፋ ለማድረግ እየጣረ እንደሆነ የገባን። ወላጅ አባቴ፣ ወ/ሮ ማርቲን እና ሌሎች የእርሱ ተቀጣሪዎች ያሳዩትን ነው ለእኛ ለማሳየት የሞከረው። አንዳንዴ የሚጠቀምባቸው ምሳሌዎች ጨካኝ ሊያሰኘው የሚያስችል ቢሆንም፣ እውነቱ ግን ያ አይደለም። ምክንያቱም በምሳሌዎቹ አዕምሯችን እንዲሰፋ ጥረት አድረጓል።

‹‹ተመልከቱ፣ ሁላችንም ወጥመድ ውስጥ ነን። የምመክራችሁ ብዙዎችን የያዘው ይህን ወጥመድ ጥሳችሁ እንድትወጡ ነው። የፍርሃትና የስግብግብነት ወጥመድ።

እናንተን ለሚጠቅም ነገር ብቻ፣ በመልካምነት ማግኘውንም ነገር ተጠቀሙ:: ይህን ነው እንግዲህ መማር ያለባችሁ:: የገንዘብ ክምር እንድትፈጥሩ ማስተማር ሳይሆን፣ የራሳችሁን ገንዘብ በአግባቡ መጠቀምን እንደትችሉ ማድረግ ነው የትምህርቱ ቁልፍ ነው:: ምክንያቱም ይህ ነው ከፍርሃትና ስግብግብነት /መቋመጥ/ ነፃ የሚያወጣችሁ::

‹‹በትድሚያ እነዚህን ካላስወገዳችሁ ደግሞ ገንዘብም በብዛት አግኝታችሁ ሀብትን ብትፈጥሩም የገንዘብ ባሪያ መሆናችሁ አይቀርም›› አለን::

‹‹ይህን ወጥመድ እንዴት ልናስወግደው እንችላለን?››

‹‹የድሃነት ዋናው ምክንያት ፍርሃትና አለማስተዋል ናቸው:: ይህ ወጥመድ ብዙዎችን ዘወትር ዕረፍት እየነሳ፣ ለከፍተት መሙያ ብለው በስራ መዳከርን ያስከትልባቸዋል:: ስለዚህ ልጆች በትምህርታችሁ ዲግሪያችሁን ያዙ - እኔ ደግሞ ከወጥመዱ እንድትወጡ አደርጋለሁ›› አለን::

ወላጅ አባቴ የተሻለ ትምህርትና ገቢ ያለው ይሁን እንጂ የሚያገኘውን ገቢ እንዴት እንደሚጠቀምበት ለማወቅና ፍርሃትን ማስወገድ ግን አልቻለም::

ሁለት አባት ስላለኝ የተለያዩ ዕውቀቶችን ለመገንዘብ ችያለሁ::

‹‹ያለገንዘብ መኖር ስለሚፈጥረው ፍርሃትና ስለሚያመጣው የአስተሳሰብ ጫና ልትነግረን ትችላለህ?›› ማይክ ነበር ጠያቂው::

‹‹የደሞዝ ጭማሪን ተንተርሼ ስፈትናችሁ ምን ተሰማችሁ? የመቋመጥ ስሜት ውስጣችሁን አልተቆጣጠራችሁም?›› ብሎ ጠየቀን::

በመስማማት ጭንቅላታችንን ነቀነቅን:: ‹‹ከሁሉም በላይ አስፈላጊው ነገር ስሜትን ተቆጣጥሮ ከድርጊት ለመቆጠብ መቻል ሊሆን፣ የስሜታዊነትን ስዋዊ ተፈጥሮ ተረድቶ በገንዘ መልኩ ለቁምነገር ማዋል ብቻ ነው:: እዚህ ላይ ስሜትን ሳይሆን ቀም ነገርን (አስተዋይነትን) ማስቀደም አለባችሁ:: ብዙዎች ችግራቸው ስሜታዊነታቸውን ለጥፋት ይጠቀሙበታል:: ያ ደግሞ የአስተዋይነት መገለጫ አይደለም:: ብዙዎች ከደሞዛቸው የጡረታ ገንዘብ ይቆረጥባቸዋል:: ለዚህም ምክንያቱ ከሥራ ውጪ በኋላ ምን እበላለሁ ከሚል ፍርሃት የመነጨ ነው::

‹‹ስለዚህ መልሱ ምን ይሆን?›› ማይክ ጠየቀ::





‹‹ፍርሃትን የሚወልደው አለማስተዋል ነው:: ማስተዋል የሌለበት ሀብት ደግሞ በበዛ ቁጥር ፍርሃትንንና ለሁሉም ነገር መቋመጥን ያስከትላል:: የመጨረሻ ውጤቱም ጥፋት ይሆናል:: የሰው ህይወት በትግል የተሞላ ሲሆን፣ ትግሉም የሚካሄደው በማስተዋልና በአለማዋስተዋል መካከል ነው::››

‹‹አለማስተዋል ከፍርሃትና ከስግብግብነት ጋር ምን ያገናኘዋል?››

‹‹ምክንያቱም ማስተዋል ፍርሃትን እና ስግብግብነትን ይፈጥራል፤ እስኪ ጥቂት ምሳሌ ልስጣችሁ:: አንድ ሀኪም የቤተሰቡን ኑሮ ለማሳደግ ሲል ገቢውን ከፍ ያደርገዋል:: ገቢው ከፍ የሚለውም የህክምና አገልግሎት ዋጋው ከፍ ሲል ነው:: ተመልከቱ ይህ ደግሞ ደሃውን ይጎዳዋል:: ከፍሉ መታከም ስለማይችል::ስለዚህ ድሆች ከሀብታሞች ያነሰ ጤና ሊኖራቸው ይችላል ማለት ነው::

ሁሉም የአገልግሎት ዋጋን በጨመረ ቁጥር ግብርም እንደዛው መጨመሩ አይቀርም:: ከዚያማ የኑሮ ልዩነት በደሃና በሀብታሙ መካከል እየተፈጠረ ለሀብት ትርምስ በር ይከፍታል:: አብዮትም የሚፈጠረው የድሃና የሀብታሙ የኑሮ ልዩነት ከፍተት በጣም ሲሰፋ መሆኑን ማወቅ አለባችሁ:: ለዚህ ጥሩዋ ምሳሌ ደግሞ አሜሪካ ስትሆን፣ ከታሪክ መማር ባለመቻላችን ታሪክ ራሱን ሲደግም በቋፍ ላይ ነን:: ከታሪክ ከመማር ይልቅ፣ ታሪኩ የተጻፈበትን ዓመት፣ቀን፣ ወር እንዲሁም ባለታሪኮቹን ማሰብ ይቀለናል::››

‹‹የአገልግሎት ዋጋዎች መጨመር የለባቸውም?›› ስል ጠየቅኩት::

የተማረና የሰለጠነ ማህበረሰብ እንዲሁም መሠረቱ ጠንካራ የሆነ መንግስት ባለበት አገር ዋጋዎች መጨመር ሳይሆን እየቀነሱ መምጣት ነው የሚኖርባቸው::በርግጥ ይህ በቲዎሪ ብቻ እውነት መሆኑ አይካድም:: ዋጋዎች የሚወደዱት ግን በእጥረት ብቻ ሳይሆን በስግብግብነትና በፍርሃት ነው:: ለዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያት አለማስተዋል ነው: ት/ቤቶች ስለገንዘብ አጠቃላይ ግንዛቤን ቢፈጥሩ የተሻለ ገንዘብና የዋጋ ቅናሽ እናይ ነበር:: ሆኖም ት/ቤቶች የሚያስተምሩት እንዴት ገንዘብ ማግኘት እንደሚቻል ብቻ ነው::

እንዴት ተደርጎ ገንዘብን ማበልፀግና በአግባቡ መጠቀም እንደሚቻል ግንዛቤ አይፈጥሩም::

‹‹የንግድ ሥራ ት/ቤቶች የሉንም እንዴ?›› ማይክ ጠየቀ::

‹‹በእርግጥ አሉ! ትምህርታቸው ግን ዘመናዊ ትምህርትን ተጠቅሞ ዶላርን ከመቁጠር አያልፍም፡፡ ሰው ሳይሆን ማሽኖቹ የንግዱን ሥራ ተቆጣጠሩት! ይህ ደግሞ የሰዎችን ሚና ይቀንሳል›› ሲል በንዴት ተናገረ፡፡

‹‹ስሜታችሁ ለማስተዋል ተጠቀሙበት እንጂ ባለማስተዋል በስሜት አትነዱ፡፡ ስሜትን ስትቆጣጠሩ ደግሞ ነገን ተስፋ በማድረግ በነፃም ቢሆን ስራን መስራት አትፀየፉ፡፡ ብዙ ገንዘብ ልጨምርላችሁ ብዬ ስፈትናችሁ ማስተዋልን እየተለማመዳችሁ ነበር፡፡ ያ ባይሆን በስሜት በመነዳት እሺ ትሉ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ የማስተዋል ጅማሮ ነው››

‹‹እንዴት ጅማሮ ሆነ?›› ጠየቅኩት፡፡

‹‹ደህና ይህ የሆነበትን ምክንያት እናንተ ልትደርሱበት ይገባል፡፡ መማር ከፈለጋችሁ ደግሞ እሾሃማ ወደሆነ አንድ ሥፍራ እወስዳችኋለሁ፡፡ ብዙዎች አካባቢውን ይፈሩታል፡፡ ከእኔ ጋር ከሄዳችሁ ለገንዘብ መስራትን በመተው ገንዘብ ለእናንተ እንዲሰራ ማድረግን መማር ትችላላችሁ፡፡››

‹‹ከአንተ ጋር በመሄዳችን ምን የምናገኘው ነገር አለ? የምንማረውስ ምንድን ነው?›

‹‹ልክ- በዚያ እሾሃማ ስፍራ እንዳሉት ጥንቸሎች ነፃ ትወጣላችሁ፡፡ እናንተ ግን ከፍርሃትና ከስግብግብነት ነው ነፃ የምትወጡት›› አለን፡፡

‹‹በእርግጥ በዚያ ስፍራ እንደዚያ አይነት ነገር አለ?›› ጠየቅኩት

‹‹አዎን የናንተ ወጥመድ ግን እንዳልኩት ፍርሃትና ስግብግብነት ነው፡፡ ወደዚያ ዐይነት ስሜት መግባት ድክመታችን ሲሆን ከዚህ መውጫ መንገዱም አዕምሮአችንን በመጠቀም አለማስተዋልን በማስተዋል በመተካት ነው›› ሲለን ማይክም ቀጠል አድርጎ! ‹‹ማስተዋልን ካለማስተዋል መምረጥ?›› አለ፡፡

‹‹አዎ መምረጥ፡፡ በስሜት ተነድተን ወደ ተግባር ሳንገባ የችግሩን ምንጭ ማጤንና ዘላቂ መፍትሄ መፈለግ ይገባል፡፡››

‹‹ይህን እንዴት ልናደርገው እንችላለን?›› ማይክ ጠየቀ





‹‹እንግዲህ ይህን እንድታውቁትና ማስተዋልን እንድትለማመዱት ነው ላስተምራችሁ የወሰንኩት፡፡ ይህንን በማድረጌ ከጥድፊያ ህይወት ውስጥ ሳትገቡ ቆም ብላችሁ በህይወት ዙሪያ እንድታስቡ ያደርጋችኋል ከአጉል መጣደፍም ይገታችኋል፡፡

‹‹አስታውሱ ሥራ ማለት እንደነገርኳችሁ ለረጅም ጊዜ ችግር! የአጭር ጊዜ ወይም ዘላቂ ያልሆነ መፍትሄ ሰጪ ሲሆን! ችግርን በዘላቂነት የማያስወግደውም፣ ልክ እንደ ቤት ኪራይ በየወሩ ወይም በየተወሰነ ጊዜ በመደጋገሙ ነው፡፡ በእንደዚህ ዐይነት ህይወት ውስጥ ያሉትን ሰዎች የሚመራቸው ገንዘቡ ነው ወይስ ፍርሃትን አለማስተዋሉ? ገንዘብን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው አለማስተዋል /አለማወቅ/ ስለሆነም በዚህ ዐይነት ሂደት ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች ልጆቻቸውም ይሄንኑ ይከተላሉ፡፡ ጠዋት ከእንቅልፋቸው ይነሳሉ - ልብስ ይለብሳሉ! የተገኘውን በልቶ ወደ ሥራ መሮጥ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ የተለየ ሌላ አማራጭ መንገድ ይኖር ይሆን? ብለው እንኳ ራሳቸውን አይጠይቁም፡፡ ሀሳባቸውን እና ውጥናቸውን የሚመራው አዕምሮአቸው ሳይሆን ስሜታቸው ነው›› አለና ዝም ብሉ ቆየ፡፡

‹‹በስሜትና በአዕምሮ መመራት መካከል ልዩነት አለ?›› ማይክ ጠየቀ፡፡

‹‹ይህንን ብዙ ጊዜ እሰማዋለሁ፡፡ ስለሆነም ሥራ መቀየርን ወይም የደሞዝ ጭማሪ እንደሚያስፈልገቸው ሲናገሩ ይደመጣል፡፡ መገፋት የሰብኝም አሊያም ደግሞ ይህን ሥራ የምሰራው ደህንነቴ የተጠበቀ በመሆኑ ነው ይላሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነርሱ መናገር የነበረባቸው! ይህን ሥራ እየሰራሁ ያለሁት ለምንድነው? የሚለውን ነበር፡፡ እንዲህ ያለውን ሃሳብ መተግበር ሲጀምሩ ከውስጣቸው ስሜታዊነትን አውጥተው! በራሳቸው አቋም ወይም ማስተዋልን ይለማመዳሉ፡፡››

‹‹ሰዎች ከስሜት ርቀው በማስተዋል መናገርን ማወቅ ደግሞ በህይወት ውስጥ ዋናው ትምህርት ነው፡፡ በተለይ እኔው ራሴ በስሜት ውስጥ ሆኜ! አንድ ተግባር ስከውን እና በማስተዋል መፈፀሜን ስረዳ እጅግ ተልቅ ትምህርት ማግኘቴን አረጋግጣለሁ›› ብሎ በዝርዝር አስረዳን፡፡

ከተቀመጥንበት ቦታ ተነስተን ወደ ሥራ ቦታ መጓዝ ስንጀምር! ሀብታሙ አባቴ ‹‹ ሀብታሞች ‹ገንዘብን በማስራት› ሥራን ይሰራሉ እንጂ ሥራን የሚሰሩት ገንዘብን ብቻ ለማግኘት ብለው አይደለም›› አለ፡፡

በዚህ ሁኔታ እኔና ማይክ የነበረንን አመለካከት በመተው ወደ እርሱ ሀሳብ እንድንመጣ አደረገን። ችግሩ፣ ግን አሁንም ቢሆን የእኛ አካሄድ የሚያዋጣ መሆኑን አለመረዳታችን ነበር። ገንዘብን በማሰራት ሀብታም መሆን በሚያስችለው ዘዴ ውስጥ ህጋዊና ህገወጥ የሆኑ መንገዶች እንዳሉ መረዳትም እንደሚገባን ገለፀልን። በመንግስትና በባንኮች ብቻ ከገንዘብ ጋር ተያይዞ የሚሰሩ ሥራዎች እንዳሉና እነዚህ በሌሎች ወገኖች ቢተገበሩ ህገ ወጥ አካሄድ መሆናቸውን ከገለፀልን በኋላ፣ ይሁን እንጂ ሀብታም መሆን ለሚፈልግ ማንም ታታሪ ገንዘብን ሲያሰራ የሚችልበት በርካታ መንገድ መኖሩን ጠቆመን።

ገንዘብን በፍርሃትና በስግብግብነት መጠቀም በደመነፍስ እንደመመራት ማለት ሲሆን፣ ብዙ ሰዎች ገንዘብን የሚመለከቱት ከማስተዋል ጋር ዝምድና የሌለውና በቀቢፀ ተስፋም እንደመታመን አድርገው መኾኑን ከነገረን በኋላ፣ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ልጆች ልብ በሉ ድሃዎችና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ገንዘብ ብቻውን ለችግራቸው መፍትሄ እንደሆነ አድርገው ሲያስቡ፣ የሰሩበትን የቀጠራቸው ኩባንያና መንግስት እንደሚነጥቋቸው ማመን ይጀምራሉ።›› ሲል ገለፀልን።

ሀብታሙ አባቴ እንዲህ ብሎ ሲገልፅልን ሙሉ መልዕክቱን አልተረዳነውም፣ ነገር ግን እስካሁንም ድረስ በአዕምሮአችን ውስጥ ቀርቷል።

**ለሌሎች ያልታየውን፣ ለመመልከት መቻል**

ስራችንን ወደምንሰራበት መጋዘን ስንደርስ፣ ሀብታሙ አባቴ ወደ መኪናው ማምራት ጀመረ። ከዚያም ወዲያውኑ ፊቱን ወደእኛ በማዞር፣ ‹‹ልጆች ስራችሁን ቀጥሉ፣ ከፍያን መርሳት ስትጀምሩ የወደፊት ህይወታችሁ የተቃና እየሆነ መምጣት ይጀምራል። አዕምሯችሁን መጠቀም ስትጀምሩና ከፍያን ግምት ውስጥ ማስገባት ስታቆሙ እነ ከምከፍላችሁም በተሻለ መልኩ የተሻለ ሀብትን ማካበት ትችላላችሁ።

ሌሎች ያላዩትንም ማየትን ትለማመዳላችሁ፣ ህይወት ውስጥ ብዙ አማራጮች በቅርባችሁ እንዳሉ ስትረዱ የገንዘብን ብቸኛ መፍትሄነት ማየት ታቆማላችሁ። በእጋጣሚ አንድ አማራጭን ስታገኙ ለህይወታችሁ መቀጠል መንስኤ እንደሆነ ማሰብ ትጀምራላችሁ። በዚያን ጊዜ ደግሞ ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችን አላያችኋለሁ። ያን በምታደርጉ ጊዜ እንዱን ወጥመድ መስበር ትጀመራላችሁ።





እኔና ማይክ በመጋዘኑ ውስጥ ያስቀመጥናቸውን የራሳችንን ዕቃዎች በመያዝ ወ/ሮ ማርቲንን ተሰናብተን ወጣን። ከዚያ ቅድም ወነበርንበት ፓርክ ተመልሰን ሄድን። እዚያም ትንሽ እረፍ ብለን በአንዳንድ ጉዳዮች ዙሪያ ለበርካታ ሰዓታት ስንነጋገርና በጥልቀት ስናስብበት ዋልን።

በቀጣዩ ሳምንት በትምህርት ቤት ቆይታችን በጉዳዩ ላይ አተኩረን ማሰቡን ቀጠልንበት። በዚያው አላቆምንም - ለቀጣይ ሁለት ሳምንታት በትኩረት እየተነጋገርንበት አሰብንበት።

በሁለተኛው ሳምንት ቅዳሜ ወ/ሮ ማርቲንን ስሰናበታት የመፅሃፍ ግዢ ልማዱ በሃሳቤ መጣ። ከዚያም መፅሐፍት መደርደሪያው ላይ ዐይኔን ተከልኩኝ። ይሁን እንጂ በዚህም ሳምንት የ30 ሳንቲም ከፍያዬን ስላላገኘሁ የቀልድ መፅሃፍትን ለመግዛት አልቻልኩም። ወዲያውኑ ወ/ሮ ማርቲን እኔና ማይክን ‹ሰላም ሁኑ› ብላ ተሰናበተችን። በወቅቱ ወደ ወ/ሮ ማርቲን ስመለከት ከዚህ በፊት ስትሰራው ያላስተዋልኩትን የሥራ ዐይነት ስትሰራ ተመለከትኩ።

በውስጤም እንዲህ ብዬ አሰብኩኝ። እዎ በፊትም ይህንን ተግባርዋን እየተወጣች ያየኋት ቢሆንም ጉዳዩ ብዙ አላስተዋልኳትም።

ወ/ሮ ማርቲን በዕለቱ የቀልድ መፅሃፉን ሽፋን ሁለት ቦታ በመቁረጥ፣ የቁራጩን የላይኛውን ክፍል ራስዋ ጋ በማስቀረት፣ የተቀረውን ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃ ውስጥ ትጥለዋለች። ከዚያም እነዚህን የቀልድ መፅሃፍት ምን እያደረግሻቸው ነው ብዬ ጠየቅኋት። ገሚሶቹን ቁራጮች ጥያቸዋለሁ፣ የሽፋኑን የላይኛውን ቁራጭ ግን የቀልድ መፅፍ አከፋፋዩ አዳዲስ መፅሃፍትን ሲያመጣ እመልስለታለሁ - መፅሃፍቶቹም በሰዓታት ውስጥ እዚህ ይደርሳሉ።››አለችኝ።

እኔና ማይክ ለአንድ ሰዓት ያህል የመፅሃፍ አከፋፋዩን ስንጠብቀው ቆየን። ከዚያም አከፋፋዩ ሲመጣ፣ ወደርሱ ጠጋ በዬ፣ ‹‹የቀልድ መፅሃፍ መውሰድ እንችላለን? በማለት ጠየቅኩት።

እርሱም፣ ‹‹እዚህ የምትሰሩ ከሆናችሁ መውሰድ ትችላላችሁ፣ ግን ለሌላ አሳልፋችሁ መሸጥ አይቻልም›› አለን።

አሁን የማይክና የእኔ ጉድኝት እንደገና ነፍስ ዘርቶአል። የማይክ እናት፣ ምድር ቤት ውስጥ አገልግሎት የማይሰጥ አንድ ክፍል እንድንጠቀምበት ፈቅዳለች። ክፍሉን በደንብ ካፀዳነው በኋላ በመቶዎች የሚቆጠሩ የቀልድ መፅሃፍትን ማከማቻ አደረግነው።

የቀልድ መፅሀፍቶቻችን እየበዙ ከመምጣታቸው የተነሳ፣ የቤተ መፅሐፍት ደረጃን በመያዙ፣ ሌሎች ሰዎች መጥተው እንዲገለገሉበት ክፍት አደረግነው። ከዚያም የማይክ ታላቅ እህትን በቤትመፅሃፍት ውስጥ እንትሰራ ቀጠርናት። የማይክ እህት በጣም ጥናት የምታበዛና የቤተ መፅሃፍ ዋና ኃላፊ ሆና መስራት የምትፈልግ ነበረች። እሷም በቤተ መፅሃፍቱ መገልገል የሚፈልጉ ልጆች ሲመጡ የ10 ሳንቲም ክፍያ በማስከፈል አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ጀመረች። ሁሌም ከትምህርት ሰዓት ውጪ ከቀኑ 8:30 እስከ 10:30 ድረስ ክፍት ሆና ስራ መስራት ጀመረ።

በተለይ የሱፐር ማርኬት ደንበኞቻችን፣ በአካባቢው ያሉ ልጆች በየቀኑ ያላቸውን ሁለት ሰዐት ተጠቅመው በርካታ የቀልድ መፅሀፍት ሊያነቡ ቻሉ።

ወደ ቤተ መፅሃፍታችን የሚመጡ እንግዶች በየቀኑ ለሁለት ሰዓት ያህል ክፍት ሆና ወደምትቆየው መፅሃፍት ቤት በመምጣት ከአምስት እስከ ስድስት የቀልድ መፅሀፍትን ያነባሉ። ለእያንዳንዱ መፅሀፍም የ10 ሳንቲም ክፍያ መፈፀም ግድ ይል ነበር።

የማይክ እህትም ከመፅሃፍት ቤቱ የሚወጡ ልጆችን መፅሃፍ ይዘው እንዳይሄዱ በደንብ ትቆጣጠራለች። ምን ያህል መፅሃፍት እንደተነበቡና የሚያሳውቅ መረጃና ደንበኞች የሚሰጡትን ሃሳብ የመሰብሰብ ሥራም ትሰራለች።

የቤተ መፅሃፍቷ ገቢ እያደገ በመምጣቱ እኔና ማይክ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ በየሳምንቱ በአማካይ ዘጠኝ ዶላር ከ50 ሳንቲም እናገኝ ነበር። ለማይክ እህት በየሳምንቱ አንድ ዶላር የምንሰጣት ሲሆን፣ የቀልድ መፅሃፍትን ብዙም የማታነብ ቢሆንም፣ ያለ ክፍያ ማንበብ እንድትችል ፈቅደንላታል። እሷ ግን ብዙውን ጊዜ በራስዋ ጥናት ላይ ነው የምታተኩረው።

ሁኔታዎች በእንደዚህ ሁኔታ እየሄዱ ቢሆንም፣ እኔና ማይክም ዘወትር ቅዳሜ በሱፐር ማርኬት ውስጥ ለመስራት የገባነውን ስምምነት ጠብቀን እየሰራን እንገኛለን። የተለያዩ የቀልድ መፅሃፍትን ከሌሎች መደብሮች ሳይቀር መሰብሰቡን ተያይዘነዋል።





ለአከፋፋዮች እነዚህን የቀልድ መፅሃፎች በድጋሚ እንደማንሸጥ በሚገባ አስመስከረናል። ሌላው ቢቀር መፅሃፎቹ እያረጁ ሲመጡ፣ ሰብስበን እናቃጥላቸዋለን እንጂ ሌላ አማራጭ እንፈልግላቸውም። ቀስ እያልን ተጨማሪ ቅርንጫፍ ለመክፈት ብንሞክርም የማይክን እህት ያህል የሚታመን ጠንካራ ሰራተኛ ለማግኘት አልቻልንም።

ገና በለጋ ዕድሜያችንም ጥሩ ሰራተኛ ማግኘት ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ተረዳን።

ቤተመጻሕፍቱ ከተከፈተ ከሶስት ወራት በኋላ በአንደኛው ቀን ክፍሉ ውስጥ ጥል ተነሳ።ከሌላ ሰፈር የመጡ ልጆች ናቸው ሰብረው ገብተው ጥሉን ያሥነሱት። ከክስተቱ በኋላ የማይክ አባት ቢዝነሱን ብናቆመው እንደሚሻል ስለመከረን ቤተ መጻሕፍታችንን ዘጋነው። ቅዳሜ ቅዳሜ መስራታችንንም አቆምን።ሀብታሙ አባታችን በኹነው ሁሉ ተደስቶ ነበር። የመጀመሪያውን ትምህርት በጥሩ ሁኔታ በማጠናቀቃችን ተደስቷል። አሁን ገንዘብ ለእኛ እንዲሰራ የማድረግን ጥበብ ቀስመናል።

ሀብታሙ አባታችን ገንዘብ በመክፈል ፋንታ ከዚያ በእጅጉ የሚልቅ ጥበብን ሰጠን።

## ትምህርት ሁለት

### ገንዘብ ነክ ዕውቀት ለምን ያስፈልጋል?





## ምዕራፍ ሶስት

## ሁለተኛው ትምህርት

# ገንዘብ ነክ ዕውቀት ለምን ያስፈልጋል?

በ1990 ጓደኛዬ ማይክ የአባቱን ንግድ ወርሶ ከአባቱም በተሻለ መልኩ ንግዱን እያካሄደ ነበር። እሱና ባለቤቱ ልትገምቱት ከምትችሉት በላይ እጅግ ሀብታም ሆነዋል። አሁን ሀብታሙ አባታችን እኛን ይኮተኩተን እንደነበረው እሱም ልጁን በእውቀት እየኮተኮተ ነው።

በ1994 በ47 ዓመቴ ጡረታ ወጣሁ። ጡረታ መውጣት ማለት ስራ ማቆም አይደለም። ስንፈልግ እንሰራለን ሳንፈልግ አንሰራም። ገንዘቡ ብቻውን ራሱን ችሉ መስራት ይችላል። ልክ ዛፍ እንደመትከል ነው። ለዓመታት ውሃ ስታጠጣው ትቆይና አንድ ቀን ያላንተ እርዳታ ዕደገቱን ይቀጥላል። ከዚያም ዛፉ የምትዝናናበት ጥላ ይሆንሀል።

*የናጠጡት ነጋዴዎች*

በ1932 የአገሪቱ ሀብታሞችና መሪዎች በኢጆዋተር የባህር ዳርቻ ሆቴል ስብሰባ ላይ ተቀምጠው ነበር።ከነሱ መካከል የትልቁ የብረት ፋብሪካ ባለቤት ቻርለስ ሽዋብ፣ የዓለማችን ታላቁ የመጠጋገኛ ዕቃዎች አምራች ድርጅት ፕሬዚዳንት ሳሙኤል ኢንሱል፣ የታላቁ ጋዝ አምራች ኩባንያ ኃላፊ ሀዋርድ ሆፐሰን፣የባንኮች ጉዳይ ኃላፊ ሊዮን ፍራዚየር፣ የኒውዮርክ ስቶክ ኤክስቸንጅ ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ዊትኒይ እንዲሁም አርተን ኮተንና ጄሲ ሊቨርሞር ብሎም የፕሬዚዳንቱ ካቢኔ አባል አልበርት ፎል ተጠቃሽ ናቸው። ከአምስት ዓመታት በኋላ ከላይ የተጠቀሱት ሰዎች መጨረሻ እንደሚከተለው ነበር።ሽዋብ ዓምስት ዓመታትን በብድር ገንዘብ ከኖረ በኋላ ባዶ ኪሱን ሞተ።ኢንሱል በስደት አገር ያለባላቤስቲን ሞተ።ክሮገርና ኮተንም ደህይተው አለፉ።ሆፐሰን ሲያብድ ዊትኒና አልበርት ፎል ደግሞ ከእስር ቤት መውጣታቸው ነበር። ፍራሲየርና ሊቨርሞር ራሳቸውን አጠፉ።

ማንም በእርግጠኝነት ሰዎቹ ላይ የደረሰውን ነገር መናገር የሚችል ያለ አይመስለኝም።ጊዜውን ስናጤነው ግን 1923 ከታላቁ የኢኮኖሚ ድቀት(1929) አምስት ዓመታት በፊት በመሆኑ ምናልባትም የኢኮኖሚ ድቀቱ ሰለባ ሳይሆኑ እንዳልቀሩ እገምታለሁ። ነጥቡ ይኸውላችሁ፦ ዛሬ የምንገኝበት ዓለም እነዚያ ሰዎች ከነበሩበት ጊዜ በበለጠ ተለዋዋጭ ነው። በቀጣዮቹ 25 ዓመታት ከላይ የጠቀስነውን ዓይነት ውድቀቶችና መነሳቶች እንደሚኖሩ እገምታለሁ።

በ1997 በድንገት ሚሊየነር ለመሆን የበቁ በርካታ ሰዎች አውቃለሁ። ጥያቄው የሚመስለኝ ግን እንዴት ሀብታም ትሆናለህ ብቻ ሳይሆን ያለህን ሀብት ለምን ያህል ጊዜ ማስቀጠል ትችላለህ የሚለው ነው።

ለዚህም ነው ሰዎች ‹‹ሀብታም የምሆነው እንዴት ነው?›› ወይም ‹‹በእቋራጭ ለመክበር ከምን መጀመር አለብኝ?›› የሚል ጥያቄ ሲያቀርቡልኝ የምሰጣቸው መልስ ተስፋ አስቆራጭ የሚሆንባቸው። የእኔ ምላሽ ‹‹ሀብታም መሆን የምትፈልጉ ከሆነ ገንዘብ ነክ ትምህርት ያስፈልጋችኋል›› ነውና።

እኔና ማይክ ትልልቅ ሰዎች በሆንን ጊዜ ምርጫዎቻችን የተሳኩልን ገንዘብ ነክ ትምህርትን በታዳጊነታችን የጠማርናቸው በመሆኑ ነበር።

ንብረት ገንዘብ ወደኪስ የሚያስገባ ነገር ነው።

ዕዳ ደግሞ ገንዘብ ከኪስ የሚያስወጣ ነገር ነው።

ማወቅ የሚገባህ ይህንን ነው። ሀብታም መሆን የምትፈልግ ከሆነ በሕይወትህ ሙሉ ንብረት ግዛ። ደሃ ወይም መካከለኛ ገቢ ያለው ሰው መሆን የምትፈልግ ከኾነ ደግሞ ዕዳና አከሳሪ ነገሮችን ስትገዛ ኑር። በእውነተኛው ዓለም የገንዘብ እጥረተ የሚፈጥረው ልዩነቱን ማወቅ አይደለም።

የፋይናንስ እጥረት መሰረቱ ለቃላትም ለቁጥሮችም መሃይም ሆኖም ገኘት ነው። ሰዎች የገንዘብ ችግር ውስጥ ተዘፍቀው ከተገኙ ማንበብ የማይችሏቸው ቃላት ወይም ቁጥሮች አሉ ማለት ነው። አንዳች የተምታታ ነገር አለ። ሃብታሞቹ ሀብታም የሆኑት በተለያዩ ዘርፎች ከገንዘብ እጥረት ከሚሰቃዩት በተሻለ የሚያውቁት ነገር ስላለ ነው። ስለዚህ ሀብታም መሆንና ሀብትንም ቀጣይነት ያለው ለማድረግ የምትሻ ከሆነ ስለገንዘብ ያለህ ዕውቀት በቃላትም በቁጥሮችም ከፍ ያለ መሆን አለበት።





ምስሉ ላይ የሚታየው ቀስት የጥሬ ገንዘብን ፍሰት የሚያመለክት ነው። ቁጥሮች ብቻቸውን ትርጉማቸው እምብዛም ነው። ቃላት ብቻቸውንም እንደዚያው። ወሳኙ ነገር አጠቃላይ ታሪኩ ነው። በፋይናንሽያል ሪፖርቶች ቁጥሮችን ማንበብ አፅመ ታሪክን እንደመፈለግ ነው። ጥሬ ገንዘብ ከየት ወዴት እንደሚፈስ የሚያሳውን ታሪክ። ከአብዛኞቹ ቤተሰቦች የ80 ከመቶ ያህሉ የገንዘብ ታሪክ ለመሻሻል በርትቶ የመሥራት ታሪክ ነው። ደሃ የኾኑት ገንዘብ ስለማያገኙ ሳይሆን በሚያገኙት ገንዘብ ንብረት በመግዛት ፋንታ ዕዳና ኪሳራ በመግዛት ሕይወታቸውን ስለሚገፉት ነው።

ለምሳሌ የሚከተለው የደሃ ሰውን የገንዘብ ፍሰትን የሚያመለክት ሰንጠረዥ ነው።




የሚከተለው ደግሞ መካከለኛ ገቢ ያለው ሰው የገንዘብ ፍሰት ነው።



ሥራ




የሚከተለው ደግሞ የሀብታም ሰው የገንዘብ ፍሰትን ያመለክታል






ከላይ የተቀመጡት ሰንጠረዦች በጣም ቀለው የተቀመጡ መሆናቸው ግልፅ ነው:: ሁሉም ሰው የመኖሪያ ወጪዎች፣ የምግብ፣ መጠለያና ልብስ ግዴታዎች አሉበት::

ሰንጠረዦቹ የሚያሳዩት በደሃ፣ መካከለኛ ገቢ ባለውና በሃብታም ሰው ሕይወት ውስጥ ያለው የገንዘብ ፍሰት ምን እንደሚመስል ነው:: ታሪኩን የሚናገረው የገንዘብ ፍሰቱ ነው:: ሰዎች ያገኙትን ገንዘብ እንዴት እንደሚጠቀሙበት፣ እጃቸው ላይ ሲገባ ምን እንደሚያደርጉበት የሚያሳይ ነው::

በአሜሪካ ቱጃሮች ታሪክ የጀመርኩበት ምክንያት በበርካቶች ዘንድ ያለውን የአመለካከት ግድፈት ለማሳየት ነው:: ግድፈቱ ገንዘብ ሁሉንም ችግሮች ይፈታል ብሎ ማሰብ ነው:: ለዚህ ነው ሰዎች በአቋራጭ ሀብታም የሚሆኑበትን መንገድ ሲጠይቁኝ የምሸማቀቀው:: ብዙ ጊዜ የምሰማው «ዕዳ ውስጥ ነኝ:: ስለዚህ ተጨማሪ ገንዘብ ማግኘት አለብኝ» የሚለውን ነው::

እንደ እውነቱ ከሆነ ተጨማሪ ገንዘብ ችግሮችን አይፈታም:: እንዲያውም ብዙ ጊዜ ያባብሳቸዋል::

ገንዘብ ብዙ ጊዜ ሰውኛ ግድፈቶቻችን ያጋልጣል:: ገንዘብ የማናውቀውን ነገር እንድንመለከተው ያደርጋል:: ለዚህም ነው ብዙ ጊዜ በድንገት ገንዘብ ያገኙ ሰዎች (በውርስ፣ በደመወዝ እድገት ወይ በሎተሪ) ተመልሰው ወደነበሩበት የገንዘብ ችግር ውስጥ የሚገቡት:: እንዳንዱ እንዲያውም ገንዘቡን ከማግኘታቸው በፊት ከነበሩበትም ደረጃ ዝቅ ይላሉ:: ገንዘብ የሚከተለው ጭንቅላትህ ውስጥ ያለውን የገንዘብ ፍሰት ሂደት ነው:: ልማድህ ያገኘኸውን ነገር ሁሉ ማጥፋት ከሆነ ተጨማሪ ገንዘብ ማግኘትህ የማጥፋት ልማድህን ነው የሚያሳድገው:: በተረቱም የሚባለው «ሞኝና ገንዘብ ተያይዘው ይጠፋሉ» ነው::

ደጋግሜ እንደተናገርኩት ወደ ት/ቤት የምናመራው ሙያዊ ዕውቀትን ለመቅሰም ነው:: በሙያዊ ችሎታችን ገንዘብ መሥራት እንዴት እንደሚቻል እንማራለን:: እኔ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በምማርበት የ1960ዎቹ ወቅት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገ ተማሪ ካለ ያልጥርጥር ሀኪም እንደሚሆን ነበረ የሚታሰበው:: ያን ተማሪ ምን መሆን

እንደሚፈልግ የሚጠይቀው ግን የለም:: እንዲሁ ነው የሚገመተው:: ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስገኘው የሙያ ዘርፍ እርሱ ነበርና::

ዛሬ ግን ሀኪሞች ለጠላቴ እንኳን በማልመኘው ዓይነት የገንዘብ ችግር ውስጥ ናቸው:: ዛሬ ህፃናት መሆን የሚፈልጉት የቅርጫት ኳስ ኮከብ፣ እንደታይገር ውድስ የተሳካላቸው የጎልፍ ተጫዋች፣ የኮምፒውተር ልሂቃች፣ የፊልም ተዋናይ፣ ዘፋኝ፣ ሞዴል ወይም ነጋዴ ነው:: ምክንያቱም ገንዘቡ፣ ዝናና ክብሩ ያሉት እነዚህ ሥራዎች ዘንድ ነው:: ለዚህም ነው ዘንድሮ ተማሪዎችን በቀላሉ በትምርታቸው ማበረታታት የሚከብደው:: በአንድ ወቅት እንደነበረው ሙያዊ ስኬት በት/ቤት ስኬት ጋር ብቻ የተያያዘ እንዳልሆነ ያውቃሉ::

ተማሪዎች ያለፋይናንስ ዕውቀት ከትምህርት ቤት ስለሚወጡ ሚሊዮኖች ለሙያቸው ውጤታማ ይሆኑና በገንዘብ ግን ሲቸገሩ ይታያሉ:: ጠንክረው ይሰራሉ ግን አያሻሉም:: ትምህርታቸው የጎደለው ገንዘብ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ሳይሆን ካገኘሽው በኋላ እንዴት እንደምታጠፋው ነው:: ባገኘው ገንዘብ ምን እንደምትሰራበት፣ ሰዎች ገንዘብህን እንዳይወስዱብህ ስለመጠበቅ፣ ለምን ያህል ጊዜ እንደምትጠብቀው እንዲሁም ገንዘብ ምን ያህል ለአንተ በርትቶ እንደሚሰራ የማወቅ ችሎታ ነው:: በርካቶች የገንብን ፍሰት ሂደት ስለማይረዱት የገንዘብ ችግር ለምን እንደገጠማቸው ማብራራት አይችሉም:: አንድ ሰው በጣም የተማረና በሙያው የተሳካለት ግን ደግሞ ምንም ዓይነት የገንዘብ ዕውቀት የሌለው ሊሆን ይችላል፡ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ከሚጠበቅባቸው በላይ ሊሰሩ ይኖራሉ:: ምክንያቱም የተማሩት ጠንክሮ መስራት እንዴት እንደሚቻል እንጂ ገንዘብ ለእነሱ እንዲሰራ ስለማድረግ አይደለም::

### የገንዘብ ስኬታማነት ሕልም ወደ ቅዠት የሚቀየርበት ታሪክ

ሁለቱም በከፍተኛ ደረጃ የተማሩ ደስተኛ ጥንዶች እንደተጋቡ በኪራይ ቤት መኖር ይጀምራሉ:: ወዲያውም ገንዘባቸውን በመቆጠብ በተቻላቸው መጠን በዝቅተኛ ገንዘብ ለመኖር ይሞክራሉ::

ችግሩ የሚኖሩበት ቤት ይጠባቸዋል:: እናም ልጆች ሊወልዱ ሰፋ ያለ ቤት ስለሚያስፈልጋቸው የራሳቸውን ቤት ለመግዛት ገንዘብ መቆጠብ እንዳለባቸው ይወስናሉ:: አሁን ሁለት ገቢ ስላላቸው በሥራቸው ላይ ልዩ ትኩረት ማሳየት ይጀምራሉ::



ገቢያቸው ማደግ ይጀምራል::

ገቢያቸው ማደግ ሲጀምር ... ወጪያቸውም አብሮ ያድጋል







የበርካታ ሰዎች ቁጥር አንድ ወጪ ታክስ ነው:: ብዙ ሰዎች የሚመስላቸው የገቢ ግብር ነው:: ነገር ግን የበርካታ አሜሪካውያን ትልቁ ወጪ የጡረታ ክፍያ ነው:: ለተቀጣሪ የጡረታ ክፍያ ከጤና ኢንሹራንስ ጋር ተዳምሮ የገቢን 7.5 ከመቶ ይሸፍናል:: ቀሪውን 7.5 ከመቶ ቀጣሪው መክፈል ስላለበት አጠቃላዩ 15 በመቶ ነው:: ይህ ገንዘብ ቀጣሪው ለተቀጣሪው ሊከፍለው የማይችለው ነው:: ከዚያም በላይ ለጡረታ ከደመወዝህ ላይ ለተቀነሰው ገንዘብ የገቢ ግብር ትከፍላለህ::




ይህን ይበልጥ ለመረዳት ወደ ወጣቶቹ ጥንዶች መመለስ ያስፈልጋል:: ቤታቸው ገቢያቸው ማደጉን ተከትሉ የሚያልሙትን አይነት ቤት ለመግዛት ይወስናሉ:: ከዚያም አዲሱን ውስጥ ከገቡ በኋላ የንብረት ግብር የሚባል አዲስ ግብር ይጠብቃቸዋል:: ድንገት ሳያስቡት ቤታቸውን ለማሳመር አዲስ መኪና አዳዲስ የቤት ዕቃዎች ይገዛሉ:: ራሳቸውን በባንክና በክሬዲት ካርድ ብድር ተዘፍቀው ያገኙታል::

አሁን አዙሪቱ ውስጥ ገብተዋል፡፡ ልጅ ይመጣል፡፡ በርትተው ይሰራሉ፡፡ ሂደቱ ራሱን ይደጋግማል፡፡ ገቢያቸው ሲያድግ ደግሞ ታክሱም አብሮ ከፍ ይላል፡፡ አበዳሪ ድርጅት ደውሎ የቤታቸው ዋጋ ከፍ ማለቱን ይነግራቸዋል፡፡ ገንዘብ እንደሚያበድራቸውና በብድሩም ከፍተኛ ወለድ የሚያወጡባቸው ያልከፈሉትን ክሮዲት ካርዶች ቀድመው እንዲከፍሉ ያግባቧቸዋል፡፡ የክሮዲት ካርድ በድሮቻቸውን ይከፍሉና እፎይ ይላሉ፡፡ አሁን ብድሮቻቸውን በሙሉ በቤታቸው ላይ ጠቅልለውታል፡፡ በየወሩ መክፈል ያለባቸው ገንዘብ ዝቅ ይላል፡፡ ምክንያቱም ጊዜውን ወደ 30 ዓመት አራዝመውታል፡፡

ጎረቤቶቻቸው ይደውሉና ሽመታ እንዲሄዱ ይጋብዟቸዋል፡፡ ለራሳቸው ‹‹ምንም ነገር አልገዛም፡፡ ተመልክቼ ብቻ እመለሳለሁ›› ብለው ይነግሩትና ይሄዳሉ፡፡ ከሄዱ በኋላ ግን የሚያስፈልጋቸው የሚመስላቸውን ነገር ሲያገኙ ያንን ንፁህ ክሬዲት ካርድ መልሰው ይከቱታል፡፡

እንደዚህ ዓይነቶቹን ወጣት ጥንዶች ብዙ ጊዜ ነው የማገኛቸው፡፡ ስማቸው ይለዋወጣል! የገንዘብ ችግራቸው ግን ተመሳሳይ ነው፡፡ ከንግግሮቼ አንዳኛውን ለመከታተል ይመጡና ‹‹ገቢያችንን እንዴት መጨመር እንደምንችል ትነግረናለህ?› ብለው ይጠይቁኛል፡፡

የችግራቸው ምንጭ ያላቸውን ገንዘብ እንዴት እንደሚያጠፉት የሚያደርጉት ውሳኔ መሆኑን እንኳን አይገነዘቡም፡፡ ዋናው የገንዘብ ችግራቸው መንስዔም ይኸው ነው፡፡ የሚከሰተውም ከገንዘብ ነክ ዕውቀት ማነስና በንብረትና በዕዳ መካከል ያለውን ልዩነት ካለመገንዘብ ነው፡፡

ተጨማሪ ገንዘብ የየትኛውንም ሰው የገንዘብ ችግር ቀርፎ አያውቅም፡፡ ችግሮችን የሚፈታው ብልሃት ነው፡፡ በብድር ለተዘፈቁ ሰዎች አንድ ጓደኛዬ አባባል አለው፡፡

***መቀበሪያህን እየቆፈርክ መሆንህን ስትገነዘብ መቆፈርህን አቁም፡፡***

ልጅ እያለን አባቴ ስለጃፓኖች ሶስት መሰረታዊ ኃይሎች ይነግረን ነበር፡፡ የጎራዴ፣ የጌጥና የመስታወትን ኃይል፡፡

ጎራዴው የመሳሪያዎች ኃይል ተምሳሌት ነው፡፡ አሜሪካ ለጦር መሳሪያ በርካታ ትሪሊየን ዶላሮችን ታፈሳለች፡፡ ስለዚህም የዓለማችን ቁንጮ የመከላከያ ኃይል ባለቤት ነች፡፡





ጌጡ የገንዘብ ኃይል መገለጫ ነው፡፡ ‹‹ሕጉን የሚያወጣው ወርቁን የያዘው ነው›› የሚለው አባባል በተወሰነ ደረጃ እውነትነት አለው፡፡

መስተዋቱ የራስ ዕውቀት ነፀብራቅ ነው፡፡ እንደ ጃፓኖቹ አገላለፅ ከሶስቱም የሚልቀው ዕውቀት ነው፡፡

ድሆችና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ የገንዘብ ኃይል እንዲቆጣጠራቸው ይፈቅዱለታል፡፡ በየጠዋቱ እየተነሱ በርትተው በመሥራት የሚሰሩት ነገር ለውጥ ማምጣት አለማምጣቱን ሳይጠይቁ ይቀጥላሉ፡፡ በርካቶች የገንዘብን አሰራር ሳይገነዘቡ የገንዘብ ኃይል እንዲቆጣጠራቸው ያደርጋሉ፡፡ የገንዘብ ኃይል እነርሱን ለማጥቃት ይውላል፡፡

የመስተዋቱን ኃይል ቢጠቀሙ ኖሮ እራሳቸውን ‹‹የማደርገው ነገር ትርጉም አለው?›› ብለው ይጠይቁ ነበር፡፡ ብዙውን ጊዜ ውስጣቸውን በማዳመጥ ፋንታ በርካቶች ብዙሃኑን ተከትለው ይነጉዳሉ፡፡ ነገሮችን የሚያደርጉት ሌሎች ሰዎች ስለሚያደርጓቸው ነው፡፡ በመጠየቅ ፋንታ ይስማማሉ፡፡ ብዙ ጊዜም የተነገራቸውን በዘፈቀደ ይደግማሉ፡፡ የሚደጋግሟቸው ሀሳቦችም "ቤትህ ንብረት ነው"! "ቤትህ ታላቅ ኢንቨስትመንት ነው"! "አስተማማኝ ሥራ አግኝ"! "ስህተቶችን አትስራ"! "100% እርግጠኛ ያልኾንክበትን ነገር አትጀምር" የመሳሰሉትን ነው፡፡

ለበርካቶች በተሰበሰበ ሕዝብ ፊት ማውራት ከሞት የበለጠ የሚያስፈራቸው ነገር ነው፡፡ ሳይኪያትሪስቶች እንደሚሉት በተሰባበሩ ሰዎች ፊት የመናገር ፍርሃት ትችትን፣ መገለልን፣ ሰድብን ከመፍራት የሚመነጭ ነው፡፡ አብዛኞቹ የተለዩ ናቸው እንዳይባሉ በመፍራት ለችግሮቻቸው አዳዲስ መፍትሔ ከመሞከር ይቆጠባሉ፡፡

ምሁሩ አባቴ እንደሚለው ጃፓኖች የመስተዋትን ኃይል ከሁሉም አብልጠው የሚያስቀምጡበት ምክንያት እንደ ሰው ልጅነታችን እውነቱን ልናውቅ የምንችለው ወደመስተዋቱ ውስጥ ስንመለከት ብቻ ስለኾነ ነው፡፡ ብዙ ሰዎች "ጠንቀቅ በል" የሚሉት ከፍርሃት የተነሳ ነው፡፡ ለስፖርት፣ ግንኙነቶች፣ ሥራ፣ ገንዘብ ለሁሉም እንደዚያው ነው፡፡

ያው ተመሳሳይ የመተቸትና የመገለል ፍርሃት ነው ሰዎችን ከመጠየቅ ይልቅ የተለመዱ አካሄዶችን በፀጋ እዲቀበሉ የሚያደርጋቸው፡፡ "ቤትህ ንብረት ነው"! ‹‹ቤትህን

"ጠንክረህ ሥራ"፣ አስይዘህ ከባንክ የረዥም ጊዜ ብድር ወስደህ ሌሎችን ዕዳዎች ክፈል"፣ "ጠንክረህ ሥራ"፣ "የሥራ ዕድገት አገኛለሁ"፣ "አንድ ቀን ምክትል ፕሬዝዳንት እሆናለሁ"፣ "ገንዘብ ቆጥብ"፣ "ደመወዝ ሲጨመርልኝ የተሻለ ቤት እገዛለሁ"፣ "የጋራ ቁጠባዎች አስተማማኝ ናቸው" ወዘተ. .

አብዛኞቹ የገንዘብ ችግሮች የሚከሰቱት ከብዙሃኑ ጋር ለመጓዝ ከመሞከር ነው። አንዳንዴ ሁላችንም በመስተዋቱ ወደ ውስጣችን ተመልክተን ከፍርሃታችን ይልቅ ውስጣዊ ጥበባችንን ማዳመጥ አለብን።

በ16 ዓመታችን ማይክና እኔ ትምህርት ቤት ውስጥ ችግሮች ያጋጥሙን ጀመር። መጥፎ ልጆች ስለኾንን ግን አልነበረም። ከብዙሃኑ መነጠል ጀምረን ነው። ከትምህርት መልስና ሰንበትን ለማይክ አባት እንሰራለን። ከሥራ በኋላ ደግሞ ለሰዓታት የማይክ አባት የሂሣብ ባለሙያዎችን፣ የባንክ ሰዎችን፣ ጠበቆችን፣ ደላሎችን፣ ባለሃብቶችን፣ ሥራ አስኪያጆችንና ሠራተኞችን ሲያናግር ቢሮው ውስጥ ቁጭ ብለን እናዳምጣለን። ይህ ሰው ትምህርቱን ያቋረጠው በ13 ዓመቱ ሆኖ ሳለ የተማሩ ሰዎችን ሰብስቦ እየጠየቀ፣ መመሪያ እየሰጠና እያዘዘ ነው። ቀጠሮ አስይዘው መጥተው ሀሳባቸውን ሳይቀበለው ሲቀር ይሸማቀቃሉ።

ይህ ሰው ከብዙሃኑ ጋር ያልተመመ ነው። የራሱን መንገድ የመረጠና "ሁሉም ሰው ይህንን ስለሚያደርግ እኛም እንደዚያ ማድረግ አለብን" የሚለውን አባባል የተፃረነ "አይቻልም" የሚለውን ቃል የጠላ ነው። እንዲሰራላችሁ የምትፈልጉት ነገር ካለ "የምትችለው አይመስለኝም" በሉት።

ማይክና እኔ ስብሰባዎቹን በማዳመጥ ከት/ቤት ካገኘነው በእጅጉ የላቀ ዕውቀት አግኝተናል። የማይክ አባት የት/ቤት ምሁር አልነበረም፤ ነገር ግን የገንዘብ ምሁርና የተሳካለት ሰው ነበር። ሁሌም ደጋግሞ የሚነግረን "ጎበዝ ሰው ከእርሱ የበለጠ ጎበዞችን መቅጠር የሚችል ነው" እያለ ነበር። እናም ማይክና እኔ ለሰዓታት ጎበዝ ሰዎች ሲወያዩ የማዳመጥና የመማር ዕድል አገኘን።

ይሁንና በዚሁ ትምህርታችን የተነሳ አስተማሪዎቻችን ከሚያነበንቡት የተለመደ መንገድ ጋር መጣጣም አልቻልንም። ያም ችግር ፈጠረ። አስተማሪው "ጥሩ ውጤት ካላመጣችሁ በሥራ ዓለም ውጤታማ አትኾኑም" በሚል ጊዜ ሁሉ ማይክና እኔ





ቅንድባችንን እንሰቅላለን። የወጡ ደንብና መመሪያዎችን እንድናከብርና እንድንከተል ሲነገረን ይህ ዓይነቱ የማስተማር ሂደት ፈጠራን እንደሚያዳትት ተገንዘብን። ሀብታሙ አባታችን ት/ቤቶች የሚያስተምሩት ጥሩ ቀጣሪዎችን ሳይኾን ጥሩ ተቀጣሪዎችን ለማፍራት ነው ይለን የነበረውን መረዳት ጀመርን።

አልፎ አልፎ ማይክና እኔ የምንማረውን ነገር በሥራ ላይ እንዴት እንደምናውለው ብሎም ስለገንዘብ ለምን እንደማንማር አስተማሪዎቻችን እንጠይቃቸው ነበር። ስለገንዘብ ለምናነሳው ጥያቄ ብዙ ጊዜ የሚሰጠን ምላሽ ገንዘብ ጠቃሚ እንዳልኾነና በትምህርታችን ከጎበዝን ገንዘቡ ተከትሎ እንደሚመጣ ነው።

ስለገንዘብ ኃይል ይበልጥ እየገባን ሲመጣ ከአስተማሪዎቻችንና ከክፍል ጓደኞቻችን እየራቅን ሄድን።

ምሁሩ አባቴ ስለውጤቴ እምብዛም አስጨንቆኝ አያውቅም። ለምን እንደኾነ ይገርመኛል። ነገር ግን በገንዘብ ዙሪያ መከራከር ጀምረናል። እድሜዬ 16 ሲደርስ ምናልባትም ከአባቴና ከእናቴ የተሻለ የገንዘብ መሰረት ነበረኝ። መጽሀፎች አነባለሁ፣ የታክስ የሂሳብ ባለሙያዎችን፣ የጠበቆችን፣ የባንክ ሰራተኞችን፣ የሪልስቴት ደላሎችን፣ የባለሃብቶችን ንግግር አዳምጣለሁ። አባቴ ግን የሚያወራው ከአስተማሪዎች ጋር ብቻ ነበር።

አንድ ቀን አባቴ ቤታችን ከሁሉም የበለጠ ሀብቱ ስለመኾኑ እየነገረኝ ነበር። እኔ ቤትን ብዙም ጥሩ ያልኾነ ሀብት አድርጌ እንደማስበው ስናገር በመካከላችን የማያስደስት ክርክር ተካሄደ።

ቤትን በተመለከተ ደሃው አባቴና ሀብታሙ አባቴ ያላቸው የአመለካከት ልዩነት ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ላይ የሰፈረውን ይመስላል። አንደኛው አባቴ ቤቱ ንብረት ነው ብሎ ሲያስብ ሌላኛው ግን ዕዳ እንደኾነ ያስባል።

ሀብታሙ አባቴ

| ንብረት | ዕዳ |
| --- | --- |
| | ቤት |

ደሃው አባቴ

| ንብረት | ዕዳ |
|---|---|
| ቤት | |

የቤት የገንዘብ ፍሰት ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ላይ የተመለከተውን ይመስላል::

ዕዳ

| ገቢ | |
|---|---|
| ወጪ | የባንክ ብድር |
| | የአፈርና የጣራ ግብር |
| | የኢንሹራንስ ወጪ |
| | የጥገና ወጪ |

ዛሬም ድረስ ቤት ንብረት አይደለም በሚለው ሀሳቤ በርካታ ተቃውሞዎች ይገጥሙኛል:: ደግሞም ለበርካቶች የህይወት ዘመን ሕልማቸውና ትልቁ ሀብታቸው እንደኾነም አውቃለሁ:: የራስ ቤት ባለቤት መኾን ከምንም ይሻላል:: ሰዎች ይህንን ጉዳይ በተለየ መነጽር እንዲመለከቱት እጠይቃለሁ:: እኔና ባለቤቴ ካለን የሚተልቅና የሚያምር ቤት ለመግዛት ካሰብን ከኪሳችን ገንዘብ የሚያስወጣን በመኾኑ ዕዳ ነው::

የእኔም መከራከሪያ እዚህ ላይ ነው:: ጥሩ ቤት የስሜት ጉዳይ በመኾኑ በርካቶች በዚህ ሀሳቤ እንዲስማሙ አልጠብቅም:: በገንዘብ ጉዳይ ደግሞ ስሜት ከፍ ሲል ንቃት ዝቅ ይላል:: ከልምዱ እንደማውቀው ገንዘብ እያንዳንዱን ውሳኔ ስሜታዊ የሚያደርግበት መንገድ አለው::

1. ስለቤቶች ስናወራ በርካቶች ንብረታቸው ሳልኾነ ቤት ዕዳ ከፋይ ኾነው እንደሚኖሩ እናያለን:: በሌላ አገላለፅ አብዛኞቹ በተወሰኑ ዓመታት ልዩነት አዲስ ቤት እየገዙ የለላ ዓመት ዕዳ ውስጥ ራሳቸውን ይዘፍቃሉ::





2. የአፈርና ጣራ ግብር:- የባለቤቴ ወላጆች በእርጅና ዘመናቸው የቤታቸው ግብር በወር ወደ 1000 ዶላር ከፍ ስላለባቸው ቤታቸውን ለቀው ለመውጣት ተገደዋል::
3. የቤቶች ዋጋ ሁሌም እያደገ አይሄድም:: በ1997 በሚሊዮን ዶላሮች የሚያወጡ ቤቶች የነበራቸው ጓደኞቼ ነበሩኝ:: ዛሬ ቤቶቹ ከ700 ሺ ዶላር በላይ አያወጡም::
4. ከኪሳራዎች ሁሉ የሚልቁት እጋጣሚን ካለመጠቀም የሚመነጩ ናቸው:: ገንዘብህ በሙሉ በቤትህ ከተያዘብህ የምትንቀሳቀስበት ብር ስለማይኖርህ ለብድርና ከአቅም በላይ ለመስራት ትገደዳለህ:: ወጣት ጥንዶች በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በንብረታቸው ላይ ትኩረት ሰጥተው ቢሰሩ ኖሮ ልጆቻቸው ለኮሌጅ በሚበቁባቸው ዘመናት ነገሮች ይቀሉላቸው ነበር:: ንብረቶቻቸው እድገው ወጪዎቻቸውን በቀላሉ ለመሸፈን ያስችሏቸዋልና:: ብዙ ጊዜ ግን ቤት ለረዥም ዘመን ተከፍሎ የማያልቅ ዕዳ የሚያመጣ ንብረት ከመኾን አያልፍም::

ስናጠቃልለው በሕይወት የመጀመሪያዎቹ ዘመናት የቤት ባለቤት ለመኾን መወሰን ሰዎችን ቢያንስ በሶስት ዓይነት መልኩ ተፅዕና ያሳድርባቸዋል::

1. ሌሎች ንብረቶቻቸውን ማሳደግ የሚችሉበትን ጊዜ ያሳጣቸዋል::
2. ከቤቱ ጋር በተያያዘ የሚመጡ የጥገናና ማስዋቢያ ወጪዎች ለሌላ ሥራ ማዋል ሲቻል ብዙ ገንዘብ ይባክናል::
3. የትምህርት ዕጦት:- ብዙ ጊዜ ሰዎች ቤታቸውን ዋነኛውና ትልቁ ሀብታቸው አድርገው ስለሚቆጥሩት ገንዘባቸውን በሙሉ እዚያ ላይ ያውሉና በሌሎች የንግድ ዘርፎች ላይ የሚሳተፉበት አቅም ያጣሉ:: ይህም የንግድ ልምድ እንዳይኖራቸው ያደርጋቸዋል::

እያልኩ ያለኹት ቤት አትግዙ አይደለም:: እኔ የምለው በንብረትና በዕዳ መካከል ያውን ልዩነት ተገንዘቡ ነው:: ካለኝ የተሻለ ቤት ስፈልግ የማደርገው ተጨማሪውን ወጪ ለመሸፈን የሚያስችለኝን ገንዘብ የሚያስገኝልኝ ንግድ መጀመር ነው::

የምሁሩ አባቴ የገንዘብ ፍሰት መረጃ የገንዘብ ችግር አዙሪት ውስጥ የገቡ ሰዎችን ኹነት ከምንም በላይ የሚያስረዳ ነው:: ገቢው ባደገ መጠን ወጪዎቹም እያደጉ

በመሄድ መቼም ቢሆን ንግድ ላይ የሚያውለው ገንዘብ እንዳይተርፈው ያደርጋሉ:: የሚቀጥለው ሰንጠረዥ በዚህም የተነሳ ሁሌም ዕዳው ከንብረቱ በላይ ሆኖ ይቀጥላል:: የሚቀጥለው ሰንጠረዥ ይህንኑ ፍንትው አድርጎ ያሳያል::

የሙሁሩ አባቱ
የገንዘብ ፍሰት ሪፖርት




በአንፃሩ የሀብታሙ አባቴ የገንዘብ ሪፖርት የሚያሳየው ኑሮውን ንብረቱን በማሳደግና ዕዳውን በመቀነስ እንዳሳለፈ ነው::

የሀብታሙ አባቴ
የገንዘብ ፍሰት ሪፖርት




የሀብታሙ አባቴ የገንዘብ ፍሰት ሪፖርት ሀብታሞች ለምን የበለጠ ሀብታም እየሆኑ እንደሚሄዱ የሚያስረዳ ነው:: ንብረቱ ዕዳውን ሸፍኖ ትርፋማ የሆነ ንግድ ላይ መዋል





የሚችል በቂ ገንዘብ ይተርፋል:: ንብረቱ እያደገ ስለሚሄድም ገቢውም በዚያው መጠን እየጨመረ ይሄዳል::

በሀብት ላይ
ሀብት ለምን
እንደሚደራረብ




መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ሁሌም ራሳቸውን በገንዘብ ችግር ውስጥ ነው የሚያገኙት:: ቀዳሚው ገቢያቸው ደመወዝ በመሆኑ ደመወዛቸው ሲያድግ ግብሩም አብሮ ያድጋል:: በሌላም በኩል ገቢያቸው ሲያድግ ወጪዎቻቸውም በዚያው መጠን ከፍ ይላሉ:: የማይወጣበት አዙሪት ማለት ይህ ነው እንግዲህ:: ትርፍ በሚያስገኙ ንግዶች ላይ እንደመሳተፍ ቤታቸውን እንደ ትልቅ ንብረት በመቁጠር አድሜያቸውን ይገፋሉ::

መካከለኛ ገቢ ያላቸው
ሰዎች አዙሪት



ይህንን ዓይነቱ ቤትን እንደ ውጤታማ የንግድ ሥራ መቁጠርና ደመወዝ ሲጨመር የተሻለ ቤት መግዛት ይቻላል የሚለው ፍልስፍና ነው እንግዲህ የዚህን ዘመን በዕዳ የተዘፈቀ ማህበረሰብ የፈጠረው፡፡ ይህ ዓይነቱ የገንዘብ አወጣጥ በርካታ ቤተሰቦችን ወደበለጠ ዕዳና የገንዘብ አቅም መዋዠቅ ያስገባቸዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አደጋው የበዛ ኑሮ በገንዘብ ነክ ዕውቀት ማነስ የሚከሰት ነው፡፡

በ1990ዎቹ የተከሰተው በርካታ የሥራ ቦታዎች የመታጠፍ ክስተት መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ያልተረጋጋ የገንዘብ መሰረት ላይ እንደኾኑ ያሳየ ነው፡፡ በድንገት የኩባንያ ጡረታ በ"401K" ዕቅድ ተተካ፡፡ ማህበራዊ ዋስትና ችግር ውስጥ በመውደቁ እንደጡረታ መውጫ መንገድ ማገልገል አልቻለም፡፡ እናም መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሰዎች ዘንድ መረበሽ ኾነ፡፡ ጥሩው ነገር እነዚያ ሰዎች ዛሬ ዕውነታውን ተመልክተው የጋራ አክስዮኖችን መግዛት ጀምረዋል፡፡ አሁን አሁን የባለመካከለኛ ገቢ ሰዎችን ፍላጎት ለማርካት በርካታ አክስዮን ማህበራት እየተቋቋሙ ነው፡፡

የአክስዮን ማህበራት ተፈላጊ የሚኾኑበት ምክንያት አስተማማኝ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ አብዛኞቹ የአክስዮን ገዢዎች በግብርና በብድር የተጨናነቁ እንዲሁ ለልጆቻቸው የኮሌጅ ክፍያ በማጠራቀም የተጠመዱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ንግድ እንዴት እንደሚካሄድ ለመማር ጊዜ ስለሌላቸው በማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ምክርና ዕውቀት ይመራሉ፡፡ ደግሞም እነዚህ ንግዶች በርካታ ዘርፎች ስላሏቸው አስተማማኝ መስለው ይታያሉ፡፡

የተማሩት ባለመካከለኛ ገቢ ቡድኖች ብዙ አደጋ የሌለበት ንግድ ላይ በመሰማራት ያምናሉ፡፡

ባለመካከለኛ ገቢ ሰዎች የሚገጥማቸው አደጋ ምንጩ አስቀድመው ስለገንዘብ ትምህርት ባለማግኘታቸው ነው፡፡ አደጋ የሚጋፈጡበት ምክንያት የገንዘብ አቋማቸው የማያስተማምን በመኾኑ ነው፡፡ የገቢና ወጪ ሚዛናቸው የተዛባ ነው፡፡ ብቸኛው የገቢ ምንጫቸው ደመወዛቸው ነው፡፡ ሕይወታቸው ሙሉ በሙሉ በቀጣሪዎቻቸው ላይ የተመሰረተ ነው፡፡





እናም ጥሩ የንግድ ዕድሎች ሲመጡ እነዚህ ሰዎች ሲጠቀሙባቸው አይችሉም፡፡ ጠንክረው ሰርተው ከሚያገኙት ገንዘብ ከፍተኛ ግብር ስሚከፍሉና በዕዳ የተዘፈቁ በመኾናቸው በገንዘባቸው ምንም መሞከር አይፈልጉም፡፡

በዚህ ክፍል መጀመሪያ ላይ እንዳልኩሁ ከሁሉም የሚበልጠው መመሪያ በንብረትና በዕዳ መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ ነው፡፡ ልዩነታቸውን ከተገንዘብክ ትኩረትህን ገቢ የሚያስገኙ ንብረቶችን በመግዛት ላይ አድርግ፡፡ የሀብትን ጉዞ ለመጀመር የተሻለው መንገድ እሱ ነው፡፡ ይህንን ማድረግህን ስትቀጥል የንብረትህ መጠን እያደገ መሄድ ይጀምራል፡፡ ዕዳዎችህና ወጪህ ዝቅ ብለው እንዲቆዩ አድርግ፡፡ እንደዚያ ስታደርግ ወደንብረትነት ፈሰስ የምታደርገው የገንዘብ መጠን ከፍ ይላል፡፡ በሂደትም የንብረትህ መጠን በጣም ከፍ ስለሚል እስኪ የሚባሉትን የንግድ ዘርፎች ጥምር መመልከት ትችላለህ፡፡ ከ100 እስከ የትየለሌ ትርፍ የሚያስገኙ ንግዶችን፣ 5000 ብርን ወደ ሚሊየን የሚያሻግሩ ንግዶችን፡፡ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች "አደጋ አለባቸው" የሚሏቸውን ንግዶች፡፡ አደጋ ያለበት ንግዱ አይደለም፡፡ ሰዎች ስለ ገንዘብ ያላቸው የዕውቀት መጠን ነው አደጋው፡፡

ብዙሃኑ የሚሰራውን ከሰራህ የምታገኘው የሚከተለውን ስንጠረዥ ነው፡፡

| | |
|---|---|
| ገቢ | ለባለሃብት መሥራት |
| ወጪ | ለመንግሥት መሥራት |

| | |
|---|---|
| ንብረት | ዕዳ<br>ለባንክ<br>መሥራት |

በአጠቃላይ ቤት እንዳለውና ተቀጥሮ እንደሚሰራ ሰው የሥራህ ሂደት
የሚከተለውን ነው የሚመስለው::

1. ለሌላ ሰው እየሰራህ ነው:: አብዛኞቹ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰዎች ባለሃብቶችን ወይም የባለ አክስዮኖችን ሀብት በመጨመር ላይ ናቸው:: የአንተ ጥረትና ስኬት የባለቤቱን ስኬት ነው::
2. ለመንግሥት እየሰራህ ነው:: መንግሥት ደመወዝህን ከመቀበልህ በፊት የራሱን ድርሻ ይወስዳል:: ጠንክረህ በሰራህ መጠን መንግሥት የሚወስደውን ድርሻ ከፍ ታደርግለታለህ::
3. ለባንክ እየሰራህ ነው:: ከግብር መልስ ምናልባትም ትልቁ ወጪህ የባንክ ብድርና የክሬዲት ካርድ ወጪዎችን መክፈል ነው::

ጉልበትህን ገዝም ብሎ ጠንክሮ የመሥራት ችግሩ ከላይ የተጠቀሱት ሶስቱ ባለድርሻዎች ተጠቃሚ የሚበዘብዙበት መጠንም ከፍ ይላል:: የሥራ ትጋትህ አንተና ቤተሰብህን
የሚያደርግበትን መንገድ መማር አለብህ::

እንዴት በራስህ ጥቅም ላይ ለማተኮር ከወሰንክ በኋላ ግብህን የምታስቀምጠው
ነው? ብዙ ሰዎች ሙያቸው ላይ በመቆየት በደመወዛቸው ንብረት ለማፍራት ይሞክራሉ::
የንብረታቸው መጠን ከፍ ሲል ስኬታቸውን የሚለኩት እንዴት ነው? ሰዎች
ሀብታም መኾናቸውን የሚያውቁት መቼና እንዴት ነው? ንብረትና ዕዳን በተመለከተ
የራሴ ትርጉም እንዳለኝ ሁሉ ለሀብትም የራሴ ትርጉም አለኝ:: ለነገሩ በክሚኒስተር ፉለር
ከተሰኘ ሰው የወሰድኩት ነው:: በ1961 አርክቴክቶችን ሁሉ ባስገረመ መልኩ ጂኦዴስክ
ዶም ለተሰኘ ሥራው የባለቤትነት መብት ጥያቄ አቀረበ:: ባቀረው ማመልከቻ ውስጥ ግን
ስለ ሀብት አንድ ነገር ብሎ ነበር:: መጀመሪያ ሲያዩት ግራ የሚያጋባ ደጋግመው
ሲያነቡት ግን ትርጉም የሚሰጥ ነገር ነው:: ሀብት ማለት የአንድ ሰው ከአሁን በኋላ
ሊቆይባቸው የሚችላቸው ቀናት ብዛት ነው:: ወይም ባጭሩ ዛሬ ሥራ ባቆም ለምን ያህል
ቀናት መኖር እችላለሁ?

ንብረትና ዕዳ ተቀናንሰው ከሚሰጡት የተጣራ ሀብት ከሚባለው መግለጫ ይልቅ
ይህኛው ቅልብጭ ያለ ምላሽ ይሰጣል:: ሀብት ንብረትህ ወጪህን ምን ያህል መሸፈን
ይችላል እንደማለት ነው::





አስረጂ ምሳሌ እንጠቀም:: ከንብረቶቼ በወር 1,000 ዶላር ገቢ አለኝ:: ወርሃዊ
ወጪዬ ደግሞ 2,000 ዶላር ነው:: ሀብቴ ምን ያህል ነው?

ወደ በክሚኒስተር ፉለር ትርጉም እንመለስ:: ለምን ያህል ቀናት መቆየት
እችላለሁ? 30 ቀናት ያሉትን ወር ብንወስድ ለ15 ቀናት የሚኾን ገንዘብ አለኝ::

የወር ወጪዬን 2,000 ዶላር የሚሸፍን ገቢ ከንብረቶቼ ማግኘት ስችል ያኔ
ከድህነት እወጣለሁ::

ከድህነት ወጥቻለሁ ግን ሀብታም አይደለሁም:: አሁን ወጪዎቼን በሙሉ
ሊሸፍን የሚችል ገቢ ከንብረቶቼ እያገኘሁ ነው:: በዚህ ሁኔታ ለመቀጠል ወጪዎቼን
መጨመር ስፈልግ በቅድሚያ ከንብረቶቼ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ አለብኝ:: እዚህ ነጥብ
ላይ ነው እንግዲህ ከደመወዜ ተፅዕኖ ነፃ መኾኔ የሚታየው:: ዛሬውኑ ሥራ ባቆም
ወርሃዊ ወጪዎቼን ከንብረቶቼ በማገኘው ገቢ መሸፈን እችላለሁ::

ቀጣዩ ግቤ ከወጪዎቼ የሚተርፈውን ገንዘብ መልሶ ንብረት በማፍራት ላይ
ማዋል ነው:: ወጪዎቼን ከንብረቶቼ ከማገኘው ገቢ ያነሱ አድርጌ ማቆየት እስከቻልኩ
ድረስ ሀብታም እየኾንኩ እሄዳለሁ:: ገቢዎቼም የእኔን ቀጥታ ጉልበት ወይም ተሳትፎ
የማይጠይቁ ይኾናሉ::

ይህንን ዓይነት ሂደት ሲቀጥል ሀብታም ለመኾን መንገድ ላይ ነኝ:: ትክክለኛው
የሀብታምነት ትርጉም እንደየሰው ይለያያል:: መቼም ቢኾን ግን ከሚገባው በላይ ሀብታም
ልትኾን አትችልም::

የሚከተሉትን ነገሮች ልብ በላቸው::

ሀብታሞች ንብረት ይገዛሉ::

ድኾች ወጪ ብቻ ነው ያላቸው::

መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ዕዳ እየገዙ ንብረት ነው ብለው ያስባሉ:: ታዲያ
የራሴ ጥቅም ላይ የማተኩረው እንዴት ነው? የማክዶናልድን መስራች አዳምጡት::

# ትምህርት ሶስት

# ያለህበትን ንግድ ጠንቅቀህ እወቅ





## ምዕራፍ አራት

## ሦስተኛው ትምህርት

# ያለህበትን ቢዝነስ እወቅ

የማክዶናልድ ኩባንያ መስራች የነበረው ሬይ ክሮክ እኢአ በ1974 ዓ.ም በዩናይትድ ስቴትስ አውስቲን ውስጥ በሚገኘው የቴክሳስ ዩኒቨርስቲ ቢዝነስ አስተዳደር የማስተርስ (MBA) ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርግ ተጋብዞ ነበር።

የእኔ የልብ ጓደኛዬ ኪይዝ ኩኒንግሃም በወቅቱ በቢዝነስ አስተዳደር የማስተርስ ተማሪ ነበር። ሬይ ክሮስ በዕለቱ ማራኪና ጥልቅ የቢዝነስ ተሞክሮውን የተመለከተ ንግግሩን ካቀረበ በኋላ፣ ከተማሪዎቹ የቀረበለትን የቢራ ግብዣ በማክበር ተቀበለ።

የመዝናናኛ ዝግጅቱ እየተካሄደ በነበረበት ወቅት ሬይ፣ ተማሪዎቹን ‹‹እኔ የምሰራበትን ቢዝነስ እስኪ ንገሩኝ?›› በማለት ጥያቄ አቀረበላቸው።

ጓደኛዬ ኪይዝ እንደነገረኝ ከሆነ፣ ተማሪዎቹ ጥያቄውን እንደሰሙ በጥያቄው ተገርመው በሙሉ ነው በሳቅ የተንከተከቱት። ብዙዎች ተማሪዎች እንዲያውም የሬይ ክሮክ በጥያቄው ሆን ብሉ እያሞኛቸው እንደሆነ አስበዋል።

ለጥያቄው መልስ ያላገኘው ሬይ በድጋሚ ‹‹የምሰራበትን ቢዝነስ ንገሩኝ?›› ብሎ ጠየቃቸው።

ተማሪዎቹ አሁንም በድጋሚ ሳቁ። በመጨረሻም አንድ ደፋር ተማሪ፣ ‹‹ሬይ፣ እንደው ማን ይሙት አንተ የሀምበርገር ቢዝነስ እንደምትሰራ የማያውቅ ይኖራል?›› በማለት ጠየቀው።

ሬይ ጉሮሮውን እያጠራ፣ ‹‹እዎ፣ እንዲህ ብላችሁ መለስ እንደምትሰጡኝ አስቤያለሁ›› በማለት ዝም አለና እንደገና ፈጠን ብሎ ‹‹ክቡራትና ክቡራን፣ እኔ በሃምበርገር ቢዝነስ ውስጥ አይደለም የምሰራው፣ የእኔ ቢዝነስ የሪል ስቴት ልማት ነው›› ተናገረ።

ኪይዝ እንደነገረኝ የማክዶናልድ መስራቹ ሬይ የራሱን የቢዝነስ ምልከታን ሲገልፅ የጊዜ አጠቃቀሙ የሚገርም ነበር። ሬይ በቢዝነስ ዕቅድ ውስጥ በቅድሚያ

ትኩረት ያደረገው የሀምበርገር ቢዝነሱን ፍራንቻይዝ ለማድረግ ነበር። (በፍራንቻይዝ አሰራር፣ አንድ ትርፋማ ቢዝነስን ሌሎች የቢዝነሱን ስምና መላውን አሰራርን ተከትሉ በህጋዊ ስምምነት የሚሄድ ጥምር ቢዝነስ ነው)

በዚህም እያንዳንዱ ፍራንቻይዝ የሚደረገው ቢዝነስ የት አካባቢ መሆን እንዳለበት አልጠፋውም። በተለይ ደግሞ የሪል ስቴት የሚባልበት አካባቢ፣ ፍራንቻይዝ በሚያደርገው ቢዝነስ ስኬታማ እንዲሆኑ ትልቁን ሚና ሊጫወት ችሏል። በዋነኝነት የሬይ የሃምበርገር ቢዝነሱን ፍራንቻይዝ የሚያደርግላቸው ወገኖች ክፍያ የሚፈፅሙት ለሃምበርገር ቢዝነሱ ብቻ ሳይሆን፣ ከሬይ የሪል ስቴት ልማት በሚገዙት ሱቅ የመሬት ክፍያ ይፈፅማሉ።

በአሁኑ ወቅት ማክዶናልድ በመላው አለም ትልቁን የሪል ስቴት ብቸኛ ባለቤትነት የሚደርስበት የለም። በዚህም ክካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሁሉ ሳይቀር ይበልጣል።

በዚህም የተነሳ፣ ማክዶናልድ በአሜሪካ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በርካታ አገሮች፣ ዋና ዋና የቢዝነስ እንቅስቃሴ በተጧጧፈባቸው ከተሞች ውስጥ የሚገኙ ውድ ቦታዎች ባለቤትም ጭምር ነው።

እንደ ኬይዝ ገለፃ፣ በህይወቱ ውስጥ ካገኛቸው በጣም ጠቃሚ ዕውቀቶች የገበያው የዚያን ዕለት ነበር። በአሁኑ ወቅት ኬይዝ የመኪና ዕጥበት አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎች ባለቤት ሆኗል። ነገር ግን የኬይዝ ቢዝነስ የሪል ስቴት ልማት ቢሆንም፣ በነዚህ በለሙ ሪል ስቴቶች ውስጥ የመኪና ዕጥበት አገልግሎትን በሰፋት ለማካሄድ አስችሎታል።

ከዚህ በፊት የነበረው ምዕራፍ ሲጠናቀቅ የቀረበው ዲያግራም ውስጥ እንደተገለፀው፣ በርካታ ሰዎች የሚሰሩት ለሌላ ሰው እንደሆነ ቢያስቡም፣ የሚሰሩት ለራሳቸው ነው። በቅድሚያ ለኩባንያው ባለቤት ይሰራሉ - በመቀጠልም ለመንግስት ይሰራሉ - በታክስ መልክ ይከፍላሉ። በመጨረሻም ለባንኮች ነው የሚሰሩት - የራሳቸው መኖሪያ ቤት እንዲኖራቸው ከባንኮች ጋር ውል ይፈፅማሉ።

ልጅ በነበርኩበት ወቅት፣ የማክዶናልድ ሱቅ በቅርባችን የለም ነበር። ከዚያም ሀብታሙ አባቴ፣ ለእኔና ማይክ ሊያስረዳን የፈለገው የማክዶናልድ መስራች ሰውዬ



የቴክሳስ ዩኒቨርስቲ አስመልክቶ የተናገረውን መሰረት ያደረገ ነበር። ይህም ሚስጥር ሀብታሞችን የተመለከተ ነው። ይህ ሚስጢር «የራስህን ቢዝነስ ቅረፅ» የሚለው ነው። ገንዘብ በማግኘት የሚደረግ ልፋት ወይም «ግብግብ» ዘወትር በቀጥታ የሚገናኘውና የመጨረሻ ውጤቱም፣ ሰዎች መላውን ህይወታቸው ሁሉ አንድን ሰው ለማገልገል ከማዋል ጋር ሲገናኝ ነው።

እንዲያውም ብዙዎች ቀኑን ሙሉ ሰርተው ከሥራ ሲወጡ በእጃቸው ላይ ቤሳ ቤስቲን የላቸውም።

አዎ፣ የአንድ ምሥል ዋጋ ከሺህ ቃላቶች በላይ ይበልጣል። ከዚህ በታችም የቀረበው ምስልም የገቢ መረጃዎችን እና የወጪና የቀሪ ሃሳቦችን የሚያሳይ ሲሆን፣ የሬይ ካርልን ምክርም በሚገባ የሚገልፁ ናቸው።




በአሁኑ ወቅት እየተሰራበት የሚገኘው የትምህርት አሰጣጥ ስልት ትኩረት የሚያደርገው፣ ወጣቶች ከትምህርት በኋላ ጥሩ ገቢ የሚያስገኝ ስራ እንዲያገኙ ክህሎታቸውን ማሳደግ ላይ ነው። የነዚህ ወጣቶች ህይወት የሚሽከረከረው በሚያገኙት ደሞዝ ዙሪያ ብቻ ነው። ወይ ቀደም ተብሎ እንደተነገረው፣ ትኩረት የሚያደርጉት የገቢያቸውን ዝርዝር በሚያሳውቀው አምድ ላይ ብቻ ነው።

እነዚህ ወጣቶች በት/ቤቶች ውስጥ የአካዳሚ ክህሎታቸውን ካሳደጉ ተጨማሪ የሙያ ባለቤት እንዲሆኑ ወደሚያደርጓቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይሄዳሉ። ከዚያም መሃንዲስ፣ ሳይንቲስት፣ የፖሊስ ኦፊሰር፣ አርቲስት ወይም ፀሃፊ ወዘተ በመሆን ጥናት ይጀምራሉ። በዚህ የሙያ ክህሎት ደግሞ እነዚህ ወጣቶች የሥራ ኃይል በመሆን ገንዘብ በማግኘት ሲሉ ብቻ ሥራ ይገባሉ።

እዚ ጋ በዋነኝነት መዘንጋት የሌለበት በሰዎች ሙያና ቢዝነስ መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን ነው። ዘወትር ሰዎችን ‹‹ቢዝነስህ ምንድነው?›› በማለት ስጠይቃቸው በአንድ ወቀት አንዱ ‹‹አ እኔ የባንክ ሰው ነኝ›› ብሎኛል። ከዚያም፣ ‹‹የራስህ ነው ባንኩ?›› ብዬ ስጠይቃቸው። ‹‹አይ የምሰራው እዚያ ነው›› ብሎ መለሰልኝ።

እዚ ጋ የምንረዳው ሰዎች ሙያውን እና በቢዝነስ መካከል ያልገባቸው ነገር መኖሩን ነው። በሙያቸው የባንክ ሰራተኞች ሊሆኑ ቢችሉም፣ አሁንም ድረስ የራሳቸውን የሆነ ቢዝነስ መፍጠር ይገባቸዋል። የማክዶናልድ መስራቹ ሮይ ክሮክ ግን፣ በባለሙያነቱ እና በቢዝነስ መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቆ የተረዳ ነው። የእሱ ባለሙያነት ምንጊዜም ቢሆን አንድ አይነት ብቻ ነው። አዎ፣ በሙያው የሽያጭ ሰራተኛ ነው። በአንድ ወቀት የወተት ማቀነባበሪያ ማሽንን ሲሸጥ ቢቆይም፣ ብዙም ሳይቆይ የራሱን የሃምበርገር ንግድ ፍራንቻይዝ እንዳደረገ ለሌሎች ቢዝነሱን መሸጥ ጀመረ። በዚህ ሁኔታ የሬይ ክሮክ ሙያ የሃምበርገር ቢዝነስን ፍራንቻይዝ ማድረግ ሲሆን፣ በዋነኝነት ግን ከዚያ ያባበተውን ገንዘብ ወደ ሥራ በመቀየር ወደ ሪል ስቴት አልሚነት ቢዝነስ ተየቀረ።

በት/ቤቶች ያለው ችግር ይኸው ነው። የእናንተ የዘወትር ተግባር ማጥናት የሚገባቸውን አጠናቆ መጨረስ ነው። ለምሳሌ ስለምግብ ዝግጅት ያጠናችሁ ከሆነ፣ በመጨረሻ የምግቡ አብሳይ ባለሙያ ትሆናላችሁ። ያጠናችሁት ህግ ከሆነ፣ በመጨረሻ የአቃቤ ህግ ሥራ መያዝ ትችላላችሁ።

ወይም ደግሞ የተማራችሁት አውቶ ሜካኒክ ከሆነ፣ የመካኒክነት ሙያ ባለቤት ትሆናላችሁ። እዚህ ጋ እንደ ስህተት የሚጠቀሰው፣ ብዙዎች የአንድ የሙያ ባለቤት ከሆኑ በኋላ፣ ስለራሳቸው ቢዝነስ ለመፍጠር ሲዘናጉና ጨርሰውኑ ሲረሱት መስተዋሉ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች ህይወታቸውን ሙሉ የራሳቸው ቢዝነስ በአዕምሮአቸው ለመቅረፅ የሚተጉ ቢሆኑ ኖሮ፣ በመጨረሻ ሀብታም ሰው መሆን ይችሉ ነበር።





አንድ ሰው አስተማማኝ የገንዘብ አቅም የሚኖረው ከሆነ፣ የራሱን ቢዝነስ የሚቀርፅበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልገዋል። የእናንተ ቢዝነስ የሚሽከረከረው በቋሚ ሀብታችሁ አምድ ዙሪያ ከሆነ፣ በቀጥታ ከገበያችሁ አምድ ጋር ይጋጫል።

ከዚህ በፊት በሰፊው እንደተመለከትነው፣ የመጀመሪያው ቁጥር አንድ ደንብ የሚገልፀው፣ በቋሚ ሀብት፣ በዕዳዎችና በቋሚ ሀብት ግዢ መካከል ያሉትን ልዩነቶች በሚገባ ማወቁ ላይ ነው። ሀብታም ሰው ሁሌም ትኩረት የሚያደርገው በቋሚ ሀብት አምዱ ላይ ሲሆን፣ በአንፃሩ የብዙዎች ትኩረት ግን የሚያዘነብለው በገበያ ዝርዝር መግለጫ ላይ ነው።

ከዚህ የተነሳ ነው ዘወትር ከገቢ ጋር የተያያዙ ሃሳቦች የምናደምጠው። ‹‹ገቢዬን ማሳደግ እፈልጋለሁ›› ፣ ‹‹ገቢዬ እንዲጨምር ከመሥራት ሌላ አማራጭ የለም›› ‹‹ተመልሼ ወደ ት/ቤት በመግባት ተጨማሪ ስልጠናዎችን በመውሰድ የተሻለ ሥራ የማግኘት አጋጣሚን መፈጠር ይኖርብኛል››፣ ‹‹አሁን ከምሰራው የሥራ ሰዓት በተጨማሪ መሥራት አሰብኙ››፣ ‹‹ተጨማሪ ሁለተኛ ሥራ ባገኝ እመርጣለሁ›› የሚሉ ምኞቶችን ሁሌም የምሰማቸው።

በአንድ አይነት አዙሪት ውስጥ የሚገኙ እንደዚህ ዓይነት ሃሳቦች ስሜታዊ ሊባሉ የሚችሉ ናቸው። አሁንም ቢሆን፣ የሬይ ክሮክን ልምድን በተመለከተ ያስረዳኋችሁ ቢሆንም የራሳችሁን ቢዝነስ ግን በአዕምሮአችሁ ልትፈጥሩ አልቻላችሁም። እነዚህ ሁሉ ሃሳቦች አሁንም ድረስ ትኩረት የሚያደርጉት በገቢ ላይ ሲሆን፣ ሊጠቅሙ አይችሉም። በሃሳቦች ተጠቃሚ የሆነ ግለሰብ የገንዘብ እጥረት ችግር ውስጥ እንዳይገባ ከማድረጉም በላይ፣ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ ቋሚ ሀብቶችን ለመግዛት ያስችለዋል።

በአመዛኙ ደሃና መካከለኛ ገቢ ያላቸው የመደብ ክፍሎች ብዙውን ጊዜ ግትሮችና ሌላ አዲስ አማራጭ መንገድ መኖሩ የማይታያቸው ናቸው። ይህም ማለት ‹‹ለዚህ አደጋ ወይም ኪሳራ ለሚያመጣ ቢዝነስ ገንዘቤን አላወጣም።›› ሲሉ፣ እነዚህ ሰዎች መጀመሪያውኑ የፋይናንስ እቋም በውስጣቸው የለም ማለት ነው። ሁሌም ቢሆን አላማቸው የተቀጠሩበትን ሥራ ሙጭጭ አድርጎ መያዝ ነው። ጨዋታውን የሚጫወቱት በጥንቃቄ ነው።

ብዙዎቻችን መኖሪያ ቤት ወይም መኪና ለመግዛት ከባንክ የብድር መጠየቂያ ደብዳቤ እንዳስገባን እገምታለሁ:: በዚህ የብድር መጠየቂያ ደብዳቤ ዝርዝር ውስጥ ትኩረት የምንሰጠው ከባንክ በብድር የሚፈለገው ‹‹ጠቅላላ የገንዘብ መጠን›› ላይ ነው:: በሌላ በኩል ባንኮቻችን ለብድር ጥያቄ የሚሰጡት በጎ ምላሽ መሠረት የሚያደርገው በብድር መጠየቂያ ሰነድ ውስጥ መደበኛ የሂሳብ አያያዝ ደረጃ ላይ ነው:: ይህም ነው ተበዳሪው ግለሰብ ከባንኩ ባገኘው ብድር የቋሚ ሀብት ባለቤት የሚያደርገው::

በአንድ ወቅት ከባንክ ብድር ለማግኘት ብፈልግም፣ በባንክ ዘንድ አሳማኝ የሆነ የፋይናንስ አቅምን የሚያሳይ ሁኔታ ላይ አልነበርኩም:: ለዚህ መፍትሄ እንዲሆነኝ፣ ለባንኩ ባቀረብኩት ማመልከቻ ላይ ያሉኝን ቋሚ ሀብቶች ዝርዝር መዝገቤ አካተትኩ:: ከነዚህም ውስጥ አዲሱን የጎልፍ ክለቤን፣ የሥነ ጥበብ ስብስቦቼን፣ መፅሐፍትን፣ ቴሌቪዥን እና ሌሎች የቋሚ ሀብቶቼን ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎችን በዝርዝር አሰፈርኳቸው::

ይሁን እንጂ የብድር ጥያቄዬ ተቀባይነት ለማግኘት አልቻለም፣ ምክንያቱም በሪል ስቴት ልማት ላይ ከመጠን በላይ ኢንቨስት ያደረግኩ በመሆኑ ነበር:: የባንኩ የብድር ኮሚቴ ከፍተኛ መጠን ያለውን ገንዘብ በአፓርትመንት ቤቶች ግንባታ ላይ ማውጣቴን በበጎ አይን አላየውም:: ከዚህም በተጨማሪም፣ ኮሚቴው፣ ደምዝ የማገኝበት መደበኛ ሥራ እንዳለኝ ወይም እንደሌለኝ ለማወቅ ፈልጓል:: ይሁን እንጂ፣ ስለ ጎልፍ ክለቤ ወይም ስለ የሥነ ጥበብ ስብስቦቼ ጥያቄ ለማቅረብ አልፈለጉም:: ህይወት አንዳንዴ አስቸጋሪ ይሆናል:: በተለይ የህይወት ታሪክህ ከሚፈለገው ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ ሳይገኝ በሚቀርበት ወቅት ማለት ነው::

በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሌም ደስተኛ አይደለሁም:: የሰውየው አጠቃላይ የተጣራ ሀብቱ አንድ ሚሊዮን ዶላር፣ ወይም 100 ሺ ዶላር ወይም የሆነው ይሁን:: አንድ ሰው ያለው አጠቃላይ የተጣራ ሀብቱ በራሱ የሰውየውን የፋይናንስ አቅም የመግራት አቅም የለውም:: በተለይ ደግሞ በፍጥነት ያሉህን ቋሚ ሀብቶች በመሸጥ ላይ ከሆንክ ማለት ነው:: በሌላ በኩል ከማንኛውም ገቢህ ውስጥ ግብርም መክፈልህ አይቀርም::

በዚህ ምክንያት ነው በርካቶች ገቢ እያጠራቸው ለስራ ሲንቀሳቀሱ የተወሳሰበ የፋይናንስ ቀውስ ውስጥ ራሳቸውን ከተው የሚገኙት:: በእጃቸው ላይ ያለውን ገንዘብ ለማሳደግ የራሳቸውን ቋሚ ሀብቶች ይሸጣሉ:: ከዚያም በግል ሀብታቸው ዝርዝር ውስጥ





ተካተው የነበሩት ቋሚ ሀብቶች ከዋጋቸው ባነሰ ዋጋ የመሸጥ አጋጣሚዎች ይፈጠራሉ:: በሌላ በኩል እነዚህ ቋሚ ሀብቶች ለሽያጭ ቀርበው ከተሸጡ በኋላ፣ ከተገኘ የሽያጭ ገቢ ላይ ግብር የመክፈል ግዴታም አለባቸው:: በዚህ ምክንያት መንግስት ከገቢው ላይ የራሱን ድርሻ በግብር መልክ ስለሚወስድ፣ የቋሚ ሀብቶች ሽያጭ ገቢ፣ ወደተፈለገበት አላማ ከመድረሱ በፊት ተቆራርጦ ያልቃል - ከብር ውጪ ሊሰራ የታሰበው ሥራም በጥያቄ ውስጥ ይገባል:: ከዚህ በመነሳት ነው የተጣራ ሀብት (net worth) ሁሌም የተሰበሰትን ያህል ዋጋ አለው ተብሎ በድፍረት ለመናገር የማይቻለው::

አሁን የራሳችሁን ቢዝነስ በአዕምሮአችሁ በመቅረፅ ሥራችሁን ጀመሩ:: ዕለታዊ መደበኛ ሥራችሁን በአግባቡ እየተወጣችሁ፣ ምንጊዜም በሆነ ዋጋው የማይወርድ ቋሚ ሀብት መግዛት ጀምሩ፣ እነዚህን ቋሚ ሀብቶች ስትገዙ ምንም ዓይነት ዕዳ ውስጥ ላለመዘፈቅም ተጠንቀቁ::

ገና ለጋ ወጣት እያለሁ ወላጅ አባቴ እንድማር በትምህርቴ ውጤታማ ስሆን አጥጋቢ ደምዝ የሚያስገኝ ስራን እንድሰራ ሲያበረታታኝ ሀብታሙ አባቴ ግን ዘወትር ይጎተጉተኝ የነበረው ሀብትን ማካበት ግቤ እንዲሆን ማድረግ ነበር:: የኔም ዝንባሌ ወደ ሀብታም አባቴ ሀሳብ ነበር:: የወደድከውን ነገር ደግሞ ማግኘትህ አይቀርም፤ ካልወደድከው ደግሞ ብትሰበሰበውም መበተኑ አይቀሬ ነው::

ሪል ስቴትን ስለምወድም ለሪል ስቴት የሚሆኑ ቦታዎችን መግዛትና በእነርሱም ላይ ህንፃን መገንባት፣ የሰራሁትንም ስመለከት መደሰት ልምዴ ሆነ:: ችግር ውጣ ውረድ እንኳን ሲያጋጥመኝ ከመግዛት አላገደኝም:: በርግጥ እንደኔ አይነት አመለካከት (ሪል ስቴትንም ሆነ ሌላ ቢዝነስን) ከሌለህ ወጪ አውጥተህ መስራትን አትመኝ:: አያቀጣምና ፈጽሞ አታድርገው:: ትንንሽ አክሲዮኖችን በጣም ስወድ በተለይም ጀማሪ ኩባንያዎች ምርጫዬ ናቸው::

ለዚህ ዋናው ምክንያት ደግሞ እኔ ሥራ ፈጣሪ እንጂ ኮርፖሬት ስላልሆንኩ ነው:: ገና በለግላጋነቴ በትልልቅ ካምፓኒዎች መስራትን ስለጀመርኩ (ለምሳሌም በካሊፎርኒያ የነደጅ ድርጅት፣ በዩ.ኤስ. የመርከብ ንግድ ድርጅትና በዜሮክስ ኮርፖሬሽን ወዘተ) ስስራ እንደመዝናኛ መውሰድን ለማዳበር ረድቶኛል:: እስካሁንም የማይረሳ ትዝታ አለኝ:: በአሁኑ ሰዓት ግን የካምፓኒ ቅጥር ሰራተኛ ባልሆን የራሴ ቢዝነስ አለኝ::

በተጀመሩና ስራቸው ዘመን ካስቆጠረ አክሲዮኖች ጀማሪዎች ቀልቤን ሲስቡ በእነርሱም መልካም ውጤትን ማግኘት ስለተለማመድኩ ምርጫዎቼ ናቸው። አንዳንዴ እንደውም ራሴ አቋቁሜ በማህበረሰቡ ዘንድ በማውጣት አጋሮችን በስራው አካትታለሁ! በአዲስ አክሲዮኑ።

እንዳንድ ሰዎች የዕኔ እምነትና አካሄድ አደጋ የበዛበትና ለከስረት የተጋለጠ እንደሆነ ቢያምኑም! ዕውነትም ቢሆን ስራውን እስከወደድነው ድረስ መውጫ መንገዱ አይጠፋብህም። ዋናው ቁም ነገር ልትሰራ ስላሰብከው ነገር ጥሩ ግንዛቤ ይኑርህ። የአክሲዮን ቢዝነስ በጀመርኩ አመት ከቢዝነስ ጨዋታው ልወጣ የነበረ ቢሆንም አማራጭ በመያዝ ሪል ስቴትን በማንቀሳቀሴ በቀላሉ አንሰራርቼ በጥቂት ጊዜ ሀብቴን ማዳበር ችያለሁ። እዚህ ጋ ግብር አዘግይቶ መክፈል የራሱ ተፅዕኖ ሲኖረው በአጠቃላይ ለውጡ ሰባት ዓመታትን ወስዷል። እዚህ ጋር ማስተዋል የሚገባህ በቢዝነስ ውስጥ መዋዠቅ እንደማይገባ ነው።
አይቀሬ እንደሆነና ይህም ሂደት አንተን ሊያስደነግጥህ

በዜሮክስ ተቀጥሬ በምሰራበት ዓመታት ዘወትር እተገብረው የነበረው ሀብታሙ አባቴ ያዘዘኝን ቁም ነገሮች ነበር፡ ስራዬን እየከወንኩ የራሴን ሀብት ማዳበሩን ስቀጥል የሪል ስቴትና አክሲዮን ንግድ ደግሞ ለሀብቴ መጨመር የማይናቅ ሚናን ተጫውቷል።

የሐብታሙ አባቴ ምክር የዘወትር ንግግር ገንዘብን እንደ ግብዐት መጠቀም ላይ ሲያጠነጥን ስለ ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ዕውቀቴ በበሰለ ጊዜ የራሴን ቢዝነስ መጀመር እንደምችል ያስረዳኝ ነበር። የሆነውም ይሄው ነው። ማንም ቢሆን የማይወደውን ስራ መጀመር ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱን መረዳት እንዳለበት መገንዘብ ሲገባው የማይፈልገውን ስራ ይዞ ከመቀመጥ ይልቅ በኮርፖሬሽን ታቅፎ መስራት እንደአማራጭ ቢጠቀምበት መልካም ነው እላለሁ፡ ሳታምንበት ስራን መጀመር ከእስር እጅ በዘጠኙ ውድቀትን እንድትጎናፀፍ ሲያደርግህ ከዚህ ይልቅ ጊዜህን ተቀጥሮ በመስራት የራስህን ቢዝነስ ቆም ብለህ ለማሰብ አውለው።

በሌላ አገላለጽ ስራ ስትጀምር ሆነ ለመጀመር ስታስብ ጊዜ ሰጥቶ ማሰብን አትዘንጋ! ጎን ለጎንም ሀብትን ማዳበር ተግባርህ ይሁን። አንድ ቀን ይጠቅምሀል። አንድ ዶላር ባገኘህ ቁጥር ከማውጣት ይልቅ ሌላ ዶላርን የሚያስገኝ ሰራተኛህ እንደሆነ አስብ። ለዛውም እንደሰው ደከመኝ ሰለቸኝ የማይል የ24 ሰዓት ሰራተኛህ እንደሆነ ማሰብን አትዘንጋ። በጣም የሚገርምህ ቀጥረህ የምታሰራው ሰራተኛ በጊዜ ሂደት ሊደክም ሲችል ገንዘብ ግን ከትውልድ ትውልድ





ሊሸጋገር የሚችል ጠንካራ ሰራተኛህ ነው። ተቀጥረህ ስትሰራ ልክ እንደብዙሁኑ ሰርቶ መብላትን መልበስን ዋና ግብህ ማድረግን በመተው ሀብትህን ማዳበር አትተው።

የገንዘብ አቅምህ በጨመረ ቁጥር ውድ ዕቃዎችን የመግዛትና የመታየት ፍላጎትህ ይጨምራል። በሀብታምና በድሆች መካከልም ዋናው ልዩነት ሀብታሞች ውድ ዕቃዎችን የሚገዙት የሀብት መጠናቸው አስተማማኝ ደረጃ ላይ እንደደረሰ ካረጋገጡ በኋላ ሲሆን ድሆችና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ግን የገንዘብ አቅማቸው በጨመረ ጊዜ ወይም እንዳጋጣሚ ሀብት እጃቸው ሲገባ ነው። ሲታዩም ሀብታም ቢመስሉም በዕዳ መዘፈቃቸው ግን አይቀሬ ነው። ብልህና አስተዋይ ሀብታሞች ሀብትን ማበልፀግን በመጀመሪያ ሲያስቀድሙ በእርሱ በሚያገኙት ትርፍም ውድና የቅንጦት ዕቃዎችን ይገዛሉ። ድሀዎችና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች አለማስተዋል የሚጀምረውና የሚጠናቀቀው ውድ ዕቃን ሲገዙ በላባቸው እንደሆነና ልጆቻቸው ማስቀመጥ ከሚገባቸው ቅርስ ላይ መሆኑ ነው።

እንደኔ አመለካከት ውድ ዕቃ ራሱን የቻለ ትርፍ ማስገኛና የዕድገት ምንጭ ሲሆን እንደ ምሳሌም ሪል ስቴትን መጥቀስ ይቻላል። በአንድ ወቀት ዕኔና ባለቤቴ ከራሳችን መኖሪያ ሌላ አፓርትመንት ነበረን። ከአፓርትመንቱም የሚገኘው ገቢ ማደግ በጀመረ ጊዜ ባለቤቴ ብሩን አጠራቅማ ገበያ በመሄድ ለራሷ ማርሴዲስ ገዛች። ያለምንም የጉልበትና ጊዜ መስዋትነት መኪናውን መግዛት የቻለችው ከቤቱ በተገኘ ትርፍ ሲሆን ከቤቱ የሚገኘው ገንዘብ ወጪውን ለመሸፈን የወደለበትን አራት አመት መታገስ ነበረባት። ከዚህ ሂደት መረዳት የምትችለው መርሴደሱ ልክ እንደስጦታ ዕቃ መሆኑን ሲሆን ሀብትን ማዳበር ውድ ዕቃን ከመግዛት መቅደም እንዳለበት ነው። መኪናዋን ከሌሎች መኪናዎችዋ አብልጣ የምትወዳት ሲኾን ገንዘብን በአግባቡ ማስቀደም ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ አስተምሯታል።

ብዙ ሰዎችን ስትመለከት በዕዳ ውስጥ ሆነው ውድና አዲስ መኪናን ሲገዙ ግዜን ሳይወስድ ለጭንቀትና ለአእምሮ ሰላም ማጣት ከመዳረጋቸው በላይ ጊዜው ይርዘምም ይጠር እዳው የውድቀት ምንጭ ይሆንባቸዋል።

ጊዜህን፣ ጉልበትህን እውቀትህንና ሀብትህን በስራ ከለወጥከው፣ በኋላ የራስህን ቢዝነስ ስትመሰርት ተአምራዊ ለውጥን መለማመድ ትጀምራለህ።

ይህም የሀብታሞች የሀብት ሚስጥር ይባላል። ሚስጥሩ ምንድ ነው? ብለህ ብትጠይቅ ሀብትን ለውድ ዕቃዎች ቀድመህ ከማውጣት በሀብቱ ለርተህበት በውጤቱ ውድ እቃን የመግዛት ጥበብ ነው።

# ትምህርት አራት

# የግብር ታሪክ እና የኮርፖሬሽኖች ሚና



## ምዕራፍ አምስት

## አራተኛው ትምህርት

## የግብር ታሪክ እና የኮርፖሬሽኖች ሚና

ድሮ ተማሪ በነበርኩበት ወቅት መምህራችን በጣም አስደናቂ ታሪክ ይነግረን ነበር:: ታሪኩ በአሁኑ ወቀት በፊልም ኢንደስትሪው ታዋቂ አክተር እንደሆነው ኬቨን ኮስትነር ዐይነት ተወዳጅ ሰው ከሀብታሞች ገንዘብ በመዝረፍ ለድሆች ስለሚሰጠው ገፀ ባህሪ ሲሆን፣ የታሪኩ ዋና ተዋንያንም ሮቢን ሁድ ይባል ነበር::

መምህሬ፣ ገፀባህሪውን በማድነቅ እንደ ጀግና ቢያየውም፣ ሀብታሙ አባቴ ግን ከጀግና ይልቅ እንደማይረባ ቀማኛ ወንበዴ ነበር የሚመለከተው::

ሮቢን ሁድ ታሪኩን ለመሳው አለም ትቶ ቢያልፍም፣ እስከአሁን ድረስ ተከታዮቹ በህይወት ይኖራሉ:: ሁሌም ስለሮቢን ሁድ ተናግረው የማይጠግቡትና የማይሰለቻቸው አድናቂዎቹ በርካታ ተከታዮችን አፍርተዋል::

በመሆኑም ሰዎች የሮቢን ሁድን ተግባርና ድርጊትን በማመን፣ ‹‹ለምን ሀብታሞች ከሚያገኙት ትርፍ ብዙ እንዲከፍሉ አይደረግም? ከዚያም ላይ ድሃዎች ገቢ እንዲያገኙ ይደረግ›› ሲሉ ይደመጣል::

ይህ የሮቢን ሁድ አመለካከት በዋነኝነት ከሀብታም ወስዶ ለደሃ የመስጠት ሂደት ቢሆንም፣ ድርጊቱ ድሃዎችም ሆኑም መካከለኛ ገቢ ላላቸው ራሱን የቻለ ችግር ሲፈጥር፣ በተጨማሪ መካከለኛ የገቢ ምንጭ ያላቸው በግብር ክፍያ እንዲጎዱ አድርጎአል:: እዚህ ጋ ያለውን እውነት ስንመለከት ግብርን በአብዛኛው ተጎድተው የሚከፍሉት ሀብታሞች ሳይሆኑ መካከኛ ገቢ ያላቸው እንደሆኑ እንመለከታለን:: በተለይ የተማሩና በሙያቸው የሚሰሩና የተሻለ ገቢና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚያገኙትን ይመለከታል:: ልብ በሉ፣ እነዚህ ናቸው ግብራቸውን በተዘዋዋሪ ለድሃዎች የሚከፍሉት::

ከግብር ጋር በተያያዘ ወላጅ አባቴ የግብር ባለሙያና የተማረ ቢሆንም፣ ሀብታሙ አባቴ ግን ራሱን እንደ ባለሙያ በማስብና ግብርን የተመለከቱ ኦዎችን በሚገባን በኩል ጥርት አድርጎ ውብት እየሰጠው ማስረዳቱን ቀጠለ::

በእንግሊዝና በአሜሪካ ከዚህ ቀደም ቋሚ ግብር እንደሌለና
ሀብታሙ አባቴ፣ በእንግሊዝና በአሜሪካ ከዚህ ቀደም ቋሚ ግብር እንደሌለና ገልጾልኝ ይህም
አልፎ አልፎ ግን በግብር መልክ ገንዘብ ከህዝብ ይሰበሰብ እንደነበር ገልጾልኝ ይህም
በጦርነት ወቅት የሚታይና ንጉሱ ወይም ፕሬዚዳንቱ የገንዘብ መሰብሰብ ደንቡን ለህዝብ
በይፋ ይገልፅ እንደነበር አጫወተን፡፡
ለምሳሌ፣ በእንግሊዝ በዚህ አይነት ሁኔታ ገንዘብ የተሰበሰበው ከ1799 እስከ
1816 ዓ.ም ሲሆን፣ ይህም በናፖሊዮን ጦርነት ዘመን ነበር፡፡ በተመሳሳይ፣ በአሜሪካ
ደግሞ የእርስ በርስ ጦርነት ታሪክ ጋር ሲያያዝ ወቅቱም ከ1861 እስከ 1865 ዓ.ም ድረስ
ነበር፡፡

ከታሪክ እንደምንረዳው፣ አሜሪካዊያን ለገቢ ግብር ተቃውሞ የነበራቸው ሲሆን፣
ለዚህም እንደ አብነት የሚጠቀሰው፣ በእንግሊዞች ቅኝ በተያዘበት ወቅት በሻይ ቅጠል ላይ
የተጫነውን ከፍተኛ ግብርን በፀጋ ያልተቀበሉት ከመሆኑም በላይ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ
በቦስተን ወደብ የተፈጠረው ችግር ጭራሹኑ የጦርነት ሰበብ ሆኖ፣ ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት
እንዲወጡ በር የከፈተ ነበር፡፡ በእንግሊዝና በአሜሪካ የገቢ ግብር ታክስን ሀሳብና አላማን
በህዝብ ውስጥ እንዲሰርፅ በማድረግ ከ50 ዓመታት በላይ ፈጅቷል፡፡
ከዚህ ታሪካዊ ገጠመኝ ተነስተን የግብርን ይዘት ስንመለከት፣ የተለያዩ የግብር
ዓይነቶች የተፈጠሩት በሀብታሙ ማህበረሰብ ላይ በመጫን እና ድሆችና መካከለኛ ገቢ
ያላቸው የህብረተሰብ ክፍልን ለመርዳት በማሰብ ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ
ተጠቃሚ የሚባሉት የህብረተሰብ ክፍሉች፣ ይህንን ችግር ቢረዱት ግን የጉዳዩ ዋና ገፈት
ቀማሽ ከሀብታሙ ይልቅ ተጎጂዎቹ እነሱ መሆናቸውን ሀብታሙ አባቴ ለሁለታችንም
ዘርዝሮ አጫውቶናል፡፡
‹‹መንግስት የግብርን ጥቅም ቀስ በቀስ እያጣጣመ ሲመጣ፣ በግብር ዙሪያ ያለው
ፍላጎት ‹እየጨመረ መጣ›› የሚለው ሀብታሙ አባቴ እኔና ወላጅ አባትህ ግብርን
በተመለከተ ሰፊ ልዩነት ያለን ሲሆን፣ እሱ የመንግስት ቢሮክራት፤ እኔ ደግሞ
ካፒታሊስት ነኝ፡፡ ሁለታችንም ለስራችን ክፍያ ብናገኝም፣ የምናገኝበት መንገድ ግን
ይለያያል ይላል፡፡





ሀቅ ነው! ሀበታሙ አባቴ የሚከፈለው ሀብትን ለማብዛትና የሰው ሃይልንም
የበለጠ በመቅጠር የተሻለ ሀብትን ለማፍራት ሲሆን፣ ገንዘቡን በይበልጥ ስራ ላይ ባዋለና
ሰዎችን በብዛት በቀጠረ ቁጥር ድርጅቱ በሁሉም መንገድ ይስፋፋል፡፡
መንግስት ከሆነ ግን፣ መስሪያ ቤቱ በተለቀና በተደራጀ መልኩ ስራውን
ሲያከናውን፣ ለሰራተኛው የበለጠ ክብርን ያስገኛል፡፡
ሀብታሙ አባቴ ቀጠል አድርጎ፣ ‹‹በሌላ መልኩ በድርጅቴ ውስጥ ለምሳሌ
ጥቂት ሰዎችን በመቅጠርና ዝቅተኛ ወጪ በማውጣት የተሻለ ክብርን አገኛለሁ፡፡ በዚህ
ምክንያት ነው፡፡ የእኔና የመንግስት ሰራተኛው ልዩነት የተፈጠረው፡፡ መንግስት በጠነከረ
ቁጥር ግብርን በተሻለ መልኩ የማግኘት እድሉ እየሰፋ ይመጣል - ይህም ገቢ ለጥንካሬው
መሠረት ይሆናል›› ሲል አስረዳን፡፡
የተማረው ወላጅ አባቴ መንግስት ደሃዎችን መርዳት አለበት ብሉ ፅኑ አቋም
አለው፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ ፕሬዚዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲን ይወደው ነበር፡፡ በተለይ
ለ‹የሰላም ጓዶች› አላማ ያለው አቋምን ይወድለታል፡፡ ይህንንም አቋም ለማሳካት አባትና
እናቴ፣ በፒስ ኮርፕስ የሰላም ኃይል ለመሳተፍ ወደ ታዳጊ አገራት ሲጓዙ፣ ወደማሌዢያ፣
ታይላንድና ፊሊፒንስ ሊጓዙ ችለዋል፡፡
የወላጅ አባቴ የዘወትር ጥረት፣ በሚሰራበት ትምህርት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት
ውስጥ ከቅጥር ጋር የተያያዘ ስለሆነ ለስራው ማስፈፀሚያ፣ የበጀት ጭማሪንና የሰው
ሃይል ቅጥርን ማሳደግ የነበረ ሲሆን፣ ይህንንም ተግባር በተመሳሳይ መልኩ በፒስ
ኮርፕስ ተሳታፊ በነበረበት ወቅት ይፈፅም ነበር - ደምዝ የሚያገኝበት ቋሚ ስራውም
ይኸው ነበር፡፡
ዕድሜዬ አስር አመት ከሆነኝ ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ነገሮች ትኩረት በመስጠት
በውስጤ በጥያቄ መልክ ይገኙቸው ነበር፡፡ አንደኛው ጉዳይ ወላጅ አባቴ ዘወትር
ሀብታሞች የበለጠ ግብር መክፈል የሚገባቸውና ለግብግቦች ናቸው ብሉ የሚናገረውን
ሲሆን፣ ሀብታሙ አባቴ ደግሞ የመንግስት ሰራተኞችን ለነፎችና የመንግስትን ፍላጎት
ማሟላት የማይችሉ ደካሞች ናቸው በማለት ይገልጿቸው ነበር፡፡ ሁለቱም የራሳቸውን
እውነትን ቢናገሩም፣ ማናቸውንም ግን ማመን ይከብዳል፡፡

ይሁን እንጂ የግብር ታሪክን ስናጠና ‹የተለያዩ አመለካከቶችን ማዳበር የሚቻል ቢሆንም ብዙሃኑ የሮቢን ሁድ አመለካከት ስለተመሰጠ የሌሎችም አመለካከት ከዚህ አይለይም።

በሌላ መልኩ፣ ሀብታሞች ሌላ አማራጭን ሲያስተውሉ፣ ልክ እንደ ድሆዎች በሮቢን ሁድ ሃሳብ አይሳቡም። ቀደም ሲል እንደገለፅኩት፣ ሀብታሞች፣ መርከቦችን መሸጥ በጀመሩ በጥቂት ቀናቶች ውስጥ ዕውቀትን ሳተረፉ ኮርፖሬሽኖችና መሰል ተቋማት ያላቸው ግንዛቤ ላቅ ያለ ነው። በዚህም የተነሳ ሀብታሞች በቢዝነስ የስራ ሂደት ያለውን ውጣ ውረድ በመቋቋምና ከውድቀት ራስን ለማዳን ኮርፖሬሽኖችን ፈጥረዋል።

በዚያን ወቀት የተፈጠሩት ኮርፖሬሽኖች የመርከብ ላይ ሰራተኞች በመቅጠር፣ ሰፋፊ ሀብት ሊገኝባቸው ወደሚችሉ አዳዲስ የእስማችን ክፍሎች ሲጓዙ፣ የተሻለ የገበያ አማራጭንና ሀብትን እንዲያዳብሩ ምክንያት ሆናቸው። ልብ በሉ፣ መርከብ ቢበላሽ፣ ወይ ተፈጥሮአዊ አደጋ ቢያጋጥመው - በመርከብ ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ህይወታቸውን የሚያጡ ሲሆን፣ ሀብታም ግን ሊያጣ የሚችለው ፈሰስ ያደረጋትን ጥቂት መዋዕለንዋይ ብቻ ነው።

## ሀብታሞች ሀብትን የማዳበር ሂደትን እንዴት ያንቀሳቅሱታል?

## ታክስ የሚበዛባቸውን ዕቃዎች በማስወገድ ገንዘብን ማዳን




የኮርፖሬሽኖችን ህጋዊ ተዋረድ መረዳትና ማወቅ ለሀብታሞች የተሻለ ግንዛቤን ሲፈጥር ድሆችም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ሁለት አባት ሲኖረኝ አንደኛው ካፒታሊስት ሌላኛው ደግሞ ሶሻሊስት ነው። ለእኔ የገንዘብ ግንዛቤ መዳበር ግን የካፒታሊስቱ ፍልስፍና የሳበኝ ሲሆን የሳሻሊስቱ አመለካከት ግን ከዕውቀት ማነስ የተነሳ እራሱን በገንዘብ ማጣት የቀጣ ይመስላል። ምንም እንኳን የሀብታሞች ገንዘብ ቢነጠቅና





ወከባ ቢበዛባቸውም በአሸናፊነት ሲወጡት ይታየል። ይህም ሂደት ነው በስተመጨረሻ ስሙን ቀይሮ ግብር የተሰኘው። ሀብታሞች ተማርን የሚሉትን በልጠው የሚገኙት ገንዘብ የመጠቀም በቃታቸው የላቀ ስለሆነ ሲሆን ይህንንም ዕውቀት በትምህርት ቤት ማግኘት አይቻልም።

ሀብታሞች ‹ተማርን› ከሚሉት ዕንዴት ይበልጣሉ? ከሀብታም የመውሰድ አካሄድ እንደተጀመረ ግብር መሰብሰብ ሲጀመር በውጤቱም ገንዘብ በጥሬው ለመንግስት መገኘት ጀመረ፡ በዚህ ሂደት ህዝብ ደስተኛ መሆን ሲጀምር ገንዘብን ከሀብታሙና ከሰራተኛው በመውሰድ ለመንግስት ሰራተኛው ለስራ ደሞዝና ለጡረታው ይውል ጀመር። በተዘዋዋሪ ሀብታሞች ገንዘቡን በሚሰሯቸው ስራዎችና ውጤታቸው ሲያገኙ መንግስት የገንዘብ አቅሙ ሀያል ቢሆንም በአጠቃቀም ሂደት ግን በአብዛኛው አስተዳደራዊ ሂደት ክፍተት ስላለው በአግባቡ እንዳይጠቀም ያደርገዋል። መልካም የሆነ የገንዘብ አጠቃቀም ሂደት በሌለበት ሁኔታ መለወጥ አይቻልም። በሌላ አገላለጽ የመንግስት ፖሊሲን የምታስፈጽም ቢሮክራት ከሆንክ ብር እንድታባክን ሲፈልግ ይህንንም ተግባራዊ ካላደረግክ በቀጣዩ በጀት ላይ ተገቢውን በጀት እንዳታገኝ ትደረጋለህ። ከዚህ የከፋው ብቁ እንደሆንክ ዕውቅናን ማጣትህ ሲሆን በሌላ ጎኑ የንግድ ሰዎች ክብርና ታላቅነታቸው የሚታወቀው በብዛት ለስራቸው ማስፈፀሚያ በሚያውሉት ገንዘብ ሲሆን ይህም ብቃት እንዳላቸው ይመሰክራል።

ይህ የመንግስት ገንዘብን መሰብሰብ ሂደት ሲቀጥል ወጪም እንደዚሁ በመብዛቱ መንግስት የግብርን ሂደት «ከሀብታም መቅረጥ» ከሚለው አስተሳሰብ ጎን ለጎን ደሃውንም ሆነ መካከለኛ ገቢ ያለው የማህበረሰብ ክፍል እንዲካተት አደረገ።

ትክክለኛ ካፒታሊስቶች ሀብታቸው እንዴት ከጥፋት እንደሚድን ሲያስቡ ኮርፖሬሽኖችን አቋቋሙ። ኮርፖሬሽኖችም ሀብታሞችን ከጥፋት ሲያድኑ የሚገርመው ብዙ ሰው ኮርፖሬሽን ማለት ምን ማለት እንደሆነ አለመረዳቱ ነው። በቀላሉ ኮርፖሬሽን ማለት ተአምር ማለት ሳይሆን በራሱ ህግና ደንብ የሚመራ ጠበቃ ያለው የፋይሎች ስብስብን ያካተተ በመንግስት ሙሉ ፈቃድ ስር የሚንቀሳቀስ አካል ማለት ነው።

ትልቅ ህንፃ ወይ ፋብሪካ አልያም የህዝብ ስብስብ ሳይሆን በአጭሩ የህግ ፍቃድ ያለው ዶክመንትን የያዘ ማለት ነው። ይህ ነው እንግዲህ የሀብታሞችን ሀብት የሚጠብቀው።

ከወጪም አንፃር በኮርፖሬሽን ስም የሚወጣው የግብር ወጪ ዝቅተኛ ሲሆን ሀብታሙ በግለሰብ ደረጃ ከሚያወጣው የግብር መጠንም ጋር ሲነፃፀር አንሶ ይታያል። በተጨማሪም ቀደም ብዬ እንደገለጽኩልህ የተወሰነ ወጭ በቅድመ ግብር ሂደት ይከፈላል።

ሀብት ያላቸውና የሌላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ጦርነት ለብዙ አመታት የቀጠለ ሲሆን ዋነኛ ምክንያቱም ‹‹ከሀብታም መንጠቅ›› የሚል ነበር። ጦርነቱ በማንኛውም ጊዜ ቦታ ሲቀሰቀስ እንዳይፈፀም ህግ ቢኖርም መቀጠሉ ግን አይቀርም። የሚያሳዝነው ተጎጂዎቹ ጠንካራ ሰራተኛ የሚባሉት ሲሆኑ ሀብታሞች እንዴት ሂደቱን እንደሚቃኙት ከተገነዘቡ እነርሱም መቀጠላቸው አይቀርም። ለዛም ይመስለኛል ወላጆች ልጆቻቸው ወደ ት/ቤት በመሄድ ተምረው የተሻለ ውጤትን ማስመዝገብ በጥሩ ደሞዝ ተቀጥረው እንዲሰሩ የሚፈልጉት። ይህ ግን አስረኛ ከመሆን አያድንም።

በአማካይ አሜሪካኖችን ስናይ በአሁኑ ጊዜ ከ5-6 ወራትን ለመንግስት ይሰራሉ፤ ይህም ግብርን ከመክፈላቸው በፊት ይከናወናል። በኔ አመለካከት ግን ይህ ሂደት ጊዜ ወሳጅ ሲሆን ጠንክረህ በሰራህ ቁጥር በይበልጥ ግብርን ትከፍላለህ፡ ስለዚህ ‹‹ከሀብታም መንጠቅ›› በተዘዋዋሪ የሚጎዳው ደሀውን ነው። ብዙ ጊዜ ህጎች ሀብታሙን ለመቅጣት ቢወጡም ሀብታሙ ግን ሳይጠቃ ይታያል። ምክንያቱም ነገሮችን ለመቀየር ገንዘብ፣ ጊዜና አስፈላጊው ነገር በእጁ አለ።

ሀብታሞች እንደደሀው እጃቸውን አጣምረው የሚወጡ የግብር ህጎችን በይሁንታ ከመቀበል ይልቅ ምርጥ የተባሉ ጠበቆችንና የሂሳብ ባለሙያዎችን በመቅጠር ህጎች እንዲሻሻሉና እንዲቀየሩ ያደርጋሉ። የአሜሪካ ግብር ሕግ ግብርን መቆጠብ ሊያስችል ይህም አካሄድ ሁሉንም ጠቃሚ ቢሆንም ተረድተው የሚጠቀሙበት ግን ሀብታሞቹ ናቸው። ለምሳሌም ያህል ተራ ቁጥር ‹‹103››ን ብንመለከት ማንኛውም በሪል ስቴት ቢዝነስ ውስጥ የተሰማራ ነጋዴ ግብርን አዘግይቶ መክፈል የሚችል ሲኾን ይህም ለባለሀብቱ መልካም አጋጣሚ ፈጥሯል።

ድሆችና መካከኛ ገቢ ያላቸው ግን እንደዚህ አይደሉም። እራሳቸውን ለመንግስት ግብር ተገዢ በማድረግ ደምን እንደመመጠጥ ያህል ግብር ይከፍላሉ። እኔም የሚከፍሉትን ግብር መጠን ስሰማ በጣም ይገርመኛል። ለዚህ ደግሞ ዋና መንስኤው መንግስትን መፍራት ነው። በእርግጥ የመንግስት ግብር አለመክፈል ምን ያህል





እንደሚጎዳ አውቃለሁ። ወላጅ አባቴም ሆነ እንጀራ አባቴ ግብርን አይቃወሙም። ሆኖም ሀብታሙ አባቴ ሳይጎዳው የሚከፍልበትን መንገድ አመቻቸ። ስሙም ኮርፖሬሽን ይባላል። የሀብታሞች የሀብት ሚስጥር ነው ቢባል ውሸት አይሆንም፤ ኮርፖሬሽን።

ከሀብታሙ አባቴ መጀመሪያ የቀመስኩትን ትምህርቴን ታስታውሱ ይሆናል። በዙያ የ9 ዓመት የዕድሜ ጨቅላነት ሀብታሙ አባቴን ለማነጋገር ቢሮውን ደጅ ስጠና እርሱ ግን ከመጤፍ ሳይቆጥረኝ አንድ ቀን እኔም እንደርሱ ሀይል እንዲኖረኝ አንድረዳ ይጥር ነበር። እርሱ ጋር ባሳለፍኩባቸው የውይይትና የትምህርት ጊዜያቶች ዘወትር ሊነግረኝ የሚፈልገው የዕውቀትን ሀያልነት ነበር። ገንዘብ መጣም አልመጣም ዕውቀት ከሌለበት ከልማት ይልቅ ጥፋት ከመውለድም ባለፈ ሰው ሁሉ ይንቅሀል፣ ይገፋሀል አንተ ለሰዎች የምትናገረውም ዋጋ ያጣል።

ለእኔና ለማይክ ‹‹ግብር ሰብሳቢው አለቃ ወይም ተቆጣጣሪ እንዲሆን በፈቀድክለትም ቁጥር ሀብትህን ለመዝረፍ ወደ ኋላ አይልም›› ሲል ይነግረን ነበር ሀብታሙ አባታችን።

በመጀመሪያው ትምህርት በገንዘብ መስራትን ማዳበር እንጂ ልክ እንደ ድሆች ገንዘብን የዕለት ጉርስ መሸፈን ጋር መያያዝ እንደሌለበት ነበር የተማርነው። ይህንንም መገንዘብ ማለት ሀይልን ማዳበር ነበር። ልክ እንደ ድሆቹ ለገንዘብ መስራትን ከተለማመድክ ሀይልህን /ብቃትህን ለሰራተኛህ አስረከብክ ማለት ሲሆን ገንዘቡ ለአንተ ሀብት ማፍሪያ ከሆነህ ግን ሐይልን ተቆጣጥርክ ማለት ነው።

በገንዘብ መስራትንና ሀብትን ማትረፍ ከተለማመድን በሂደቱ ቆጥብነትና ምክንያታዊነት ማዳበር ስንችል ማንም አይገዳደረንም። ምን ማድረግ እንደሚገባን ካወቅን አሸናፊነትን መቀናጀት ቀላል ሲሆንልን ብቁ ባለሙያዎችን ለምሳሌ ጠበቃንና የሂሳብ ባለሙያዎችን በመቅጠር ለግብር የምናወጣውን እንቀንሳለን። ሀብታሙ አባቴ ካለኝ ዘወትር የማልረሳው ‹‹ብቁ ሁን ማንም አይገፋህም! አይንቅህምም›› የሚለው ሲሆን! ዘወትር በአእምሮዬ ያቃጭላል።

ህግን ጠንቅቆ አለማወቅ እንደነጋዴ ወጪው የከፋ ነው። ‹‹ሕጉን ማወቅህን ከተረዳህ ለሚመጣው ነገር ሁሉ ምላሽ ለመስጠት አትቸገርም›› ይህ ዕውቀት እንኳን በካፒታሊስት ስርአት በሮቢን ሁድ አካሄድም ይጠቅምሀል።

የተማረው አባቴ ዘወትር የሚያበረታታኝ የተሻለ ስራ በኮርፖሬቶች መስራትን ሲሆን በስርአቱ ቀስ በቀስ የስራ ድርሻን በማሻሻል ገቢ መጨመር ነው፡፡ እዚህ ጋ ግን አንድ ያልተረዳው ነገር ይህም በወር ክፍያ ተወስኖ መስራት ልክ ለመታሰብ እንደተዘጋጀች ላይም እራስን አሳልፎ መስጠት መኾኑን ነው፡፡

ወላጅ አባቴ የመከረኝን ለሀብታሙ አባቴ ስነግረው ‹‹ለምን በአንዱ የዕድገት መሰላሉን እንድትቆጣጠር አይመክርህም›› ነበር የሚለኝ፡፡

እንደታዳጊ ወጣት ልጅ፣ ሀብታሙ አባቴ ስለኮረፖሬሽን ምስረታ ሲነግረኝ ዝርዝሩ ሊገባኝ ባይችልም ሀሳቡ ግን በቀላሉ የሚሳካ ነው የሚል ዕምነት አልነበረኝም፡፡ ምንም እንኳን ሀሳቡ በደንብ ባይገባኝ የመሆኑን የመሳካትን ነገር ሳስብ ዘወትር ደስታ ይሰማኝ ነበር፣ በዛ በልጅነት እድሜዬ፡፡

ሀብታሙ አባቴን ባልተዋወቅ ኖሮ የወላጅ አባቴን ምክር በመቀበል የርሱን አርአያነት የምከተል እሆን ነበር፡፡ የራሴን ኮርፖሬሽን ፈጥሬ የራሴ የህይወት መስመር የመፍጠር ሀሳብ የመነጨውም ዕርሱን ከመተዋወቁ ጋር ነው፡፡ ዕድሜዬ በ15 ወይ 16 ውስጥ ሳለሁም ወላጅ አባቴን መከተል እንዳቆምኩ ተሰማኝ፡፡ እንዴት እንደሆነ በትክክል ባላውቀውም በዛው ዘመን የክፍል ተማሪዎቼ ከሚከተሉት የትምርት አቀባበል ሂደት በላቀና በተሻለ መልኩ ገንዘብን ማበልፀግ ማሰብ እንጂ እንደ ክፍል ተማሪዎች ትምህርት ላይ ብቻ ሙጭጭ አልልም ነበር፡፡ ይህም ውሳኔ ህይወቴን ቀየረው፡፡

ሀብታሙ አባቴ የመከረኝ ምክር በህይወቴ ውስጥ ትርጉም መስጠት የጀመረው ዕድሜዬ በ20ዎቹ መካከል ላይ እያለ ሲሆን በዚህም ጊዜ ከማሪን ኮርፕስ ወጥቼ ዜሮክስ ነበር የምሰራው፡፡ የሚከፈለኝም የወር ደሞዝ ጥሩ ሲሆን እኔ ግን የደሞዜ መቀበያ ደረሰኜን ስመለከት እበሳጭ ነበር፡፡ ለብስጭቴም ዋናው መንስኤ ደሞዜ ጥሩ ስለነበር የሚቆረጥብኝ ገንዘብ ብዙ ስለነበር ሲሆን በስራዬም ስኬታማነቴ በጨመረ ቁጥር እሰቆቼ ስለ ዕድገትና የደሞዝ ጭማሪ ይነጋገሩ ጀመር፡፡

በርግጥ ደሞዜ የሚጨመረው እኔ በመጓጓት ተግቼ እንድሰራ የሚደረግ ማታለያ ሲሆን ሀብታሙ አባቴ ግን ይህን ስውር ደባቸውን የተረዳ ይመስል ከዕለታት አንድ ቀን ‹‹ለማነው የምትሰራው? ማንንስ ነው ሀብታም እያደረግክ ያለኸው?›› ሲል ጠየቀኝ፡፡





ወቅቱ 1974 ነበር፣ በዜሮክስ ካምፓኒ ቅጥር ስሆን የመጀመሪያ ኮርፖሬሽን ለመክፈትና ስለ ራሴ የንግድ ሥራ የማስብበት ወቅትም ነበር፡፡ በእጄ ላይ ጥቂት ሀብት ስላለኝ እሱን ለማሳደግ አስብ ነበር፡፡ ከሚቆረጥብኝ ውጭ ያለው ደመዜ ሀብታሙ አባቴ በነገረኝ መሠረት ጥቂት የማይባል ጥሪት እንዳጠራቅም ረድቶኛል፡፡ የወላጅ አባቴን ምክር ብሰማ ኖሮ ወደፊት ሊሆን የሚችለውን ስረዳ ምክሩም ዋጋ ያጣ ነበር፡፡

ብዙዎቹ ቀጣሪዎች ሰራተኞቻቸው ከተቀጣሪነት ወጥተው የራሳቸውን የንግድ ስራ እንዲያንቀሳቅሱ መምከር በስራቸው ላይ ጥሩ አስተዋጽኦ የለውም ብለው ስለሚያምኑ አይመክሩም፡፡ ሀብቴን እንዳዳብር የሀብታሙ አባቴ ምክር ጠቅሞኛል፡፡ አሁን ተቀጥሬ ብሰራም ብሩህ የሆነ ተስፋ አለኝ፡፡ ስለሆነም በስራዬ ትጋትን ጥረትን እከዩበት በትጋት ለመስራት ማለዳ ስራዬ ቦታ ስገባ የማገኘውንም ደሞዝ በጥንቃቄና በቁጠባ በመጠቀም በሪል ስቴት ኢንቨስት ለማድረግ ወሰኛለሁ፡፡ ሀዋይ በዕድገት ላይ ስትሆን የመልካም ዕድል መፍጠሪያና የዕድገት ስፈርም ሆናለች፡፡

በዕድገት ጎዳና እንዳለሁ ሳስብ የዜሮክስ ማሽን ሽያጭን አጧጧፍኩት፡፡ በብዛት ስሸጥ የተሻለ ገቢ ባገኝም የዜያት ያህል ግብርም ይቆረጥብኛል፡፡ የግብር መቆረጡ የሚያነጫንጨኝ ቢሆንም አሁን ግን ከተቀጣሪነት ወጥመድ መገላገያ እንደሆነ ማሰብ ጀምሪያለሁ፡፡ ከዚህም አልፎ በትጋት በመስራት አላማዬን እንዳሳካ ረድቶኛል፡፡ በሚገርም ሁኔታ በ1978 ከተዋጣላቸው 5 የሽያጭ ሰራተኞች አንዱ ስሆን በሂደትም በደረጃ የአንደኝነቱን ቦታ ያዝኩ፡፡ ይህ ደግሞ ከተቀጣሪነት ወጥመድ እወጣ ዘንድ የራሱን ሚና ተጫወተ፡፡

ሦስት አመት ባልሞላው ጊዜ ወስጥ በዜሮክስ በተቀጣሪነት ስርቼ ከማገኘው ገቢ ይልቅ ባቋቋምኩት ኮርፖሬሽን የተሻለ ገቢ ማግኘት ጀመርኩ፡፡ የሪል ስቴት የተገኘውም ገቢ ከዚህ በፊት ተቀጥሬ በምሰራበት ወቅት እንደማገኘው ገንዘብ ለስት ጉርስ ከማዋል በቅርስነት መከማቸት ጀመረ፡፡ ስለሆነም ይህ ገንዘብ ሀብትን ማዳበሪያ ሆነኝ፡፡

ለዚህ ሁሉ የአመለካከትና የዕንቅስቃሴ ለውጥ የሀብታሙ አባቴ ምክር ከፍተኛ ሚና ሊኖረው ብዙም ጊዜ ሳይወስድ ካምፓኒዬ ሀብቱ ስለበዛ ለመጀመሪያ ጊዜ የራሴን ቤት ገዛሁ፡፡ ይህም ሲሆን በዜሮክስ አብሮኝ ይሰራ የነበረ ጓደኛዬ ቤቱን ጉርሻ አግኝቼ

እንደገዛሁት ቢያምንም ይህ ግን ዕውነት አይደለም። እውነቱ ያገኘሁትን ጉርሻ ወደራሴ የሪል ስቴት ስራ ተጠቅሜ ባገኘሁት ትርፍ መግዛቴ ነው።

የሀብታም አባቴን ምክርና ትምህርት ተግባራዊ በማድረጌ ከፐንታዊው ምሳሌያዊ አባባል ማለትም ከአዙሪቱ መውጣት ስችል ይህም በመሆኑ በሰጋ ዕድሜዬ ባገኘሁት እውቀት የተሻለ የሀብት መጠንን ማፍራት ችያለሁ።

እኔ ገንዘብን በአግባቡ ለመጠቀም የአእምሮ ክፍልን በእውቀትና በአስተዋይነት መጠቀምን በተግባር ባላውለው ለደረስኩበት የኑሮ ለውጥ እንደማልደርስ ስለተገንዘብኩ ከሰዎች ጋር በንግድ ዙሪያ ስወያይ ይህንኑ እናገር ነበር። ይህ የአእምሮ ክፍል (IQ) አራት የተለያዩ ክፍሎች ሲኖሩት እነርሱም፦

**ቁጥር 1፦** የሂሳብ አያያዝ፣ እኔ ገንዘብን ጠንቅቆ ማወቅ እለዋለሁ። ይህ የአእምሮ ክፍል በአእምሮአችን በስተግራ አቅጣጫ ሲገኝ ጥቅሙም ገንዘብ ያለውን አቅም በመረዳት የንግድ ሥራህ ያለውን ጠንካራና ደካማ ጎን እንድትገንዘብ ያደርግሀል። ልብ በል፣ ገንዘብ በብዛት ሊኖርህ ይችላል። ዕውቀት ከሌለህ ግን ሀብትህን ተጠቅመህ የተሻለና ቁጥር አንድ የንግድ ሰው እንዳትሆን ያደርግሀል።

**ቁጥር 2፦** መዋለ ነዋይን / ገንዘብን ለስራ ማዋል፦ ይህን ሂደት እኔ በገንዘብ ገንዘብን የማፍጠር ዕውቀት ስለው ዋና መገለጫውምእቅድንና የአካሄድ አቅጣጫን ማወቅ የሚያስችል የአእምሮ ቀኝ ክፍልና የፈጠራ አካል ነው።

**ቁጥር 3፦** ገበያን መረዳት፣

ይህ እንግዲህ ሁለት ነገሮችን የመረዳት ዕውቀት ሲሆን አንደኛው ፍላጎት ሌላኛው አቅርቦትን ጠንቅቆ ማወቅ ማለት ነው። በዚህም ሂደት ውስጥ የገበያውን ቴክኒካዊ ወይም ስሜት መሪ አካሄዱን መገንዘብ መቻል አንዱ ቁምነ ገር ሲሆን ሌላኛው መሠረታዊው ወይም ለስራ የማውለውን ገንዘብ የሚያስገኘውን ውጤት መገንዘብና በስራ ላይ ቢውል በእርግጥ ትርፍን ከወቅቱ አንፃር ያዋጣል ብሎ ማሰብን ይሻል።

**ቁጥር 4 -** ህገ ደንብ፣

በማንኛውም የኮርፖሬሽን ህግና አካሄድ የሂሳብ አያያዝ ዕውቀት፣ ገንዘብ ለስራ ማዋልን መገንዘብ፣ ገበያን ከአቅርቦትና ፍላጎት አንፃር ማወቅን ሲፈልግ ከግብር ማዳን አንፃር የኮርፖሬሽንን ጥቅም ተረድቶ ንግዱን በኮርፖሬሽን የሚያካሂድ ሰው ከተቀጣሪና





ከኮርፖሬሽን ነፃ በመሆን ከሚንቀሳቀስ ነጋዴ የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናል። ልዩነቱ የሰፋ መሆኑን ለመገንዘብም በእግር አንድ ስፍራ መሄድን በኮርፖሬሽን እሰመነገድ ስንለው ኮርፖሬሽንን መጠቀም ደግሞ በአየር ላይ በርሮ የተፈለገ ስፍራ እንደመድረስ ያህል ይቆጠራል።

1. የግብር ጥቅሞች፦

በኮርፖሬሽን ታቅፎ መነገድ በግል ከመነገድ ከመስራት በእጅጉ ብዙ ስራዎችን መስራት ሲያስችል ይህም ለምንገዛው ዕቃ ወጭን ከግብር ነፃ እንደማድረግ ይቆጠራል። ይህም ባለሃብቱ ብዙ ገንዘብ ሳይኖረው የንግዱን እንቅስቃሴ እንዲመራ ያስችለዋል።

2. ክክስ ራስን መከላከል

የምንኖረው ተመልካች ማህበረሰብ በበዛበት በመሆኑ እያንዳንዱ ሰው የሌላውን እንቅስቃሴ ያስተውላል። ሀብታሞች ሀብታቸውን በኮርፖሬሽኖችና በመድህን ጥላ ስር ሲያኖሩ ይህም ከብድርና ዕዳ ነፃ ይደረግላቸዋል። ስለሆነም አንድ ግለሰብ ከሀብታሙ ሰው ገንዘብ ለማግኘት ቢከስም ሀብታሙ እራሱን በህግ ጥላ ስር በማድረጉና ከኩትትል ነፃ ይሆን ዘንድ እራሱን እንደተራ ሰው በማድረጉ ሰዎች ትኩረት እንዳይሰጡት ያደርጋል። ሀብታሞች ሁሉ ነገር በእጃቸው ሲኖር እራሳቸውን ግን ምንም እንደሌለው አድርገው ያቀርባሉ። ድሆችና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ግን ሁሉ ነገር የእነርሱ እንዲሆን ቢመኙም ያገኙትን ገንዘብ ግን ተጠቅሞ ከመበልፀግ ይልቅ ለመንግስትና ለሀብታሞች ሲሳይ ያደርጉታል። ይህንንም ከሮቢን ሁድ ታሪክ ሊማሩት ልክ ከሀብታሙ ነጥቆ ለደሀው እንደመስጠት ይቆጠራል።

የዚህ መጽሐፍ አላማ ስለ ኮርፖሬሽን ማስረዳት ባይሆንም ሀብት ኖሮህ ሀብትህን ለማበልፀግ ከፈለግክ ግን ኮርፖሬሽን መመስረት ብዙ ጥቅም አለው።

ኮርፖሬሽኖችን እንዴት መመስረት እንዳለብህ ለመረዳት ደግሞ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ የተፃፉ መጽሐፍት ሲኖሩ ለምሳሌ "think and Grow rich" የተሰኘው መጽሐፍ ምርጥ ከሚባሉት ውስጥ ይጠቀሳል።

ገንዘብን በአግባቡ መጠቀምና መበልፀግ የብዙ ክህሎቶችና ብቃት ውጤት መሠረት ሲሆን ይህም የአራት ቴክኒካዊ ክህሎቶችን መሠረት በማድረግ ብልህነትን ተጠቅመህ በልዩነት መስራትን መረዳት ነው።

እንግዲህ ሀብታም የመሆን ምኞት ካለህ እነዚህን አራት ነገሮች መረዳት ሲገባህ መረዳትህም ገንዘብን በአግባቡ ተጠቅመህ ብልህ እንድትሆን ያደርግሃል።

ማጠቃለያ

| <u>ሀ. ሀብታሞች</u> | <u>ለ. ለኮርፖሬሽኖች ተቀጥረው የሚሰሩ</u> |
|---|---|
| 1. ይከፍላሉ | 1. ይከፈላቸዋል |
| 2. ወጪ በተለያየ ሁኔታ ያወጣሉ | 2. ግብር ይከፍላሉ |
| 3. ግብር ይከፍላሉ | 3. ወጪ ያወጣሉ፡፡ |

ከላይ በቀረበው ንጽጽር ውስጥ ተመሳሳይነት ቢኖርም በ‹‹ሀ›› ስር ያሉት ግብርን የሚከፍሉት ከሁሉም ነገር በኋላ ሲሆን በ‹‹ለ›› ስር ያሉት ግን የፈለጉትን ነገር ሳያደርጉ ክፍያ ይፈፅማሉ፡፡ እናም የኮርፖሬሽን ባለቤት እንድትሆን እንመክርሃለን፡፡





# ትምህርት አምስት

## ገንዘብን የፈጠሩት ሀብታሞች ናቸው

# ምዕራፍ ስድስት

## አምስተኛው ትምህርት

## ገንዘብን የፈጠሩት ሀብታሞች ናቸው

ትናንት ማታ ጽሑፌን ተወት አድርጌ አሌክሳንደር ግረሃም ቤል ስለተሰኘ ወጣት ታሪክ በቴሌቭዥን እየተከታተልኩ ነበር፡፡ ቤል ስልክን ፈልስፎ የፈጠራ መብቱን እንዳስከበረ የምርቱ ፈላጊዎች በእጅጉ በማደጉ ጭንቀት ላይ ወድቆ ነበር፡፡ እናም የተሻለ አቅም ያለው ድርጅት ለማቋቋም በወቅቱ ኃያል ወደነበረው ዌስተርን ዩኒየን ሄዶ የፈጠራ መብቱንና ትንሽዬ ድርጅቱን እንዲገዙት ጠየቃቸው፡፡ የዌስተርን ዩኒየን ፕሬዝዳንት ዋጋው በጣም ተወደደ በሚል ሰቆበት በእምቢታ አሰናበተው፡፡ አጠቃላይ የጠየቀው ገንዘብ 100 ሺ ዶላር ነበር፡፡ ቀሪው ታሪክ ነው፡፡ ኤቲ ኤንድ ቲ የተሰኘ የባለ ብዙ ቢሊየን ዶላር ኩባንያ ተቋቋመ፡፡

ከአሌክሳንደር ግረሃም ቤል ታሪክ በኋላ የምሽቱ ዜና ቀጠለ፡፡ ዜናው ውስጥ የአንድ ትልቅ ድርጅት ሰራተኛ ቅነሳ ታሪክ ነበረበት፡፡ ሰራተኞቹ በጣም ተናደው ስለኩባንያው ባለቤትነት ሚዛናዊ አይደለም የሚል ቅሬታ ያቀርባሉ፡፡ ከስራ የለቀቀ የ45 ዓመት ጎልማሳ ሚስቱና ሁለት ልጆቹ ፋብሪካው ውስጥ በመኾናቸው በድጋሚ እንዲቀበሉት ለመጠየቅ ጥበቃዎቹን በመጠየቅ ላይ ነበረ፡፡ ገና ቤት መግዛቱ ስለነበር እንዳያጣው ሰግቷል፡፡ ካሜራው ሰውዬው ሲለማመጥ ለዓለም እያስተላለፈ ነበር፡፡ የእኔንም ትኩረት ሰቦት ነበር፡፡

ከ1984 ጀምሮ በሙያዬ ሳስተምር ቆይቻለሁ፡፡ ትልቅ ልምድ የቀሰምኩበት ቢኾንም የሚረብሽ ሙያም ነው፡፡ ምክንያቱም በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ሳስተምር እኔን ጨምሮ ሁላችንም ላይ አንድ ዓይነት ነገር ተመልክቻለሁ፡፡ ሁላችንም ተዝቆ የማያልቅ አቅምና የየራሳችን ተሰጥኦዎች አሉን፡፡ እንዲያም ኾኖ ወደፊት እንዳንራመድ የሚያግደን ራሳችንን መጠራጠራችን ነው፡፡ ወደኋላ የሚጎትተን ክህሎት ማጣት ሳይኾን በራስ አለመተማመን ነው፡፡ የተወሰኑት ደግሞ በዚህ ችግር ከሌሎቹም ይበልጥ የተተበተቡ ናቸው፡፡





አንዴ ከትምህርት ቤት ከወጣን በኋላ አብዛኞቻችን ወሳኙ ነገር የኮሌጅ ዲግሪ ወይም ጥሩ ውጤት አለመኾኑን እንገነዘባለን፡፡ በእውነተኛው ዓለም ከትምህርቱ ዓለም በተቃራኒው ከጥሩ ውጤት የዘለለ ነገር ያስፈልጋል፡፡ ይህንኑ ነገር ሰዎች "ፅናት"፣ "ጉብዝና"፣ "ድፍረት"፣ "ጀግንነት" ወዘተ በሚል ሲጠሩት ሰምቻለሁ፡፡ ስሙ ምንም ይሁን ምን ይህ ነገር የሰዎችን የወደፊት ሕይወት ከትምህርት ቤት ውጤት በበለጠ መልኩ ይወስናል፡፡

በእያንዳንዳችን ውስጥ ያ ደፋር፣ አይበገሬና ጎበዝ ሰብዕና አለ፡፡ የዚህ ተቃራኒ ሰብዕናም እንዲሁ፡፡ አስፈላጊ ሲኾን ተንበርክኮ መለማመጥ፡፡ በባህር ኃይል ፓይለትነት ለአንድ ዓመት ቬትናም ውስጥ ከቆሁ በኋላ ሁለቱንም ሰብዕናዎች በውስጤ አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ሁለቱ አይበላለጡም፡፡

እንደ አስተማሪ የደረስኩበት ሃቅ የሰውን ልጅ ጉብዝና ከሚነጥቁ ነገሮች መካከል ከሚገባው በላይ የኾነ ፍርሃትና ራስን መጠራጠር ዋንኞቹ መኾናቸውን ነው፡፡ ተማሪዎች መልሱን እያወቁት መልሱን የመናገር ድፍረት ሲያጡ ማየት ልቤን ያደማው ነበር፡፡ በገሃዱ ዓለምም ወደፊት የሚሄደው ጎበዙ ሳይኾን ደፋሩ ነው፡፡

በእኔ ተሞክሮ የፋይናንስ ይዞታህ ሙያዊ ዕውቀትም ድፍረትም ይጠይቅሃል፡፡ ጠንካራ ፍርሃት ሲኖር ዕውቀትህ ይደፈጠጣል፡፡ በማስተምርበት ወቅት ተማሪዎቼን የምነግራቸው አደጋን እንዲጋፈጡና ዕውቀታቸው ፍርሃታቸውን ወደ ኃይል መቀየር እንዲችል ነው፡፡ ለተወሰኑት ሲሰራ ሌሎችን ደግሞ ያስደነግጣቸዋል፡፡ የገባኝ ነገር ገንዘብን በተመለከተ ብዙዎቹ ጨዋታውን ማካሄድ የሚፈልጉት ያለምንም የኪሳራ አደጋ ነው፡፡ ምክንያቱም የሚከተሉት ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ቀርበውልኛል፡- "ለምንድነው ስጋትን የምጋፈጠው?"፣ "ለምንድነው ገንዘብን የምጋፈጠው?"፣ "የፋይናንስ ዕውቀቴን ለማሳደግ የምጨነቀው ለምንድነው? እስመልክቶ አዋቂ መኾን ያለብኝ ለምንድነው?"

የእኔ ምላሽ "ብዙ አማራጮች እንዲኖራችሁ" የሚል ነው፡፡

ወደፊቱ ታላላቅ ለውጦች ይመጣሉ፡፡ ስጀምር እንዳወራሁለት አሌክሳንደር ግረሃም ቤል ዓይነት በርካቶች ወደፊት ይመጣሉ፡፡ ቢል ጌትስን የመሰሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ይፈጠራሉ፤ ማይክሮሶፍትን መሳይ ድርጅቶች በየዓመቱ በመላው ዓለም ብቅ ይላሉ፡፡ ደግሞም ብዙ ኪሳራዎችና የሰራተኛ ቅነሳዎች ይኖራሉ፡፡

ታዲያ የፋይናንስ ዕውቀትህን ማሳደግ ያለብህ ለምንድነው? ይህን ጥያቄ ከአንተ በስተቀር ሊመልሰው የሚችል ሰው አይኖርም:: ይሁንና እኔ ለምን እንዳደረግሁት ልነግርህ እችላለሁ:: ምክንያቱም አሁን ያለንበት ለመኖር የሚያጓጓ ጊዜ ነው:: ለውጥን ከምረግም ለውጥን ብቀበል ይሻለኛል:: የደመወዝ ጭማሪ ባለማግኘቴ ከምበሳጭ ሚሊየኖችን ስለ መሥራት ባልም ይሻለኛል:: አሁን የምንገኝበት ጊዜ የለውጥ ጊዜ ነው:: አሮጌው ተቀብሮ አዲሱ የሚወለድበት በአስደናቂ ድብልቅልቅ ክስተቶች የተሞላ::

ታዲያ ስለ ገንዘብ ያለህን ዕውቀት ማሳደግ የሚገባህ ለምንድነው? ምክንያቱም እንደዚህ ካደረግህ በእጅጉ ትበለፅጋለህ:: ያለበለዚያ ግን ጊዜው በጣም አስፈሪ ነው::

ከ300 ዓመታት በፊት መሬት ሀብት ነበር:: እናም መሬት ያለው ሀብት ነበረው:: ቀጥሎ ፋብሪካዎች ሲመጡ አሜሪካ የበላይ ኾነች:: ሀብቱን የሚቆጣጠረው ባለሀብቱ ነበር:: ዛሬ ግን የመረጃ ጊዜ ነው:: በጣም ወቅታዊ መረጃ ያለው ሰው ነው ሀብቱን የሚቆጣጠረው:: ችግሩ መረጃ በብርሃን ፍጥነት ነው ዓለምን የሚያዳርሰው:: አዲሱ ሀብት እንደ መሬትና ፋብሪካዎች በድንበር ወይም በአጥር ተከልሉ ሊያዝ አይችልም:: ለውጡ ፈጣንና ተለዋዋጭ እየኾነ ነው የሚሄደው:: የአዳዲስ ሚሊየነሮች ቁጥር ከፍ ይላል:: በድህነት ወደኋላ የሚቀሩ ሰዎች ቁጥርም እንደዚያው::

ዛሬ ከድሮው ሀሳብ ጋር በመጣበቃቸው ብቻ በርካታ ጠንካራ ሰራተኞች በድህነት ሲንገላቱ እያለሁ:: ነገሮች እንደነበሩ እንዲቀጥሉ ይፈልጋሉ:: ለውጥን ይጠሉታል:: ሥራቸውንና ቤታቸውን ሲያጡ ኢኮኖሚውን፣ ቴክኖሎጂን ወይም አለቃቸውን የሚኮንኑ ሰዎች አውቃለሁ:: ችግሩ የራሳቸው ሊኾን እንደሚችል ለመገንዘብ አይሞክሩም:: ትልቁ ዕዳቸው አሮጌ ሀሳቦች ናቸው::

በአንድ ከሰዐት በኋላ ስለንግድ ካሸፍሉው የተሰኘውን ጨዋታ ተጠቅሜ በማስተማር ላይ ነበርኩ:: ጓደኛዬ ስልጠናውን እንድትከታተል አንዲት ሴት ይዛ መጥታለች::: የጓደኛዬ ጓደኛ በቅርቡ ትዳሯን የፈታ በመኾኗ ለአእምሮዋ ማሳረፊያ በርካታ መልሶች በመፈለግ ላይ ያለች ናት:: ጓደኛዋ ምናልባት ይህ ስልጠና ሊጠቅማት ይችላል ብላ አስባለች::

ጨዋታው ሰዎች ስለገንዘብ አሰራር እንዲገነዘቡ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው:: በጨዋታው ውስጥ በገቢ ሪፖርትና በባላንስ ሺቱ መካከል ያለውን ቁርኝት ይማራሉ::





ሀብትን በማዳበርም ሆነ በብልፅግና ጎዳና ውስጥ ራስን በማግኘት፣ ወርሃዊ ገቢን ከቋሚ ሃብት ጋር እንዲጨምር ማድረግ የሚገባ ሲሆን፣ በወር ውስጥ ለተለያዩ ነገሮች የሚወጣው ገንዘብ ከገቢ ጋር ሲነፃፀር፣ ገቢው ሊበልጠው ይገባል:: ይህም በሚሆንበት ጊዜ ለዕለት ተዕለት ጉርስ ከማሰብ ይልቅ እራስን ማውጣት ማስቻሉ ብቻ ሳይሆን፣ ለዕድገትና ሀብትን ለማካበት ወደሚያስችል መስመር በፍጥነት ለመግባት ያስችላል:: በፊት እንደገለጽኩላችሁ፣ ሰዎች የተለያየ አመለካከት ስላላቸው፣ አንዳንዶቹ በዚህ አይነት ስልት ማደግን የሚቀበሉ ባይሆኑም፣ ጥቂቶች ግን ይወዱታል:: የተቀሩት ደግሞ ይህን ሳይረዱ ይቀራሉ:: ይህች ሴትዮ ያገኘችውን መልካም ዕድል ሳትረዳው ስለቀረች መማር አልቻለችም:: ገና በጅማሬዋ ገቢዋን እና ወጪዋን በማስተካከል የሚያስችልና የሚያስረዳ ሂሳባዊ ቀመርን በጀልባው ውስጥ አሰረች:: ከዚያም በኋላ የደስታ ስሜት ስለተሰማት ‹‹አ|ጀልባ አገኘሁ›› አለች:: ጓደኞችዋም ስለሂሳባዊ ቀመሩ ሲያስረድዋት የሂሳብ ቀመሩን ባለመቻልዋ፣ ደስታው ወደ ጭንቀት ተቀየረ:: ስለ ገንዘብ አጠቃቀም፣ ገቢን እና ወጪንም ስለማመጣጠን ጓደኛዋ ማስረዳትዋን ስትቀጥል፣ ጠረጴዛዋ በዕሑፍና ወረቀቶች ተመልቶ ነበር:: ከዚያ በድንገት የቁጥሮችን መስራት አቅም ስትገነዘብ፣ ጀልባዋ እርሷን በቁምዋ እየበላት እንደነበር ተረዳች:: በጨዋታው ማብቂያ ሰዓት ላይ ልጅ እንደነበራትና አካሄድዋም መልካም እንዳልነበር ተረዳች::

የትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ካበቃ በኋላ፣ ጓደኛዋ ወደ እኔ በመምጣት በጉዳዩ እንደተናደደች ከነገረችኝ በኋላ፣ ወደዚህ ትምህርት ቤት የመጣችውም ገንዘብን ሥራ ላይ በማዋል፣ እንዴት ሃብትን ማዳበር እንደሚቻል ለመማር ቢሆንም፣ የትምህርቱን አካሄድ ባለመውደድዋ በጨዋታው ውስጥ ያለውን ቁም ነገር እንደተራ ጨዋታ ቆጠረችው - በሁኔታውም አለመደሰቷን ገለፀች::

ጓደኛዋ፣ በጨዋታው ውስጥ ራስዋን እንድትመለከትና ጨዋታውም እንደመስታወት የራስዋን መልክ ሊያሳያት መቻሉን ስትጠይቃት፣ በምላሽዋ ግን ሃሳብዋን ከመቀበል ይልቅ እንደዚህ አይነት ጨዋታ ዋጋ የሌለውና ህይወትዋን እንደማይቀይር በማመን፣ የከፈለችው ክፍያ እንዲመለስላት ጠየቀች::

ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የማይሰራበትን ዘዴ በመጠቀም በት/ቤት ውስጥ በርካታ መምህራን በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብን አግኝቼያለሁ::

የሚያስተምሩት ‹ሌክቸር› በመስጠት ነው። እንደ ተማሪ ሆኜ ሳየው ‹ሌክቸር›
አልወድም፣ ምክንያቱም በትምህርት አሰጣጥ ወቅት መሰላቸት የሚፈጥርብኝ ከመሆኑም
በላይ፣ አዕምሮዬ ትምህርቱን ከመረዳት ይልቅ ሌላ ነገር ማሰብን ይመርጣል።
በ1984 ዓ.ም የተለያዩ የጨዋታና ተዛማጅ ነገሮችን በመጠቀም ማስተማር ስጀምር፣
አዋቂ ሰዎችን በጨዋታው አማካኝነት ራሳቸውን እንዲመለከቱና ከሚያውቁት ጋር
እንዲያያይዙት አበረታታ ነበር። ይህንን ደግሞ እንደ ትምህርት ይወስዱት ዘንድ
ማስረዳቴን ቀጠልኩ። የጨዋታው ቀዳሚ ጥቅም፣ የሰውን ባህሪ ማሳየት መቻሉ ሲሆን፣
አስተማሪነታቸው ደግሞ መምህሩ ከሚያስረዳው በላይ የላቀ ነው። ከት/ቤት በተሻለ
ሁኔታ አንድን ሰው እንደ መስተዋት ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ።
በስተመጨረሻ ከክፍል የወጣችው ሴት ጓደኛ ደውላልኝ፣ ጓደኛዋ በአሁኑ ጊዜ
አመለካከትዋ እንደተሻሻለና እየተረጋጋች እንደሆነ ነገረችኝ። እም|እየተረጋጋችና ይህንንም
እየለመደች ስትመጣ፣ በጨዋታውና በህይወትዋ መካከል ያለውን መመሳሰል ወይም
ግንኙነት በመጠኑም ቢሆን መረዳት ጀምራለች።
ምንም እንኳን እርስዋና ባለቤትዋ የራሳቸው የሆነ ጀልባ ባይኖራቸውም፣ በሚገርም
መልኩ የብዙ ነገሮች ባለቤቶች ነበሩ። ይሁን እንጂ ባለቤትዋ ሀብቱን ከአንዲት ወጣት
ሴት ጋር ማንቀሳቀስ መጀመሩን ስታውቅ፣ በ20 ዓመት የትዳር ህይወታቸው ውስጥ
የተሻለ ሀብትን ማፍራት ያልቻሉት ለዚህ እንደሆነ ሲገባት፣ በንዴት ትዳርዋ በፍቺ
ተደመደመ። ከዚያም ቀስ በቀስ ጉዳዩን ውስጥዋ ያብሰለሥለው ጀመር፣ በፍቺው ማግስት
ሊከፋፈሉት የሚችሉት ሀብት ያለመኖሩ ጉዳይ ለሰሚ የማይታመን ነበር።
ገቢና ወጪን በተመለከተ፣ ቁጥሮችን ተጠቅማ መደመር፣ መቀነስ... ስትጀምር በድንገት
የመበሳጨት ስሜት ውስጥ ገባች። የብስጭቷ ዋናው ምክንያት፣ ከዚህ ቀደም ያለማወቋ
ችግር ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በፊት የነበራት አመለካከት ገንዘብን ማንቀሳቀስ፣
ማሰራትና ሀብትን ማዳበር የወንዶች ብቻ ስራ፣ የመኖሪያ ቤቱን ሥራና ቤተሰብን
መንከባከብ የሴቶች/የእሷ/ ኃላፊነት እንደሆነ ማመንዋ ነበር።
እርግጠኛ መሆን ባትችልም፣ ትዳራቸው ከመፍረሱ አምስት አመት ጀምሮ፣ ባለቤትዋ
ከእርስዋ ገንዘብ ሊደብቅ ይችላል በማለት ትጠረጥረው የነበር ቢሆንም ገንዘቡን የት





እንደሚያጠፋና ስለውሽማው ምንም አይነት መረጃን ያለማወቋ የዘወትር የብስጭቷ
መንስኤ ነበር።
በመጫወቻ ሰሌዳ ላይ እንደሚገኘው ልምድ፣ አለምም በራስዋ ህይወትን በተመለከተ
የራስዋን ግብረመልስ በፍጥነት ታቀርብልናለች። እኛም ከተመራመርን እና ባስተዋልን
ቁጥር ትምህርቱን ይበልጥ እናገኘዋለን። የገንዘብ ፍሰትን የሚያስረዳው ጨዋታ
መጀመሪያውኑ ተቀርጾ የተዘጋጀው ሁሉም ሰው ራሱን እንደ መስታወት
እንዲመለከትበት ተደርጎ ሲሆን፣ አላማውም በህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ምርጫን
ያስቀምጣል። በጨዋታው ደልባ ያለበትን ካርድ በገፋህ ቁጥር ወደ ዕዳ ያስገባሃል።
ጥያቄው ‹‹አሁን ምን ማድረግ ትችላለህ?›› ምን ያህል ገንዘብን የመጠቀም አማራጮች
አለህ?›› በሚል የጨዋታው አላማ ተጨዋቾች የአመለካከት አድማሳቸውን በማስፋት
በአማራጭነት የተለያዩ የገንዘብ አጠቃቀም ዘዴዎችን እንዲያዳብሩ ነው።
ይህን ጨዋታ ከ1 ሺህ ሰዎች ላይ ሲጫወቱ የተመለከትኩ ሲሆን፣ ከማነቀው
የሚወጡትም ስለቁጥር ቶሎ የሚገባቸውና በተሻለ ሁኔታ ሰፋ አድርገው መመልከት
የሚችሉ ሰዎች ናቸው። ገንዘብን በተለያየ መልኩ መጠቀም መቻላቸው ደግሞ ልዩ
ያደርጋቸዋል። ጨዋታውን ለመረዳት ብዙ ጊዜ የሚወስድባቸው ሰዎች ስለ ቁጥር ብዙም
የማያገናዘቡ ሲሆን/ መዋዕለ ነዋይን አፍስሶ ሀብትን ማዳበርንም አይረዱትም። ሀብታም
ሰዎች ገንዘብን በመጠቀም የፈጠራ ስራዎችን መስራት ቢችሉ ቀደም ብለውም ከከስረት
ለመዳን ጥንቃቄ ያደርጋሉ።
የንዘብ ፍሰት ጨዋታን ሲጫወቱ፣ ብዙ ገንዘብ የሚያገኙ ሰዎች ቢኖሩም፣ የገንዘብ
አያያዝን ባለማየታቸው፣ በገንዘብ መጠቀም የማይችሉ ሰዎች አሉ። ከዚያም ወደ
እውነተኛው አለም የሀብት ማዳበር ሂደት ውስጥ ቢገቡም፣ ስኬታማ የመሆናቸው ነገር
ውጤት ያጣል። በውጤቱም ገንዘብ ቢኖራቸውም በሌሎች ግን ሲበለጡ ይታያል።
ገንዘብ መጠቀምን በተመለከተ ምርጫዎችን መግፋት ከኋላ ቀርነት ጋር የሚመደብ ነው።
ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጀምሮ ጓደኛዬ የሆነ ሰው፣ በአሁኑ ጊዜ በሶስት የተለያዩ ቦታዎች
ሥራዎችን ይሰራል። ይህ ጓደኛዬ ከ20 ዓመት በፊት፣ በከፍላችን ውስጥ ከሚገኙ
ተማሪዎች ይበልጥ እጅግ ሀብታም የነበረ ሲሆን፣ የአካባቢው የስኳር እርሻ ሲዘጋ
የሚሰራበት ኩባንያም ከሰረ።

ጓደኛዬ በቂ ሀብት እንዳለው ቢያስብም ገንዘቡን በተመለከተ ግን ሰፋ ያለና በአማራጭ የተሞላ የመጠቀም ክህሎት ያልነበረውና በተቃራኒው በአርጌ አመለካከት የተተበተበ ነበር። ሀብትን ለማዳበር ጠንክሮ መሥራትን ብቻ እንደመፍትሄ የሚወስድ ሀሳብን ብቻ የሚከተል በመሆኑ፣ የችግሩም መሠረት ይኸው ነበር። ስለዚህም ይሰራበት የነበረው ኩባንያ የእርሱን የስራ ልምድና ብቃት የሚጠይቅ ቦታ ሲያገኝለት ባለመቻሉና ከሚፈለገው ሙያ በላይ (over qualified) የያዘ በመሆኑ፣ አሁን ለሚሰራበት ሥራ አነስተኛ ደሞዝ ይከፈለዋል። በአሁኑ ሰዓትም የተሻለና በቂ ገንዘብ ለማግኘት ሰስት የተለያዩ ሥራዎችን ይሰራል።

ከገንዘብ ፍሰት ጋር ተያያዥነት ያለውን ጨዋታ በሚጫወቱ ሰዎች መካከል ትክክለኛዋ ለአሸናፊነት ምክንያት የሆነችው ካርድ እነርሱ ጋ እንደማትደርስ አማርረው የሚናገሩ ሰዎች አጋጥመውኛል። ስለሆነም በገሃዱ አለም ተፈላጊውን ጥረት ወደ ጎን አድርገው ቁጭ ብለው መልካም አጋጣሚን ሲጠብቁ ይታያሉ።

ሌሎች ደግሞ በእጃቸው የገባውን የዕድል ካርድ ከቁብም ሳይቆጥሩት፣ ገንዘብ የለኝም ስለሆነም መስራት አልችልም ሲሉ ይስተዋላል። በውጤቱም ኮማንቀው ለመውጣት ብቸኛው መፍትሄ ገንዘብ ማግኘት ብቻ ነው ይላሉ። ልክ እንደ ጨዋታው መልካም አጋጣሚ ኖሯቸው በገንዘብ ማጣት የተነሳ ገንዘብ የሚያገኙበትን ጊዜ በተስፋ በመጠበቅ እጅና እግራቸውን አጣምረው ሲቀመጡ ይታያሉ።

ሌሎች ደግሞ መልካም ገጠመኝን የሚያሳይ ካርድ ኖሯቸው እርሱንም ጮክ ብለው እያነበቡት ቢናገሩም፣ በእጃቸው ስለገባው መልካም አጋጣሚ ያላቸው ግንዛቤ ምንም ነው። እነዚህ ሰዎች ገንዘብም ሆነ መልካም ጊዜ አላቸው። የዕድል ካርዱም በእጃቸው ገብቶ መልካም ገጠመኙን አይረዱትም። ስለዚህም ከወጥመዱ ነፃ ሊሆኑ አይችሉም።

እነዚህኞቹ ደግሞ ከሌሎቹ በቁጥር ይበዛሉ። በአብዛኛው እነዚህ ሰዎች ሁሉም ነገር ተመቻችቶላቸው መጠቀም ግን አይችሉም። ምን አልባትም ሌሎች ከእነሱ በኋላ ተንቀሳቅሰው ሀብታም ከሆኑ በኋላ ያማርራሉ።

ሀብትን የማዳበር ብልህነት አማራጮችን የማየት ብቃት ሲሆን፣ አማራጮች ወደ አንድ ሳይመጡ ሲቀሩ፣ ምን ማድረግ እንዳለብህ ቆም ብለህ ማሰብን ያካትታል። ዕድል ወደ አንተ ከመጣና ገንዘብ ግን ከሌለህ አበዳሪ ባንክም ካላገኘህ፣ ዕድል እንዴት ወደ አንተ



መጥታ መጠቀም እንደምትችል ማሰብ አለብህ። አካሄድህ የሚያዋጣ ካልሆነ ሀብትን ማዳበርም ሆነ መበልፀግ አትችልም። ይህም አምስት ሳንቲምን ወደ ሚሊዮን የመቀየር ያህል ከባድ ነው።

ገንዘብን የማበልፀግ ሂደት አስተዋይነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ ገንዘብ በብዛት የመኖር ወይም ያለመኖር ጉዳይ ሳይሆን፣ ቁልፉ አማራጮችን በተለያዩ ሁኔታ አሰባስቦ በመጠቀም በእጅህ ላይ ያለን ማንኛውም ነገር ወደ ገንዘብ ለመቀየር የሚያስችል ብቃትን መላበስ ላይ ነው።

ይህም ሲሆን በሀብት ማበልፀግ ሂደት ውስጥ ያሉብህን ችግሮች ለመፍታት ትችላለህ። ለዚህም ዋናውና ተጠቃሹ ገንዘብ የራስህን ዕድል ከመልካም አጋጣሚ ጋር እንድታቀናጅ ያደርግሃል። ጥቂቶች ብቻ ናቸው ዕድል እንደ መና ከላይ የማይወርድ እንደሆነ የሚገነዘቡት። በእንፃሩ ዕድል በራሳቸው ሊፈጠር የሚችልና በእጃቸው ላይ ያለን ማንኛውም ነገር በመጠቀም ለውጤታማነት ምክንያት እንደሆነ ይረዱታል። ሀብትን እንደሀብትነት ስናነሳም መሠረታዊው ነገር፣ ጠንክሮ መስራት ቢሆንም፣ የአጠቃቀም ብልሃትን ማወቅ ወሳኝ ነው።

ትክክለኛና መልካም አማራጭን ቁጭ ብለው የሚጠብቁ ሰዎች ለማደግና ለመለወጥ ብዙ ጊዜ ሊወስድባቸው፣ ልክ እንደ ትራፊክ መብራት ውሳኔን በራሳቸው ሳይሆን የሚወስኑት፣ ከሁኔታዎች መፈጠርና ከነውን ጋር በመያያዝ ተስፋ ማድረግ ሲጀምሩና ይህም አካሄድ ጥገኛ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

ለእኔና ማይክ በተደጋጋሚ ሀብታሙ አባቴ ይነግረን የነበረው፣ «ገንዘብ ማለት በራሱና ብቻውን ተዐምር ፈጣሪ እንዳልሆነ ነው። እንደነዚህ አይነት አመለካከት፣ በሂደት ገንዘብን ተጠቅም ሀብትን ለማዳበር መንስዔ ሊሆነን እንደሚችል ይነግረን ነበር።

ድሆዎችና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ገንዘብን ለዕለት ጉርሳቸው ውጪ መሸፈኛ ብቻ እንደሚያደርጉት ካሳሰበን በኋላ፣ ቀጠል አድርጎ «ሃብታሞች ግን ሀብትን በማበልፀግና በገንዘቡም ወደ ከፍተኛ የሀብት ደረጃ ባለቤትነት ለመሸጋገር ነው። ይሁን እንጂ ገንዘብ ብቻውን የሀብት መሠረት እንደሆነ አድርጎ ማሰብ ውጤት አልባ ነው» ብሎናል።

ሀብታሙ አባቴ ‹‹ገንዘብን ብቻውን ማካበት ትርጉም እንደማይሰጥና ይህም ለዕድገት መሠረት እንደሆነ ማሰብ ስታቋሙ፣ ሀብታም በመሆንና ለማደግ ብዙም ጊዜ አይወስድባችሁም›› ብሎ አሳስቦን ነበር።

በወቅቱ ‹‹ምን እያለ ይሆን?›› ስንል እኔና ማይክ ራሳችንን ጠይቀናል። ከዚያም ገንዘብ ማለት ምን ማለት እንደሆነና እና ‹‹ለብቻ መስራት ይቻላል ወይ?›› በማለት ጠየቅነው። በምን አይነት ስምምነት ከሰዎች ጋር መስማማት እንችላለን የሚለው ጥያቄ ብዙ ሀብታሞች የሚጠይቁት መኾኑን ጠቁሞን የሰው ልጅ በዋነኝነት ያለው ትልቁ ሃብቱ፣ አዕምሮው ሲሆን፣ ገንዘብ ሳይኖረውም፣ አዕምሮውን ተጠቅሞ ሀብት ማዳበር እንደሚችል አስረዳን።

ሀብት ከ300 ዓመት በፊትና ከዚያም ጀምሮ በነገስታቶች ዘንድ ጭምር እንደ ተዓምር የሚቆጠር ነበር። በተጨማሪ የሰለጠነ አዕምሮ የሌለውም ሰው ከመጠን ያለፈና ማብቂያ የሌለው ድህነትን ለቤተሰቦቹ ማስተማር ይችላል።

ባለንበት የመረጃ ዘመን ገንዘብ በብዛት እየጨመረ ሲሆን፣ በጣም ጥቂት ሰዎችን ከምንም ተነስተው በማይታመን ሁኔታ ሊያካብቱት ይችላሉ። ለዚህም ዋናው ነጥብ አዕምሮን ተጠቅሞ የፈጠራ ክህሎትን በማዳበር ሀሳብ አመንጭቶ ወደ ተግባር በመግባት ላይ የተመረኮዘ ነው። በንግድ ዓለም ውስጥ ያሉ ሰዎችን ሀብት እንዴት ሊበለፅግ እንደሚችል ብትጠይቁ፣ በሚሊዮን የሚቆጠር ሀብትን ከባዶ በመነሳት ማካበት እንደሚቻል ይነግሯችኋል። ይህም ትልቁን ሚና የሚጫወተው አዕምሮን በአግባቡና በሚገባ መጠቀም ብቻ እንደሆነ ያሳስበናል።

ገንዘብ በራሱ ከሀገር ሀገር እንደ ሰው መንቀሳቀስ ባይችልም፣ ስምምነት ከተፈጠረ ግን በደላሎች አማካኝነት ሀብትን ማዳበር ይቻላል። ልብ በሉ፣ ሐሳብ ማመንጨትና ስምምነቶች የሀብት ማዳበሪያ ዋነኛ መንገዶች ናቸው።

ስለዚህ የገንዘብ አቅምን ማዳበር ለምን አስፈለገ? ይህን መመለስ ይቻል ይሆናል፣ ሆኖም መጀመሪያ በምን ብልህነትን እንዳዳበርኩ ልንገራችሁ። ለዚህም ዋናው ምክንያቱ ሀብትን በፍጥነት ማካበት እንድችል ነው።

ይህን እንድሆን ያስቻለኝ ስለ ገንዘብ ያለኝ ግንዛቤ ሲሆን፣ በፈጣኑ የሀብት ማበልፀግ ‹መንገድ› ውስጥ በፍጥነትና በታላቅነት በመጫወት ጭምር ነው።





በዚህ ዘመን ሀብት የሚገኝባቸው ሥራዎች የሚፈልጉት የአካል ብቃትን ሳይሆን የአዕምሮን የመሥራት አቅም ነው። እርግጥ ነው የአካል ብቃት ሊያስፈልግ ይችላል ነገር ግን አካልን የሚያዘው አዕምሮ እንደሆነ ተገንዘቡ። ለዚህም ነው ያለኝን ቋሚ ሀብት ማለትም አዕምሮዬን ተጠቅሜ ከፍተኛ ገንዘብን ወደ ስራ በመቀየር ከደፋሮች ጋር በመሆን ወደ ኋላ የሚያፈገፍጉትን ፈሪዎች በመተው፣ ለለውጥ ተንቀሳቅሼ በውጤቱም ሀብትን ለማካበት የቻልኩት።

ገንዘብን ስለማካበት አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ። በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ የፎኒክስ የገንዘብ አቅም በጣም አስጊ ነበር። ወደ ከስረት የሚያመራ አካሄድ ወስጥ የተዘፈቀ ነበር ማለት ይቻላል። አንድ ቀን ‹‹Good morning America›› የተሰኘውን ፕሮግራም በቴሌቪዥን ስመለከት ገንዘብን ከማካበትና ከማጣት ጋር እያይዞ የሙያው ተንታኝ እየተናገረ ነበር።

እርሱም ‹‹ገንዘብ ቆጥቡ›› ካለ በኋላ ‹‹በወር 100 ዶላር ብታስቀምጡ ከ40 ዓመት በኋላ ሚሊየነር ትሆናላችሁ›› አለ።

ተመልከቱ፣ በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ ማስቀመጥ መልካም ነው። አንዱም አማራጭ ሊሆን ይችላል። ችግሩ ግን ገንዘቡን የሚቆጥበው ግለሰብ፣ ገንዘብ ማስቀመጡን እንጂ በአገሩና በአለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄደውን የገንዘብ ልውውጥ የመውጣትና የመውረድ ሁኔታን ሳያገናዝብ በየወሩ በማስቀመጥ ብቻ ነው ለዕድገቱ ተስፋ የሚያደርገው።

በፊት እንደገለፅኩት ዘመኑ በአክሱሃማ ግሽበት የታጀበ ነበር። ከኢንቨስተሮች ፍፅም ጥንቃቄ የተሞላበት እንቅስቃሴ ይጠበቃል። የእኔም ገንዘብ በተለያዩ ሥራዎች ላይ ውሉ ስለነበር በጥሬው እጄ ላይ የቀረ ነገር አልነበረም። ገንዘቤን ከመሰብሰብ ይልቅ በስራ ላይ ስለማውለውና የተለያዩ ቁሶችን ስለምገዛበት ምንም ቀሪ ገንዘብ በእጄ ላይ አልነበረኝም። ከባለቤቴ ጋርም በገበያው ውስጥ ከአንድ ሚሊዮን ዶላር በላይ በጥሬ ሊንቀሳቀስ የሚችል ገንዘብ ስለነበር ነው ቁሶችን ልንገዛበት የቻልነው። ይህም ለእኛ ዕድገት መልካም አማራጭ ፈጠረልን። ምንም እንኳ የኢኮኖሚ ግሽበቱ አገር አቀፋዊ ችግሮች ቢኖሩትም

ምንም የተስፋ ጭላንጭል ማሳለፍ ስላልነበረብኝ ወደ ተግባር ገባሁ። በአንድ ወቅት 100 ሺህ ዶላር ያወጡ የነበሩ ቤቶች 75 ሺህ ዶላር ሲገቡ፣ ከአካባቢው ለሚገኝ ሪል ስቴት ከመግዛት ይልቅ ገንዘብ ያለአግባብ ከሚያጠፉ ሰዎች መግዛት

ጀመርኩ:: በዚህ አካባቢ 75 ሺህ ቤቶችን እንዳንዳቸውን በ20 ሺህ ዶላር ወይ ከዚያም ባነሰ መግዛት ይቻል ነበር::

ከጓደኛዬ በ90 ቀናት ውስጥ የሚመለስ ሁለት ሽህ ዶላር ወስጄ ከራሴም 200 ዶላር ጨምሬ፣ እነዚህን የ75 ሺህ ዶላር ቤቶች፣ በ60 ሺህ ዶላር መግዛት እንደሚቻል ማስተዋወቁን ቀጠልኩ:: ብዙም ሳይቆይ ስልኮች ማንቃጨል ጀመሩ:: ከነዚህም ውስጥ ለመግዛት ፍቃደኛ የሆኑትን መርጬ ንብረቱ ወደ እኔ ስም ከተዘዋዋረ በኋላ ቤቶቹን ማሳየት ጀመርኩ:: በጣም የሚገርም ነበር:: ለሽያጭ የቀረቡት ቤቶች በደቂቃዎች ውስጥ ተሸጠው ሲያልቁ፣ ለስራ ማስኬጃ የጠየቅኋቸውን 2 ሺህ 500 ዶላር የሰጡኝም በደስታ ነበር:: እኔም ጉዳዩ ለሚመለከተው ኩባንያ ከፍዬ፣ ከጓደኛዬ ጋር ባለን ስምምነት መሠረት ካበደረኝ 2 ሺህ ዶላር ተጨማሪ 200 ዶላር አክዬበት መለስኩለት:: በዚህ ሁኔታ የቤቶቹ ገገርም ሆነ ሻጭ፣ እንዲሁም እኔና ጓደኛዬ ደስተኞች ነበርን:: ልብ በሉ፣ በ20 ሺህ ዶላር ገዝቼ በሦስት እጥፍ 60 ሺህ ዶላር ስሸጠው፣ 40 ሺህ ዶላር ባለኝ ሀብት ላይ ጨምሬያለሁ:: የወሰደውም ሰዓት በአጠቃላይ አምስት ሰዓት ብቻ ነበር:: ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ገንዘብን እንዴት ማካበት እንደሚቻልና የቁጥሮችን አስገራሚ የመጨምርና የመስራት ሀይል ተረድቻለሁ:: ይህም የሆነበትን ሂደትና ምሳሌያዊ ሂደት ቀለል ባለ መልኩ አስረዳችኋለሁ::

40 ሺህ ዶላር በሀብትነት ሲፈጠር ይህም ገንዘብ ያለ ግብር ክፍያ የተገኘ ነው::

| |
|---|
| ገቢ |
| ወጪ<br>ግብር |

| | |
|---|---|
| ቋሚ ሀብት<br>(40,000) | ብድር<br>20,000ዶላር |

ይህን የገበያ አስገራሚ ሂደት፣ እኔና ባለቤቴ በትርፍ ጊዜያችን መስራት ስንቀጥል፣ የሀብታችን ብዛትም በቋሚ ንብረትና በስቶክ መልኩ እየጨመረ ነበር:: 190 ሺህ ዶላር ሊሆን የሚችል ብር ከ10 ፐርሰንት ወለድ ጋር በነዚያ ስድስት የግዢ፣ የፈጠራ፣ የሽያጭና የገንዘብ እንቅስቃሴዎች ማግኘት ቻልን፣ ይህም በግምት 19 ሺህ





ዶላር በዓመት ገቢን እንደማግኘት ይቆጠራል:: ገንዘቡም በዚህም ወደ ግል ሀብታችን ውስጥ እንዲካተት አድርገናል:: ስለሆነም በገንዘቡ፣ መኪናዎችን፣ ነዳጅ፣ የጉዞ ወኪልን፣ ኢንሹራንስ፣ ከደንበኞቻችን የዕለት ግብዣን እና የመሳሰሉትን በዓመት እንድገሸፍን አስችሎናል:: መንግስትም በዚህን ወቅት ተጨማሪ ግብር ለመሰብሰብ የቻለ ሲሆን፣ የግብር ክፍያችንንም በቅድሚያ በመክፈል ተጠቃሚ አድርገነዋል::

እስኪ 190 ሺህ ዶላር ለመቆጠብ ምን ያክል ጊዜ እንደሚወስድ ራስህን ጠይቅ:: ባንክ 10 በመቶ ወለድ ይከፍልሃል? እንደኔ እንደኔ ግን የትኛውም ባንክ ያን ያህል ገንዘብ በወለድ ይከፍለኛል ብዬ አላስብም:: ከዚህ በተጨማሪ ለመንግስት ግብርም መክፈል አለብኝ::

ድንገት ሰውየው ባይከፍለኝስ ብለው የሚጠይቁ ሰዎች ያጋጥሙኛል:: እርግጥ ነው ያጋጥማል:: ይህም መልካም ዜና ነው:: ከ1994-1997 ድረስ በፊኒክስ የሪል ስቴት ገበያ የደራበት ወቅት ነበር:: ሌላ 2 ሺህ 500 ዶላር ደግሞ ዝውውር ማስፈፀሚያ ክፍያ ነበር:: ልምድ በሌለው ገገር ዘንድ ይሄ ግብይት ምንም ትርፍ የሌለው ሊመስል ይችላል:: ይህ ሂደትም መቀጠሉ አይቀርም:: ስለዚህ ፈጣን ከሆንክ፣ መጀመሪያ ቤቱን ስሸጥ ያገን ሁለት ሺህ ዶላር መልሼ ከፈልኩ:: በመሰረቱ ከሆን በዚህ ግብይት ወቅት እጅ ላይ የሚገባ ገንዘብ አልነበረም:: በመዋዕለ ንዋይ ምልሰት (Return on infinity) የማገኘው ጥቅም ግን የትየለሌ ነበር:: ይህ ያለ ገንዘብ ገንዘብ የማግኛ ምርጥ ምሳሌ ነው::

በሁለተኛው ግብይት ሁለት ሺህ ዶላር ኪሴ ሲገባና ብድሩንም ለ30 ዓመታት ላራዝም እችላለሁ:: ታዲያ ገንዘብ ለማግኘት ገንዘብ የማወጣ ከሆነ የመዋዕለ ንዋይ ምልስቴ ምን ሊሆን ይችላል? አላውቅም፤ ግን በእርግጠኝነት በየወሩ 100 ዶላር ወለድ ለ40 ዓመታት እንዲሁም አምስት በመቶ ግብር ይኖረዋል:: ይሄ ብልህነት አይደለም:: ምናልባት የጥንቃቄ ውጤት ሊሆን ይችላል፤ ግን ብልሀት አይደለም::

ዛሬ ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት 1997 ዓ.ም የገበያው ሁኔታ ከአምስት ዓመት በፊት ከነበረው በፍፁም የተለየ ነው:: ያኔ 60 ሺህ ዶላር ይሸጡ የነበሩት ቤቶች ዛሬ 110 ሺህ ደላር ደርሷል ዋጋቸው፡ ዛሬም ቤትን በማስያዥነት ተጠቅመው የሚካሄዱ ግብይቶች አሉ ግን ዋጋቸው ጣራ ነክቷል:: ገበያው ተለውጧል:: አሁን ወደፊት ተንቀሳቅሶ የተሻለ ጥቅምን ለማስከበር የሚተጋበት ጊዜ ነው::

‹‹ይሄን ያህል መስራት አትችልም››፣ ‹‹ይሽ ህገ-ወጥ ነው››፣ ‹‹እየዋሸህ ነው›› የሚሉ አስተያየቶችን ‹‹እንዴት እንደሚቻል ታሳየኛለህ?›› ከሚለው ጥያቄ የበለጠ ብዙ ሰምቼአለሁ::

ቀላል ሂሳብ ነው:: አልጀብራና ካልኩለስ ማወቅ አይጠበቅብህም:: በወረቀት ልውውጥ የሚካሄዱትን ሥራዎች ውክልና በሰጠኹት ኤጀንሲ በኩል አስፈፅማለሁ:: ቤቱን በማደስም ጊዜና ገንዘቤን አላባክንም:: ይሄ የቤቶቹ ጣጣ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ተዋውለው ከገቡ በኋላ ገንዘቡን ከፍለው ሳይጨርሱ የሚወጡ ያጋጥማሉ:: ይሄ ደግሞ የፍ/ቤት ጣጣ ነው:: ገንዘቤን ከማስመለሴ በተጨማሪ ቤቱን ለሌሎች በድጋሚ አሸጠዋለሁ:

ምናልባት በእናንተ አካባቢ ይሄ የገበያ ሁኔታ የለም ይሆናል:: ነገር ግን የዚህ ምሳሌ ዋና ዓላማው ጥቃቅን የገንዘብ ዝውውሮች አደጋንና ኪሳራን በሚቀንስ መልኩ ሚሊዮን ዶላሮችን መፍጠር እንደሚቻል ለማሳየት ነው::

ቢሆንም ግን ብዙ ሰዎች ይህንን የብልሆች ምክር አይሰሙም:: ይልቁንስ በልማዳዊው ‹‹ጠንክሮ በመስራት ገንዘብ መቆጠብ›› መርህ መኖርን ይመርጣሉ::

30 ሰዓታትን ብቻ በሚፈጅ ሥራ ከ190 ሺህ ደላር የሚልቅ የገንዘብ መጠን በጥሬት መልክ ማግኘት ይቻላል:: ለዚህ ደግሞ ምንም ዓይነት ግብር አይከፈልም::

ጠንክሮና በከፍተኛ ድካም ሰርተው ካገኙት ላይ 50 በመቶ ግብር መክፈል፤ ከዚያ የተረፈችውን መቆጠብ ከተቆጠበው ላይ ደግሞ አምስት በመቶ በድጋሚ ግብር መክፈል?

ወይስ

የገንዘብ ክህሎትህን (ገንዘብ የማግኘት ጥበብ) በማዳበር የአዕምሮ ብቃትህን ተጠቅመህ ከፍተኛ ገንዘብ ከማግኘትህም በላይ ጊዜህን መቆጠብ? (በነገራችን ላይ ጊዜ እጅግ የከበረ ኃብት ነው)

የመጀመሪያው ጥያቄ ለአንተ ተስማሚ ከሆነ ወላጆች ‹‹ልጄ በትምህርቱ ጎበዝ ነው::›› ብለው ሲያወሩልኝ ለምን በዝምታ ራሴን እንደምነቀንቅ አሁን ልትረዳ ይገባል:: በትምህርት ጎበዝ መሆን ጥሩ ሊሆን ይችላል:: ግን በቂ አይደለም::

የመጀመሪያው የኢንቨስትመንት ስትራቴጂ ትንሽ መሆኑ ይገባኛል:: ግን ዋናው ዓላማው ከትንሽ ተነስቶ ወደ ትልቅ እንዴት መኬድ እንደሚቻል ያሳያል:: እንዲሁም





የእኔ ስኬት በጠንካራ የፋይናንስ ትምህርት ላይ መሰረት ያደረገን ጠንካራ የገንዘብ መሰረት ጥቅምን ያሳያል::

ቀደም ብዬ የገለፅኩት ቢሆንም የገንዘብ ብልሀት ከአራት ክህሎቶች ይገነባል::

1. በገንዘብ ዕውቀት - ቁጥሮችን ማንበብ መቻል
2. የኢንቨስትመንት ስትራቴጂ - በገንዘብ ገንዘብ የመሥራት ሳይንስ
3. የገበያው - አቅርቦትና ፍላጎት::
4. ሕጉ የሂሳብ አያያዝ፣ የኮርፖሬት፣ የክልሎችና የሐገሪቱ ሕጎጋትን ማወቅ:: እኔ የምመክረው ሁሌም ቢሆን በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ መስራትን ነው::

የእነዚህ አራቱ ቅንጅት ነው ትናንሽ ቤቶችን ገዝቶ በመሸጥም ሆነ፣ በአክሲዮንና ቦንዶችን አሊያም የከበሩ ማዕድናትን በመግዛት ባለፀጋ ለመሆን የሚያስችለው::

በ1994 የሪል ስቴት ገበያ እንደገና እያገለሰራ ነበር:: የአክሲዮን ገበያውም ጦፏል:: የአሜሪካ ኢኮኖሚም ይበልጥ ጠንክሯል:: የሽያጭ ስራዬን የጀመርኩት በ1996 ሊሆን፣ ወደ ፔሩ፣ ኖርዌይ፣ ማሌዥያና ፊሊፒንስ ተደጋጋሚ ጉዞዎች አድርጌያለሁ:: አሁን ኢንቨስትመንቱ ተለውጧል:: ግዢው እስኪደራ ድረስ ከሪል ስቴት ገበያው ወጥተናል::

የቤት ግዥና ሽያጭ ውስጥ ተመልሼ ለመግባት በቅድመ ሁኔታነት የምጠብቀው ለኮንግረስ የቀረበ አንድ ሕግ መፅደቅ አለመፅደቁን ነው:: እነዚያን ትንንሽ ቤቶች ከሸጥኩኝ በኋላ ተጣርቶ የሚተርፈኝን 40 ሺህ ዶላር መስመር እንዲያሲዘው የሂሳብ ባለሙያዬን መጥራት ያስፈልገኛል:: እዚህ ጋር ግልፅ ማድረግ የምፈልገው ነገብ ገበያ ሊደራም ሊቀዘቅዝም ይችላል፤ ኢኮኖሚም ሊያድግና ሊወድቅ ይችላል:: ዓለም ግን የማናስተውላቸውን ዕድሎች በየቀኑ እንኩ እንደምትለን ነው:: ዓለም በየጊዜው በተለዋወጠች ቁጥር ዕድላችንም እየሰፋ ነው የሚሄደው::

ታዲያ የገንዘብ ብልሀትህን ለማሳደግ ምንድን ነው ችግርህ? ለዚህ ምላሽ ያለው አንተ ጋር ብቻ ነው:: ለማወቅና ለማደግ ትምህርት ለምን እንደቀጠልኩ አውቃለሁ:: ይህን የማደርገው ለውጥ እየመጣ መሆኑን ስለምገነዘብ ነው:: ስለዚህ ድሮ ላይ ተንጠልጥዬ ከመቆም ለውጥን በፀጋ እቀበላለሁ ማለት ነው:: በገበያ ውስጥ መለዋወጥ

እንደሚኖር በደንብ ተረድቼአለሁ። ስለዚህ የገንዘብ ብልሀቴን በየጊዜው አዳብራለሁ። ገበያ በወደቀ ቁጥር ወደ ችግር የሚገቡ እንዳሉ ሁሉ በዚህ ወቅት ሕይወት የምታበረክትላቸውን ዕድል በአግባቡ የሚጠቀሙ አሉ። ይህ ነው የገንዘብ ብልሀት ማለት።

ብዙ ጊዜ ህይወት ያበረከተችልኝን ዕድል በአግባቡ ተጠቅሜ እጅግ ትርፋማ ስለሆንኩባቸው ጉዳዮች እጠየቃለሁ። በዕውነቱ ከሆነ ስለግል ኢንቨስትመንቶቼ እየጠቀስኩ ብዙ ምሳሌ መስጠቱ አይመቸኝም። ጉረኛ የሆንኩ ይመስለኛል። ምሳሌዎችን የምጠቅሰው ነገሮች ቀላል እንደሆኑ ለማሳየት ነው። አራቱን የገንዘብ ብልሀት ምሰሶዎች ጠንቅቆ ላወቀ ሁሉ ነገር ይቀልለታል።

ሐብታም ለመሆን ሁለት ነገሮችን ተጠቅሜአለሁ፤ሪልስቴትና አነስተኛ አክሲዮኖችን። እኔ ያደረግኩትን ሌሎች የግዴታ እንዲደግሙት አልመክርም። በምሳሌነት ከጠቀሙ ይበቃል። ያገኘሁት የቢዝነስ አጋጣሚ እጅግ ውስብስብ ከሆነና ምንም አልገባ ካለኝ ወደ ውል ውስጥ አልገባም። በገንዘብ ረገድ ብልጥ ለመሆን መሠረታዊ የሂሳብ ዕውቀትና የተፈጥሮ ማስተዋል በቂ ናቸው።

**የራስን ተሞክሮዎች በምሳሌነት ለማቅረብ አምስት ምክንያቶች**

1. ሰዎች የበለጠ እንዲማሩ ለማነሳሳት
2. መሠረቱ ጠንካራ ከሆነ ሌላው ቀላል መሆኑን ለሰዎች ለማሳወቅ
3. ማንኛውም ሰው ታላቅ ባለፀጋ መሆን እንደሚቻል ለማሳየት
4. ግብን ለማሳካት ሚሊዮን መንገዶች እንዳሉ ለማመላከት
5. ሐብት ለማግኘት ያን ያህል የተራራቀ ሳይንስ እንደማይፈልግ ለማሳየት

በ1989 ፖርት ላንድ ውስጥ በአንድ መንደር አቅራቢያ ጠዋት ጠዋት እሮጥ ነበር። በአካባቢው ባሉ ቤቶች ላይ ሁሉ ‹‹የሚሸጥ›› የሚል ምልክት ተለጥፎ ይስተዋላል። ወደ አንዱ ቤት ጎራ አልኩና ባለቤቱን ‹‹ስንት ትሸጠዋለህ?›› አልኩት።

‹‹ከአንድ ዓመት በላይ ለመሸጥ ብፈልግም ማንም መጥቶ ያነጋገረኝ የለም›› አለኝ። ትንሽ ካወራን በኋላ መጀመሪያ ካስቀመጠልኝ ዋጋ በ20 ሺህ ዶላር ቀንሼ ገዛሁት። ቤቱ አራፍና ሁለት መኝታ ክፍል ያለው ነበር። ማንም ሊገዛው የማይፈልገውን





ቤት በ45 ሺህ ዶላር ገዛሁት። ይህንን ቤት ትንሽ ቆይቼ ከካሊፎርኒያ ለመጡ ጥንዶች በ95 ሺህ ዶላር ነው የሸጥኩት።

በወር ውስጥ አንድ አፓርታማ አገኘሁ። ባለቤቶቹ የጀመሩን ነዋሪ የሆኑና የቤታቸውን ትክክለኛ ዋጋ ያልተገነዘቡና ትልቁ ፍላጎታቸው ቤቱን ለቆ መውጣት ብቻ ነበር። 450 ሺህ ዶላር የሚያወጣ ቤት 275 ሺህ አቀረብኩላቸው ተደራድረን በ300 ሺህ ዶላር ገዛኋቸው። ይህን ቤት ከሁለት ዓመት በኋላ በ495 ሺህ ዶላር ሸጥኩት።

ከዚያ ወደ ፊኒክስ ሄጄ አንድ ቤት ገዛሁኝ። በወቅቱ በፊኒክስም የሪል ስቴት ገበያው እጅግ ተዳክሞ ነበር። ይሄኛው የአፓርታማ ቤት ትልቅ ሲሆን ዋጋውም ጥሩ ነበር። ቀስ በቀስ የሪል ስቴት ዋጋ በድጋሚ ሲያንሰራራ በ875 ሺ ዶላር የገዛነውን ቤት በ1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶላር ለመግዛት አንድ ኢንቨስተር ዋጋ አቀረበ።

ሆኖም ይህን ቤት ከመሸጣችን በፊት ኮንግረሱ ያንን ሕግ ያፀድቅ እንደሆነ መጠበቅ እንዳለብን ወስነን ለጊዜው አቆየነው። ሕጉ ከፀደቀ የቤቱ ዋጋ ከ15-20 በመቶ ሊጨምር ይችላል። የዚህ ምሳሌ ዓላማ ትናንሽ ገንዘቦችን እንዴት ሚሊዮን እንደሚሆኑ ማሳየት ነው። አሁንም ዋናው ጉዳይ የገንዘብ ውሉችን መረዳት፤ የኢንቨስትመንት ስትራቴጂዎችን መንደፍና ሕግን ማወቅ ነው።

ሰዎች እነዚህን ጉዳዮች ካላወቁ በተለመደው አካሄድ እጅግ ሲበዛ እየተጠነቀቁ በጣም እርግጠኞች በሆኑበት ጉዳይ ላይ ብቻ ኢንቨስት ቢያደርጉ ነው የሚሻለው። ችግሩ ግን እንዲያ ያሉት ‹‹በጣም እርግጠኛ›› የሚሆንባቸው ኢንቨስትመንቶች አዋጭነታቸውና የሚያስገኙት ጥቅም እጅግ አነስተኛ መሆኑ ነው።

የምር አሪፍ የሆኑ ንግዶች ገና ምንም ሳልገባቸውና እጅግ ፈሪ ለሆኑ ሰዎች አይገባቸውም። ሐብታሞች ባላቸው ላይ እየጨመሩ የበለጠ እየከበሩ የሚሄዱት የጨዋታውን ሕግ በደንብ ስለሚገነዘቡ ነው።

የበለጠ በተራቀቅኩኝ ቁጥር ዕድሎች የበለጠ ወደ እኔ ይመጣሉ። የገንዘብ ብልሀትህን ለማበልፀግ በርካታ ዕድሎች አሉልህ። የፋይናንስ ኢንተለጀንስህ /የገንዘብ ብልሀትህ/ በዳበረ ቁጥር የምትገባበት ውል አዋጪ እንደሆነና እንዳልሆነ መናገር ትችላለህ። ከጊዜ ወደ ጊዜ የሐብት መጠኔ የሚጨምረው ዓመታት ባለፉ ቁጥር ልምዴ እየካበተ በመሄዱ ነው።

የገንዘብ ብልሀታቸውን አጎልብተውና አጋጣሚዎችን በአግባቡ ተጠቅመው ሀብታሞች በመሆን ፋንታ እዚያው በያዙት አንድ ሙያ ላይ ሙጭጭ ብለው ቀን ተሌት የሚደክሙ ጓደኞች አሉኝ። የእኔ ፍልስፍና ደግሞ ከእነሱ ይለያል። ከትንሽ ነው የምጀምረው። ዘር ከተዘራ የተወሰነው ያድጋል የተወሰነው ይጠፋል። በሪል ስቴት ኮርፖሬሽኔ ውስጥ በበርካታ ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ንብረት አለኝ።

እያልኩኝ ያለሁት እነዚህ ሚሊዮን ዶላሮች ሲጀመሩ አምስት ሺህ ዶላር ነበሩ ነው። እኔና ባለቤቴ ልክ እንደኛው ደፋርና የጨዋታው መርህ በገባቸው ኢንቨስተሮች የተካተቱበት ኮርፖሬሽን ውስጥ ያለን ሲሆን፣ ሊያከስሩ የሚችሉና ዋጋቸው የሚዋዥቅ እና መንግስት ሊወርሳቸው ከጫፍ የደረሱ ድርጅቶችን አሜሪካና ካናዳ ውስጥ በጨረታ እንገዛለን።

በፍጥነት እንዴት ማትረፍ እንደሚቻል የሚያሳይ ምሳሌ ልንገራችሁ። ወደ መንግስት ንብረትነት ሊዘዋዋር የነበረን ድርጅት 100 ሺህ አክሲዮን አንድ አክሲዮን በ25 ሳንቲም ዋጋ እንገዛለን። ከስድስት ወራት በኋላ የአንዱ አክሲዮን ዋጋ ሁለት ዶላር መድረሱ አይቀርም። ድርጅቱ በአግባቡ ከተያዘ ዋጋው ጨምሮ የአንዱ አክሲዮን ዋጋ 20 ዶላር ሊደርስም ይችላል። 25 ሺህ ዶላር አውጥተን ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሚሊየን ዶላር የደረሰባቸው በርካታ ጊዜያት አሉ።

የምትሰራውን ካወቅክ ቁማር አይሆንብህም። ሥራውን ሳታውቀው ገንዘብህን ከወረወርክ በኋላ ፀሎትና ምኸላ ከጀመርክ ነው ቁማር የሚሆንብህ። እርግጥ ነው ሁሉም ነገሮች እልጋ ባልጋ አይሆኑም። ለችግሮች መፍትሔው የገንዘብ ብልሀት ነው። ስለዚህ የአንዱ ጨለማ ለሌላው ብርሐን ሊሆን ይችላል። ለዚህ ነው ሰዎች አክሲዮን ከመግዛታቸው በፊት ስለገንዘብ ማግኛ ዘዴዎችና የአጠባበቅ ብልሀቶችን መማር እንደሚገባቸው የምመክራቸው። ብልህ ስትሆን ነው ችግሮችን ማለፍ የምትችለው።

እኔ የምሳተፍባቸው ብዙዎቹ ሥራዎች ለሌሎች ሰዎች እጅግ አደገኛና የማይመከሩ ይመስላሉ። ነገር ግን ኹኔታውን በፅሞና ከመረመርክና እንዲህ ያሉት ኢንቨስትመንቶች ለምን አስፈሪ መስለው እንደሚታዩ ከተረዳህ 25 ሺህ ዶላርን በአጭር ጊዜ ወስጥ ወደ አንድ ሚሊዮን ዶላር እንዴት መለወጥ እንደሚቻል ይገባሀል፣ የሕይወትህ አቅጣጫም የዚያኔ ይቀየራል።





ታላላቅ ዕድሉችን ዐይኖች አያዩም። እነዚህን ዕድሎች የሚያስተውላቸው። ብዙ ሰዎች ደህይተው የቀሩት በእጃቸው ላይ ያሉትን ዕድሎች ለመጠቀም የሚያስችል ስልጠና ባለመውሰዳቸው ነው።

ሰዎች አዘውትረው ‹‹እንዴት ነው መጀመር የምችለው?›› ሲሉ ይጠይቁኛል። በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ የገንዘብ ነፃነቴን እንዳውጅ የረዱኝን አስር ደረጃዎች ዘርዝሬአለሁ። ነገር ግን ሁሌም መጨናነቅን ከአንተ ዘንድ ማስወገድ እንዳለብህ አትዘንጋ።

በጨዋታው ልታሸንፍም ልትሸነፍም ትችላለህ። ስለዚህ ዘና በል። ብዙ ሰዎች አሸናፊ የማይሆኑት ሽንፈትን ስለሚፈሩ ነው። ለዚህ ነው አሁን ያለውን የትምህርት ሥርዓት ቀሽም ሆኖ ያገኘኹት። በት/ቤት ስህተት መጥፎ እንደሆነና ቅጣት እንደሚስከትል ነው የተማርነው። ነገር ግን ሰዎች የተፈጠርነው ከስህተታችን እንድንማር ነው። መራመድ የምንችለው እየወደቅን እየተነሳን ነው። ካልወደቅን መራመድ አንችልም። አሸናፊዎች ሽንፈትን አይፈሩም። ከሽንፈት የሚሸሹ እነሱ ከስኬት የሚሸሹ ናቸው።

እኔ ገንዘብን ልክ እንደቴኒስ ጨዋታ ነው የምቆጥረው። በጣም እጫወታለሁ፣ ስህተት እፈፅማለሁ፤ ከዚያ እስተካክላለሁ … የተሻልኩ እሆናለሁ።

**ሁለት ዓይነት ኢንቨስተሮች አሉ**

1. የመጀመሪያው የተለመዱት ናቸው። ለምሳሌ ሪል ስቴትና የአክሲዮን ድርሻ ገዝተው እያተረፉ የሚሸጡት ናቸው።
2. ሁለተኛዎቹ ደግሞ ኢንቨስትመንት የሚፈጥሩ ኢንቨስተሮች ናቸው። እነዚህ ኢንቨስተሮች ሰከን ያሉና ጨዋታው በደንብ የገባቸው ናቸው። እንዲህ ዓይነቶቹን ኢንቨስተሮች እንድሆን ነው ሐብታሙ አባቴ ያበረታታኝ የነበረው። እርግጥ ነው ኢንቨስትመንትን ፈጥሮ ኢንቨስተር መሆን ይከብዳል።

ሁለተኛውን ዓይነት ኢንቨስተር መሆን ከፈለግክ ሶስት መሠረታዊ ክህሎቶች ያስፈልጉሀል። እነዚህ ክህሎቶች ለገንዘብ ብልሀት ከሚረዱህ ተጨማሪ ናቸው።

ABS
@Amharicbookstore
ABS የተመረጡ የአማርኛ መፅሀፍት
የሚቀርብበት የቴሌግራም ቻናል።

1. ሁሉም ሰው ልብ ያላለውን ዕድል መጠቀም:: ፊት ለፊት ሕይወት ያስቀመጠችልህን ዕድል አስተውሉ ለመጠቀም ዐይኖችህን ሳይሆን አዕምሮህን ተጠቀም::
2. ገንዘብ የማግኛ ምንጮች ለዪዎች:: አብዛኛው ሰው ኢንቨስትመንት ለመጀመር የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማግኘት ወደ ባንክ ይሄዳል:: ነገር ግን ከባንክ ውጪ በርካታ አማራጮች መኖራቸውን አትዘንጋ:: የራል ስቴት ሥራ ይህን በደንብ አስተምሮኛል:: ባንክ ውስጥ አምስት ሳንቲም ሳይኖረኝ በርካታ ጊዜያት ቤት ገዝቼ ሸጫለሁ:: ገንዘብ ከሌሎች ኢንቨስተሮችም ማሰባሰብ ሌላው አማራጭ ነው:: ግን ወዲያው መክፈል አለብህ:: በመሠረቱ ኢንቨስትመንት ንግድ ብቻ አይደለም ዕውቀትም ጭምር ነው::
3. ብልህ ሰዎችን ማቀናጀት:- ብልህና አዕምሯቸው ብሩህ የሆኑ ሰዎች ከነሱ የተሻሉ ሰዎችን የሚቀጥሩ አሊያም አብረዋቸው ለመስራት የሚፈልጉ ናቸው:: ምክር ስትፈልግ አማካሪህን በጥንቃቄ መምረጥ አለብህ:: ከብልህ ሰዎች ብዙ ተምረህ ታላቅ ጥቅም ማግኘት ትችላለህ:: እነዚህን ክህሎቶችና ጥበባት መማር ካልፈቀድክ የመጀመሪያውን ዓይነት ኢንቨስተር ብትሆን ይመከራል:: ዕውቀትህ ነው ታላቁ ሐብትህ:: ታላቁ አደጋህ ደግሞ የማይታወቀው ነው::

ሁሌም ቢሆን አደጋ አለ፤ አደጋን ከመሸሽ ይልቅ እንዴት እንደምትቋቋመውና እንደምታልፈው ተማር::





## ትምህርት ስድስት
## ለመማር እንጂ ለገንዘብ አትስራ

## ምዕራፍ ሰባት

## ስድስተኛው ትምህርት

# ለመማር እንጂ ለገንዘብ አትስራ

በ1995 ሲንጋፖር ውስጥ ለሚታተም አንድ ጋዜጣ ቃለ ምልልስ እየሰጠሁ ነበር:: ወጣቷ ጋዜጠኛ ካለሁበት ሆቴል የደረሰችው በሰዓቱ ሲሆን ቃለ ምልልሱንም የጀመርነው ወዲያው ነበር:: ከሆቴሉ አዳራሽ ቁጭ ብለን የጠዋት ቡናችንን እየተጎነጨን የእኔ የሲንጋፖር ጉብኝት /ጉዞ/ ዙሪያ ነበር:: የእኔ የሲንጋፖር የምናካሂደው ቃለ-ምልልስ በእኔ ሲንጋፖር ጉብኝት /ጉዞ/ ዙሪያ ነበር:: የጋራ ጉዞ ዓላማ ዚግ ዚግላር ከተባለ የራስን አቅም የማወቅ ጥበብ አስተማሪ ሰው ጋር የጋራ ስልጠና ለመስጠት ነበር::

ከቃለ ምልልሱ መጠናቀቅ በኋላ ጋዜጠኛዋ ‹‹አንድ ቀን ልክ እንዳንተ በብዛት የተሸጠ መጽሐፍ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ›› አለችኝ:: እኔም በምላሹ ካዘጋጀቻቸው ጽሑፎች ውስጥ የተወሰኑትን እንዳየሁና የአፃፃፍ ዘይቤዋ የአንባቢን ቀልብ የሚስብ መሆኑን ነገርኳት:: ቀጠል አድርጌም ‹‹ታዲያ ህልምሽን እንድታሳኪ ምን አገደሽ?›› አልኳት::

‹‹ሥራዎቼ ብዙም ተቀባይነት ያገኙ አይመስለኝም›› አለች ረጋ ባለ ድምፅ:: ብዙዎቹ የምታውቃቸው ደራሲዎች መጽሐፍቶቻቸው ምርጥ ቢሆኑም ብዙም እንደማይሸጥላቸው ሲናገሩ በመስማቷ ከመጽሐፍ ድርሰት ይልቅ ቢያንስ በየወሩ ቋሚ ገቢ የሚያስገኝላትን ሥራ መቀጠል አዋጪ ሆኖ እንዳገኘችው በመግለፅ ምክር እንድለግሳት ጠየቀችኝ::

እኔም ፊቴ ፈካ ብሎ ‹‹አዎን ምክር አለኝ:: እዚሁ ሲንጋፖር ውስጥ ያለ ጓደኛዬ ከፍተኛ ተቋማት ሰዎች ሥራዎቻቸውን እንዴት መሸጥ እንደሚችሉ ያሰለጥናል:: ስለዚህ እሱ ዘንድ ሳይቀር የሽያጭ ሰራተኞቻቸውን እንዲያሰለጥንላቸው ይጋብዙታል:: ስለዚህ እሱ ዘንድ ትንሽ ብትሰለጥኚ የሚበጅሽ ይመስለኛል›› ስል ምክሬን ለገስኳት::





ነገር ግን ፊቷን ቅጭም አድርጋ ‹‹ስለሽያጭ ሥራ ለመማር ትምህርት ቤት እንድገባ ነው እየመከርከኝ ያለኸው?›› አለችኝ:: እኔም ራሴን በመነቅነቅ ‹‹ምን ማለትሽ ነው?›› ምንም ነገር ባልናገር ይሻለኝ እንደነበር መመኘት ጀመርኩ::

ፊቷን እንዳኮሳተረች በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሁለተኛ ዲግሪ እንዳላትና የምትወደው ሙያ ኖሯት ሳለ የምትጠላውን የሽያጭ ሥራ ለመማር በድጋሚ ት/ቤት የምትገባበት ምክንያት እንደሌለ እንዲሁም የሽያጭ ሰራተኞች ከገንዘብ ውጪ ሌላ የሚታያቸው ነገር ባለመኖሩ በጣም እንደምትጠየፋቸው ጨምራ ነገረችኝ::

ከፊታችን ካለው ጠረጴዛ ላይ በከፍተኛ ደረጃ የተሸጠውን የእኔን መጽሐፍና ስለ እኔ ማስታወሻ ስትይዝበት የነበውን ማስታወሻ ደብተሯን አንስቼው ‹‹ይህን ተመልከቺ›› ወደማስታወሻዋ እየተመለከተች ‹‹ምን?›› አለች:: በድጋሚ ወደ ማስታወሻዋ እያመለከትኩ ‹‹ሮበርት ኪዮሳኪ ከፍተኛ ሽያጭ ያስመዘገበ ደራሲ›› የሚለውን አሳየኋት:: ቀጠል አድርጌም ‹‹ከፍተኛ ሽያጭ ያስመዘገበ መጽሐፍ ደራሲ›› እንጂ ‹‹ምርጥ ደራሲ›› እንደማይል ነገርኳት::

ዐይኖቿ ሲበለጠጡ ታየኝ:: ‹‹እኔ ጸሐፊ ነኝ:: አንቺ ደግሞ ታላቅ ጸሐፊ ነሽ:: እኔ ያለኝን አቅም መጠቀም እንዴት ገንዘብ ማግኘት እንዳለብኝ ስልጠና ወስጃለሁ: አንቺ ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪ አለሽ:: እነዚህን አንድ ላይ ብትጠቀሚባቸው ምርጥ ደራሲና ከፍተኛ ሽያጭ ያስመዘገበ መጽሐፍ ደራሲ ትሆኛለሽ›› ስል አከልኩበት::

በንዴት በግ ብላ ‹‹ገንዘብ ለማግኘት ስል ክብሬን ዝቅ አላደርግም:: እንዳንተ ያሉ ሰዎች ስለ ሥነ ጽሑፍ የምታውቁት ነገር የላችሁም:: እኔ እኮ የተማርኩ ጸሐፊና ባለሙያ ነኝ አንተ ደግሞ ነጋዴ:: ይህ ተገቢ አይደለም›› ይህን ተናግራኝ እየተመናጨቀች ከሆቴሉ ወጣች::

ዓለም ተሰጥኦ ባላቸው! ብልህ በሆኑ! በተማሩና በአስተዋይ ሰዎች የተሞላች ነች:: እነዚህ ሰዎች በዙሪያችን ያሉ ሲሆን ሁሌም እናገኛቸዋለን:: ከጥቂት ቀናት በፊት መኪናዬ ተበላሽታብኝ ነበር:: ወደ ጋራዥ ወስጃት አንድ ወጣት ሜካኒክ በደቂቃዎች ውስጥ ጠገነልኝ:: የመኪናዋ ችግር ምን እንደነበር የሞተሩን ድምፅ በመስማት ብቻ ነበር ያወቀው:: በዚህ ችሎታው በጣም ነው የተደነቅኩት:: የሚያሳዝነው ግን ታላቅ ችሎታ ብቻውን በቂ አለመሆኑ ነው::

ሁሌም ብቃት ያላቸው ሰዎች በሚያገኙት ገቢ ትንሽነት በጣም እንደደነገጥኩኝ ነው:: አንድ ቀን ደግሞ ከአሜሪካ አጠቃላይ ሕዝብ ውስጥ ከአምስት በመቶ ያነሱት በዓመት ከ100 ሺህ ዶላር በታች እንደሚያገኙ ሰምቼአለሁ::

የሕክምና ዕቃዎችን በመሸጥ ብዙ ገቢ የሚያገኝ አንድ ወዳጅ በርካታ ሕክምና ባለሙያዎች ዕውቀታቸውን ወደ ገንዘብ መለወጥ ባለመቻላቸው በችግር ውስጥ እንደሚኖሩ አጫውቶኛል:: ይኸው ወዳጅ የእነዚህን ባለሙያዎች ሁኔታ ‹‹ጥበበኞች ቢሆኑም ሐብት የሚያገኙበት አንድ ጥበብ ይጎድላቸዋል›› ሲል ነበር የገለፀው::

ይህ አባባል በሌላ መልኩ ሲተረጎም ብዙ ሰዎች አንድ ሙያ ላይ አተኩረው ራሳቸውን ከመገደብ ይልቅ ገንዘብ የማግኘት ጥበብንም አዳብረው ገቢያቸውን በእጅጉ ማሳደግ እንደሚችሉ ነው የሚያስረዳው:: ከዚህ በፊት እንደገለፅኩት ገንዘብ የማግኘት ጥበብ የሃሳብ ሥራ፣ የመዋዕለ ንዋይ፣ የገበያ ሥራ እና የሕግ ዕውቀት ጥምርታ ነው:: እነዚህን ነገሮች አንድ ላይ በመጠቀም ውጤታማ መሆን ቀላል ነው::

ገንዘብ ማግኘትን በተመለከተ ብዙ ሰዎች የሚያስቡት ብቸኛው መንገድ ‹‹ጠንክሮ መስራት›› ብቻ ነው:: ክህሎቶችን አቀናጅቶ የመጠቀም (synergy) ችግር ጥሩ ምሳሌ ልትሆነን የምትችለው ቅድም ታሪኳን በመጠኑ ያካፈልኳችሁ ጋዜጠኛ ነች:: እኔ የሽያጭና ገበያ ማፈላለግ ጥበብን ብትማር ገቢዋ በሚገርም መልኩ ይጨምር ነበር:: እኔ እሷን ብሆን ኖሮ ስለማስታወቂያ፣ ኮፒ ራይትና ሽያጭ ስልጠናዎችን እወስድ ነበር:: ከዚያም በጋዜጣ ድርጅት ውስጥ ተቀጣሪ ከመሆን ይልቅ በማስታወቂያ ኤጀንሲ ውስጥ ሥራ እፈልግ ነበር::

በማስታወቂያ ኤጀንሲ ውስጥ የሚከፈላት ገንዘብ ግማሽ ያነሰ እንኳን ቢሆን በማስታወቂያ ስራ የሚጠቅሟትን አካላትና ግለሰቦች በቀላሉ እንዴት ማግኘትና መግባባት እንደምትችል መንገዱን ስለሚያሳያት ተጠቃሚነቷ ይጨምራል:: በዚያው አግረመንገዷንም የሕዝብ ግንኙነት ዕውቀቷን በማዳበር በነፃ ማስታወቂያ ሚሊዮኖች ዘንድ እንዴት መድረስ እንደሚቻል ትገነዘባለች:: ከዚሁ ሥራዋ ጎን ለጎን በምሽትና በእረፍት ጊዜዋ መጽሐፏን በማዘጋጀት ሲጠናቀቅ የቀሰመችውን ዕውቀት እና ያለችበትን ቦታ እንደሁም የምታውቃቸውን ሰዎችና ተቋማት ተጠቅማ ከምርጥ ፀሐፊነቷ በተጨማሪ በርካታ ቅጂዎች የተሸጡላት ፀሐፊም መሆን ትችላለች::





‹‹ሐብታምና ደስተኛ መሆን ከፈለግህ ትምህርት ቤት አትሂድ›› የተሰኘውን የመጀመሪያ መጽሐፌን አዘጋጅቼ ጨርሼ ወደ ሕትመት ሊገባ ሲል አሳታሚው ‹‹የትምህርት ኢኮኖሚክስ› ወደሚል ርዕስ እንድትቀይረው መከረኝ:: እኔ ግን ከቀደመው ርዕስ ውጪ እንደማልቀይር ነግሬው ‹‹እንዲህ ባለ ርዕስ መፅሐፍ ባዘጋጅ ሁለት ቅጂ ብቻ ነው ላሳትምና ልሸጥ የምችለው፤ አንዱን ለቤተሰቤ ሌላውን ለወዳጄ:: ችግሩ ግን እነሱም መፅሐፉን በነፃ እንድሰጣቸው ነው የሚፈልጉት›› አልኩት::

‹‹ደስተኛና ሐብታም መሆን ከፈለግህ ትምህርት ቤት አትግባ›› የሚለውን ርዕስ የመረጥኩት እጅግ ከፍተኛ ትኩረት እንደሚስብ ስለተረዳሁኝ ነው:: እኔ በትምህርት አስፈላጊነት እምናለሁ፤ ከዚህ በተጨማሪም የትምህርት ሥርዓቱ ሊሻሻል እንደሚገባውም እሟገታለሁ፡ ለዚህ ነው እንዲህ ባለው አወዛጋቢ ርዕስ የተነሳ ቴሌቪዥንና የሬዲዮ ትኩረትን በመሳብ መጽሐፌን እንደጉድ የቸበቸብኩት::

በ1969 ዓ.ም ከአሜሪካ የንግድ መርከብ ባሕርተኞች ት/ቤት ስመረቅ አባቴ እጅግ ነበር የተደሰተው:: የካሊፎርኒያው ስታንዳርድ አይል የተባለ ድርጅት ቀጥሮኝ ሥራ የጀመርኩት ወዲያው ሲሆን፣ ደመወዜ ግን ከጓደኞቼ ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነበር:: ደመወዜ ዝቅተኛ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዓመት ውስጥ እየከፈሉኝ አምስት ወር እረፍት መውጣት እችል ነበር:: በነዚያ የእረፍት ወራቶቼ ወደ ቬየትናም ነዳጅ በሚያመላልስ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሬ ገቢዩን በእጥፍ እንዲጨመር ማድረግ እችል ነበር::

ነገር ግን ከዚያ የንግድ መርከብ ድርጅት በስድስት ወር ውስጥ ለቅቄ የአሜሪካ አየር ወለድን ተቀላቀልኩኝ:: አባቴ በዚህ ውሳኔዬ በጣም ነበር ያዘነው:: በት/ቤቶችም ሆነ በሥራ ቦታዎች በአንድ ነገር ላይ ማተኮር (ስፔሻላይዜሽን) የበለጠ ገንዘብ ለማግኘትና ለመሾም ዋናው ቁልፍ እንደሆነ ይታመናል:: ለዚህም ነው ሐኪሞች የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንዳገኙ ወዲያውኑ ስፔሻላይዝ ለማድረግ ትምህርት የሚጀምሩት:: ይህ የስፔሻላይዜሽን ጉዳይ ለሌሎች ባለሙያዎችም ያው ነው::

የተማረው አባቴም በዚህ ‹‹መርህ›› ያምን ነበር:: ለዚህም ነው የዶክትሬት ዲግሪውን እስኪያገኝ ድረስ በአንድ ዘርፍ ላይ ብቻሙሉ ትኩረቱን ያደረገው:: ‹‹ስለትልቁ ጉዳዩ ‹‹ሐብታሙ አባቴ› ደግሞ ተቃራኒውን እንዳደርግ ያበረታታኝ ነበር::

በጥቂቱ ማወቅ ነው የሚያስፈልግህ›› ምክሩ ነው:: ለዚህም ነው በድርጅቶቹ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ እያፈራረቅኩኝ የሰራሁት:: በተወሰነ ጊዜ በድርጅቱ ውስጥ የሂሳብ ባለሙያ ሆኜ የሰራሁ ሲሆን፣ ዕውቀትን ከተያያዥ ጉዳዮች እንዳገኝ አድርጎኛል:: የአውቶብስ ሹፌር፣ የግንባታ ሰራተኛ እና የሽያጭ ሰራተኛም ሆኜ ሰርቻለሁ::

የገነባውን የንግድ ኢምፓየር ምስጢራት እንድገነዘብና በእሱ መንገድ እንድሄድ ለማድረግ ከአበዳሪዎቹ፣ ከሕግ አማካሪዎቹ፣ ከሂሳብ ባለሙያዎቹ እና ከአሻሻጮቹ ጋር በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ላይ እንድገኝ ያስገድደኝ ነበር::

ከፍተኛ ገንዘብ ከጥቅማጥቅሞች ጋር የሚያስገኝልኝን እንዲሁም በጣም ሰፊ የእረፍት ጊዜ ሳገኝ የምችልበትን ሥራ ማቆሜ የተማረው አባቴን እጅግ ነበር ግራ ያጋባው::

አንድ ምሽት ‹‹ግን ለምንድን ነው ሥራህን ያቆምከው?›› ብሎ ሲጠይቀኝ ምክንያቴን ሳስረዳው አልቻልኩም:: የእኔ አመክንዮ ከእርሱ አመክንዮ ጋር አልገጥም አለ:: ትልቁ ችግር የእኔ አመክንዮ የሐብታሙ አባቴ አመክንዮ በመሆኑ ነው::

የሥራ ዋስትናና መማር ለተማረው አባቴ ከምንም በላይ ናቸው:: የተማረው አባቴ ወደ ትምህርት ቤት የገባሁት መርከበኛነት ለመማር ብቻ ነው የሚመስለው:: ሐብታሙ አባቴ ግን እዚያ የንግድ መርከበኝነት ት/ቤት የገባሁት ስለ ዓለም አቀፍ ንግድ ልምድ ለማካበት መሆኑን ያውቃል:: በመርከበኝነት ዘመኔ የተለያዩ የንግድ መርከቦችን ወደ ሩቅ ምስራቅና ደቡብ ፖሲፊክ ይዤ ተጉዣለሁ:: ሐብታሙ አባቴ ወደ አውሮፓ ከምሔድ ይልቅ ወደ ኤዢያ እንድሄድ ነበር የሚመክረኝ:: ለዚህ ምክንያቱ ወደ ፊት የገበያ ዋና ማዕከላት የሚሆነው ኤዥያ እንጂ አውሮፓ አለመሆኑን በመረዳቱ ነበር::

ማይክና ሌሎች ጓደኞቼ በከተማ ውስጥ ሲዝናኑ እኔ በኤዢያ ስለ ንግድና ስለባሕል ሳጠና ነበር:: የተማረው አባቴ ስራዬን አቁሜ የአየር ወለድ ባልደረባ ለመሆን የመወሰኔን ምስጢር ሊረዳ አልቻለም:: መብረር እንደምፈልግ ብነግረውም በእውነቱ ከሆነ ግን ወታደሮችን መምራት ነበር ፍላጎቴ:: ሐብታሙ አባቴ ለአንድ የድርጅት ባለቤት ትልቁ ፈተና ሰራተኞቹን ማስተዳደር መሆኑን አስረድቶኛል::

ሐብታሙ አባቴ ሶስት ዓመታትን በወታደርነት ያሳለፈ ሲሆን፣ በአደገኛ ኹኔታ ውስጥ ሰዎችን መምራት የመቻልን ዋጋ አስተምሮኛል:: አዘውትሮም ‹‹አመራር ቀጥሎ





ማወቅ የምትፈልገው ነው፤ ጥሩ መሪ ካልሆንክ ከጀርባህ በጥይት ትመታለህ፤ ልክ በንግዱ ዓለም እንደሚኾነው ማለት ነው›› ይለኝ ነበር::

ምንም እንኳን በረራ እጅግ ቢያስደስተኝም በ1973 ከሺየትናም ስመለስ ከውትድርና ወጣሁ:: ከዚያ በዜሮክስ ውስጥ ተቀጠርኩኝ:: ዜሮክስን የተቀላቀልኩት ለአንድ ምክንያት ብቻ ነበር:: በጣም ዓይን አፋር የነበርኩኝ ሲሆን በተለይም የሽያጭ ስራ እጅግ ነበረ የሚያስፈራኝ:: ዜሮክስ ደግሞ ምርጥ የሽያጭ ሥራ ስልጠና ከሚሰጡ ድርጅቶች አንዱ ነው::

በዚህ ወቅት ሐብታሙ አባቴ በእኔ ሲኮራ የተማረው ደግሞ እጅግ ያፍር ነበር:: ከምሁርነቱ የተነሳ የሽያጭ ሰራተኞች ከእርሱ በታች እንደሆኑ አድርጎ ያስብ ነበር:: በሮችን ለማንኳኳትና ‹‹ዞር በል›› መባልን መፍራቴን እስካቆም ድረስ ዜሮክስ ውስጥ ለአራት ዓመታት ያክል ሰርቻለሁ::

በ1977 የራሴን ድርጅት አቋቋምኩ:: ሐበታሙ አባቴ እኔና ማይክን ካምፓኒዎችን እንዴት መውረስና ማስተዳደር እንዳለብን ሲያለማምደን ቆይቷል:: ስለዚህ አሁን እኔ ካምፓኒዎችን እንዴት መፈጠርና ማስተዳደር እንዳለብኝ መማር አለብኝ:: የመጀመሪያው ለሽያጭ ያቀረብኩት የናይለንና ቬልክሮ ዋሌት የተመረተው ሩቅ ምስራቅ ሲሆን፣ አሜሪካ መጥቶ በመጋዘን የተቀመጠው ደግሞ ኒውዮርክ ውስጥ በቀድሞው ት/ቤቴ አቅራቢያ ነው::

አሁን የትምርት ጊዜዬ ተጠናቆ ‹‹ለመብረር ክንፎቼን የምፈትሽበት›› ወቅት ነው:: ከወደቅኩኝ መሰበሬ ነው:: ሐብታሙ አባቴ ዕድሜዬ 30 ዓመት ከመድረሱ በፊት ‹‹ወድቄ ብሰበር›› ምንም ማለት እንዳልሆነ ሲያስተምረኝ ‹‹ከ30 ዓመትህ በፊት ብትሰበርም ለማገገምና ለመነሳት ጊዜ ይኖርሃል›› ይለኝ ነበር:: በ30ኛው የልደት በዓሌ ዋዜማ የመጀመሪያው የጅምላ ንግዴን ከኒውዮርክ ወደኮሪያ ጀመርኩ::

ዛሬም ዓለም አቀፍ ንግዶችን እሰራለሁ:: ሐብታሙ አባቴ በመከረኝ መሠረት አዳዲስ የገበያ መናኸሪያ የሚሆኑ አገራትን እሰላለሁ:: ዛሬ በራሺያ፣ ናርዌይ፣ ደቡብ አሜሪካና ኤዢያ መዋዕለ ንዋይ አፍስሼአለሁ::

በሥራ አስተዳዳር ውስጥ ‹‹ሰራተኞች ላለመባረር ጠንክረው መሥራት አለባቸው፤ አሰሪዎች ደግሞ ሰራተኞች ሥራውን እንዳያቆሙ ማድረግ የሚያስችል ብቻ

ገንዘብ መክፈል ነው የሚጠበቅባቸው›› የሚል አስደንጋጭ አባባል አለ፡፡ እርግጥም የብዙዎቹን ድርጅቶች የደሞዝ ስኬል የተመለከተ ይህ አባባል እውነት እንዳለው ይገነዘባል፡፡

የዚህ ውጤቱ ሰራተኞቹ ለወደፊቱ ጥሩ ሕይወት እንዳይኖራቸው ማድረግ ነው፡፡ አብዝተው የሚጨነቁት ስለ ‹‹ሥራ ዋስትናቸው›› በመሆኑ ኃላፊነቶችን በመውሰድ የሕይወት አቅጣጫቸውን ሊቀይር የሚችል ሥራ የማከናወን ድፍረት አያገኙም፡፡

ከዚህ ይልቅ ግን እኔ ለወጣቶች የምመክረው ከገንዘብ ይልቅ ዕውቀት በሚያስገኝላቸው ሥራ ላይ እንዲሰሩ ነው፡፡ አንድ ጊዜ ሰዎች ደምዝተኛ ሆነው በወር ገቢ ብቻ መተዳዳርን ከለመዱ ልክ ለሰርከስ ሲባል መቆሚያ በሌለው የብረት ወንፊት ሽክርክሪት ውስጥ እንዳሉት አይጥ ዓይነት ኑሮ ነው የሚኖራቸው፡፡

ቶም ክሩዝ በሚተውንበት ‹‹ጆሪ ማጉር›› ፊልም ላይ ይህንን ሁኔታ በደንብ የሚገልፅ ትርኢት አለ፡፡ ቶም ክሩዝ ከሚሰራበት ድርጅት ሲባረር ሌሎች ባልደረቦቹ በተሰበሰቡበት ‹‹ማን ነው ከእኔ ጋር ይህን ድርጅት መልቀቅ የሚፈልግ?›› የሚል ጥያቄ አቅርቦ ሁሉም በዝምታ በተዋጡ ጊዜ አንዲት ሴት ‹‹እኔም መልቀቅ እፈልግ ነበር ግን ከሶስት ወራት በኋላ የደረጃ ዕድገት ስለማገኝ ይቅርብኝ›› ስትል ይታያል፡፡

የዚያች ሴት አባባል ብዙ ሰዎች ቅጥረኛ ሆነው በወር ደመወዝ ብቻ እየተቸገሩ ለምን እንደሚኖሩ በደንብ ያሳያል፡፡ የተማረው አባቴ በየዓመቱ በደሞዝ ጭማሪ ማነስ ሊበሳጭ አስታውሳለሁ፡፡ ስለዚህ ይህን ብስጭቱን ለማስወገድ ት/ቤት ገብቶ የትምህርት ደረጃውን ያሻሽላል፡፡ ነገር ግን በዓመቱ በድጋሚ ሌላ ብስጭት ነበር የሚጠብቀው፡፡

ሰዎችን ብዙ ጊዜ ‹‹ይህ ሥራ የት ያደርሳችኋል?›› ስል እጠይቃለሁ፡፡ ሁሌም ለእነዚህ ሰዎች የምሰጠው ምክር ከዛሬ ባሻገር ነገንና ከነገ በስቲያንም እንዲመለከቱ ነው፡፡ እርግጥ ነው የሥራ ዋስትና ጠቃሚ ነው ነገር ግን በአንድ ሥራ ላይ ብቻ ተወስነው ከሚቀሩ ሌላ ሁለተኛ ሥራ በመስራት ተጨማሪ ገንዘብና ክህሎት ቢያዳብሩ የተሻለ ነው፡፡ የሽያጭ ሥራን በአግባቡ መረዳት የሚፈልጉ ሰዎች የኔትወርክ ማርኬቲንግ በቀላሉ ምርጥ እንደሚሆን ሁሉም እመክራቸዋለሁ፡፡



እንዲህ ያሉት የኔትወርክ ማርኬቲንግ ድርጅቶች ለሰዎች ስኬት ማጣት ምክንያት የሆነውን ከተቋማትና ግለሰቦች ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ፍርሀት ለማስወገድ የሚረዱ ስልጠናዎችን ይሰጣሉ፡፡ እርቆ ለሚያስብ ከገንዘብ ይልቅ ዕውቀት ይበልጣል፡፡

ነገር ግን ብዙ ጊዜ ይህን ምክሬን ስሰግስ የማገኘው ምላሽ ‹‹ሉፍ እሱ በጣም ያደክማል›› አልያም ‹‹መሥራት የምፈልገው ቀልቤ የወደደውን ሥራ ብቻ ነው›› የሚሉ መልሶች ናቸው፡፡ ለመጀመሪያው ‹‹ሁለተኛ ሥራ መስራት ያደክማል›› ለሚለው የማቀርበው ጥያቄ ‹‹ስለዚህ ከገቢህ ግማሹን ለመንግስት እየገበርክ ዕድሜ ዘመንህ ማገፋት ነው የሚበጅህ?›› ሲሆን፣ ለሁለተኛው ‹‹ቀልቤ የወደደውን ብቻ ነው መሥራት የምፈልገው›› ለሚለው ምላሽ ደግሞ ‹‹እኔ ወደ ጂም መሄድ አልወድም ግን ረጅም ዕድሜ እንዲኖረኝና ጤናማ እንድሆን የግዴታ እሄዳለሁ›› ስል እመልሳለሁ፡፡

በሚያሳዝን ሁኔታ ‹‹ያረጀ ውሻ አይሰለጥንም›› የሚለው አባባል ዕውነትነት አለው፡፡ ሰዎችን መቀየር በጣም ነው የሚያስቸግረው፡፡ አዲስ ነገር ለመማር ፈቃደኛ ባልሆኑ ሰዎች የሚያስተላልፈው መልዕክት፣ ‹‹ሕይወት ልክ ጂም እንደመሄድ ነው፡፡ ትልቁ አስቸጋሪ ነገር ለመሄድ መወሰን ነው፡፡ አንዴ መሄድ ከጀመርክ በኋላ እየቀለለህ ይመጣል፡፡ ሽሬ እንዲያውም ያስደስታል›› የሚል ነው፡፡ ሌሎች ሥራዎች ላይ ተሰማርተህ አዳዲስ ክህሎቶችን ማዳበር ምርጫህ ካልሆነ የሙያ ማሕበራት አባል ሁን፡፡ እነዚህ ማህበራት ልክ እንዳንተ በአንድ ሥራ ላይ ብቻ አተኩረው መኖርን ምርጫቸው ያደረጉ ሰዎችን ለመጠበቅ የተቋቋሙ ናቸውና፡፡

የተማረው አባቴ የመንግስት ሥራውን ከለቀቀ በኋላ በሐዋይ የመምህራን ማሕበር ሊቀመንበር ነው የሆነው፡፡ ይህ ስራው ከእስካሁኑ ይልቅ እጅግ ፈታኝ እንደሆነበት አጫውቶኛል፡፡ ሐብታሙ አባቴ ደግሞ በሌላ በኩል ድርጅቶቹ በማሕበራት እንዳይከፋፈሉ ሲጠነቀቅና ሲታገላቸው ነው የኖረው፡፡

በበኩሌ የትኛውንም ወገን አልይዝም፡፡ ምክንያቱም የሁለቱንም አስፈላጊነትና ጥቅም እገነዘባለሁና፡፡ ልክ መምህራኖችህ እንዳስተማሩህ በአንድ ሙያ ብቻ ተወስነህና እሱ ላይ ትኩረት አድርገህ የምትሰራ ከሆነ የግድ የሙያ ማሕበር ውስጥ መግባት አለብህ፡፡ ለምሳሌ በአብራሪነት ሥራዬ ቀጥዬበት ቢሆን ኖሮ ጠንካራ የፓይለቶች ማህበር ባለው ካምፓኒ ውስጥ ነበር የምቀጠረው፡፡

የተመሰረተው በአንድ ሙያ ላይ ብቻ ለምን? ምክንያቱም ሕይወቱ በሙሉ ያዳበርኩት ልምድ በሌሎች መስኮች በመሆኑ:: ከዚህ ሥራ ብፈናቀል በሕይወቴ ሙሉ ሊያሰራኝ አይችልም:: መምህራንም ምሳሌዎች ናቸው:: ዛሬ በአሜሪካ ትልቁና የገንዘብ አቅሙ ጠንካራ የሆነው ማሕበር የመምህራን ማሕበር ነው:: መምህራን በማሕበር መታቀፍ ግድ የሆነባቸው ያላቸው ሙያ ከትምህርት ዘርፍ ውጪ የትም ሊያሰማራቸው ስለማይችል ነው::

ስልጠና በምሰጥበት ጊዜ ‹‹ስንቶቻችሁ ከማክዶናልድ የተሻለ ሐምበርገር ማዘጋጀት ትችላላችሁ?›› የሚል ጥያቄ አቅርቤ ብዙዎቹ ተማሪዎች በእምንታ እጃቸውን አውጥተዋል:: እነዚያኑ ተማሪዎች በመቀጠል ‹‹እና ታዲያ የተሻለ በርገር ማዘጋጀት እየቻላችሁ እንዴት ማክ ዶናልድ ከእናንተ የበለጠ ገንዘብ ያገኛል?›› ስል ጠይቄያቸው ነበር:: መልሱ ግልፅ ነው:: ማክዶናልድ ንግድ እንዴት እንደሚካሄድ በደንብ ያውቃል:: የንግድ አሰራርን በደንብ ሳያውቁ ሐምበርገር ቆንጆ አድርጎ ማዘጋጀት ብቻውን ሐብታም አያደርግም::

ሐዋይ ውስጥ አንድ አርቲስት ጓደኛ አለኝ:: እናቱ ስትሞት 35 ሺህ ዶላር አውርሳው ነበር:: ልክ ገንዘቡን እንዳገኘ የማስታወቂያ ዋጋው እጅግ ውድ በሆነ መጽሔት ላይ ማስታወቂያ በማውጣት የመጽሔቱ አንባቢ የሆኑ ሐብታሞች የስዕል ሥራውን እንዲገዙ ለማድረግ አሰበ:: እንዳሰበውም ውድ ዋጋ ከፍሎ ማስታወቂያውን ለሶስት ወራት አስወጣ:: ሆኖም ከማስታወቂያው ያተረፈው ነገር ቢኖር ከእናቱ በውርስ ያገኘውን ገንዘብ ማጣት ብቻ ነው:: አሁን ይህ ጓደኛዬ ካደረበት ከፍተኛ ብስጭት የተነሳ መጽሔቱን ለመክሰስ በዝግጅት ላይ ነው:: ይህን ጓደኛዬን ከክስተቱ ምን እንደተማረ ስጠይቀው የሰጠኝ መልስ ‹‹የማስታወቂያ ሽያጭ ሰራተኞች ሌቦች ናቸው›› የሚል ሲሆን፣ የሽያጭና ገበያ ማፈላለግ ስልጠና እንዲወስድ ስመክረው ደግሞ ‹‹ለስልጠና ጊዜ የለኝም፤ ገንዘብም ማባከን አልፈልግም›› ነበር ያለኝ::

ዓለም ድንቅ ችሎታ እያላቸው ደሀ በሆኑ ሰዎች የተሞላች ነች:: እነዚህ ሰዎች ደሀ የሆኑት አሊያም ገበያቸው የቀነሰው ችሎታ አጥተው ሳይሆን ይህን ችሎታቸውን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ማወቅ ባለመቻላቸው ነው፡ እንዲህ ያሉት ሰዎች መሉ ትኩረታቸው ምርጥ ሐምበርገር ማዘጋጀት እንጂ ሐምበርገሩን እንዴት ለገበያ ማቅረብ





እንደሚችሉ አያውቁም:: ምናልባት ማክዶናልድ ምርጡን ሐምበርገር አያዘጋጅ ይሆናል፤ ምርታቸውን በመሸጥ በኩል ግን ምርጥ ናቸው::

ደሃው አባቴ በአንድ ሙያ ላይ ብቻ ትኩረት እንዳደርግ ይፈልግ ነበር:: የበለጠ ገቢ ማግኘት የሚቻለው እንደዚያ በማድረግ ይመስለዋል:: በሐዋይ አገር ገዢ የመንግስት ሥራውን መቀጠል እንደማይቻል ተነግሮት እንኳን የተማረው ደሀው አባቴ ልክ እንደርሱ በአንድ ሙያ ብቻ እንድወሰን ይወተውተኝ ነበር::

ሐብታሙ አባቴ ግን እኔና ማይክ ራሳችንን እንድንኮተኩት ነበር የሚመክረን:: ብዙዎቹ ኮርፖሬሽኖችም እንዲህ ነበር የሚያደርጉት:: ከቢዝነስ ት/ቤቶች የሚመረቁ ወጣቶችን በመቅጠር ልጆቹን ያንጿቸዋል:: እነዚህ ብሩህ ተስፋ ያላቸው ወጣት በአንድ የሥራ መደብ ላይ ብቻ አይወሰኑም:: ሁሉንም የቢዝነስ ሥራ ለማወቅ ይረዳቸው ዘንድ በድርጅቱ ሁሉም የሥራ መደቦች ላይ እያፈራረቁ ይሰራሉ:: ዕድሜያቸው የገፋ ሰዎች ከድርጅት ድርጅት እያቀያየሩ መሥራትን አይወዱትም:: ነገር ግን ይህ ዘዴ ብልህነት ነው:: ከአንድ ድርጅት ሌላ ድርጅት እየተዘዋወሩ በመስራት አንድ ሙያ ላይ ብቻ ከማተኮርና ከመወሰን ይልቅ እንዲያ በማድረግ ብዙ መማር ይበጃል:: ይህ ብልህነት ምናልባት ብዙ ገቢ ላያስገኝ ይችል ይሆናል፤ በረጅም ጊዜ ግን የበለጠ ይጠቅማል::

ለስኬት የሚያስፈልጉ የሥራ አመራር ክህሎቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የገንዘብ ፍሰት ቁጥጥር
2. የሥርዓት ቁጥጥር (የጊዜ አጠቃቀምና ራስህን ፕሮግራም ያጠቃልላል)
3. ሰራተኞችን የማስተዳደር ችሎታ

ከእነዚህ በተጨማሪ በጣም ጠቃሚዎቹ ክህሎቶች የሽያጭና ገበያ ማፈላለግ ጥበብ ናቸው:: ምርትን ለመሸጥ ከደንበኞች ጋር፣ ከሰራተኞች ጋር፣ ከሥራ ኃላፊዎች ጋር የሚኖረን የመግባባት ችሎታ ወሳኝ ነው:: የመፃፍ፣ የመናገርና የመደራደር ችሎታም ለስኬት ቁልፍ ናቸው:: እነዚህን ለማዳበርም ትምህርት ተከታትዬአለሁ፣ ዕውቀቴንም ለማዳበር የተለያዩ ትምህርታዊ ቴፖችን ገዝቼ አዳምጥ ነበር::

ቅድም እንዳልኩት የተማረው አባቴ በየጊዜው ጠንክሮ ነበር የሚሰራው:: ጠንክሮ ከመስራቱም በላይ በአንድ ነገር ላይ ብቻ ተወስና ስፔሻላይዝ በማድረጉ ከአንድ ሙያ ውጪ ሌላ ክህሎትና ዕውቀት አልነበረውም:: በዚህም የተነሳ ከመንግስት ሥራው

በተፈናቀለ ጊዜ ምን ያክል ተጋላጭ እንደሆነ አውቆታል:: አባቴን በአትሌቶች መመሰል ይቻላል:: ከስፖርት ውጪ ሌላ ሞያ የሌላቸው አትሌቶች ሲያረጁ አልያም ጉዳት ሲደርስባቸው ብቸኛው የገቢ ምንጫቸው መድረቁ አይቀርም:: ለዚህም ነው የተማረው አባቴ እንዲህ ካለው ችግር ራሱን ለመጠበቅ የማሕበር አባል የሆነው::

ሐብታሙ አባቴ በጥቂት በጥቂቱ ብዙ ነገር እንድናውቅ እኔና ማይክን አበርትቶናል:: ከእኛ የተሻለ ዕውቀት ካላቸው ሰዎች ጋር እንድንሰራና ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች ወደ ሥራ ቡድናችን እንድናካትት ሁሌም ይመክረን ነበር:: ይህም የባለሙያዎች ጥምረት ተብሎ መሠራት ይችላል::

ዛሬ ዛሬ በዓመት እጅግ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ የቀድሞ መምህራንን እውቃለሁ:: ከፍተኛ ገቢ ለማግኘታቸው ምስጢሩ ከመምህርነት በተጨማሪ ሌሎች ክህሎቶችንም በማዳበራቸው ነው:: ከሽያጭ ሥራ ክህሎት የበለጠ ጠቃሚ ሥራ አላውቅም:: የሽያጭ ሥራ ለብዙ ሰዎች አስቸጋሪ የሚሆነው ‹‹ዞር በል›› መባልን አሲያም ተፈላጊነት ማጣትን ስለሚፈሩ ነው::

ተፈላጊነት ማጣትን መቋቋም መቻል ሕይወትን ያቀላል:: በአንድ ሙያ ሳይ ብቻ ስፔሻላይዝ ማድረግ የራሱ የሆነ ጥንካሬም ድክመትም አለው፡ ድንቅ አዕምሮ ያላቸው ጓደኞች አሉኝ:: እነዚህ ጓደኞቼ ምንም እንኳን ምርጥ ክህሎት ቢኖራቸውም ከሰዎች ጋር የመግባባት ችሎታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ ገቢያቸው እጅግ ዝቅተኛ ነው:: እኔ የምለግላቸው ምክር የሽያጭ ሥራና ገበያ ማፈላለግ ስልጠና እንዲወስዱ ነው:: ምንም ገቢ ባያገኙ እንኳ (ለጊዜው) ይህን ስልጠና በመውሰዳቸው የመግባባት ችሎታቸው ይዳብራል! ይህ ደግሞ ዋጋው ይህ ነው ተብሎ የማይተመን ውድ ነገር ነው::

አሪፍ ተማሪዎች! ሻጮችና የገበያ ባለሙያዎች ከመሆን በተጨማሪ አሪፍ አስተማሪዎችም ልንሆን ይገባል:: የዕውነት ሐብታም ለመሆን መስጠትም ሆነ መቀበል መቻል አለብን:: የገንዘብ ችግር ባጋጠመንና የሥራ ቦታችን ባልተስማማን ወቅት ሰጥቶ መቀበል አስቸጋሪ መሆኑ አይጠረጠርም:: ብዙ ሰዎች ለድህነታቸው ምንጭ አሪፍ ተማሪ እናም አሪፍ መምህር መሆን አለመቻላቸው ነው::

ሁለቱም አባቶቼ ለጋሶች ነበሩ:: ሁለቱም ቅድሚያ መስጠትን ባሕላቸው አድርገውት ኖረዋል:: ያላቸውን ለመስጠት ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ውስጥ ማስተማር





አንዱ ነበር:: የበለጠ በሰጡ ቁጥር የበለጠ ያገኙ ነበር:: በዚህ መስጠት ጉዳይ በመካከላቸው የነበረው አንድ ትልቅ ልዩነት ገንዘብ መስጠትን የተመለከተ ነው:: ሐብታሙ አባቴ ብዙ ገንዘብ ይሰጥ ነበር:: ለቤተክርስቲያንና ለእርዳታ ሥራዎች በርካታ ገንዘብ ይሰጣል:: ገንዘብ ለማግኘት ገንዘብ መስጠት እንዳለበት ያውቅ ነበር:: የብዙዎቹ ባለፀጋዎች የሐብት ምስጢር ገንዘብ መስጠት ነው:: በዚህ ረገድ የፎርድና ሮክ ፌለር ፋውንዴሽንኖችን መጥቀስ ይቻላል:: እነዚህ ፋውንዴሽኖች የተቋቋሙት የድርጅቶቹን ሐብት ለመጨመርና ከሚገኘው ሐብት ውስጥም የተወሰነውን እንዲያው በነፃ ለሌሎች ለመስጠት ነው::

የተማረው አባቴ ሁል ጊዜ ‹‹ያለኝን ትርፍ ገንዘብ በሙሉ መስጠት አለብኝ›› ሲል እሰማዋለሁ:: ችግሩ የምንም ነገር ‹‹ትርፍ›› የሚባል አለመኖሩ ነው:: ስለዚህ ይህን ዕቅዱን ለማሳካትና ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ‹‹ስትሰጥ ታገኛለህ›› የሚለውን የገንዘብ መርህ በመተው በያዘው ሙያ እጅግ ጠንክሮ ነበር የሚሰራው! የሚከተለውም መርህ ‹‹ስታገኝ ስጥ›› የሚለውን ተቃራኒ መርህ ነበር::

በመጨረሻ እኔ ሁለቱንም አባቶቼን ነው የሆንኩት:: አንደኛው እኔነቴ በገንዘብ ገንዘብ የማግኘትን ጨዋታ የማካሄድ ካፒታሊስት ነው:: ሁለተኛው ማንነቴ ደግሞ ማሕበራዊ ኃላፊነት የሚሰማውና በሐብታምና በደሐ መካከል እየሰፋ የመጣው ክፍተት የሚያሳስበው መምህር ነው:: በግሌ ለዚህ ክፍተት መስፋት ተጠያቂ የማደርገው በጥንት ዘልማድ የተቃኘውን ትምህርት ነው::

## ጅማሮዎቹ





# ምዕራፍ ስምንት

## ፈተናዎችን ማለፍ

ሰዎች ስለገንዘብ አያያዝና የገንዘብ ምንጮችን እንዴት መፍጠር እንደሚችሉ አያውቁም:: በቂ ገንዘብ ሳያገኙ ይችላሉ:: የገንዘብ አያያዝ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች በቂ ገንዘብ እንዳያገኙ የሚያደርጓቸው አምስት እንቅፋቶች አሉ:: እነሱም:-

1. ፍርሐት
2. ጨለምተኛነት
3. ስንፍና
4. ክፉ ልማድ /ሱሰኝነት
5. ዕብሪት /ትዕቢት

1. ***የገንዘብ የማጣት ፍርሃትን ማስወገድ:-*** በሕይወት ዘመኔ ሙሉ ገንዘብ ማጣትን የሚወድ ሰው አግኝቼ አላውቅም:: በዛው ልክ ገንዘብ ሳያጣ /ከኪሱ ሳያወጣ/ሐብታም የሆነ አንድም ሰው አይቼ አለውቅም:: ነገር ግን አምስት ሳንቲም ሳያወጡ /ኢንቨስት ሳያደርጉ/ ያገኙትን እንደያዙ ደሐ ሆነው የቀሩ በርካታ ሰዎችን አውቃለሁ::

ገንዘብ የማጣት ፍርሐት የምር ነው:: በሁሉም ሰው ዘንድ ይህ ፍርሐት አለ:: ሐብታሞችም ዘንድ:: ችግሩ ፍርሐቱ አይደለም:: ዋናው ችግር ይህን ፍርሐት እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል አለመታወቁ ነው:: በአንድ ሰው ሕይወት ላይ ልዩነት የሚያመጣው የገንዘብ ማጣትንና ውድቀትን የምንመለከትበትና የምንቋቋምበት መንገድ ነው:: ይህ ዕውነት ለገንዘብ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ነገር ይሆናል::

በሐብታምና በደሐ መካከል ያለው ልዩነት ይህን ፍርሐት የሚቋቋሙበት መንገድ ነው:: መፍራት መልካም ነው:: ለገንዘብ እጅግ መጠንቀቅም ጥሩ ነው:: እንዲህ መሆን ከሐብታምነት አያግድም:: ሁላችንም በአንድ ነገር ጀግና በሌላ ደግሞ ፈሪ ልንሆን እንችላለን:: የጓደኛዬ ሚስት የድንገተኛ ክፍል ነርስ ነች:: ደም ስታይ ፈጥና የተጎዳውን

ለመርዳት ትንቀሳቀሳለች፡፡ ስለ ኢንቨስትመንት ሳወራባት ግን ወኔዋ ይከዳታል፡፡ እኔ ደግሞ ላይ እወድቃለሁ፡፡ ለኢንቨስትመንት ደግሞ ልቤ ይቆማል፡፡

ሐብታሙ አባቴ የገንዘብ ፍርሐትን በደንብ ያውቃል /ይገነዘባል፡፡ ይህንንም አስመልክቶ ‹‹አንዳንድ ሰዎች በእባብ የሚደነግጡትን ያክል ገንዘብ ማጣት ያስደነግጣቸዋል፡፡ ሀብቱም ፍርሐት ነው›› ይላል፡፡ ገንዘብ የማጣት ፍርሐትን ለማስወገድ የሚለግሰው ምክርም፡- ‹‹ውድቀትን የምትፈራ ከሆነ ሥራህን ቀድመህ ጀምር›› የሚል ነው፡፡ ለዚህ ነው ባንኮች ገና ከወጣትነትህ ጀምሮ የቁጠባ ሂሳብ እንድትከፍት የሚመክሩህ፡፡ ከወጣትነትህ መጎበዝ ከጀመርክ ሐብታም ለመሆን አይቸግርህም፡፡ በ20 ዓመቱ ቁጠባ በጀመረ በ30 ዓመቱ በጀመረ መካከልም እጅግ ከፍተኛ ልዩነት አለ፡፡

በምድር ላይ ካሉ ድንቅ ነገሮች አንዱ የወለድ ኃይል መሆኑ ሲነገር ይሰማል፡፡ የማንሐታን ደሴት ግዢ በዘመን ሁሉ ከተስተዋሉ ድርድሮች የላቀው እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ኒው ዮርክ የተገዛችው በ24 ዶላር ነበር፡፡

ነገር ግን ያ 24 ዶላር በየዓመቱ በምንት በመቶ በሆነ ወለድ ኢንቨስት ቢደረግ ኖሮ በ1995 ከ28 ትሪሊዮን ዶላር በላይ ዋጋ ይኖረው ነበር፡፡

ሥራህን ቀደም ብለህ ጀምረህ ለጡረታ መውጫ ጊዜህ ዕቅድ ከወዲሁ መንደፍ አለብህ፡፡ መዋዕለ ንዋይህን ከማፍሰስህ በፊት በትክክለኛ አቅጣጫ ሊመራህ የሚችል ታማኝ አማካሪ መቅጠር ያስፈልግሃል፡፡

ነገር ግን ጡረታ የመውጫ ጊዜህ ቢደርስ እሊያም ቀድመህ ስራ ማቆም ከፈለግክ እንዴት ነው ገንዘብ የማጣት ፍርሐትህን የምታቋቁመው?

ደሐው አባቴ በዚህ ጉዳይ ላይ መነጋገር እንኳን አይፈልግም፡፡ ሐብታሙ አባቴ ደግሞ ልክ እንደቴክሳሶች እንዳስብ ይመክረኝ ነበር፡፡ ቴክሳሶችን የሚወደው ሐብታሙ አባቴ ‹‹በቴክሳስ ሁሉም ነገር ትልህ ነው፡፡ ድል ሲቀዳጅ ወይም ሲያገኙ እጅግ ብዙ ነው የሚያገኙት፡፡ ያገኙትን ለማጣትም አይፈሩም፡፡ ቴክሳሶች እዚህ እንዳሉ ሰዎች ለአምስት ሳንቲምና ለጥቃቅን ፍርፋሪ ቦታ አይሰጡም፡፡ ዛሬ ቢያጡ ነገ እንደሚያገኙ ያውቁታል›› ይለኛል፡፡

ዘወትር ለእኔና ለማይክ ሰዎች ሐብት የማያገኙበት ዋናው ምክንያት እጅግ ሲበዛ ፈሪዎች በመሆናቸው መሆኑን ይነግረናል፡፡ ብስክሌት መጋለብ ከመልመዴ በፊት ብዙ





ጊዜ ወድቄያለሁ፡፡ የጎልፍ ኳስ ያልጠፋበት ጎልፍ ተጫዋች አጋጥሞኝ እንደማያውቀው ሁሉ ገንዘብ ሳያወጣ ሐብታም የሆነ ሰው አይቼ አላውቅም፡፡ ከቴክሳሶች አባባል አንድ ልጨምር፡- ‹‹ሁሉም ሰው ወደ ገነት መግባት ቢፈልግም መሞት ግን ማንም አይፈልግም››፡፡ ብዙ ሰዎች ሐብታም ለመሆን ያልማሉ ግን ገንዘብ ለማውጣት አይፈልጉም፡፡ ስለዚህ ‹‹ገነት›› ዕድሜ ልካቸውን አይገቧትም፡፡

ሐብታሙ አባቴ ይህን የቴክሳሶች ልበ ሙሉነት ታሪክ ሁሌም ትልልቅ ውሉችን ሲፈራረም ሲል ይነግረናል፡፡ ስህተት ሳለመስራትና ገንዘብ ሳለማውጣትና ሳለማጣት በፈራ ጊዜያት ሁሉ ይህን ታሪክ ያጫውተናል፡፡ ይህ የቴክሳሶች ደፍረት የገንዘብ ኪሳራን ወደ ትርፍ መለወጥ የሚያስችል ድፍረት ይሰጠዋል፡፡ ሐብታሙ አባቴ እንቅፋት እንደሚያበረታው ያምናል፡፡ ይህ ነው የአሸናፊነቱ ምስጢር፡፡

ቴክሳሶች ውድቀቶቻቸውን አይደብቁም፡፡ ከውድቀቶቻቸው ይማራሉ፡፡ ውድቀት ቴክሳሶችን አሸናፊ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ ቀመር የቴክሳሶች ብቻ ሳይሆን ውድቀቱ የሁሉም አሸናፊዎች ቀመር ነው፡፡

ብስክሌት መንዳት ስለማመድ ብዙ ጊዜ መውደቄ እልህ ውስጥ ነበር የከተተኝ፡፡ ጀግናዎች እንቅፋት ሲያበረታቸው ሰነፎችን ግን ለሽንፈት ይዳርጋቸዋል፡፡

‹‹እያንዳንዱን ችግር ወደ ትሩፋት ለመለወጥ ነው የምተጋው›› የሚለውን የጆን ፎክፌለርን አባባል እዘወትሬ እጠቀማለሁ፡፡

ግማሽ ጃፓናዊ ግማሽ አሜሪካዊ መሆኔ የፐርል ሐርበር ክስተትን ያስታውሰኛል፡፡ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ጃፓን በአሜሪካዋ ወደብ ፐርል ሐርበር ላይ ከፍተኛ የአውሮፕላን የቦምብ ድብደባ በመፈፀም በአሜሪካ ላይ ጉዳት አድርሳለች፡፡ ሆኖም አሜሪካ ለዚህ ጥቃት እጇን ሳትሰጥ ጃፓን ላይ የአቶም ቦምብ ድብደባ መፈፀሟ የዓለም ኃያል አገር ሆና እንድትወጣ አስችሏታል፡፡

ይህን ምስጢር ሰነፎች ሊገነዘቡት አይችሉም፡፡ ማሸነፍ ማለት ሽንፈታችንን አለመፍራት ነው፡፡ እንደ ፋራን ታርኬንተን ያሉ ሰዎች ማንነታቸውን ስለሚያውቁ ሽንፈትን አይፈሩም፡፡ ሽንፈትን በመጥላትና ሽንፈትን በመፍራት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ ብዙ ሰዎች ገንዘብ አውጥተው መክሰርን ስለሚፈሩ በጣም በጥንቃቄ ትንሽ ገንዘብ ነው ለማውጣት የሚፈቅዱት፡፡ ትልቅ መኪናና ትልቅ ቤት ሊገዙ ይችላሉ ትልቅ

ኢንቨስትመንት ግን ለማካሄድ ይፈራሉ። ከ90 በመቶ በላይ የሆኑት በገንዘብ ችግር የሚሰቃዩ ሰዎች እንዲህ ለመሆናቸው ዋነኛው ምክንያት የሚጠንቀቁት ለማሸነፍ ሳይሆን ላለመሸነፍ መሆኑ ነው።

ያለህ ገንዘብ ትንሽ ቢሆንና ሐብታም መሆን ከፈለግህ በመጀመሪያ ደረጃ ማድረግ ያለብህ በጣም ፈሪነትና ጠንቃቃነትህን አስወግደህ ትኩረትህን መለየት ነው።

የተሳካላቸው ሰዎችን ካየህ ፈሪዎችና ሲበዛ ጥንቁቆች አይደሉም። ምንም እንኳን ጥንቃቄ አስፈላጊ ቢሆንም ከመጠን በላይ ሲሆንና ከፍርሐት ጋር ሲደመር እንቅፋት ነው የሚሆነው። እንዲህ ያሉ ሰዎች የትም አይንቀሳቀሱም።

ቶማስ ኤዲሰን ውድቀቱ የሚያሳስበው አልነበረም። ቢል ጌትስም ትኩረቱን ለይቶ ያስቀመጠ ልበ ሙሉ ነው። ሌሎች ብዙ ሰዎችን መዘርዘር ይቻላል። ሐብታም የመሆን ፍላጎት ካለህ ድሆች እንደሚያደርጉት ያለህን ጥቂት እንቁላል በብዙ ቅርጫት ውስጥ አትክተት፤ ይልቅስ በርካታ እንቁላሎችን በጥቂት ቅርጫት ውስጥ አስቀምጥ።

ገንዘብ ማጣት የማያስፈራህ ከሆነና ሽንፈትህ የማያደክምህ ከሆነ ጠንቃቃ ብቻ ብትሆን አይከፋም። ፈሪም ሆነህ ዕድሜህ ከ25 ዓመት በላይ ከሆነ ሥራህን ቀድመህ ጀምር። ነገረ ግን ነፃ የመሆንና ሐብታም የመሆን ሕልም ካለህ ራስህን ‹‹እንቅፋትን እንዴት ነው የማልፈው?›› ስትል ጠይቅ። ጊዜያዊ እንቅፋት የሚያበርታህ ከሆነ በጀመርከው ጉዞ ቀጥታ እንቅፋት ለሽንፈት የሚዳርግህ ከሆነ ደግሞ ጥንቁቅ ይሁን። ሥራህን አትተው አሊያም በንድና ሌሎች የዋስትና ሰነዶችን ግዛ። ነገር ግን እነዚህ የዋስትና ሰነዶችም ቢሆኑ ሙሉ በሙሉ እንደማያስተማምኑ ልታውቅ ይገባሀል።

ምክንያት 2 - የበዛ ጨለምተኝነትና ተጠራጣሪነት

እያንዳንዳችን ውስጥ ጨለምተኝነት ተጠራጣሪነት በተወሰነ መልኩ አለ። ‹‹እኔ ብልህ አይደለሁም››፣ ‹‹ይሕን ማድረግ አልችልም›› ወዘተ... የጨለምተኝነታችን የተጠራጣሪነታችን ውጤቶች ናቸው። ነገር ግን ተጠራጣሪነታችን ሲበዛ ሽባ አድርጎ ነው የሚያስቀምጠን። ሕይወታችን የተቃኘው በ‹‹ቢሆንስ?›› ነው። ጥያቄዎቻችን ‹‹እኔ ገንዘቤን ካወጣሁ በኋላ የኢኮኖሚ ውድቀት ቢከሰትስ?››፣ ‹‹ብከስርና ገንዘቤን መመለስ ባልችልስ?›› የሚሉ ናቸው። ጓደኞቻችንም ከፊት ለፊታችን የሚገጥመንን ችግር ዘወትር የሚያስታውሱ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ማስፈራሪያቸውም ማጠናከሪያ ‹‹ይኼ በፍፁም





የማይሳካ ነገር ነው፤ የምታወራውን አታውቅም›› ይላሉ። ከእነዚህ ቃላት የበለጠ ሰውን ፈሪና ምንም የማይሰራ ግዑዝ የሚያደርግ ምንም የለም። ስለዚህ የያዝነውን ይዘን ሐብታም ሊያደርገን የሚችልን አጋጣሚ እናሳልፋለን። ሁላችንም በሕይወታችን አንድ ጊዜ እንዲህ ያለው ክስተት ሊያጋጥመን ይችላል፤ የተወሰኑት ደግሞ በተደጋጋሚ።

የፊደልቲ ማጅላን ሙቹዋል ፈንድ መሥራች ፒተር ሊንች እንዲህ ያሉትን ማስጠንቀቂያዎች ‹‹ባዶ ጩኸት›› ሲል ይጠራቸዋል። ሊንች በ195ዎቹ የነበረውን ትርምስ ያስታውሳል። በዚያ ወቅት የኒውክሌር ጦርነት ሊከሰት ይችላል ብለው በርካታ ሰዎች በመስጋታቸው የተነሳ መሸሸጊያ ቤቶችን በመገንባትና ለረዥም ጊዜ የሚሆን ቀለብ በመሸመት ብዙ ገንዘብ ያጠፉ ሲሆን፤ ያንን ገንዘብ ግን በኢኮኖሚው ውስጥ ቢያውሉት ኖሮ ዛሬ ሐብታም መሆን ይችሉ እንደነበር በቁጭት ያስታውሳል።

በአንድ ወቅት ሎስ አንጀለስ ውስጥ ብጥብጥ የተከሰተ ጊዜ የሽጉጥ ገበያ በጣም ነበረ የደራው። ብዙ ሰዎች ደህ የሆኑት ከንቱ ማስፈራሪያ የሚነግሯቸውን ሰዎች አምነው በመስማታቸው ነው። እንዲህ ያለውን ‹‹ጩኸት› የሚያሰራጩ ሰዎች ደግሞ ሲበዛ ውጤታማ ናቸው። ምክንያቱም እንዳንዳችን ውስጥ ፍርሐትና ተጠራጣሪነት አለና።

እነዚህን ተራ ወሬዎችና ባዶ ጩኸቶች ለማከሸፍ ጥርጣሬና ፍርሐትን ተቋቁሞ ወደ ስኬት ለመጓዝ መወሰን ታላቅ ድፍረትን ይጠይቃል።

በ1992 ሪቻርድ የተባለ ጓደኛዬ ከቦስተን ወደ ፊኒክስ መጥቶ እኔና ባለቤቴን ጎብኝቶን ነበር። በወቅቱ እኔና ባለቤቴ ከሪል ስቴት ኤጀንሲ ምርጥ ቤት ገዝተን የነበረ ሲሆን በዋጋው ርካሽነት በጣም ተገርሞ ነበር።

ለዚህ ጓደኛዬ የሚሆን ቤት ፈላልገን አገኘንለትና ከደላላው ጋር አስማማናቸው። ሁለት መኝታ ክፍል ያለውን ቤት በ42 ሺህ ዶላር። ደስተኛ ሆኖ ወደ ቦስተን ተመለሰ ከሁለት ሳምንታት በኋላ የቤቱ ደላላ ደውሉ ጓደኛዬ ውሉን እንዳፈረሰ ነገረኝ። ከፍጥነት ደውዬ ለምን ውሉን እንዳፈረሰ ጠየቅኩት። እሱም ጎረቤቱ የቤቱ ዋጋ በጣም ውድ መሆኑን ስለነገረው መሆኑን ነገረኝ።

ሪቻርድን ጎረቤቱ ኢንቨስተር እንደሆነ ጠይቀው እንዳልሆነ የነገረኝ ሲሆን፤ ታዲያ ምክሩን ለምን እንደተቀበለ ስጠይቀው ቆጣ ብሎ ‹‹ብቻ ሌሎችንም ማየት አለብኝ›› ነገር

ቤት በዓመቱ ዋጋው 65 ሺህ ዶላር ያለኝ:: ሪቻርድ 42 ሺህ ዶላር አግኝቶ የተወው ቤት በዓመቱ ዋጋው 65 ሺህ ዶላር ደረሰ:: የሪቻርድ ውል ማፍረስ ምንም አላስገረመኝም:: እንዲህ ያለው ክስተት ‹‹የገዢዎች ፀፀት›› ይሰኛል::

እዚ ጋ ማስቀመጥ የፈለግሁት ነጥብ ጥርጣሬና ጨለምተኝነት ለብዙ ሰዎች ድህነት ዋና መንስኤዎች መሆናቸውን መግለፅ ነው:: ዓለም በዕድሎች የተሞላች ነች:: ቀደም ብዬ እንዳልኩት ከዚህ የመጠራጠር አባዜ መውጣት እጅግ ቀላልና ጥልቅ ምርምር የሚጠይቅ አይደለም::

ሐብታሙ አባቴ ‹‹ጨለምተኞች መቼም ቢሆን አያሸንፉም›› ይላል:: ‹‹መሠረተ ቢስ መጠራጠርና ፍርሐት ጨለምተኝነትን ይወልዳል:: ጨለምተኞች ነገሮችን ያብጠለጥላሉ፤ አሸናፊዎች ግን ነገሮችን ይተነትናሉ›› ሌላው ተመራጭ አባባሉ ነው:: ሐብታሙ አባቴ ነገሮችን ዝም ብዬ ማብጠልጠል እንደሚያሳውርና መተንተን ደግሞ ዓይን እንደሚያበራ ሁሌም ይገልፅልኛል:: ትንተና ሌሎች ማግኘት ያልቻሉትን ዕድል ለመጠቀም በር የሚከፍት ሲሆን፣ ሰዎች የሚጎድላቸውን ነገር ለይቶ ማወቅ ደግሞ ለስኬት ቁልፍ ነው::

በአክሲዮን ገበያ ውስጥ ብዙ ጊዜ ሰዎች ‹‹ገንዘቤ እንዲከስር አልፈልግም›› ሲሉ እሰማለሁ:: ጥሩ፤ እኔ አሊያም ሌሎች ሰዎችስ ብንሆን ገንዘባችን እንዲከስር እንፈልጋለን እንዴ? እነዚህ ሰዎች ገንዘብ ስለማያወጡ ገንዘብ አያገኙም:: ነገሮችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች መተንተን ስለማይችሉ እንደታወሩና እንደደኸዩ ይኖራሉ::

በታህሳስ 1996 ከአንድ ጎረቤቴ ጋር በአቅራቢያችን ወዳለ ነዳጅ ማደያ ሄድን:: ይህ ጓደኛ በየጊዜው እየጨመረ በሚሄደው የነዳጅ ዋጋ በጣም ይማረራል:: ከመማረር ውጪ ግን የነዳጅ ዋጋ ጭማሪውን ወደ ዕድል የሚቀይርበትን አጋጣሚ መፍጠር አልቻለም::

እቤት እንደተመለስን የነዳጅ ዋጋ ጭማሪው የሚገዛውን አካሄድ አሳየኝ:: በእርግጥም የነዳጅ ዋጋ በየጊዜው በጣም እየጨመረ ነው:: ጎረቤቴ ይህንን በምሬት ሲነግረኝ ግን አልተማረርኩም፤ አሊያም አልተጨናነኩም ወዲያው ወደ አንድ የነዳጅ ኩባንያ ሄጄ በርካታ አክሲዮኖችን ገዛሁ:: በእውነትም ጓደኛዬ እንዳለሰው የነዳጅ ዋጋ መጨመሩን ቀጥሏል፤ የእኔም ትርፍ እንደዚያው::



ሰዎች ከሚፈልጉት ነገር ይልቅ በማይፈልጉት ላይ የሚያተኩሩት በጭንቅላታቸው ውስጥ የሚያቃጭለው ‹‹ባዶ ጩኸት›› ከፍተኛ በመሆኑ ነው:: ሁሉም ነገር ለእነሱ የመጣላቸው ሳይሆን የመጣባቸው ነው መስሉ የሚታያቸው:: ስለዚህ በሕይወት ማሟላት የሚፈልጉትን ነገር አያገኙም::

ሐብታሙ አባቴ ችግርን እንዴት መቋቋም እንዳለብኝ ሲመክረኝ የኮሎኔል ሳንደርስን ታሪክ ያጫውተኛል:: ካሎኔሉ በ66 ዓመቱ ከስሮ ከመንግስት በሚያገኘው ዕርዳታ ላይ ጥገኛ ለመሆን ተገደደ:: ይህ የማህበራዊ ዋስትና ገንዘብ በቂ ባለመሆኑ የተጠበሰ ዶሮ ለመሸጥ በመላው አገሪቱ ተንከራቷል:: ይህ የዶሮ ጥብሱ ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት አንድ ሺህ ዘጠኝ ጊዜ ‹‹አንፈልግም፤ ዞር በል›› ተብሏል:: ይህን ሁሉ በፅናት በመቋቋሙ ግን የኋላ ኋላ ሚሊየነር ለመሆን ችሏል:: እንዴት ያለ ጀግናና ጠንካራ ሰው ነው!

## ምክንያት 3 - ስንፍና

ብዙዎቹ ሰነፍ ሰዎች በጣም ፋታ የለሽ ናቸው:: ሁላችንም አንድ ሰው ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ጠንክሮ /ፋታ አጥቶ/ መሥራት እንዳለበት ሲነገር ሰምተን ነው ያደግነው:: እንዲህ ያሉ ሰዎች ለልጆቻቸው እና ለሚስቶቻቸው በቂ ገቢ ለማስገኘት እጅግ ይታትራሉ:: ረጅም ሰዓት ቢሮ ውስጥ ከማሳለፋቸው ባሻገር ቀሪ ስራዎቻቸን በዕርፍት ጊዜያቸው ሳይቀር ሲሰሩ ያሳልፋሉ:: ከድካማቸው የተነሳ ድንገት ቢሮ ውስጥ ተኝተው ቢገኙ ከሥራቸው ወዲያው ነው የሚባረሩት::

ዛሬ ዛሬ ከጤንነታቸው ይልቅ ለሐብታቸው የሚጨነቁ በርካታ ሰዎች አስተውባለሁ:: ምክንያታቸው አንድ ነው:: ራሳቸውን በሥራ የሚጠምዱት መጋፈጥ የማይፈልጉትን ነገር በመፍራት እንደኾነ ብትጠይቋቸው በቁጣና ኃይል ቃል ዝም ያሰኟችኋል::

ከስንፍና መገለጫዎች ሁሉ ዋነኛውና የተለመደው ስንፍና ራስን በሆነ ባልሆነው ፋታ መንሳት ነው:: ስለዚህ ለስንፍና መድኃኒቱ ምንድን ነው? መልሱ ኃብት ፍለጋ ነው::

ለብዙዎቻችን ኃብትን መፈለግ (ስግብግብነት) መጥፎ መስሉ ይታየናል:: ‹‹ስግብግብ ሰዎች መጥፎዎች ናቸው::›› ትለኝ ነበር እናቴ:: ሁላችንም ውስጥ ምርጥ

ፍላጎት አለ፡፡ ይህንን ገደብ የለሽ ፍላጎታችንን አስደሳች ነገሮች የራሳችን የማድረግ ለመገደብ ወላጆቻችን ፍላጎትን ከሀጢያት ጋር ደብልቀው መጥፎ መጥፎውን ይነግሩናል፡፡ ወንድሞችና እህቶች እንዳሉህ «አንተ ሁሌም ስለራስህ ብቻ ነው የምታስበው፡፡

አታውቅም» ስትል እናቴ አዘውትራ ትወቅሰኝ ነበረ፡፡ አባቴ ደግሞ አዘውትሮ እኔ የምፈልጋቸውን ነገሮች በሙሉ መግዛት እንደማይችሉና ገንዘብ ከዛፍ ላይ እንደማይሸመጠጥ ይነግረኝ ነበር፡፡

በጣም የሚያበሳጨው ደግሞ «ይህን በመግዛት ራሴን መስዋዕት እያደረግኩልህ ነው፡፡ ይህን የምገዛልህ እኔ በአንተ ዕድሜ ሳለሁ ይህን ዕድል ባለማግኘቴ ነው» ማለታቸው ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ጎረቤታችን ያሉ ልጆች ከነበራቸው አሻንጉሊቶች ብዛት የተነሳ አባታቸው ጋራዥ ውስጥ መኪና ማስገባት ሁሉ ተቸግሮ ነበር፡፡ የጎረቤቶቼ አባት «የፍላጎት ስሜት እንዲያድርባቸው አልፈልግም» ነበር የሚለው፡፡ ይህ ሰው ልጆቹን እጅግ አሞላቆ ያሳደገ ቢሆንም ሲያድጉ የኮሌጅ ትምርታቸውን ወጪ የሚሸፍን አሊያም ለጊለኛ ዘመኑ መጦሪያ የሚሆን በቂ ገንዘብ አላስቀመጠም ነበር፡፡

ሐብታሙ አባቴ «ይህን መግዛት አልችልም» የሚለውን ቃል በጣም ነው የሚያወግዘው፡፡ ሐብታሙ አባቴ ልጆችን የሚመክረው «እንዴት ነው ልገዛው የምችለው?» ብለው እንዲያስቡ ነው፡፡ «አልችልም» የሚል ቃል አዕምሮን እንደሚደፍን በመግለፅ ለችግሮች መፍትሔ ለመፈለግ የሚገፋፋውን «እንዴት ነው ልገዛው የምችለው?» የሚለውን ቃል እንድጠቀም ነበር የሚያበረታታኝ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ «መግዛት አልችልም» የሚል ቃል ውሸት እንደሆነ አድርጎ ነው የሚወስደው፡፡ የሰው ልጅ መንፈስም ይህን በደንብ አድርጎ ያውቀዋል፡፡ ሐብታሙ አባቴም «የሰው ልጅ መንፈስ በጣም ኃይለኛ ነው! ማንኛውንም ነገር ማድረግ እንደሚችል ያውቀዋል» ይላል፡፡

«ይህን መግዛት አልችልም» የሚል ሰነፍ አዕምሮ ባለቤት መሆን በውስጥህ ጦርነት እንዲቀሰቀስ ያደርጋል፡፡ መንፈስህ ቁጡ ነው! ሰነፉ አዕምሮህ ውሸቱን ሊያቆም ይገባል፡፡ መንፈስ እንዲህ ይላል «ደሀ መሆን ሰልችቶኛል፡፡ ሐብታም ለመሆን እንጣር» ሰነፍ አዕምሮ ደግሞ «ሐብታሞች ስግብግቦች ናቸው፡፡ ሐብት ሲበዛ ምን ያደረግልኛል፡፡





ልከስር እችላለሁ፡፡ ያው ዞሮ ዞሮ ብዙ እየሰራሁ አይደል? ዛሬ ማታ እንኳን የምሰራውን አታይም? አለቃዬ ጠዋት ጨርሼ እንዳስረክበው ይፈልጋል» ይላል፡፡

«ልገዛው አልችልም» ብስጭትንም ያመጣል፡፡ ረዳት አልባነት ወደ ተስፋ መቁረጥ ይመራል፡፡ «ግድየለሽ» ሌላ ቃል ነው፡፡ «እንዴት ልገዛው እችላለሁ?» ብሎ ማሰብ አዳዲስ አማራጮች ደስታንና ሕልሞችን ወደ ምናብ ያመጣል፡፡

ስለዚህ ሐብታሙ አባቴ ለእኔም ሆነ ለማይክ እምብዛም ስጦታ አበርክቶልን አያውቅም፡፡ ይልቁን «እንዴት ልታገኙት ትችላላችሁ?» ብሎ ነበር የሚጠይቀን፡፡ ይህ በራሳችን ገንዘብ የምንማረውን የኮሌጅ ትምህርትንም ያካትታል፡፡ ኮሌጅ መግባታችን ዋናው ግብ ሳይሆን ግባችንን ለማሳካት የምናልፍበት መንገድ/ሂደት ነው፡፡

ዛሬ የማስተውለው ችግር በርካታ ሰዎች በስግብግብነታቸው ሲሸማቀቁና ጥፋተኛነት ሲሰማቸው ማየቴ ነው፡፡ ይህ ከልጅነታቸው ጀምሮ የታነፁበት መንገድ ያመጣው ችግር ነው፡፡ ብዙ ሰዎች ሳያስቡት «ይህን ማግኘት አትችልም» እንዲሉ ታንፀው ነው ያደጉት፡፡

ልክ ሥራዬን እቁሜ ራሴን ሐብታም የማድረግ ጥረት ስጀምር ለራስ «በድጋሚ ወደ ሥራ ሳልመለስ እንዴት መኖርና ሃብታም መሆን እችላለሁ?» የሚል ቀላል ጥያቄ ነበር ያቀረብኩት፡፡ ልክ ይህ ጥያቄ ሳቀርብ አዕምሮዬ በፍጥነት መልሶችንና መፍትሔዎችን ያመነጭ ጀመር፡፡ አስቸጋሪው ነገር ወላጆቼ «ድጋሚ አንተን ልንከባከብ አንችልም! ይህን ውሳኔህን አንቀበልም! ስለራስህ ብቻ ማሰብ አቁም» በሚል የሚያቀርቡትና ሎሎች እኔን ጥፋተኛ የሚያደርጉ ተቃውሞዎች ስለነበሯቸው ነበር፡፡

ስለዚህ ቅድም እንዳልነው ስንፍናን ለማሸነፍ መፍትሔው ስግብግብነት ነው፡፡ አንድ ሰው ስንፍናን ለማስወገድ «ይሄን ያክል ራሴን ሳለማጨናነቅ ብሰራስ ህይወቴ እንዴት ሊሆን ይችላል?» አሊያም «የምፈልገውን ያክል ገንዘብ ባገኝስ ምን ልሰራበት እችላለሁ» ብሎ ሊጠይቅ ይገባዋል፡፡ ያለ ስግብገብነትና የተሻለ ነገር እንዲኖረን ካለመፈለግ ለውጥ አይታሰብም፡፡ ዓለም የምትሻሻለው ሁላችንም የተሻለ ሕይወት እንዲኖረን ስለምንፈልግ ነው! አዳዲስ ፈጠራዎች ዕውን የሚሆኑት የተሻለ ነገር ስለምንፈልግ ነው፡፡

ባሸሸኸው ቁጥር ‹‹ይህ ነገር ለእኔ ምን
ስለዚህ የግድ መሥራት ያለብህን ነገር ስግብግብ ሁን:: ለስንፍና
ትርጉም አለው?›› ብለህ ራስህን ጠይቅ:: በመጠኑም ቢሆን ስግብግብነት ጥሩ ላይሆን ይችላል::
መፍትሔው እሱ ነውና:: እርግጥ ነው የበዛ ስግብግብነት ስሜት ከስግብግብነት የከፋ ነው፤
ሐብታም አባቴ ደግሞ በተለየ መልኩ ‹‹የጥፋተኝነት ስሜት ከስግብግብነት የከፋ ነው፤
ፀፀት ነፍስን ያሸብራልና›› ይላል ለእኔ ደግሞ ኤሊኖር ሩዝቬልት ‹‹በሰራኸው
ባልሰራኸውም መወገዝህ ካልቀረ ውስጥህ ትክክል ነው ብሎ ያመነውን አድርግ›› ያለው
በይበልጥ ይስማማኛል::

**ምክንያት 4 ከፉ ልማድ**

ሕይወታችን ከትምህርታችን ይልቅ የልማዳችን ነፀብራቅ ነው:: ሽዋዚንገር
የሚተውንበትን ካሩፕ የተሰኘ ፊልም ካየን በኋላ አንዱ ጓደኛችን ‹‹እንደሽዋዚንገር ዓይነት
ጡንቻ ቢኖረኝ እመኛለሁ›› አለ:: ብዙዎቻችን በስምምነት ራሳችንን ወዘወዝን::
ሌላኛው ጓኛችን ‹‹በፊት ቀጫጫ እንደነበር ሰምቼአለሁ::›› አለ ‹‹አዎ እኔም
ሰምቼአለሁ፤ እንዲህ የሆነው ስፖርት በየዕለቱ በመስራቱ ነው›› አለ ሌላኛው::
አንዱ ተጠራጣሪና ጨለምተኛ ጓደኛችን ግን ‹‹እንዲህ የሆነው ከተፈጥሮው ነው፤
ይልቅስ ይሄን እንተውና ቢራ እንጠጣ›› አለ::

ይህ ልማድ ባሕሪያችንን እንዴት እንደሚቆጣጠር የሚያሳይ ምሳሌ ነው:: አንድ
ጊዜ ሐብታሙ አባቴ ስለ ሐብታሞች ልማድ የጠየቅኩት ትዝ አለኝ:: ለዚህ ጥያቄዩ
ቀጥተኛ መልስ በመስጠት ፋንታ በምሳሌ ያስረዳኝ ጀመር

‹‹አባትህ ለመብራትና ውሃ የሚከፍለው መቼ ነው?›› ሐብታሙ አባቴ ጠየቀኝ::

‹‹በወር መጀመሪያ›› መለስኩ

‹‹መከፈል ያለበትን ከከፈለ በኋላ ምን ያክል ይተርፈዋል?›› ደግሞ ጠየቀ::

‹‹በጣም ትንሽ›› የእኔ መልስ

‹‹ለዚህ ነው የሚቸገረው፤ እጉል ልማድ አዳብሯል››

‹‹ሐብታሙ አባትህ ከራሱ አስቀድሞ ለሎችን ይከፍላል:: ለራሱ የሚከፍለው
ከተረፈው ብቻ ነው›› ቀጠለ ሐብታሙ አባቴ

‹‹ብዙ ጊዜ ዕዳውን ከፋፍሎ የሚተርፈው አይኖርም:: ነገር ግን ዕዳውን መክፈል
የለበትም ብለህ ታስባለህ?››





‹‹በጭራሽ:: ዕዳን በጊዜ መክፈል ተገቢ እንደሆነ በፅኑ ነው የማምነው:: ነገር ግን
ለራሴ የምከፍለው ከመንግስት እንኳን ሳይቀር አስቀድሜ ነው::››

‹‹ቆይ በቂ ገንዘብ ባይኖርህስ?›› አልኩት ተገርሜ::

ዘና ብሎ ‹‹ያው ነው፤ ገንዘብ እንኳን በበቂ ሁኔታ ባይኖረኝ ከራሴ የሚበልጥ
ባለመኖሩ ለእራሴ ነው ቅድሚያ የምከፍለው›› አለኝ::

ግራ እየተጋባሁ ‹‹እእ... ለመንግስት ዕዳህን ባትከፍል ችግር አይፈጠርም?››
አልኩት::

‹‹አዎ:: ግን ያ የሚሆነው ካልከፈልኩ ነው:: እኔ እያልኩ ያለሁት ግን
አልከፍልም ሳይሆን ራሴን አስቀድማለሁ ነው›› አለኝ::

‹‹በቂ ገንዘብ ሳይኖርህ እንዴት እንዲህ ማድረግ ትችላለህ?››

‹‹ጥያቄው መሆን ያለበት እንዴት? ሳይሆን ለምንድን ነው››

‹‹እሺ... ለምን?›› ጥያቄ አቀረብኩ::

‹‹ተነሳሽነት›› ቀጠለ ‹‹ሳልከፍል ብቀር በጣም የሚያስጨንቀኝ ማን ይመስልሀል
አበዳሪዎችና መንግስት ወይስ ራሴ?›› ጠየቀኝ::

‹‹አበዳሪዎች ሳትከፍላቸው ብትቀር ከራስህ ይልቅ ቁጣቸው ይነዳል››

‹‹አየህ፤ ለራሴ ከከፈልኩ በኋላ ግብርና ዕዳዬን የመክፈል ከፍተኛ ሸክም
በጫንቃዬ ላይ ያርፋል ስለዚህ ይህ ጫና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን እንድፈጥር
ያነሳሳኛል:: ተጨማሪ ሥራዎችን እሰራለሁ፤ ሌሎች ድርጅቶችን እከፍታለሁ፤ አክሲዮን
ገዝቼ እሸጣለሁ ብቻ እነዚህ እኔ ላይ ገንዘብ ያላቸው አካላት ሳልከፍላቸው ቀርቼ ማሳደድ
ሳይጀምሩኝ በፊት ገንዘባቸውን ለመክፈል በጣም እተጋለሁ:: አየህ ለራሴ የምከፍለው
መጨረሻ ቢሆን ኖሮ ከሌሎች አካላት የሚመጣብኝ ጫና አነስተኛ በመሆኑ ስለማልተጋ
ደሐ ሆኜ እቀር ነበር›› ሲል በሰፊው አብራራልኝ::

አፌን ከፍቼ ካዳመጥኩት በኋላ ‹‹ስለዚህ መንግስትንና አበዳሪዎችህን ፍርሐት
ነው ሐብታም እንድትሆን ያደረገህ?›› የሚል ጥያቄ አቀረብኩለት::

‹‹ትክክል›› አለኝ ሐብታሙ አባቴ::

የሐብታም አባቴ ገለፃ ተመችቶኝ ‹‹ስለዚህ ለራስ ቅድሚያ የምከፍል ከሆነ
በገንዘብ አቅም ጠንካራ እሆናለሁ ማለት ነው?›› ስል ጠየኩት::

በእምንታ ራሱን ነቀነቀ::

‹‹ሰራሴ የምከፍለው መጨረሻ ከሆነ አሊያም ምንም የማልከፍል ከሆነ ደሐ መሆኔ የማይቀር ነው:: ከዚያ መንግስትና ሌሎች አበዳሪዎቼ ሕይወቴን ማመሳቀላቸው አይቀርም ማለት ነው?››

አሁንም ሐብታሙ አባቴ በእምንታ ራሱን ነቃነቀ::

ምክንያት 5 - ዕብሪት

ሐብታሙ አባቴ ይህን አስመልክቶ ዘወትር ‹‹የማውቀው ነገር ገንዘብ ያስገኝልኛል:: አለማወቄ ደግሞ ያከስረኛል:: እብሪተኛ በሆንኩ ቁጥር መከሰሬ የማይቀር ነው:: ምክንያቱም ዕብሪት ሲጠናወተኝ የማላውቀው ነገር አስፈላጊ መስሎ አይታየኝም›› ሲል ይነግረኛል::

ብዙ ሰዎች ድንቁርናቸውን ለመሸፈን ሲሉ ዕብሪተኞች ይሆናሉ:: በገንዘብ ዙሪያ ከሂሳብ ባለሙያዎች ጋር አሊያም ከሌሎች ባለሐብቶች ጋር ሳወራ ዕብሪት ሲጠናወታቸው አስተውላለሁ::

በውይይት ሳይሆን ጮኾ በመናገር ሊያሳምኑኝ ይሞክራሉ:: የዚያኔ ስለሚያወሩት ጉዳይ በቅጡ እንደማያውቁ እረዳለሁ:: እየዋሹ ባይሆንም እውነቱን ግን እየተናገሩ አይደለም::

በአንድ ጉዳይ ላይ ዕውቀት እንደሌለህ በተሰማህ ጊዜ ባለሙያ ጋር በመሄድ አሊያም መጽሐፍት በማንበብ ራስህን ማስተማር ልመድ::





# መጀመር

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## መጀመር

ለእኔ ሀብትን ማካበት ቀላል ነበር ብዬ ማውራት ብችል ምንኛ ደስ ባለኝ ነበር!ግን አልነበረም:: እናም እንዴት ልጀምር ለሚለው ጥያቄ የምሰጠው ምላሽ ከዕለት ተዕለት ተሞክሮዬ በመነሳት ይሆናል:: በየቀኑ የንግድ ዕድሎችን ማግኘት ቀላል ነው:: ለዚህ ቃል እገባላችኋለሁ:: ልክ ብስክሌት እንደመጋለብ ነው:: ከጥቂት መነሳት መውደቆች በኋላ እጅግ ቀላል ይሆናል::

ነገር ግን የሚሊየን ዶላር ስምምነቶችን ፈልጎ ለማግኘት ገንዘብ ነክ ዕውቀታችንን መጠቀም ግድ ይለናል:: ይህንንም ለማድረግ የምትችልባቸውን ደረጃዎች እነግርሃለሁ:: የተወሰኑትን ልትከተላቸው ከወደድክ መልካም ነው! ካልወደድክም የራስህን ደረጃ መስርት::

1. ከሚታየው የበለጠ ምክንያት እፈልጋለሁ

የመንፈስ ሃይል:: በርካታ ሰዎችን ሀብታም መሆን ይፈልጉ እንደሆነ ብትጠይቋቸው መልሳቸው አዎን ነው:: ነገር ግን ከዚያ ቀጥሎ እውነታው ይመጣል:: ሀብታም ለመሆን መንገዱ ጠመዝማዛማ መሆኑ ይታያቸዋል:: እናም ቀላሉ መንገድ ለገንዘብ መስራት መሆኑን ይመርጣሉ:: አስቀድሜ እንደገለጽኩት ሀብታም መሆን ቀላል አይደለም!የዚያኑ ያህል ከባድም አይደለም:: በሕይወት ውስጥ ያለ ጠንካራ ምኞትና ምክንያት ማንኛውም ነገር ከባድ ነው:: ሀብታም ለመሆን ጠንካራ ምክንያት ከሌለህ ከዚህ በኋላ ማንበቡ ምንም አይጠቅምህም::

2. በየቀኑ እመርጣለሁ:-

የምርጫ ኃይል::ሰዎች ነጻ አገር ውስጥ መኖር የሚፈልጉበት ምክንያት እሱ ነው:: የመምረጥ ስልጣን እንዲኖረን እንፈልጋለን::

በገንዘብም በኩል በእያንዳንዷ ወደኪሳችን በምትገባ ዶላር ላይ ለመወሰን ስልጣኝ አለን:: ገንዘብ አወጣጣችን ማንነታችንን ያሳያል:: ድሆች ገንዘብ የሚያወጡበት መንገድ ያልተደራጀ ነው::

በርካቶች ሀብታም ላለመሆን ይመርጣሉ:: ምክንያቱም ከዘጠና ከመቶ በላይ ለሚኾኑ ሰዎች ሀብታም መሆን ውጣውረድ የበዛበት ነው:: እናም የሚከተሉትን ዓይነት አባባሎች





ይፈጥራሉ::‹‹ ለገንዘብ ብዙም ፍላጎት የለኝም›› ወይም‹‹ መቼም ቢሆን ሀብታም አልሆንም›› ወይም ‹‹ ልጨነቅ አይገባኝም!ገና ወጣት ነኝ›› ወይም‹‹ የገንዘብን ጉዳይ ባለቤቴ ይጨነቅበታል/ትጨነቅበታለች›› ወዘተ::

በመጀመሪያ ዕውቀት ለማግኘት ሀብትህን መስዋዕት አድርግ

ሐብት ሁሉ የሚበለፅገው በአእምሮህ እንደሆነ ማወቅ ይገባሃል:: ሀብት ሀያል ሲሆን እርሱን ተጠቅመህ የማይታመኑ ተግባራትን መፈፀም ትችላለህ:: ዕድሜያችን ከፍ ማለት ሲጀምር በአእምሮአችን የተሻለ ነው የምንለውን አኗኗር እናስቀምጣለን:: ለምሳሌ ኢምቲቪ ቀኑን ሙሉ ማየት፣ የጎልፍ ሜጋዚን ማንበብ ወይም የገንዘብ አጠቃቀም ዕቅድን መማር ትፈልጋለህ:: ምርጫው በእጅህ ሲሆን ብዙዎች አዲስ ስራን ከመጀመር በተጀመረበት ጣልቃ ይገባሉ:: መቅደም ያለበት ግን ሀብትህን በምንና እንዴት ባለ ቦታ ማዋል እንደሚገባህ መማሩ ነው::

በአንድ ወቅት አንዲት ሀብታም ሴት ጓደኛዬ የመኖሪያ ቤቷን ሌባ ሰብሮ ከገባ በኋላ ያላትን ጎጦች፣ ቴሌቪዥንና ቪሲአር ከዘረፈ በኋላ መጽሀፎችዋን ተወላት:: ልክ እንደሌባው ብዙዎቻችን (90%) ቲቪ ስንገዛ 10% ደግሞ የቢዝነስ መጽሐፍትን ገዝቶ ማንበብ ምርጫችን ነው::

ስለዚህ እኔ የማደርገው ምንድነው? ወደ ሴሚናር በመሄድ እውቀትን እገበያለሁ:: በተለይ ሁለት ቀን የሚወስዱ ሴሚናሮች (የውይይት መድረኮች) ምርጫዬ ሲሆኑ ለዚህም ዋናው ምክንያት በጉዳዩ ዙሪያ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖረኝ ስለሚያደርጉኝ ነው::

በ1973 እኤአ ቀኑን ባላስታውሰውም ቴሌቪዥን እያየሁ ነበር:: አንድ ሰው ስለ 3 ቀን ሴሚናር ሲያስተዋውቅ የሴሚናሩም አላማ ስለ ሪል ስቴት ቢዝነስ ነበር:: ከሴሚናሩ በኋላ እርግጠኛ አትራፊ ውጤት ስለማግኘት አስረዳ:: እኔም 385 ዶላር በመክፈል ሴሚናሩን ስካፈል በውጤቱም 2 ሚሊዮን ዶላር ማትረፍ ችያለሁ:: ከብሩ በላቀ መልኩ ሴሚናሩ ህይወቴን የሚቀይር ዕውቀትን ሲሰጠኝ ከኮርሱም በኋላ ብዙ ኮርሶችን ከመውሰድ አድኖኛል:: ጠቃሚነቱን ለመግለፅ ቃላቶች ያጥሩኛል::

የሚደመጡ ነገሮችን እወዳለሁ:: በፈለግኩ ጊዜ መልሼ መላልሼ ማዳመጥ መቻሌ ደግሞ ለመውደዴ ምክንያት ነው:: የፒተር ሊይንችን ካሴቶች አዳምጫ አውቃለሁ፡ ሆኖም አንድ ቀን ፈጽሞ የማልስማማበትንና የማልቀበለውን ነገር ተናገረ::

እኔ ግን ነገሩን ችላ ከማለትና ከማለፍ ደጋግሜ ማዳመጤን ቀጠልኩ! ምናልባትም ሀያ ጊዜ ይሆናል የደገምኩት። ሆኖም አእምሮዬን ሰፋ በማድረግ ሲናገር የፈለገውን ሳሰላስል በሚገርም ሁኔታ አለመስማማቴ በመስማማት ተቀይሮ እጅግ ድንቅ ትምህርትንና ልምዱን የራሴ አደረግኩ።

በውጤቱም ነገሮችን እመለከት የነበረው በአንድ ጎናቸው ብቻ እንደሆነ ከፒተር ምልከታ በመረዳት አማራጭ ማካተት እንዳለብኝ አስተማረኝ። ስለሆነም የፒተር ንግግር ደጋግሜ አዳምጬ ከተረዳ በኋላ በነገሮች ላይ ሰፋ ያለና አማራጭን የተመላ አስተሳሰብ እንዳዳብር አድርጎኛል። አመሰግናለሁ ፒተር። አንደኛው መንገድ ችግር ማየት መቻል ሲሆን ዋጋውም ከከበረው ውድ ዕቃ ይበልጣል።

አሁን ላይ ‹‹ፒተር ይህን ያለው ለምንድነው?›› ወይ ‹‹የአለማችን ቁጥር አንድ ሀብታሞች እዚህ የደረሱት እንዴት ነው?›› ብዬ እራሴን ስጠይቅ መልሱ እራሳቸውን መመልከት የሚያስችሏቸውን መጽሐፍት ማንበብና ለችግራቸው መፍትሄ ያገኙ ዘንድ አእምሮን ሰፋ አድረጎ ማሰብን በመለማመዳቸው እንደሆነ ይታየኛል። እራሱን ዝቅ አድርጎ የሚያስብና አስተዋይ ያልሆነ ሰው ሁኔታዎችን ተጋፍጦ ለስኬት መድረስን አደጋ እንዳለው ስለሚያስብ በህይወቱ ላይ ለውጥ አይታይም።

አስተውል! በህይወትህ ስለአንድ ነገር ስትማር ስህተትን ልትሰራ ትችላለህ። ስህተት መስራትህ ደግሞ ለለትምህርቱ በደንብ ለማወቅ ሂደት ላይ ነህ ማለት ነው።

አስተዋይ አለመሆን የችግሮችህ አንደኛው አካል እንደሆነ እትመን። አለማስተዋል ለመቀየር መጣርን ዘወትር አዳብር። አለማስተዋል ሳይሆን አለማስተዋልን በፀጋ መቀበል ወይ አስተዋይ ነኝ ብዬ ማሰብ መጥፎ በሽታ መሆኑን ጠንቅቀህ ተረዳ።

አንዳንድ ብልህ ነኝ የሚሉ ሰዎች አዲስ ሀሳብና አመለካከት ሲያጋጥማቸው ከራሳቸው ሃሳብ ጋር ከማስታረቅ ይልቅ የሀሳብ ፍጭትን በአዕምሮአቸው ይለማመዳሉ። ይህም ብልህነት ካለማስተዋል ጋር በመቀላቀል በውጠቱም አስተዋይ አለመሆንን ንብረታቸው ያደርጋሉ። እያንዳንዳችን የተማሩና ብቁ ናቸው የምንላቸው ሰዎች ስናውቃቸው ትክክለኛ ማንነታቸው ሲፈተሽ ግን ባዶነትን ያሳያል። ዕውነተኛ ብልህ አዲስ ሀሳቦችን ሲቀበል ከነበረው አመለካከትም ጋር ያጣጥመዋል።





ማዳመጥም ከመናገር ሲበልጥ! ባይበልጥ ኑሮ ፈጣሪያችን ሁለት ጆሮን ከአንድ አፍ ጋር ባልፈጠረልን ነበር። ብዙ ሰዎች ከማዳመጥ ይልቅ መናገር በብዛት ሲተገብሩ የሚያስቡትም በአፋቸው ነው። አንተ ግን የሰዎችን ሀሳብ በአንክሮ በማዳመጥ ካልገባህ በመጠየቅና ክርክርን በማስወገድ አዳዲስ አመለካከቶችን ንብረትህ አድርግ።

ሀብቴን ለማዳበር ረዘም ያለ ሂደት ያለፍኩ ሲሆን ለውጤቱም ማግር እንደብዙዎች ገንዘቤን ኢንቨስት አድርጌ ስራን እንዳይሰራ ከማድረግ ማሰራትን በመምረጤ ብቻ ነው። ቤትን ወይም ሪል ስቴትን ገዝቶ ያለስራ ማስቀመጥ ሀብትን ከማዳበር ማቀጨጭን ሲያስከትል በውጤቱም አላስፈላጊ ክስረትን ያስከትላል።

3. ጓደኛን በጥንቃቄ ምረጥ

የተለያዩ የኑሮ ደረጃ ያላቸው ጓደኞች ሲኖሩኝ ለጓደኝነት ምርጫ መስፈርቴም የሀብት መጠናቸው ሳይሆን ሊያስተምሩኝ የሚችሉት ቁም ነገር ብቻ ነው።

‹‹እውቀት የሀብት ምንጭ ነው›› እንዳልኩት ሁሉ የጓደኛ አመራረጥ መስፈርቴም ይሄው ብቻ ነው። ሀብት ኖሯቸው ዕውቀት ካላቸው በስራም ስለምንተጋገዝ ጥብቅ ጓደኝነትን ስንፈጥር ሆኖም የዚህ አይነት ሰዎች ለቁጥር አናሳ ናቸው፡

ሆኖም አንድ የተለየ ነጥብ /ሃሳብ ሲኖረኝ ሀብታም ጓደኞቼ ስለገንዘብ በማይሰለች ሁኔታ ስለሚነግሩኝና እኔም ሃሳባቸው ስለሚስበኝ ብዙ ቁም ነገሮችን ከዕነርሱ እማራለሁ። ድሆች ግን ይህን አይነት ጨዋታ አይስባቸውም። ከዚያም አልፎ የስግብግቦችና ያለተማሩ ዲስኩር እንደሆነ ያስባሉ። ከሁለቱም ግን ትምህርትን አገኛለሁ።

በአጭር ጊዜ በቢሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ የሚያካብቱ ብዙ ጓደኞች ሲኖሩኝ ገንዘብ በበቂ ሁኔታ የሌላቸው ጓደኞቻቸው መጥተው የሚጠይቋቸው ሀብትን እንዴት እንዳዳብሩ ሳይሆን ብድር ወይም ስራን እንዲሰጧቸው ነው።

<u>ማስጠንቀቂያ፡-</u> የምወዳቸውን የማከብራቸው ደሀ ጓደኞች አሉኝ። ሆኖም ብወዳቸውም በእነርሱ የህይወት መስመር መሄድን አልመርጥም። አንተም ድሀ ሆነው ማደግና መለወጥ በማይፈልጉ ሰዎች ሀሳብና የህይወት ፍልስፍና እትሂድ። አይቻልም ከሚሉ ሰዎች ይልቅ ይቻላል የህይወት መፈክራቸው ከሆኑ ሰዎች ጋር ጓደኛነትን ፍጠር። ተረቱም የሚለው ተመሳሳይ ክንፍ ያላቸው ወፎች አብረው ይበራሉ አይደል?

አንዳንዶች ወርቅ አይገኝም ሲሉ ሌሎች ይገኛል መፈከራቸው ነው:: አንተ ግን እንደብልሆች ሁለቱንም አዳምጥ:: ልክ እንደ ድሆች ሳይጠና አይሆንም ከማለት ግን ይሆናልን ምረጥ::

አንድ የቀረበ ጓደኛዬ ስለኢንቨስትመንት ማውራት ይቀናዋል:: ከጥቂት ዓመታት በፊት 6% ጥቅም የሚያገኝበት ሥራን እንዳገኘ ሲያዋየኝ እኔ ደግሞ 16% ጥቅም ያለውን ቢዝነስ እየሰራሁ ነው:: ራስህን አለመገደብ የተሻለ ነገር እንድታገኝ እንደሚያደርግ አስተውል:: እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል እንዲሉ::

ሐብትን ለማበልፀግ ተግዳሮት ከሚሆኑ ነገሮች ሁሉ የከፋው ግትርነት ነው:: የግትርነት ውጤት ደግሞ ከማህበረሰቡ ጋር እንዳንራመድ ደርገናል:: ሆኖም በተቃራኒው ከተንቀሳቃስን በገበያ ውስጥ ተፈላጊነታችን ብቻ ሳይሆን የምናገኘው ውጤታነታችንን ማሳደግም እንችላለን::

ከሰዎች ጋር በሚኖርህ የንግድ ስምምነት እነርሱ ከሚሉት አኳያ ብቻ ከመመልከት በእሱ ውስጥ አዲስን ነገር ማየት አድማስህን ማስፋት የተዋጣልህ እንድትሆን ያግዝሃል:: በማዕበልና ወጀብ ውስጥ አዲስ የህይወት ጭላንጭል እንዳለ ማሰብ ሲኖርብህ የአሸናፊዎችም መለያ ባህሪያቸው ይሄው የአስተሳሰብ ምጥቀታቸው ብቻ ነው::

ብቁ ባለሃብቶች ጊዜ መርጠው ወደ ገበያ የማይገቡ ናቸው:: እንዴ ስኬትን ቢያጡ እንኳን እጃቸውን አጣምረው መቀመጥን ትተው ለሁለተኛ ወይም ቀጣይ አማራጮች ቦታ በመስጠት እንደገና ይጥራሉ:: በአሁን ጊዜ ተፈላጊና ወቅታዊ ያልሆኑ ነገሮችን እያስፈልግም ከማለት ተፈላጊ ከሚሆኑባቸው ቀናት ቀድመው በመግዛት ገበያ በሚፈልግበት ወቅት ለሽያጭ ያቀርቡታል:: ወቅትን ብቻ ጠብቀው ንግድን የሚሰሩ ነጋዴዎች መንጋውን እንደሚከተል በግ ሲሆኑ ብልህ ባለሀብቶች ግን ገንዘባቸው ለስራ የሚያውሉት ቢዝነሱ ገና በሌሎች ዓይን ውስጥ ሳይገባ ነው:: የሚሰሩት ስራ ትርፋማ እንደሆነም የሚረዱት ሲሸጡ ሳይሆን በጅምሩ ለመሸጥ ሲገዙት ነው:: ከዚህም የምንረዳው ትዕግስት የህይወት ስንቃቸው እንደሆነ ሲሆን በቀጣይ ስለሚተገብሩትም ቀደሙው መረዳታቸው ልዩ ያደርጋቸዋል::





እቻ ጓደኛህን ስትመርጥ በንግድ አለም ውስጥ የመረጃ የዕውቀት ሰው መሆኑን መገንዘብ ይገባሀል:: በውጤቱም በስራህ ውስጥ ክስረትን ከመጎናፀፍ ትርፍን ታገኛለህ:: ይህ ነው እንግዲህ ገንዘብን በአግባቡ የመጠቀም ብልህነት::

4. ***ዘወትር አንድን ዕውቀት ከተጎናፀፍክ በኋላ አዲስ ነገር ለመማር አትቦዝን:*** ዕውቀት ማለቂያ የሌለው ውቅያኖስ ነውና::

በንግድ አለም የንግዱን እንቅስቃሴ በቶሎ መረዳትና ወደተግባር መግባት የሀይል ሁሉ መሠረት ነው:: ዳቦን ለመጋገር ስለዳቦ አገጋገር ቅድ መ ዕውቀት ሊኖር ሲገባ በገንዘብ ተጠቅሞ ሀብትን ማካበትም ገንዘቡን በስራ ላይ ከማዋል በፊት ስለ ስራው ጠንቅቆ ማወቅን ይጠይቃል::

‹‹የበላ ቢያብል ገላው ይመሰክራል›› እንዲሉ እኔም የእንተንተህ መሰረት የዕውቀት ደረጃህ መገለጫ ነው እላለሁ:: በሌላ አባባል አንድን ድርጊት ከመፈፀምህ በፊት ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግን አትዘንጋ:: ምክንያቱም አእምሮህ የሚያስብና ወደ ተግባር የሚቀይረው አንተ የሰጠኸውን ነው:: ለምሳሌ ምግብ ማብሰልን ከተመኘህ ምግብ አብሳይ ስትሆን ከጠላኸው ደግሞ በሌላ ሙያ መተካት ከተመኘህ እስክትማርና እስክታውቅ ጊዜን ይወስድብሀል:: ስለሆነም ምርጫ ከማድረግህ በፊት ቆም ብለህ ከፍላጎትና ከብቃትህ አንፃር ልትሰለች የማትፈልገውን ሙያ መስክ ምረጥ::

ወደ ገንዘብም ስንመጣ ለዕድገትና መሻሻል መጠቀምና ያለመጠቀም መብቱ በአእምሮህ የሚወሰን ሲሆን ብዙ ሰዎችም የሚያገኙትን ገንዘብ ጥቅም ላይ የሚያውሉት ት/ቤት በተማሩት ቀመር መሠረት ነው:: ይህም ለገንዘብ መስራት ይባላል:: ጠዋት መነሳት፣ ስራ መሄድ መስራት ከዚያ ዕለት ወጪ ማውጣት ወዘተ::

ከ26 ዓመት በፊት ‹‹How To Buy Real Estate Foreclosures›› በሚል ርዕስ የአንድ ሳምንት ስልጠና የወሰድኩ ጊዜ አንድ አዲስ ቀመርን ለመማር ቻልኩ:: ከስልጠናው በኋላ በቀጣይ የተገንዘብኩት ነገር ቢኖር፣ አንድን ሃሳብ ወደ ተግባር ለመቀየር ዲሲፒሊን ወሳኝና ወሳኝ ነገር መሆኑን ነው:: ብዙ ሰዎች ያጡት ነገር ይህንን ነው:: ለሦስት ዓመታት ያህል በዜሮክስ ኩባንያ በምሰራበት ወቅት ፎርክሎዥርን እንዴት መጠቀም እንደምችል በተከታታይ ትምህርት እወስድ ነበር:: በዚህ ተጠቅሜ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ማግኘት ቻልኩ:: በአሁኑ ሰዓት ግን እኛን የበለጠ ተጠቃሚ ያደረገን

ቢዝነስ አሁን አዝጋሚና ብዙ ሰዎች የሚንቀሳቀሱበት ዘርፍ ሆኗል:: ለትርፋማነቱ መቀነስ ዋናው ምክንያት በዘርፉ አትራፊነት የተነሳ የብዙዎችን ትኩረት መሳብ በመቻሉ ነው::

በተማርኩት ቀመር አትራፊ መሆን ከቻልኩ በኋላ፣ በተጨማሪ ሌላ አዲስ ቀመርን በመማር ዝግጅት ጀመርኩ:: ከዚህ በፊት ብዙ ትምህርቶችን ስማር ጠቃሚ የምላቸውን ዕውቀቶች አልገበየሁም ነበር:: ምንም እንኳ አዳዲስ ነገሮች ማግኘቴን የማልክደው ሀቅ ቢሆንም::

በንግድ ዙሪያ የተለያዩ ትምህርቶች እና ስልጠናዎችን በመውሰዴ በሪል ስቴትና በአክሲዮን ገበያ ዘርፍ ውጤታማ እንድሆን አድርጎኛል:: አብዛኛዎቹ መለስተኛ ኮሌጆችና የማህበረሰብ ተቋማት በገንዘብ ዕቅድ ዙሪያ የሚሰጣቸው አጫጭር ስልጠናዎች ጥሩና ገንቢ ዕውቀትን ይሰጣሉ:: የወሰድኳቸውን ስልጠናዎች በቶሎ በጥቅም ላይ የማውላቸው ይመስለኛል:: ብዙ ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚወስድባቸውን የንግድ እንቅስቃሴ እኔ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ትርፋማ ቢዝነስ የምቀይራቸው::

ሌላው ነጥብ በዚች እንደ ሸማኔ መወርወሪያ ከወዲያ ወዲህ በምትጣደፈው አለም ውስጥ አንተን ሰው የሚያዳርግህ የምታውቀው ነገር ብቻ ሳይሆን በአብላጫው ነገሮችን በፍጥነት መረዳት መቻል ያለው ዋጋ ነው:: ይህ ነው እንግዲህ መተኪያ የሌለው እውነታ:: ለገንዘብ መስራት ደግሞ ከዚህ ቀደም ብሉ እንዲያውም ከጋርዮሽ ማህበረሰብ ጊዜ ጀምሮ እያደገ የመጣ አስተሳሰብ እንደሆነ ይታወቃል::

5. ለራስ ቀድሞ መከፈል

ለራስ ቀድሞ የመከፈል ጥበብ ከሁሉም በላይ የሰው ልጅ ትልቁ ሀብት ሲሆን፣ በራስህ ህይወትህ ተግባራዊ ካላደረግከው ፈፅሞ ባለፀጋ መሆን አትችልም:: ብዙ ጊዜ የሉተሪ ዕጣ አሸናፊዎችን ስንመለከት ባሸነፉ በጥቂት ጊዜ ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘባቸውን ጨርሰው ይገኛሉ:: የገዙትም ንብረት ለምሳሌ መኪና እና ቤት የመሳሰሉትን ንብረቶች ከችግራቸው የተነሳ ሲሸጡ ማየት የዕለት ተዕለት ተግባራችን ነው:: በመሆኑም በሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት፣ ሀብታምና ደሃ ወይ መካከለኛ ገቢ በሚል ደረጃ የመከፋፈል ሃይል አለው ቢባል ሀሰት ሊባል አይችልም::





በድፍረት ልናገር የምችለው ስለራሳቸው ዝቅተኛ አመለካከት ያላቸው ሰዎችና ትዕግሥት የሌላቸው ሰዎች ሀብታም ሊሆኑ ቀርቶ በማንኛውም የህይወት መስክ ስኬታማነታቸው አጠራጣሪ መኾኑን ነው::

ከሀብታሙ አባቴ የተማርኩትም፣ ‹‹ጠንካራ፣ ብቁና ትዕግስተኛ ካልሆንክ አለም ታገልሃለች›› የሚልን አባባል ነው:: አለም የምትገፋህ በቆዳህ የቀለም አይነት ወይም በመልክህ ሳይሆን ባለህ ውስጣዊ ልፍስፍስነትና ጥንካሬ አልባው ህይወትህ ብቻ ነው::

በስራ ፈጣራ ዙሪያ ከሰዎች ጋር በምወያይበት ወቅት፣ ሰዎች ልብ እንዲሉት የምፈልገው አንድ ቁም ነገር፣ ከምርታቸው፣ ከአገልግሎትና ከክፍያ ይልቅ የአስተዳዳር ብቃት ክህሎትን ማዳበር እንዲችሉ መጣርን ነው:: የራስህን ቢዝነስ ስትመሰርት ሶስት መሠረታዊ የአስተዳዳር ክህሎቶችን ማዳበር ወሳኝ እርምጃ ነው::

- የገዘብ ፍሰትን መቆጣጠር /ማስተዳደር
- ሰራተኛን በብቃት ማስተዳዳር
- ጊዜን በብቃት መጠቀም

ከላይ የተጠቀሱትን የአስተዳደር ክህሎቶች በስራ ፈጠራ ብቻ ሳይሆን በሁሉም መስኮች ተግባራዊ በሚሆኑበት ወቅት፣ ሁሉም ክህሎቶች ውጤታማ የሚሆኑት ደግሞ ራስን በመግዛትና በመቆጣጠር ነው:: ይህንን ስል ነገሩ ሁሉ ጠበቅ ተደርጎ መያዝ እንዳለበት ልብ ሊባል ይገባል ለማለት ነው::

‹‹የባቢሉን ሀብታሙ ሰው›› በሚል ርእስ በጆርጅ ክላስን በፃፈው መፅሃፍ ውስጥ ለራስ ቀድሞ መክፈል የሚለውን ሀሳብ ሲገልፀው፣ ብዙዎች በአንደበታቸው ለራስ ቀድሞ መክፈል የሚለውን ቃል ደጋግመው ሲናገሩ ቢሰማም፣ በህይወታቸው ግን የሚተገብሩት ቁጥራቸው አናሳ ነው:: በት/ቤት የሚገኙ ዕውቀቶችን ማንበብና መረዳት የሂሳብ ቀመሮችን ጭምር ፈታትቶ ማወቅ ሲያስችሉ፣ ለራስ ቀድሞ መክፈል ግን በት/ቤት ሳይሆን ከህይወት ተመክሮ በመማር የምናዳብረው ዕውቀት ነው::

ከብዙ ቃላት ይልቅ አንድ ሥዕል ብዙ ትምህርት ሲሰጠን፣ ለራስ ቀድሞ መክፈልም በት/ቤት ከሚገኝ ዕውቀት የበለጠ ነው::




ለራሳቸው ቀድመው የሚከፍሉ ሰዎች

ከላይ የተጠቀሰውን ምስል በመመልከት ልዩነቱን ነቅሰህ አውጣ። የትኛው ሥዕል የገንዘብ ፍሰትን ያሳያል። ብዙ ሰዎች ቁጥሩን በማየት ታሪክን ሲዘነጉ፣ የገንዘብ ፍሰትን ከተረዳህ ግን ሥዕሉ የት ጋ ስህተት እንዳለው በቀላሉ ትረዳለህ። ከዘጠና በመቶ በላይ ሰዎች ያለትርፍና ያለሰውጥ ጠንክረው ቢሰሩም እንዴት ውጤታማ እንዳልሆኑ በቀላሉ ትረዳለህ።

ተመልከት! ምስሉ ለራሱ ቀድሞ ስለሚከፍል ሰው የሚያሳይ ሲሆን፣ ግለሰቡ ወጪ ከማውጣቱ በፊት በየወሩ ከሚያገኘው ገቢ ተቀማጭ ማድረግን አይዘነጋም። ብዙዎች ግን ቀደም ብለን የጠቀስነውን የጆርጅ ክላሰንን መፅሃፍ ቢያነቡም በተግባር ላይ ሲያውሉት ግን አይታዩም።

አሁኑኑ ለራስ ቀድሞ መክፈልን ቀዳሚ አድርጉና ዕዳችሁን መክፈል ለጊዜው አቁሙ። ይህን ነው እንግዲህ የምስሉ መልዕክት የሚገልፅልን።








እኔና ባለቤቴ በስራ አጋጣሚ፣ በርካታ የሂሳብ ሰራተኛ፣ መዝገብ ያዥና የባንክ ቤት ሰራተኞችን የመተዋወቅ ዕድል ነበረን። በእነዚህ ባለሙያዎች ዕምነት ለራስ ቀድሞ መክፈል ትርጉም የሌለው ነገር ነው። ራስን ስለመግዛት ግንዛቤ የሌላቸው እነዚህ የሂሳብ ባለሙያዎች ዞሮ ዞሮ ማህበረሰቡም በእነሱ እንዲመራ ማድረጋቸውን ቆም ብለው አስበውት አያውቁም።

በህይወቴ ውስጥ አንዳንዴ ያለምንም ምክንያት የገንዘብ ፍሰቴ ከዕዳዬ የሚያንስና ባለሙያዎች ግን ዕዳዬን እንዲከፍል አለበለዚያ በዕዳ ምክንያት የመታሰርችግር እንደሚያጋጥመኝ ሲያሳስቡኝ፣ እኔ ግን በምላሹ ለራስ ቀድሞ መክፈል ይቅደም ነው የምላቸው።

‹‹በምን?›› ብላችሁ ልትጠይቁኝ ትችላላችሁ። የእኔ መልስ ደግሞ ‹‹ብባቢሉን የከበርቴዎች ከበርቴ›› ታሪክ ውስጥ የሚታየው ለራስ ቀድሞ መክፈልና ውስጣዊ መነቃቃት ለማዳበር የመቻል ታሪክን ነው። ልብ በሉ ሀብታሙ አባቴ ያሳለበኝ እውነታ ከዚህ የሚለይ አይደለም። ከእርሱ ጋር መስራት ስጀምር ዘወትር የሚነግረኝ፣ ሰዎች ራሱን እየገዛ ሲመጣ ችግር እየፈጠሩበት መምጣቱን ነው። በየአቅጣጫውም ክፍያን እንዲፈፅም በስልክና በአካል ጥሪት በረከተበት። እርሱ ግን ቅድሚያ የሚሰጠው ራስን ለመክፈል ነው።

ልብ በሉ! ኃላፊነት ፈፅሞ አይሰማችሁ እያልኩ አይደለም ያለሁት:: ለራስ ቀድሞ መክፈልን ካዳበርክ ዕዳ ውስጥ የመግባት ዕድልህ ጠባብ ነው:: ግብርን ሲያበዛ ቀድሞ መክፈልን ካዳበርክ ዕዳ ውስጥ የመግባት ዕድልህ ጠባብ ነው:: ግብርን ሲያበዛ የሚችል ቢዝነስ መስራት ከአንተ ይልቅ መንግስትን ሲጠቅም፣ እንደዚህ አይነት አካሄድ የሚችል ቢዝነስ መስራት ከአንተ ይልቅ መንግስትን ሲጠቅም፣ የእኔን ገቢ ደግሞ ለቢዝነስ ሰው አይመከርም:: ‹የሀብት ምስጢር› የሚለውን ቪዲዮ፣ የኔቫዳ ኮርፖሬሽን ሂደትንም ማየት ይቻላል:: ወደ ሀብትነት እንዴት እንደቀየረ ሲያሳይ፣ የኔቫዳ ኮርፖሬሽን ሂደትንም ማየት ይቻላል:: በገንዘብ መስራት ለገንዘብ መስራት ማለት ለመንግስት ሀብትን እንደማስረከብ ሲሆን፣ በገንዘብ መስራት ግን ዘለቄታዊ ጠቀሜታን ያስገኛል:: መቼም ቢኾን የገንዘብ እጥረት ቢያጋጥመኝ እንኳ ራሴን መክፈሌን አላቋርጥም::

የሀብት ማዳበርን ሳትፈለግ ያለ ዕጦት መኖር ከተመኘህ ደግሞ ወጪን መቀነስ፣ ገንዘብህ በባንክ ማስቀመጥ፣ መክፈል ካለብህ በዛ ያለ ግብረን በመክፈል ለወደፊት ማለትም ከስራ ስትሰናበት እንዲሆንህ ማድረግና የጋራ ጥቅምን የሚያስጠብቅ አክሲዮን መግዛት አለብህ::

ይሄኛው ህግ አንተ ለሌሎች መክፈልን ወይም መስገብገብ ማለት ሳይሆን ገንዘብን በብልህነት በመጠቀም በህይወት ውስጥ ዕጦትም ሆነ የሀብት መብዛት ሳይፈጠር በመጠኑ መኖር መቻል ማለት ነው::

6. ለደላሎች የተሻለ ክፍያን ስጥ

ምክሮች በህይወታችን ወስጥ ተጽዕኖ ሲኖራቸው ብዙ ሰዎችም በቢሮአቸውም ይሁን በቤታቸው በር ላይ «የሚሸጥ» ለጥፈው ወይም በቴሌቪዥን ዛሬ ያየሁት ብዙ ሰዎች ቅናሽ ወጋ ከደላሎች ለመስማት ሲጓጉ እያለሁ::

ሀብታሙ አባቴ ግን ከላይ ከተገለፀው አካሄድ የተለየ መንገድን ነበር የሚያስተምረኝ:: በዕርግጥ ባለሙያዎችን ቀጥሮ ማሰራትን ተግባራዊ በማድረግ እኔም የዕርሱን ፈለግ ተከትዬ በውድ ወጪ ጠበቆችን፣ የሂሳብ ባለሙያዎችን፣ የሪል ስቴት ደላሎችን ቀጥሬ በማሰራት ላይ ነኝ:: ለዚህም ዋና ምክንያቱ ባለሙያን መቅጠር ማለት አገልግሎታቸው ገንዘብን ለማዳበር ሲረዳ ገንዘብን ባበዛሁኝ ቁጥር ለእኔም ሀብት ማብዛትን ይችላሉ::

ያለንበት ዘመን የመረጃ እንደመሆኑ መረጃም ዋጋው ሊተመን የማይችል መሠረታዊ ነገር ስለሆነ ብቃት ያላቸውን ደላሎች በመቅጠር ወቅታዊ መረጃን ማግኘት





ችያለሁ:: መረጃውንም ከእነርሱ በሚሰጠኝ ትንታኔ በመጠቀም ጥቂት ገንዘብ እንኳን ቢኖረኝ ጥቅም ላይ አውዬው ሀብቴን አበዛው ዘንድ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል::

በተለይ ደግሞ ከደላሎቹ ያገኘሁትን መረጃ በመጠቀም የገንዘብ አቅሜ እንዳላደግኩ ስረዳና ለእነርሱ የከፈልኩትን ሳነፃፀር ካወጣሁት ይልቅ ያገኘሁት በልጦ መገኘቱን ስረዳ ከፍተኛ ደስታን ይሰጠኛል::

ብቃት ያለው ደላላ ሀብትን እንዳበለጽግ ከማድረጉ ባሻገር ጊዜዬንም ሲቆጥብ በሚሰጠኝ መረጃ የ9,000 ዶላር ባዶ ቦታን ገዝቼ ብዙም ሳይቆይ 25,000 እንድሸጥና የራሴን ቤት በፍጥነት እንድገዛ ያስችለኛል::

ደላሎች ለባለሀብቱ አይንና ጆሮ ሲሆኑ ገበያን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃን ይሰጣሉ:: ምክንያቱም በሁሉም ጊዜ ገበያው መሀል ላይ ስለሆኑ አንተ በገበያው ውስጥ እንዳትንቀሳቀስና ጊዜህንም በጎልፍ ጨዋታ እንድታሳልፍ ያደርጉሀል::

ምንም እንኳን አንዳንድ ሰዎች በሚሸጡት ቤት ላይ የሚጠፋው እረጅም ጊዜ እንደማይጎዳቸው ባውቅም ለእኔ ግን ጊዜ ማለት የገንዘብ ማዳበርያ ስለሆነ መረጃን በተመለከተ ለደላሎች ስራውን ሰጥቼ በምትኩ እኔ ከወዳጆቼ ጋር እንድዝናና አድርጎኛል::

በጣም የሚያስቀኝ አንዱ ነገር ደሀችና መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ስለ ድለላ የሚሰጡት ወቀሳን የተሞላ አስተያየት ሲሆን ባለቤት ለደላላ ከ3 እስከ 7% የሚከፍለው ገንዘብ አግባብነት ለሌለው ሀብትን ማካበት ምክንያት ይሆናል ብለው ያምናሉ:: ይህም ከባለሀብቱ አንፃር ሲታይ ዘላቂ ላልሆነ ሀብት ማካበት የአገልግሎት ጥራት መቀነስ ለዘላቂ ውድቀት መፈጠር መንስኤ ስለሆነ መጠንቀቅ ይገባል፣ ይህን ገንዘብን በአግባቡ ተጠቅሞ የመበልፀግ ሂደት / ብልህነት አይደለም::

ደላሎች ሁሉ እኩል አይደሉም:: በአብዛኛው ደላሎች የሽያጭ ሰራተኞች ናቸው:: የሪል ስቴት አሻሻጮች ለውጥ የሚታያቸው ሳይሆን ከማሻሻጥና ከማጋባት ውጪ የራሳቸው የሆነ ሀብትን ሲያዳብሩ አይታይም:: ቤትን ከማሻሻጥና ለስራ የሚውል ቦታን ወይም ማንኛውንም ንብረት ማሻሻጥ ብዙ ልዩነት አላቸው:: እስቲ ከን፣ ቦንድና ፈንድን የሚያሻሽጡ የገንዘብ ፍሰት ቀያሽ ሲባሉ እነርሱን መጠቀም ሀብትን መስብሰብ ማለት ነው::

ማንኛውንም ተቀጣሪ ባለሙያ ሳናግር ምን ያህል ቋሚና ተንቀሳቃሽ ሀብት እንዳለው በመጠየቅ የሚከፍለውን ስረዳ ይህም በእኔ የግብር አከፋፈል ላይ ለጠበቃና ለሂሳብ ባለሙያ የምከፍለው ላይ ተግባራዊነቱን ያስረዳኛል። አንዲት የሂሳብ ባለሙያ ስትኖረኝ ከሙያዋ ባሻገር የራስዋ የሆነ የሪል ስቴት ቢዝነስ አላት። ከእርሷ በፊት ደግሞ የነበረኝ የሂሳብ ባለሙያ የራሱ የሆነ ሪል ስቴት ቢዝነስ አልነበረውም። ከዚህ ሰው ጋር ተመሳሳይ የሆነ የቢዝነስ አቋም ስላልነበረን ከስራ አባረርኩት።

ማንኛውንም ባለሙያ ልትቀጥር ስታስብ ከአንተ ጋር ተመሳሳይ አቋም እንዳለው ልብ ብለህ ተረዳ። አምሳያህን ካገኘህ ከነእርሱ ትምህርትን በማግኘት ሀብትህን ስታሳድግ ከአንተም የሚጠበቀው አግባብነት ያለውን ክፍያ በመክፈል እንዳይርቁህ ማድረግ ብቻ ነው። ከከፈልከ ለምን ይሸሹሃል?

ከዚህ ቀደም እንዳልኩት የአስተዳደር አንዱ አካል የሰው ሃይል በብቃት መምራት ሲሆን ብዙ ሰዎችም ግን ከዝቅተኛው ሰራተኛ ይልቅ ኃላፊዎቻቸውን መቆጣጠርና ትኩረት መስጠት ውጤታማ ያደርጋል ብለው ያምናሉ። እውነቱ ግን በዝቅተኛና በቴክኒክ ክፍል ውስጥ ያሉ ሰዎችን በአግባቡ በማስተዳደር ተገቢውን ክፍያ መክፈልና በቦርድ ዳይሬክተር እንዲመሩ ማድረግ ለለውጥ መሰረት ስለሆነ ጥቅም ላይ ልታውለው ይገባል።

7. እንደ ሕንዳዊ መጽዋች ሁን

የዚህ አይነት አካሄድ ከምንም ነገር የተሻለ ነገርን ማግኘት ሲሆን በአሜሪካም ነጮች መጀመሪያ ሲሰፍሩ በነባር ነዋሪ ህንዳውያን የባህል ወግ ለመጓዝ ተቸግረው ነበር። ለምሳሌ አዲስ መጤው ሲበርደው ነባሩ ነዋሪ ብርድ ልብስ ይሠጠዋል። ብርዱ ሲያልፍለት ግን መልሶ ይጠይቀዋል።አዲስ መጤዎቹ ስጦታ እየመሠላቸው ለመልመድ ተቸግረው ነበር። ህንዳዊያኑም አዲስ መጤዎቹ ንብረታቸውን ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ባዩ ጊዜ ይበሳጩ ነበር። ሕንዳዊ መጽዋች የሚለው ቃልም የመጣው ከዚያ ነው።

ሀብት ማካበት ሂደት ውስጥ የሬድ ህንዳውያን መንገድ መከተል ጠቃሚ ሲሆን ባለሀብቱ ዘወትር አንድን ገንዘብ በስራ ላይ ሲያውል የጊዜን ሚና በመረዳት ‹‹መቼ ነው ኢንቨስት ያደረግኩት ገንዘብ ተመልሶ ወደ ሀብቴ ገቢ የሚሆነው?›› ሲል ራሱን መጠየቅ ይገባቃል። ‹‹ያለምንም ወጪስ ሀብቴን ማዳበር እችላለሁ?›› ሲል ራሱን መጠየቅ





አለበት። ለዚያም ነው ወጪን በገቢ መተካት አስፈላጊ የሚሆነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በአንድ ወቅት በመኖሪያ አካባቢዬ በሀራጅ የሚሸጥ ኮንዶሚኒየም አገኘሁ። በሀራጅ የያዘው ባንክ 60,000 ዶላር ሲጠይቅ እኔ ግን 5,000 ዶላር አስቀድሚ አስያዝኩ። የባንኩ ሰራተኞች እኔ ቤቱን ምን ያህል እንደምፈልገው ሲረዱልኝ አንዳንድ ግለሰቦች ግን ‹‹ለምን ብድር ወስደህ አትገዛውም?›› አሉ። መልሱ ግን እነርሱ እንዳሉት በዕዳ መግዛት አልነበረም። በኢንቨስትመንት ካምፓኒዬ አማካኝነት ለቤቱ ያወጣሁትን ወጪ በበረዶ ወቅት ወደ አሪዞና ከሚደረግ የሽርሽር ገቢ በአራት ወር ውስጥ ቤቱን በማከራየት በወር 2,500 ሳገኝ በአራት ሲባዛም የቀረውን 10,000 ሸፍኜ ዕዳ ውስጥ ከመግባት ተረፍኩ። በበጋ ወራት በወር 1,000 ስገኝ በአጠቃላይ ያወጣሁት ወጪም በ3 ዓመታት ውስጥ ሸፈንኩ በአሁኑ ሰአት ከሦስት ዓመት በኋላ ሙሉ በሙሉ ከዕዳ የነፃ ትርፍ ገቢ አለኝ ማለት ነው።

በአክሲዮን ቢዝነስም ከዚህ የተለየ ነገር አናይም። በተደጋጋሚ ደላላዬ አዲስ ምርትን በሚያመርቱ አክሲዮኖች ላይ እንዳተኩር ሲመክረኝ እኔም ምክሩን በመስማት ተግባራዊ አደርገዋለሁ። በውጤቱም ከምንም ነፃ የሆነ ቋሚ ሀብቴን የማይነካ ትርፍን አካብታለሁ።

በእርግጥ ገንዘብን በተለያየ ምክንያት አጥፍቻለሁ። ሆኖም የማጠፋው ገቢዬን በማይጎድና ትርፍ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ነው። ለምሳሌ 10 ኢንቨስትመንት ቢኖረኝ ከአስሩ ውስጥ በአንድ ወይም በሁለቱ አልያም በሦስቱ ገንዘብ ሳጣ ስችል በተቀሩት ግን ወጪዬን በመቀነስ እንሰራራለሁ! የተሻለ ነገርንም አገኛለሁ።

አንዳንድ ሰዎች ገንዘባቸውን በባንክ በማስቀመጥ በረጅም ጊዜ ውስጥ የሚያስገኘው ወለድ እንደሀብት ማዳበሪያ ሲቆጥሩን እውነታው ግን ጊዜን ወሰጅና እምብዛም ለውጥ በህይወታቸው ውስጥ አያሳይም። ሀብትን እንቀሳቅሶ የተሻለ ገንዘብን እንዲያመጣ ማድረግ በነፃ እንደሚገኝ የገንዘብ ዝውውር ሲቆጠር ለምሳሌም ኮንዶሚኒየም አነስ ያለ የግብዣ ቤትን መግዛት፣ ባዶ ቦታዎችን ተጠቅሞ ለስራ ማዋልና ህንፃዎችን ገንብቶ መሸጥ ወይም ማከራየት የተሻለ ሀብትን ለማዳበር ይረዳል። በዚህ ዙሪያ በተያዩ ሰዎች የተፃፉ መጽሀፎች አሉ። ሬይ ክሮክ የማክዶናልድ ባለቤት ፍራንቻይዙን በመሸጥ

የተሻለ ገቢ እንዲያገኝ አድርጓል። ስለሆነም ብልህ ባለሀብቶች ገንዘባቸውን በባንክ አስቀምጠው እንዲወልድላቸው ከማድረግ በስራ ላይ በማዋል ሀብታቸውን ያበዛሉ።

8. ***ንብረት ቅንጦትን ይገዛል፡-*** የጓደኛችን ልጅ የሚያገኘውን ገንዘብ ያላግባብ ማጥፋት ይወድ ነበር። በ16 ዓመቱም የራሱ መኪና ይኖረው ዘንድ ሲመኝ ሁሉም ጓደኞቹ ወላጆቻቸው ሲገዙላቸው እርሱም መመኘትና ማግኘትን ፈለገ። ልጁም ባንክ የተቀመጠበትን ገንዘብ ተጠቅሞ ለመግዛት ሲመኝ አባትዬው ደውሎ ጠራኝ።

ምን ይመስልሃል «ሀሳቡን ልቀበልና እንደሌሎቹ ወላጆች መኪና ልግዛለት?» ሲል ጠየቀኝ።

እኔም ለጊዜው መግዛትህ መልካም ቢሆንም ለዘለቄታው ምን ልታስተምረው አስበሃል? መኪና እንዲኖረው በማድረግህስ ሌላ ትምህርት ልትሰጠው አስበሃል?» ብዬ ጠይቀው አንዳች ነገር ብልጭ ስላለለት መልስ ሳይሰጠኝ ወደቤት ተጣድፎ ሄደ።

ከሁለት ወር በኋላ ወደ ጓደኛዬ ሄጄ «አዲሱን መኪና ገዛህለት?» ስል ጠየቅኩት።

«አይ አልገዛሁለትም» አለኝ። «3500 ዶላር ሰጥቼው የኮሌጅ ገንዘቡን ሳይሆን የኔን ገንዘብ በመጠቀም እንዲገዛ ነገርኩት።»

«ደህና ይህ የአንተ መልካምነት ምሳሌ ነው።» አልኩት።

«ይህን ገንዘብ በመስጠቴ ለልጄ ትምህርት ማሳተላለፍ ነው የፈለግኩት።»

«ምኑ ላይ ነው ትምህርቱ?» ብዬ ስጠይቀው ጨዋታችን ገታ አድርጎ የገንዘብ ፍሰት ምን ማለት እንደሆነ ሲጠይቀኝ ስለገንዘብ ጠንቅቆ እንዲያውቅና አጠቃቀሙን እንዲረዳ ከዎል ስትሪት ጆርናል ማብራርያውን ያገኝ ዘንድ ጥቂት መጽሀፍትን ጨምሬ ጠቆምኩት።

በሚቀጥለው ቀን አግኝቼ ስጠይቀው «ገንዘቡን ተጠቅሞ በ3000 ብሩ መኪና ከመግዛት ስቶክ ገዝቶ በ6000 በመሸጥ በትርፉ መኪና ገዝቶ የተቀረው ለኮሌጅ ይሆነው ዘንድ አሳስቤዋለሁ።» አለኝ።

«ከዛስ ውጤቱ ምን ሆነ?» ድጋሚ ጠየቅኩት። «በጣም የሚገርመው በንግዱ እድለኛ ሆኖ ገቢ ቢያገኝም ከጥቂት ቀናት በኋላ መልሶ አጣው። በአሁኑ ሰዓት ግን





2000 ዶላር ቢኖረውም በባንክ ያለው ተቀማጭ ግን ጨምሯል። የነገርኩኝን መጽሐፍት ጨምሮ ሌሎችንም ማንበቡን ቀጥሏል። የንግድ ፍላጎቱ እንደሰማይ ወጥቷል። የቀረውን ገንዘብ ቢያጣ ለመተካት አጭር ጊዜ ብቻ እንደሚፈጅበት ማሰብ ስለጀመረም ስለገንዘብ ብዙ አይጨነቅም። መኪና ለመግዛት ያለውም ፍላጎት ቀንሷል። በ3000 ዶላሩ ብዙ ትምህርት እንዲያገኝና ከገንዘብ አባካኝነት እንዲድን አድርጌዋለሁ» አለኝ።

ብዙዎቻችን በት/ቤት የተማርነው በገንዘብ መጠቀምን ነው። በኔ አመለካከት ግን ገንዘብ ለኛ እንዲሰራልን ማወቅ ይገባናል። የቅንጦት ዕቃዎቼን እንደማንኛውም እወዳቸዋለሁ። ልዩነቱ ግን ብዙዎች ውድ ዕቃ የሚገዙት በብድር መሆኑ ሲሆን ይህም በፈቃደኝነት ወጥመድ ውስጥ እንደመግባት ይቆጠራል። ሆኖም ለስራ የሚውል ባዶ መሬት መግዛት ስፈልግ የባንክ አማካሪዬን በማማከር በእዳ ስገዛ በውጤቱም ትርፍን በማካበት እዳዬን ከመመለስ አልፌ በሀብቴ በመጠቀም ሌላ ስራ እሰራበታለሁ።

እንደ ልምድ ሆኖ ገንዘብን የመጠቀም ብልሀቴን ዘወትር መፈተሽ እወዳለሁ። ብዙዎቻችን ሀብትን ከማፍራት ይልቅ ወይንም እጃችን ላይ ያለውን ገንዘብ ተጠቅመን ስራ በመስራት ትርፍ ከማግኘት በቀጥታ ወደ ብድር መሄድን እንመርጣለን። የመጀመሪያው አማራጭ ለጊዜው ረጅም ውጣ ውረድ እንዳለበት ቢሰማንም ውጤቱ ግን እርኪ ነው። ልብ በል ቀላል የመሰለ ጎዳና ከባድ ሊሆንብን ሲችል በተቃራኒው ይከብዳል ያልከው ደግሞ መቅለሉ እሙን ነው።

ገንዘብ ኃይል እንዳለው ዘወትር ሳትዘነጋ ራስህን ለአጠቃቀሙ ዝግጁ አድርግ። እንደብዙዎችም ገንዘቡ ጉዳትን በላይህ ላይ እንዳያመጣ ተጠንቀቅ፡ ገንዘብን በዘዴና በብልሀት ካልተጠቀምክበት መጠቀሚያ መሆኑ ቀርቶ መጥፊያህ ይሆናል። በህይወት ዘመንህም እሱን ለማግኘት የማይሳካ መዋተት ውስጥ እንድትገባ እንዳያደርግህ ተጠንቀቅ።

የገንዘብ እንቀሳቃሽ ለመሆን የአእምሮህ ኃላፊ መሆን ይገባሃል። ይህም ሂደት ብልህነት ይለኛል።

9. *የተምሳሌቶች አስፈላጊነት*- ልጅ እያለሁ ጀግንነትን የሚተርኩ መጽሀፍት እጅግ ይስቡኝ ነበር። እድሜዬም ሲገፋ በመጽሀፎቹ ያየኋቸውን ጀግኖች የመተካት ህልሜ ብርቱ ነበር። እነርሱን መሆን ህልሜም በመበርታቱ ስለዕነርሱ በስፋትና በጥልቀት ለማወቅ ተግባራቸውንም በመፈፀም እተጋ ነበር።

የ9 ወይም 10 ዓመት ልጅ እያለሁ ዘወትር ስጫወት እኔ እንደምጫወት ሳይሆን የማልመው ጀግና እንደሆንኩ ነው። ይህም ለወደፊት ማንነታችን ተጽዕኖ አለው።

ዛሬ ላይ ሆኜ ህፃናት በመኖሪያ ቤቴ አካባቢ ቤዝ ቦል ሲጫወቱ ሳይ አእምሮዬ ላይ የሚመላለሰው እነርሱ የሚያስቡት እኔ በልጅነቴ አስበው እንደነበር የቤዝቦል ጀግናቸውን የሆኑ ያህል ነው።

ዕድሜዬ እየበለሰ ሲመጣ በልጅነታችን ጀግና የነበሩትን በሌሎች የመተካት ሂደት ውስጥ እንገባለን ለምሳሌ ካደግኩ በኋላ በቤዝ ቦሉ ፒተር ጃኮብስ፣ ሬድ ካፐልስና ታይገር ውድ ጀግኖቼ ናቸው። በተቻለኝም መጠን የማያደርጉትን ነገር ኮፒ ለማድረግ እጥራለሁ። ልክ እንደ ቤዝ ቦል ጀግናዬ በንግዱም አለም ፈለጉን ብከተል የሚስለኝ ጀግና ሲኖረኝ ለምሳሌም ዋረን ቡፊት የሚሰራውን የሚያነባቸውን መጽሐፍት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የእይታዬ ትኩረት ነው። አክሲዮን ምርጫን በተመለከተ የፒተር ሊይንች መጽሐፍ ማንበብ የዘወትር ስራዬ ሲሆን የዶናልድ ትራምፐ መጽሀፍ ማንበብ ደግሞ ጠቀሜታው በንግድ አለም የሚደረግ የሁለትዮሽ ስምምነት ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው ተገንዝቤያለሁ።

ልክ ልጅ እያለሁ እኔ እኔን ሳልሆን ሮል ሞዴሌን እሆን እንደነበር ካደግኩ በኋላም የንግድ ስምምነት ስደራደር ትራምፕን የተካሁ ይመስለኛል። ነገሮችንም በጥልቀት ስመለከት ፒተር ሊይንች በመንፈስ የተካሁ ያህል ይሰማኛል።





10. እስተምርና ይሰጥሃል

የመስጠት ጉልበት። ሁለቱም አባቶቼ አስተማሪዎች ነበሩ። ሀብታሙ አባቴ ሕይወቴን ሙሉ የምይዘውን ትምህርት ያስተምረኝ ነበር። ምሁሩ አባቴም በጊዜውና በዕውቀቱ አማካኝነት በርካታ ነገሮችን ይሰጥ ነበር ከገንዘብ በስተቀር። ሁሌም ትርፍ ገንዘብ ሲኖረኝ እሰጣለሁ ይል ነበር! መቼም ግን ትርፍ ገንዘብ ኖሮት አያውቅም።

ሀብታሙ አባቴ የሚሰጠው ትምህርትም ገንዘብም ነው። አንዳች ነገር የምትፈልግ ከሆነ አስቀድመህ መስጠት አለብህ በሚለው አባባል አጥብቆ ያምናል። የገንዘብ እጥረት በገጠመው ጊዜ ለቤተክርስቲያን ወይም ለግብረ ሰናይ ድርጅት ገንዘብ ይሰጣል።

ስለዚህ እንዳልኩት ‹‹ስጥ ይሰጥሀል›› የህይወትህ አንድ መፈክር ይሁን። ካስተማርክ አንተም ትማራለህ። ስለገንዘብ የበለጠ ለማወቅ ከፈለግክ ላላወቀው የምታውቀውን አካፍል። የማይታመን የዕውቀት ልዩነትን መፍጠር ይቻልሀል።

አንዳንዴ የሰጠኸው ሳይሆን ያልሰጠኸውን በምላሹ ልታገኝ ትችላለህ። ለመልካም ነው ውሰደው። በእርሱም መማር የምትችለውን በእንክሮ አሰላስል፡ ለምሳሌ ለአንድ ሰው ውለታ ውለህ በምላሹ ጥሩ ያልሆነ ነገር ቢገጥምህ ከዚያ ውስጥ ለመማር ሞክር።

ወላጅ አባቴ የሚያስተምረው አዋቂዎችን ሲሆን ሀብታሙ አባቴ ግን ወጣትና ህፃናትን ማስተማር ይቀናዋል። ያላቸውን እውቀት ማካፈላቸው ደግሞ በውጤቱ እነርሱን የተሻሉ አድርጓቸዋል። በዚህ አለም ስትኖር የስበት ህግ አለ፣ ይሰራልም። ስለዚህ ለመቀበል መስጠትን ተግባራዊ አድርግ።

# ምዕራፍ አስር

# ተጨማሪ ትፈልጋለህ?

### ከዚህ በታች የሰፈሩትን በሚገባ ተግብራቸው

በርካታ ሰዎች ከዚህ በፊት በዘረዘርካቸው አስር ደረጃዎች እርካታ ላይሰማቸው ይችላል። ምክንያቱም የተጠቀሱትን ደረጃዎች የሚመለከትዋቸው እንደ ፍልስፍና እንጂ፣ መተግበር እንደሚችሉ ነጥቦች አድርገው አይደለም። ከማሰብ ይልቅ መስራትን ወይም ማድረግን ምርጫቸው ያደረጉ በርካታ ሰዎች የመኖራቸውን ያህል፣ በአንፃሩ አንድን ውጥን በአዕምሮአቸው ይዘው ከማብሰልሰል ውጪ፣ ደፍረው ወደ አፈፃፀም የማይገቡም አሉ። እኔ በሁለቱም ውስጥ እንዳለሁ ነው የማውቀው። ለአዳዲስ ሃሳቦች ትልቅ ቦታ እንደምሰጥ ሁሉ፣ የተግባርም ሰው ነኝ።

ከዚህ በመቀጠል በውስጣቸው ያለውን አዲስ ሃሳብ ወደ ተግባር መለወጥ ለሚሉጉ ሰዎች ካለኝ ልምድ በመነሳት የተወሰኑ ነጥቦችን ላካፍላችሁ።

**የምትሰራውን ለጊዜው ቆም አድርግ፡-** በሌላ አገላለፅ፣ የምትሰራውን ለጊዜው ቆም በማድረግ፣ አካባቢህን ቃኝተህ መሰራት ያለበትን እና የሌለበትን አጥርተህ አረጋግጥ። ምክንያቱም ነገሩ ሁሉ ነገር የውሃ ቅዳ ውሃ መልስ አይነት እንዳይሆንብህ መጠንቀቅ አለብህ፤ ከአንድ አይነት ሥራ ውስጥ ሁለት የተለያዩ ውጤቶች እንደ መጠበቅ ማለት ነው። ሊሰራ የማይችልን ነገር ከመስራት ተቆጥበ፣ አዲስ ሊሰራ የሚችልን ሥራ ፈልጎ ማግኘት ተመራጭ ነው።

**አዳዲስ ሃሳቦችን ፈልግ፡-** አዲስ የመዋዕለ ንዋይ ሃሳብን ወደ ተግባር ከመለወጤ በፊት፣ ሁሌም የማደርገው ወደ መፅሐፍት መሸጪያ መደብር በመሄድ፣ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ተጨማሪ ሃሳቦችን ለማግኘት የተለያዩ መፅሐፍቶችን ለመመርመር መሞከር ነው። ከመፅሐፍት ውስጥ የማገኛቸውን አዳዲስ ሃሳቦችን ‹ቀመሮች› እያልኩ ነው የምጠራቸው። መፅሐፍቶች ከቀመር ጋር በተያያዙ እንዴት ሊገዙ እንደሚችሉ አላውቅም። እዚህ ጋር አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ። በአንድ ወቅት ከመፅሐፍት መደብር ውስጥ ‹‹The 16 percent solution›› የሚል ርእስ ያለውና በጆይ ሞስኮዊትዝ የተፃፈ መፅሐፍ አገኘሁ። መፅሐፉን ገዛሁትና ያለ እረፍት አንብቤ ጨረስኩት።





**እርምጃ ውሰድ፡-** በሚቀጥለው ሃሙስ፣ መፅሐፉን ተከትዬ እርምጃዬን ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ማድረግ ጀመርኩኝ። ከዚያም በባንክ ዕዳ የተወረሰና በፍርድ ቤት ለሽያጭ የቀረበ ሪል ስቴትን ገዝቼ ወደ ራሴ አዘዋወርኩት። ብዙ ሰዎች ፈጣን እርምጃ የመውሰድ ልምድ የላቸውም። ከዚህ ይልቅ ሌላ ሰውን በማማከርና በማጥናት ጊዜያቸውን ያጠፋሉ። እንዲያውም አንድ ጎረቤቴ ‹16 percent› የተባለውን መፅሃፍ ወደ ስራ ሊለወጥ የሚችል አይደለም ብሎኛል። ላዳምጠው አልፈለግኩም፤ ምክንያቱም የተግባር ሰው አይደለምና።

**ለመስራት በምትፈልጉት ስራ ስኬታማ የሆነ ሰው ፈልጉ፡-** የምሳ ግብዣ አድርጉለት፤ ከዚያም አንዳንድ ከንግድ ጋር የተያያዙ ስልቶችን እንዲያብራራ ጥያቄ አቅርቡለት። የእኔን ልምድ ላካፍላችሁ።

የጆይ ሞስኮዊትዝ ‹16 percent solution› መፅሃፍን አንብቤ ከጨረሱ በኋላ፣ ከግብር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በመጨረስ ወደ ግብር ጽ/ቤት በመሄድ ከመስሪያ ቤቱ ሰራተኛ ጋር ተገናኘን። በአጋጣሚ ያገኘኋት ሴት ሰራተኛ ስለ ግብር ሰርተፍኬት ስጠይቃት፣ ምሳ እየበላን እንድንነጋገር ጋበዘችኝ። ከግብር ጋር የተያያዙና ልምድ ያገኘችባቸውን ክስተቶች በሙሉ የማካፈል ፍላጎትዋ ከፍተኛ ነበር። የሚገርመው ነገር እርሷ ራስዋ ከሥራዋ ጎን ለጎን ኢንቨስት የምታደርግና ስለግብር ጠንቅቃ የምታውቅ ነበረች። ከምሳ በኋላ፣ ያለውን ሰዓት በሙሉ ጠቃሚ የምትላቸውን ምክሮች በሙሉ ስታሳየኝ ዋለች። በሚቀጥለው ቀን፣ ሁለት ንብረቶችን በእርስዋ ድጋፍ አገኘሁና በ16 ከመቶ ወለድ በእጄ አስገባኋቸው። በዚህን ያህል የወለድ መጠን ንብረቶችን ስይዝ የመጀመሪያ ጊዜ ነበር። አዎ! መፅሀፉን በማንበብ አንድ ቀን ነው የወሰደብኝ። በነጋታው ወደ እርምጃ ነው የገባሁት። ያጠፋሁት ጊዜ ለምሳ አንድ ሰዓት ብቻ ንብረቶቼን ደግሞ በእጅ ለማስገባት አንድ ቀን።

**አዲስ ክፍል ያዙ፤ ቴፕም ግዙ፡-** አዲስና ዕውቀትን የሚሰጡ የትምህርት ክፍለ ጊዜ በማግኘት ጋዜጦችን ሳገላብጥ ዋልኩ። ብዙዎቹ ነፃ ወይም አነስተኛ ክፍል የሚያስከፍሉ ነበር። በሌላ በኩል ለእኔ ጠቃሚ የሆኑና በውድ ክፍያ መከፈል የሚያስችሉ ሴሚናሮች ላይ እካፈል ነበር። ምክንያቱም ሀብታም ነኝ ደግሞም የቅጥር ሥራ አልፈልግም። ለዚህም ነው በእንደዚህ አይነት ኮርሶች ላይ የምካፈለው። እንዳንድ

ጓደኞች አሉኝ እንደ እኔ በኮርሶች ላይ መካፈል የማይፈልጉት:: እና ሁሉም ገንዘብህን ያለአግባብ ነው የምታባክነው ይሉኛል:: ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች ከማውቃቸው ጊዜ ጀምሮ የያዙትን ስራ እንኳን ለውጠው አያውቁም::

ማገኛውም የህይወት መስመር አምሳያን መፈለግና ከእርሱም ጋር ጊዜ ማሳለፍ ተገቢ ሲሆን ይህንንም ለማድረግ ምሳን አብሮ መብላት መዝናናትና መንፈስን በጋራ ማደስ ተገቢ ነው:: 16% የተሰኘውን መጽሀፍ አንብቤ እንደጨረስኩ ወደ ግብር መሰብሰቢያ ቢሮ በመሄድ የመንግስት ቅጥረኛ የሆነች አንዲት ሴትን አነጋገርኩ:: እርሷም እንደእኔ ግብር ከፋይ ስትሆን ለምሳ ጋበዝኳት:: ስለግብር የምታውቀውን ለእኔ ለመንገር ብትሰጋም ምሳ አብረን ከበላን በኂላ ያለውን ነገር ሁሉ በግልፅ አሳየችኝ፤ ስለግብር:: በሚቀጥለውም ቀን ሁለት ትላልቅ ሀብቶችን በእርሷ አማካኝነት ማግኘት ስችል ይህንንም ሃብት 16% ባነበብኩት መሠረት ጥቅም ላይ አዋልኩት:: መጽሀፉን ለማንበብ አንድ ቀን ፣ ለተግባርም እንደዚሁ አንድ ቀን ምሳ አብሮ በመብላት ሁለት ሰዓት ትላልቅ ሀብቶችን ለማግኘት ግን ሰዐታትን ብቻ ነው የወሰደው::

ትምህርት ወይም ስልጠናን በመውሰድ አንቃቂ የሆኑ ካሴቶችን ተመልከት ወይም አዳምጥ:: ለምሳሌ የፒተር ላይንችን ‹ትምህርተ ሀብት ማበልፀግ› ጋዜጣን ሳነብ ከተማርኩበት አምድ አንዱ ሀብት ማበልፀግ በተመለከተ የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያዎችን ሲሆን አብዛኞቹም ከክፍያ ነፃ ወይም ጥቂት ክፍያን ይጠይቃሉ:: አልፎ አልፎም በውድ ዋጋ ሴሚናሮችን ስከታተል ለሀብቴ ማደግ ግን ካወጣሁት ወጪ በበለጠ ትልቅ ሚና አላቸው:: ሴሚናሮቹ ስራን ከመፈለግ ውጣ ውረድም አድነውኛል :: አንዳንድ ጓደኞቼ ግን በሴሚናር ገንዘቤን ማባከን እንደሌለብኝ ሲመክሩኝ እውነታው ግን እነርሱ ባሉበት ሲቆዩ እኔ ደግሞ በእድገት መገስገሴ ነው:: የተለያዩ ውሎችን መፈፀም አትዘንጋ:: ሪል ስቴት ለመግዛት ሃሳብ አንድ ብቻ ላይ ከማተኮርና ውልን ከመፈፀም ይልቅ አማራጮችን ስመለከት በምርጫዬም አዋጭ ነው ካልኩት ጋር ውል እፈጽማለሁ:: ትክክለኛ ውል ምን ማለት እንደሆነ ካላወቅክ እኔም መልስ ስለሌለኝ አላውቅም ነው:: ይህ እንግዲህ የሪል ስቴቶች ስራ ሲሆን ውልን በመፈፀምና አዋጭም ከሆነ ውሉን መቀጠል መገለጫ ባህሪያቸው ነው::





ከዕለታት በአንዱ ቀን ጓደኛዬ አፓርትመንት እንዳጋዛት ጠየቀችኝ:: እኔ፣ እርሷና ወኪልዋ አብረን ስድስት የሚሸጡ አፓርትመንቶችን ስናይ ከነዚህ ውስጥም አራቱ በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሲሆን ሁለቱ ግን የሚረቡ አልነበሩም:: እኔም በስድስቱም ላይ ውል እንዲፈፀም በማድረግ ግማሽ ክፍያን ለመፈፀም ለባለቤቱ ነገርኩት:: ጓደኛዬና ወኪልዋም ይህን ስል ልክ የልብ ህመምተኛ ድንገት የህመም ስሜት እንደተሰማው ሲሰማቸው ታወቀኝ:: ያንንም በማለቴ ጨካኝና ለሻጭ የማላስብ እንደሆንኩ ሲያስቡ እኔ ግን ወኪልዋ ለስራ የማይነሳሳ እንደሆነ ተገንዝብኩ:: ጓደኛዬም እኔ እንዳልኩት ክፍያውን ፈጽማ ከመግዛት ሌላ አማራጭ ለማየት በመወሰን ወደ ሌላ አማራጭ ፊቷን አዞረች::

ምንም አይነት ውል ባለመፈፀሙ ያ ሰው ሌላ አማራጭ መቃኘት ሲቀጥል በተገቢው ዋጋ ተገቢውን ገዥ ማግኘትንም ተግባሩ አደረገ:: ሌሎች አማራጮች እስካላየህ ድረስ ትክክለኛ ዋጋ ምን ማለት እንደሆነ ሳታውቅ ትችላለህ :: ሻጩ ዘወትር የሚጠይቀው ዋጋ ጫን ያለ ሲሆን ዝቅተኛ ዋጋን የመጠየቅ እድሉ በጣም ዝቅተኛ ነው::

የባለቤትነት ስሜት በውስጥህ ከሌለ ለመነገድ ወይም ለመሸጥ አቅሙ የለህም:: ከዚህ ቀደም ልሸጠው የምፈልገው አንድ ሪል ስቴት ነበረኝ፤ ወራትንም ፈጅቷል:: በተሸጠበት እንዲሸጥ ስፈልግ ዋጋው ምንም ይሁን ምን በፀጋ ለመቀበል እራሴን አዘጋጅቼ ነበር:: አስር አሳማዎችን ሰጥተውኝ በምትኩ ሪል ስቴቱን ቢወስዱ እንኳን ደስተኛ ነበርኩ::

ስምምነት እንደተፈፀመ የአሳማ ማራቢያ ቦታን ለመጠየቅም እራሴን አዘጋጅ ነበር:: በማታውቀው ምክንያት ተዋዋልህ ጥቅም ልታገኝ ስለምትችል መዋዋልን አትጥላ::

ብዙ ጊዜ ውል መፈፀም ሳዘወትር በውሉም ውስጥ ማምለጫ ቃላት አክልበታለሁ:: በሪል እስቴት ውስጥ በተለይ ‹‹የቢዝነስ አጋሩን ስምምነት ይጠይቃል›› የሚል ሀረግ አክልበታለሁ:: ይህም በውሉ ውስጥ ያልጣመኝ ነገር ሲኖር ማምለጫዬ ነው:: ልብ በሉ ስሙን ግን ፈጽሞ አልጠቅስም:: ብዙ ሰዎችም አጋሬ የገዛ ድመቴ እንደሆነ አያውቁም:: አጋሬን የምጠቀምበት የተፈፀመው ውል አዋጭነቱ ካልጣመኝ ብቻ ነው::

ጥሩ ስምምነትን! ትክክለኛ ቢዝነስን! ትክክለኛ የንግድ ሰዎችንና ወቅታዊነትን በስራህ ውስጥ እንዲካተቱ አድርግ:: ወደገበያ በማቅናት ከሰዎች ጋር ተወያይ ውልንም ፈጽም በመደራደርም አዋጭ ኾኖ ካገኘህ ተቀበል:: አለበለዚያ ለመስረገዝ አታመንታ:: አንዳንድ የማውቃቸው ‹ነጋዴ ነን› ባዮች ቤታቸው ተቀምጠው የስልክ ጩኸትን ይጠባበቃሉ:: አንተ ግን ኪንዲ ክራውፎርድ ወይም ቶም ክሩዝን ስላልሆንክ እንደ እነርሱ አታድርግ:: ተንቀሳቀስ ራስህንም በገበያው መሀል አግኝ! ሱፐር ማርኬትም ቢሆን:: በህይወት ውስጥ ትልቁ ነገር መቃኘት! መዋዋል! መደራደርና መቀበል ሲሆኑ በተለይ በንግዱ አለም የህይወት መርህ ናቸው ሊባል ይችላል ::

በቀን ለአስር ደቂቃ መኪና ካለህ በመኪና ከሌለህም በእግርህ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቀስና ልትሰራ የምትችለውን ነገር ቃኝ:: እኔ ሪል ስቴትን የምሰራው በዚሁ ተሞክሮዬ ነው:: በመንቀሳቀስ ያልተሰሩ ቦታዎችን ከቃኘሁ በኋላ ወደ ስራ መቀየር ደግሞ ተግባሬ ነው:: ለአመት ያህል በአንዳንድ አካባቢዎች መንቀሳቀሴን ስቀጥል ምልከታዬም የሚያተኩረው የሚታይ ለውጥ ላይ ነው:: በለውጥ ውስጥ ትርፍ አለ:: ለትርፍ ደግሞ ስምምነትና ለውጥን መቀበል ሚና አላቸው:: ስምምነቶች ቁጥራቸው የበዛ ሊሆን ሲችል ለስምምነቶች ውጤታማነት ግን ለውጥ ወሳኝ ድርሻ አለው፤ አልፎ ተርፎም ከዕርሱ ጋር ይያያዛል:: ስለሆነም በምንቀሳቀስበት ወቅት ዘወትር የማስበው ገንዘብን በምን ወይም የትኛው ቦታ ላይ ኢንቨስት ላድርግ በማለት ሲሆን እይታዬ በአንድ ቦታ ላይ መደጋገሙ ጥቅም ደግሞ ቦታውን አጣርቶ ከማወቅ ጋር ይያያዛል:: ለሽያጭ ቀርቦ ገበያን ሳይስብ የቀረ የሪል ስቴት ብዙ ጊዜ ያጋጥመኛል:: እኔም ከንግድ ሂደት በመረዳት ባለቤቱ በተባለው ዋጋ እንደሚሸጥ ስለምገምት በሪል እስቴቱ የሚንቀሳቀሱ ከባድ መኪኖችን በማስቆም ነጂውን እጠይቃለሁ:: በጣም የሚገርም መረጃን ስለቦታው ሊሰጡኝ ይህም ክፍያ አልባ መሆኑ ሌላ ጠቀሜታው ነው:: መረጃ ሀይል በሆነበት ምንም ነገር በነፃ ማግኘት እንደዕድል ይቆጠራልና::

ጥሩ ዜና የሌለው አንድ መጥፎ ቦታ አገኘሁ:: እኔም መጥፎው ወሬ በጥሩ የሚቀየርበትን ቀን በመናፈቅ ወደ ቦታው መመላለሴን ቀጠልኩ:: ብዙ ሰዎችን ስለቦታው ምንነት ማጠያየቄንም አላቆምኩም:: ከጥቂት ወራት በኋላ ያ ቦታ በሚገርም ሁኔታ ታሪኩ ተቀይሮ ቁጭ አለ:: መጥፎ የነበረው ሁኔታም መንግስት በሰጠው ትኩረት ወደ





ጥሩ ተቀየረ:: እዚህ ጋ መገንዘብ ያለብህ ሁኔታዎች በምንም መልኩ እንዳሉ አይቀጥሉም ለውጥ በማንኛውም ነገር ላይ ይከሰታል::

አክሲዮን ግዢን በተመለከተ የፒተር ለይንችን ‹‹ገዳናን መቆጣጠር›› የተሰኘውን መጽሐፍ እወደዋለሁ:: መጽሃፉ እንዴት ተደርጎ ከትንሽ ቢዝነስ ውስጥ ትልቅ ሀብትን ማግኘት እንደሚቻል ያሳያል:: በማንኛውም ደረጃ ዋጋ ያለውን ነገር ማግኘት የቢዝነሱ አይነት ይለያይ እንጂ ቀመሩ ግን አንድ እንደሆነ መረዳት ተገቢ ነው::

መጀመሪያ የምትፈልገውን ነገር ጠንቅቀህ ማወቅ ወይም መረዳት ከዚያም ለማግኘት መጣር፤ እርግጠኛ ነኝ ታገኘዋለህ::

ተጠቃሚዎች ስለምን ሁል ጊዜ ድሆች ይሆናሉ:: ሱፐርማርኬቶች የዋጋ ቅናሽ ሲያደረጉ ቤታቸው በተጠቃሚ ይጨናነቃል:: ሆኖም አክሲዮኖች በፈጠሩት ችግር በቅናሽ ዋጋ ሰዎች እንዲቀላቀሉቸው ሲጣሩ ማንም ፍቃደኛ ሆኖ አይመጣም:: በሌላ መልኩም ዋጋ በሱፐር ማርኬት ቢጨምርም ተጠቃሚው እንደመልካም በመውሰድ መግዛትን አይተውም:: አክሲዮንም እንደዚሁ ዋጋ ሲጨመር ተጠቃሚን አያጣም::

ከላይ ከተጠቀሰው ሃሳብ መረዳት የሚቻለው ማህበረሰቡ ለሚገዛው ነገር ቅድመ ግንዛቤው አናሳና የሥሜታዊነትን የተሞላ እንደሆነ ልብ ሊባል ሲገባ አንተ ግን በምንም ተአምር በዚህ የህይወት መንገድ አትጓዝ::

**ትክክለኛ ዋጋን እጥና:-** ጎረቤቴ በ100,000 ዶላር የኮንዶሚኒየም ቤት ገዛ:: እኔ ደግሞ ከእርሱ ጎን በ50,000 ገዛሁ:: እርሱም ዋጋው የሚወደድበትን ቀን በተስፋ እንደሚጠባበቅ ሲያዋየኝ እኔም ትርፍህን የምታውቀው ስትሸጠው ሳይሆን መጀመሪያውኑ ስትገዛው ነው አልኩት::

የገዛው ምንም ንብረት ከሌላት የሪል ስቴት ደላላ ጋር ሲሆን እኔ ደግሞ የገዛሁት ከባንክ በሀራጅ ከሚሸጥ ላይ ነው:: በክፍል 500 ዶላር አውጥቼ ስገዛ ጎረቤቴ እጅግ በጣም ውድ እንደሆነ ይነግረኝ ነበር:: በዚህ ዋጋም እርሱ ቢሆን እንደማይገዛ በመግለጽ የገዛውን ቤት ዋጋው ተሰቅሎ መቼ እንደሚወጣ በጉጉት ይጠባበቅ ጀመር::

በመጀመሪያ የሚገዙ ሰዎችን አፈላለግኩ:: ከዚያም የሚሸጡትን ማፈላለግ ቀጠልኩ:: አንድ መሬት የሚፈልግ ጓደኛዬ ገንዘብ ሲኖረው ጊዜ ግን የለውም:: እኔም ጓደኛዬ ከሚፈልገው የመሬት መጠን ተለቅ ያለ ቦታን ፈልጌ የተወሰነውን የመሬቱን

አካል እንደሚፈልግ ገለፀልኝ:: ስለዚህ ቀርሺ ሽጨለት የተቀረውን እኔው ገዛሁት:: ታሪካዊ ትምህርት፤ በውጤቱም የተቀረው መሬት በነፃ የእኔ ሆነ ማለት ነው:: ብዙ ሰዎች ዕይታቸውን ይወስኑታል:: ሙሉውን ሙሉውን ገዛ የተወሰነውን ሸጥ:: ብዙ ሰዎች ዕይታቸውን ይወስኑታል:: ሙሉውን ከመግዛት ትንሹን ይገዛሉ:: ስለሆነም ከፍያቸው በዛው በትንሽ ነገር ይከስማል: ከዚህም መረዳት የሚቻለው የተሻለ ነገርን ለማግኘት አእምሮህን ማስፋትና ከትንሽ ነገር ትልቅን ነገር መምርጥ እንዳለብህ ብሎም ሀብታም ለመሆን ስትመኝ ዘወትር ምኞትህ በትንሽ ነገር ላይ የተገደበ መኾን እንደሌለበት ነው::

ቸርቻሪዎች ቅናሽ ዋጋ ሲያገኙ አብዛኛቹ የንግድ ሰዎች ደግሞ ወጪ የሚደፍሩ ደምበኞች ምርጫቸው ናቸው:: ምንም እንኳን በችርቻሮ ንግድ ውስጥ ብትሆንም ዘወትር እድማስህን በስፋት ቃኝ:: ዛሬ ቸርቻሪ ነን ምናልባትም ከነገ ወዲያ ጅምላ ሻጭ እሆናለሁ ብለህ አስብ:: የእኔ ካምፓኒ ወደ ኮምፒዩተር ቢዝነስ ሲገባ ብዙ ጓደኞቼን እንዲቀላቀሉኝ ጠይቄ ነበር:: እነርሱም ፍቃደኛ በመሆን ከእኔ ጋር አብረን ለመስራት ወደ ደላሎች ሄድን ምክንያቱም ልንገዛ ያሰብነው ብዙ ነውና:: በአክሲዮንም ተመሳሳይ ነገር ነው የማደርገው:: የአንተነትህ ሚስጥር የአመለካከት ውጤት ሲሆን ትንሽ ካሰብክ ትንሽ ትሆናለህ ትልቅ ካሰብክም ትልቅ መሆንህ አይቀርም:: በጅምላ ከማሰብ ራስህን ጠብቅ::

*ኪታሪክ ተማር፦* ሁሉም የንግድ ድርጅቶች እነሳሳቸው ከትንሽ ነው:: ኮሎኔል ሳንደርስ እድሜው 60ዎቹ ከመድረሱ በፊት ያለውን ነገር ሁሉ አጥቶ ነበር:: ቢል ጌትስ ዕድሜው 30 ከመድረሱ በፊት የሀብታሞች ሁሉ ቁንጮ ነበር::

ድፍረት ፍርሃትን ያሸንፋል::

ሕይወት በአማራጭ እንደተሞላችና በዚህም አመለካከት ለመቀጠል ጥቂት ነገሮችን ሳደርግ አስፈላጊውም ቃል «አድርግ» ወይም ፈጽም እንጂ ወደ ኋላ አትበል የሚል ነው:: እዚህ መጽሐፍ ላይ በተለያዩ ቦታዎች እንደተገለፀው በህይወትህ ውስጥ የውሳኔ ሰው ካልሆንክ የፈለግከበት ደረጃ መድረስ እንደለማይ ይርቅሀል:: ሀብትህን ለማዳበርም መጀመሪያ ወደ ስራ በተግባር መግባት ሲኖርብህ ውጤቱንም በአይንህ ታየዋለህ:: ስለዚህ ወደ ተግባር አሁኑኑ ግባ::





# በ7000 ዶላር ብቻ እንዴት የልጅህን የኮሌጅ ትምህርት ወጪ መክፈል ትችላለህ?

ያነበብኳቸው መጽሀፍት የሰጡኝ የማይታይ እውቀትን በስተመጨረሻ ሳካፍል በታላቅ ሀሴት ውስጥ ሆኜ ነው::

ይህንን መጽሀፍ ከፃፍኩባቸው አበይት ምክንያቶች አንዱና ተጠቃሹ ገንዘብ በብልሀት የመጠቀም ብቃትን ከፍ ለማድረግ ሲሆን በውጤቱ የህይወትህ ውስጥ ለሚያጋጥሙህ የገንዘብ አጠቃቀም ተግዳሮቶች መፍትሄን ታገኛለህ:: ገንዘብን በአግባቡና በብልሀት የመጠቀም ተሞክሮዎች ውስጥ ካላለፍክ ህይወትህ በድግግሞሽ ሲሞላ ጠዋት ተነስቶ ወደ ስራ በመሄድ መስራት፣ በባንክ ገንዘብን ማስቀመጥ፣ መበደርና ከመጠን በላይ ግብር መክፈል እጣ ፈንታህ ይሆናል:: ዛሬ ሳይቆም ብለህ ስለዘመኑ ማሰብ ሲገባህ መረጃ ያለውንም ሐይል ልታስተውል ይገባል:: «ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው» ይባል የለ::

ብዙ አፍላ የትዳርና የቤተሰብ ህይወትን በገንዘብ ችግር ውስጥ እንዲገቡ ከሚያደርጋቸው ጥቂት ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶቹን ስንመለከት ከችግሩ መብዛት የተነሳ ለልጆች ትምህርት ቤት መክፈልና ለጡረታ ማስቀመጥ ይከብዳቸዋል:: ለዚህ ሁሉ ችግር መንስኤው ገንዘብን በአግባቡ ያለመጠቀም ነው መፍትሄውም ጠንክሮ መስራት ቢሆንም ዋናው የመፍትሄ መሳሪያ ግን የገንዘብ አጠቃቀም ብልሀትን ማሳደግ ነው::

ከአሰታት አንድ ቀን ጓደኛዬ እንዴት አድርጎ ለአራት ልጆቹ ገንዘብ በማስቀመጥ የኮሌጅ ወጪቸውን መሸፈን እንደሚችል በምሬት ነገረኝ:: በየወሩ ለዚህ አላማ 300 ዶላር ሲያስቀምጥ በድምሩም 12000 ማጠራቀም ችሏል:: ለአራቱ ልጆቹ ግን 400,000 ዶላር ሲያስፈልግ የመጀመሪያ ልጁ 6 ዓመት ስለሆነው ለኮሌጅ ትምህርት ለመድረስ 12 ዓመታት ይቀሩታል:: አባትም 12 ዓመቱን በየወሩ 300 ዶላር ለማስቀመጥ ወስኗል:: ወቅቱ 1991 ሲሆን በፎኒክስ የሪል ስቴት ቢዝነሱ አደጋ ውስጥ የገባበት ወቅት ነበር:: ሰዎችም ቤቶቻቸውን በርካሽ ይሸጡ ነበር:: ለጓደኛዬም ከተቀማጩ ላይ በመውሰድ ቤቶችን እንዲገዛ መከርኩት:: በጉዳዩም ዙሪያ መወያየታችንን ስንቀጥል ብድር ከባንክ ሊጠይቅ እንደማይችል ሲነግረኝ ሌላ ገንዘብ የማግኛ አማራጭ መጠቀም እለብህ ስል

መከርኩት:: በሁለት ሳምንት ውስጥም ልንገዛ የምንችለውን ቤት ስናፈላልግ ብዙ አማራጮችን አገኘን:: በመጨረሻም 3 መኝታክፍል ያለውና ሁለት የመታጠቢያ ገንዳን ያካተተ ቤት ስናገኝ ባለቤቱም ወደ ካልፎርኒያ ሄዶ ስራ ለመቀጠር በመፈለጉ ቤቱን ለመሸጥ ከፍተኛ ጉጉት ነበረው::

እርሱ 102000 ዶላር ለመሸጥ ሲፈልግ እኛ ግን 79000 ዶላር ሰጠነው:: ካለበት ችግር የተነሳም ምንም ሳያቅማማ የሰጠነውን ገንዘብ ተቀበለ:: ቤት ያለ ባንክ እውቅና መግዛት ስለማይቻል እውቅና እንዲኖረው ባንክ ከሻጩ ላይ 7,000 በመቀነስ 72,000 ለሻጭ ተከፈለ:: ህጋዊነቱም ከተረጋገጠ በኋላ ጓደኛዬ ቤቱን በማከራየት በወር 125 ዶላር ማግኘት ጀመረ: ልብ በል በባንክ አካውንቱ የቀረው ገንዘብ 7,000 ብቻ ነበር::

የጓደኛዬ እቅድ ለ12 አመታት በማከራየት ወጭውን ሸፍኖ ትርፍ ገቢን ማግኘት ሲሆን በ12 ዓመታት ውስጥም ያለበትን እዳ ሁሉ ሸፍኖ የመጀመሪያ ልጁ የኮሌጅ ትምህርት ሲጀምር 800 ዶላር በየወሩ እንደሚያገኝ ተረዳን:: ከዛም በኋላ ከፈለገ ቤቱን እንደሚሸጥ ተገንዘብን:

በ1994 የሪል ስቴት ገበያ በፎኒክስ የተሻለ ለውጥ ሲያሳይ 156,000 ዶላር የግዢ ጥያቄ ቀረበለት! እኔንም አማከረኝ:: እኔም እንዲሸጠው መክሬው ግብር ከፍሎ የተጣራ 154,969 ትርፍ አገኘበት:

በዚያው ማግስት 80,000 ዶላር የመንቀሳቀሻ ገንዘብ ሲኖረው እኔም ከኦስቲን ቴክሳስ ሌላ ጓደኛዬ ጋር ደውዬ ከግብር ነፃ የሆነ አነስተኛ ሱቅ ለጓደኛዬ ይፈልግለት ዘንድ ነገርኩት:: በሦስት ወራትም ውስጥ ለልጆቹ ኮሌጅ ክፍያ ይቸገር የነበው ጓደኛዬ በየወሩ 1,000 ደላር ማግኘት ሲጀምር ለኮሌጅ ያስቀምጥ ከነበረው 300 ዶላር በሦስት እጥፉ ማስቀመጥ ቻለ:: በ1996 እኤአ ያቺን ትንሽ ሱቅ በ330,000 ዶላር ሸጦ ተለቅ ያለና በየወሩ 3000 ዶላር ሊያስገኝ የሚችል ስራን በማግኘቱ ለኮሌጅ ትምህርት 1000 ያስቀምጥ የነበረው ወደ 3000 አደገ:: በአሁኑ ሰዓት ጓደኛዬ 400,000 ዶላሩን በቀላሉ ለልጆቹ የኮሌጅ ትምህርት እንደሚያገኝ እርግጠኛ ሲሆን የችግርን ለመፍታት ጥቂት ገንዘብ ከበዙ ብልሀት ጋር ከተጣመረ መፍትሄ እንደሆነ መማር ችሏል:: በውጤቱም ለልጆቹ ኮሌጅ ትምህርት መክፈል ብቻ ሳይሆን የጡረታውን ወጪ ማስተካከል ስለሚችል በጊዜ ጡረታ ወጥቶ የራሱን ቢዝነስ ማንቀሳቀስ ይችላል! ችሏልም::





ይህን መጽሀፍ ስላነበብኩ በጣም ደስተኛ ስሆን ገንዘብን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንዳለብኝና በገንዘብ ሰርቼ መለወጥ እንደምችል አስተምሮኛል:: በዛሬ እለት ገንዘብን በብልሀት የመጠቀም እውቀት ሲያስፈልገን ለህልውናችንም መሠረቱ ይህ ብቻ ነው:: ማባከን ያልሰለጡኑ ሰዎች መገለጫ ነው:: ሆኖም ብልህ አይደሉም ማለት ሳይሆን በገንዘብ ገንዘብን ማዳበር እንደሚቻል ግን አልገባቸውም ሊባል ይችላል::

ገንዘብ ማዳበር ማለት ስለገንዘብ መረዳት ሲሆን ለማብልፀግም ከዚህ በፊት ያለህን አመለካከት በሌላ ተካው:: ማንኛውም ሰው ሲፈጠር ራቁቱን እንደተወለደ ከተረዳህ ከጥቂት ተነስቶም ትልቅ የሀብት መጠንን ማካበት እንደቻለ ዘወትር አስብ:: ኢንቨስትመንትም ተመሳሳይ አካሄድ ሲኖረው ከጥቂት ወደ ትልቅ ሀብትነት ይቀየራል:: በህይወት ዘመኔ ብዙ ገንዘብ ለስራ በማዋል ሀብት ለማካበት የሚጥሩ ሰዎችን አያለሁ:: ለእኔ ግን እነዚህ ሰዎች ሞኞች ናቸው! ምንም እንኳን በጠንካራ ሰራተኛነታቸው ቢመሰገኑም የተቀጣላቸው ባለሀብት መባል ግን አይገባቸውም::

ሀብትን ለማካበት ከምንም በላይ እውቀትና ጥበብ በጣም አስፈላጊ ነው:: በቢዝነስ ላይ የሚያተኩሩ መጽሐፍትን ገዝቶ ማንበብ! በሴሚናር መሳተፍና የተማሩትን በህይወት መተግበር ከምንም በላይ አስፈላጊ ሲሆን ስድስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥም 5000 ደላርን ወደ 1 ሚሊዮን መቀየር የቻልኩት እውቀትን መሳሪያ በማድረጌ ብቻ ነው::

ለዚህ ሁሉ የተሻለ ህይወት የመብቃቴ ምስጢር አእምሮዬን ክፍት በማድረጌና ገና በልጅነቴ በመንቀሳቀሴ ሲሆን ዋናው ነገርም ይቻላል ማለትን መተግበሩ ብቻ ነው::

መልዕክቴ ግልጽ ይመስለኛል:: አንተን አንተ የሚያደርግህ የምታስበው ሲሆን ለእጅህ ማጠርና መርዘም ወሳኙ ይሄው አእምሮህ ብቻ ነው:: ገንዘብ ማካበት የገንዘብ ኖትን መቁጠር ሳይሆን ከአእምሮ የፈለቀ ሀሳብን ተጠቅሞ ገንዘብን ለማካበት መጣር ነው:: ሀሳብ ከወረቀት ገንዘብ ይቀድማል የሚባለውም ለዚህ ነው:: ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነው ደግሞ ‹‹Think and Grow Rich››የሚለው ታላቅ መጽሀፍ ጠንክረህ በመስራት ለእድገት ጣር ሳይሆን የሚለው ‹‹ሀሳብን ወይም አእምሮህን ተጠቀመህ እደግ›› ነው:: ከዚህም መረዳት የምትችለው ገንዘብ ከአንድ ደላር ጀምሮ እስከ ትልቁ ደረስ ሰራተኛህ ሲሆን ይህንም ስትገንዘብ ህይወትህ ቀላልና ደስተኛ ይሆናል:: ከዛሬም ጀምሮ የሕይወትን ጨዋታ በንቁነትና በብልህነት ልትወጣው ይገባል::

# እርምጃ ውሰድ!

ሁላችሁም ሁለት ታላላቅ ስጦታዎች አሏችሁ፤ጊዜና አእምሯችሁ፡፡ በሁለቱም የሚያስደስታችሁን መስራት የናንተ ምርጫ ነው፡፡ ወደእጃችሁ በምትገባው እያንዳንዷ የብር ኖት ላይ የፈለጋችሁትን በመወሰን ዕጣፋንታችሁን ለመወሰን ነፃ ናችሁ፡፡ እዳ በሚያመጡ ነገሮች ላይ ካዋላችሁት መካከለኛ ገቢ ያላቸውን ሰዎች ትቀላቀላላችሁ፤ በአእምሯችሁ ላይ ካዋላችሁትና ንብረትን ማካበት ከተማራችሁበት የወደፊት ሕይወታችሁ በሀብት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን እየመረጣችሁ ነው፡፡ ምርጫው የእናንተና የእናንተ ብቻ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ቀን በእያንዳንዷ ብር አማካኝነት ሀብታም፣ባለመካከለኛ ገቢ ወይም ደሀ ለመሆን ምርጫ እያካሄዳችሁ ነው፡፡

ይሕንን ዕውቀት ለልጆቻችሁ ለማካፈል ብትወዱ ለሚመጣው ዓለም ዝግጁ ታደርጓቸዋላችሁ፡፡

የእናንተና የልጆቻችሁ የወደፊት ሕይወት የሚወስነው ነገ ሳይሆን ዛሬ እናንተ በምታካሂዱት ምርጫ አማካኝነት ነው፡፡

ሕይወታችሁ በሀብትና በደስታ የተሞላ እንዲሆንላችሁ እንመኛለን፡፡

ሮበርት ኪዮሳኪ

ሻሮን ሌችተር

ABS

@Amharicbookstore

ABS የተመረጡ የአማርኛ መፅሀፍት
የሚቀርብበት የቴሌግራም ቻናል

‹‹የፋይናንሱን ዓለም አዲስ መልክ [illegible] Rich Dad Poor Dad ሚሊየነሮች [illegible] በሉሲታል።››

[illegible]



ሮበርት ኪዮሳኪ ለምን ሚሊየነር እንዳልኾኑ ይጠይቃል ለዚህም ነው የሚሊየነርነት ትምህርት ቤት አስተማሪ ብለው የሚጠሩት።

‹‹ሰዎች በገንዘብ ችግር ውስጥ የሚዳክሩበት ዋና ምክንያት ዓመታትን በትምህርት ቤት ሲያሳልፉ ምንም ዐይነት ገንዘብ ነክ ዕውቀት ሳይቀስሙ ስለሚወጡ ነው። በውጤቱም ሰዎች ገንዘብ ለእነሱ እንዲሰራ በማድረግ ፋንታ ለገንዘብ መስራትን ይማራሉ።››

ሮበርት ኪዮሳኪ

## የሀብት መንገድ

- ሀብታም ለመሆን ከፍተኛ ገቢ ማግኘት አለብህ የሚለውን ከንቱ አስተሳሰብ ውድቅ ያደርጋል።
- ቤት ንብረት ነው የሚለውን አስተሳሰብ ይፈትናል
- ወላጆች ልጆቻቸው ስለገንዘብ ለማስተማር በትምህርት ቤቶች ላይ ሊተማመኑ እንደማይገባቸው ያሳያል
- የንብረትና የዕዳን ትርጉም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያስቀምጣል
- ልጆችዎ ስለወደፊት የገንዘብ ሕይወታቸው የሚነግሯቸውን ነገር ያስተምርዎታል



‹‹ልጆቼን ስለምወዳቸው በሚቻለኝ መጠን ምርጡን ትምህርት እንዲያገኙ እፈልጋለሁ። የተለመደው ትምህርት ግን አስፈላጊነቱ እንዳለ ሆኖ በቂ አይሆንም። ሁላችንም ገንዘብንና ገንዘብ የሚሰራበትን መንገድ ልንረዳ ይገባናል።››

ሻሮን ሌችተር

የ Rich Dad Poor Dad ተባባሪ ደራሲ.

‹‹Rich Dad Poor Dad የገንዘብ ሂደቱን መቆጣጠር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው እንደመነሻ ነጥብ ሊጠቀምበት የሚገባ መጽሐፍ ነው።››

ዩኤስኤ ቱደይ